# *እምነት እንዲህ ነው!*

*የእግዚአብሔርን መንግሥት አኗኗር ባሕርይ*
*መረዳት*

**በዶ/ር ማይልስ ሙንሮ**

ተርጓሚ ተጋፋው ትርፌ

**ራዕይ አሳታሚ**
**አዲስ አበባ 2004 ዓ.ም.**

*እምነት እንዲህ ነው!*

**ይህ መጽሐፍ የተተረጎመው**
**Re-Discovering Faith**
**ከሚለው መጽሐፍ ነው::**


**ይህንን መጽሐፍ ያለ አሳታሚው ፈቃድ ማባዛት ወይም እንደገና ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው::**



**ራዕይ አሳታሚ**
**የፖ. ሳ. ቁ 2332**
**አዲስ አበባ**

RPTR-34 3M


## ማውጫ


መታሰቢያነቱ ....4

ምስጋና ....5

መቅድም ....6

መንደርደሪያ ....10

መግቢያ ....14

ምዕራፍ አንድ፤ እምነታችሁ የት አለ? ....17

ምዕራፍ ሁለት፤ እምነት፦ የእግዚአብሔር መንግሥት ባሕል ....42

ምዕራፍ ሦስት፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት የተፈተነ እምነት ነው ....64

ምዕራፍ አራት፤ አሥሩ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ባሕርያት ..81

ምዕራፍ ዐምስት፤ እግዚአብሔርን እንደ እምላክነቱ ....99

ምዕራፍ ስድስት፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ድፍረት ....115

ምዕራፍ ሰባት፤ እምነት ከፈተና ባሻገር፤ ክፍል 1 ....134

ምዕራፍ ስምንት፤ እምነት ከፈተና ባሻገር፤ ክፍል 2 ....152

ምዕራፍ ዘጠኝ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ኃይል ....168

ምዕራፍ ዐሥር፤ ዓለምን የሚያሸንፍ እምነት ....183

መደምደሚያ ....199

## መታሰቢያነቱ

ከ30 ዓመት በላይ በትዳር አብረን ለኖርነው ለውድ ባለቤቴ ለሩት፤ እንዲሁም ለውድ ልጆቼ ለቻሪሳና ለቻይሮ ማይልስ፤ በቤተሰባችን ውስጥ ባለው የእኔ አመራር ላይ እናንተ ያላችሁ እምነት እኔ በሰማይ አባቴ ላይ ላለኝ እምነት እጅግ ታላቅ የሆነ ትምህርትን ሰጥቶኛል፡፡

ለውድ አባቴና አባ ለምለው ለማትያስ ሙንሮ፤ በብዙ መከራና ተግዳሮት ውስጥ አሥራ አንድ የተከበሩና ስኬታማ የሆኑ ልጆችን ለማሳደግ በእግዚአብሔር ላይ ያለው ጽኑ እምነት የማይቻል ነገር የለም ብዬ እንዳምን አድርጎኛል፡፡

ለእህቴ ለሱዛን ሃል እና ከዚህ ዓለም በሞት ለተለየው ባለቤቷ ለስቲቭ፡- በበሽታና እንዲያውም በሞት መካከል እናንተ ለእግዚአብሔር ያላችሁ የልብ መሰጠትና ያልተለመደ የእምነት ጥራት የወደፊቱን ሕይወቴን ባልተበረዘ ልበሙሉነት እንድጋፈጠው ድፍረትን ይሰጠኛል፡፡

ምን እንደሚያስከትል በማይታወቅ የሕይወት ጠመዝማዛ መንገድ በየዕለቱ ለሚታገሉት በሚሊዮን ለሚቆጠሩት የሦስተኛው ዓለም አገሮች፣ ይህ መጽሐፍ ለእናንተ የመጽናናት ምንጭ ሆኖ በነገው የተሻለ ሕይወት እንድታምኑ እምነታችሁን ያነቃቃው፡፡

የእምነቴ ጀማሪና ፈጻሚ ለሆነው፣ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡- በአንተ ላይ ያለኝን እምነት አጠነክር ዘንድ እስከ ሞት ድረስ በእኔ ላይ እምነት ስላለህ አመሰግንሃለሁ፡፡



## ምስጋና

ማንኛውም የሕይወት ስኬት የአንድ ግለሰብ የተናጠል ጥረት ውጤት ሳይሆን፣ በሕይወታችን ውስጥ የሚያጋጥሙን የብዙ ሰዎች አስተዋጽኦና የህብረት ድጋፍ ውጤት ነው፡፡ የዚህ መጽሐፍ ሥራም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ በዓመታት ውስጥ የእኔ የቅርብ ጓደኛና አርታኢ የሆነውን ዶን ሚላምን ለማመስገን እፈልጋለሁ፣ አሳቦቼ በዚህ ምድራዊ ጉዞ ውስጥ ሌሎችን ሰዎች ሊረዱ እንደሚችሉ በማመን በጽሑፍ እንዳሰፍራቸው ሁልጊዜ ያደፋፍረኛል፡፡ ዶን፣ አንተ በዚህ ሥራ ያደረግኸው አስተዋጽኦና ክትትል ይህንን ረቂቅ ለዓለም ለማበርከት አስችሎኛል፡፡

ደግሞም ለባለቤቴ፣ ለሩት፣ እና ለልጆቼ ለቻሪሳና ለቻይሮ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ ይህንን ሥራ ከፍጻሜ ለማድረስ ቀንና ሌሊት በምርምር ሥራ ገጾች ላይ አንገቴን እንዳቀረቅርና በኮምፒውተሬ ላይ ዓይኔን እንዳተኩር ያለ ማሰለስ ፈቅዳችሁልኛልና አመሰግናችኋለሁ፣ ሁላችሁንም እወዳችኋለሁ፡፡

ሳንድራ ኬምፐ፤ ከእምነቷ ጽናት የተነሣ ለህመም ለመንበርከክና ለመሞት ያልፈለገች፤ ነገር ግን ሥጋዊ ምኞት ከነሳት አካላዊ ስቃይዋ እንደሚታደጋት በአምላኳ ታማኝነት ላይ ፈጽሞ ባለመጠራጠር የእምነት ገድል መጋደሏን የቀጠለች ሴት ናት፡፡ ከርስዋ ስላገኘሁት መነቃቃት አመሰግናታለሁ፡፡

በባሃማስ፣ ናሳው ውስጥ ላሉት ለእምነት አገልግሎት ህብረት አባላት፤ እነርሱ በእኔ አመራር ላይ ያላቸው እምነት መልስ ለሚያስፈልጋቸው ጥያቄዎችና ጉዳዮች መልስ እንድፈልግ አስገድዶኛል፡፡ ይህ መጽሐፍ ከእነዚያ ፍለጋዎች መካከል የአንደኛው ውጤት ነው፡፡

## *መቅድም*

ከእምነቱ በላይ ለመኖር የሚችል ማንም ሰው የለም! በሕይወት ከሁሉም የሚበልጠው ጉድለት የእምነት ጉድለት ነው! በሕይወት ከሁሉም የሚበልጠው ተግዳሮት በራሱ በሕይወት መሃል የማመን ጉዳይ ነው። የየዕለቱ ሕይወት ትልቁ ተግዳሮት፣ ሕይወት በየዕለቱ የመሆኑ ጉዳይ ነው፤ ሕይወት ፈጽሞ አይቋረጥም!

መሬት ከምታደርገው ኡደት ትንሽ ቆም በማለት እርስዋ ከምትፈልግብህ ነገሮች፣ ውሳኔዎች፣ ትኩረቶች፣ ጥያቄዎች፣ ተግዳሮቶች፣ ኃላፊነቶች፣ የተስፋ ቃሎችና ግዴታዎች ለትንሽ ጊዜ እረፍት ትሰጠኛለች ብለህ ተመኝተህ ታውቃለህ? በየዕለቱ የሚጠበቅብህ የሕይወት ግዴታ ጫናው ይሰማሃልን? ገንዘብ ለመክፈል፣ ሥራን ለማክበር፣ ልጆችን ለማሳደግ፣ የትዳር ጓደኛን ለመደገፍ፣ ቤትን ለመጠበቅና ለመንከባከብ፣ ምግብ ለመብላት፣ ውሃ ለመጠጣት፣ ልብስ ለመልበስ፣ ጓደኞችን ለመያዝ፣ ቀረጥን ለመክፈልና መልካም ስምን ለመጠበቅ ይሰማሃል?

የማይጠበቅ ነገር ደግሞ አለ! ሥራ ማጣት፣ የወላጅ ወይም የትዳር ጓደኛ ወይም የልጅ በሞት መለየት፣ በቤተሰብህ ወይም በገዛ ራስህ ላይ ፈውስ የሌለው በሽታ መገኘት፣ የጓደኝነት መቋረጥ ወይም የትዳር መፍረስ፣ የግል መጥፎ ልማድ ተጽእኖ ወይም ባንድ ቤተሰብ አባል የሚፈጸም የንብረት ብክነት ወይም የራስህ የንግድ ሥራ ውድቀት የመሳሰሉ ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ በዚህኛው ምድር ላይ ያለው ሕይወት ነው፣ በምድር ላይ የሚኖሩ ሁሉ እነዚህ ተግዳሮቶች  ያጋጥሟቸዋል። እናም በእነዚህ ነገሮች የሚገጥምህ ስኬት ወይም ውድቀት የሚጠበቀውንና የማይጠበቀውን ነገር በምታስተናግድበት ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው።



ከእኛ ጋር በዚህች ምድር ላይ የሚኖሩ አብዛኛዎቹ ኗሪዎች፣ ችግር፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ትካዜና በመጨረሻም እነዚህን ተግዳሮቶች ለመቋቋም በሚያደርጉት ጥረት ውድቀት ይገጥማቸዋል። ብዙዎች ችግሩ እያለ እንደሌለ መቁጠርን የሚመርጡ ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ ችግሩን ለመቋቋም አለመቻላቸውን በአልኮል መጠጥ፣ በአደንዛዥ ዕጽና በሌሎች ራስን በሚጎዱ ፀረ ማህበራዊ ባሕርያት ባሕር ውስጥ እንዲቀበር ያደርጉታል። ብዙዎች በአገራቸው ውስጥ ባለው በፖለቲካው፣ በማህበራዊ፣ በምጣኔ ሀብቱና በሃይማኖታዊው ተቋሞች አመኔታን በማጣታቸው ከዋናው የሕይወት አካሄድ ውጪ ሆነዋል። ብዙዎች በምድር ላይ ሰላም ይኖራል ወይም የተባበሩት መንግሥታት ጦርነትን ማስቆም ይችላል ብለው ማሰብን ትተዋል። ሌሎች ደግሞ የፖለቲካ ሰዎች የአገራችንን ችግር ይፈታሉ ወይም ሳይንቲስቶች የእኛን የሕክምናና የአካባቢ ተግዳሮቶች ይቋቋማሉ ብለው ለማሰብ ተስፋ ቆርጠዋል። እንደገናም ሌሎች በየዕለቱ ሽብርተኝነትን በመፍራት ይኖራሉ፤ ወይም የሰው ሕይወት በዘር ማጥፋት፣ በጽንስ ማስወረድ ወይም በጦርነት ዘመቻ ዋጋ ሲያጣ የሚያደርጉትን በማጣት ከዳር ቆመው ይመለከታሉ። የሰው ልጅ ወሳኝ በሆነ መስቀልኛ መንገድ ላይ ቆሞአል! የሰው ልጅ እኛ ላበላሸነው ዓለም አማራጭ ይኖር እንደሆነ በመደነቅ ላይ ይገኛል። በአጠቃላይ አብዛኛው ሰው ጭራሽ አመኔታን አጥቶአል። እምነትንም ማመን አቅቶታል።

*ሥራን*፣ የትዳር ጓደኛን፣ ልጅን፣ ቤትን ወይም የንግድ ድርጅትን ማጣት በጣም አሳዛኝ ነገር ነው፤ ዳሩ ግን እነዚህ ለአንድ ሰው የመጨረሻው ትልቅ ጉድለቶች አይደሉም። በሕይወት ከሁሉ የሚበልጠው ጉድለት የማመን ጉድለት ነው። አንድ ሰው እምነትን ካጣ ተስፋን ያጣል! ተስፋም ከጠፋ ዐላማም ተደመሰሰ ማለት ነው። ትርጉምም አይኖርም። እምነት የአመክንዮ

ምንጭና የልብ መሰጠት፣ የጽናትና የታማኝነት ጥሬ ዕቃ ነው ለማለት ይቻላል:: እምነት ከጠፋ ሕይወት መግለጫ (ትርጉም) የለውም:: በየዕለቱ ኑሮህ ውስጥ ማንኛውንም ነገር ብታጣ ስንኳ፣ በሕይወትህ እምነትን ግን ፈጽሞ ማጣት የለብህም::

ይህ መጽሐፍ ስለዚሁ ተግዳሮት የሚመለከት ነው! መጽሐፉ ስለ እምነት አስፈላጊነት ብቻ ሳይሆን ስለ ትክክለኛው እምነት አስፈላጊነት ነው:: ዛሬ እምነት ብለን የምንጠራው አብዛኛው ክፍል ለእኛ የሚስማማ ምኞት ብቻ ነው! በሌላ አነጋገር፣ እኛ የምናምነው የምንፈልገውን፣ የምንጠባበቀውንና ለመቀበል የምንፈቅደውን ነገር ብቻ ነው:: የእኛ እምነት የተመሠረተው እኛ መልካም፣ ትክክለኛና ተቀባይነት ያለው ነው ብለን በተረጐምነው ነገር ላይ ነው፤ ስለሆነም በፈጣሪ የሉዓላዊነት ባሕርይና በእርሱ የማወቅ አመለካከት ላይ በማመን ፈንታ እምነታችን ብቁ ነው ብለን የምናስበው ልምምዶቻችን እኛ መልካም ነው ብለን ከተረጐምነው ነገር ጋር የሚስማሙ እስከሆኑ ድረስ ብቻ ነው::

ይህ መጽሐፍ የተጻፈው ከዘመናችን የእምነት ዘዴዎች የወረስኻቸውን የእምነት ዐይነትና ባሕርይ ለመገዳደርና፣ ብሎም በሕይወታቸው ዘመን ማንኛውንም ዐይነት ተግዳሮት ካሸነፉት በዘመን ከተፈተኑት የእምነት ጀግኖች መዝገብ አንጻር ለመፈተሽ ነው::

የእኔ ዐላማ የያዝኸውን እምነት እንድትመረምርና እምነትህ ችግርን ለመቋቋም የሚችል የጥራት ደረጃ ያለው መሆኑን እንድትመለከት ነው:: እነዚህም ያልተጠበቁ የችግር ወቅቶች - የእግዚአብሔር ዝምታና ለአንተ ውድ የሆኑትን ነገሮች የምታጣባቸው ወቅቶች ናቸው:: የያዝኸው እምነት ምን ዐይነት ነው? በብርሃን ወቅት የተነገረህን ነገር በጨለማ ወቅት ለማመን



ትችላለህን? ሁሉንም ነገር ካጣህ በኋላ በአንድ ነገር ላይ ለማመን ትችላለህን? ተስፋ በአንተ ላይ ማመንን ባቆመ ጊዜ አንተ በተስፋ ማመን ትችላለህን? በጥርጥር ውስጥ ባለህበት ጊዜ እምነት ሊኖርህ ይችላልን?

በሕይወት ውስጥ በጽናት ጉዞህን እንድትቀጥል የሚያደርግህን የእምነት ዐይነት በውስጥህ ለማቀጣጠልና ብሎም መከራን በሚቋቋምና ችግርን በሚያስቸግር እምነት ላይ ተደላድለህ እንድትቀመጥ ተስፋዬ ነው:: የጠፋውን የመንግሥት ሰማያት የእምነት ባሕል እንደገና እንድታገኝና በምድር ላይ ዘወትር በማይቋረጡት ለውጦች ረግረግ ውስጥ ሰጥሞ በማይቀር የሕይወት ደረጃ እንድትኖር የእኔ ምኞት ነው:: የዚህ መጽሐፍ ግብ ሁላችንንም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የእምነት ኃይል እንድንመለስ መርዳት ነው::

## መንደርደሪያ

በአሜሪካ ዋና ዋና የገንዘብ ተቋሞች ውድቀት የተነሣ በ2008 በዓለም ዐቀፍ ደረጃ የተከሰተው የምጣኔ ሀብት (የኢኮኖሚ) ችግር እስከ አውሮፓ፣ የእስያው ፓሲፊክ፣ አፍሪካ፣ ደቡብ አሜሪካ፣ ሩቅ ምሥራቅና ወደ እኔም የካሪቢያን አካባቢ ደረሰ፤ ይህ ችግር አገሮች በተሳካ ሁኔታ ተግባራቸውን ያከናውኑ ዘንድ በርከት ያሉ ታላላቅና አስፈላጊ ጉዳዮችን ግልጽ አደረገ፦ እነዚህም (1) የአገሮች፣ የምጣኔ ሀብቶችና የማህበረሰቦች የእርስ በርስ ተደጋጋፊነት፤ (2) በምጣኔ ሀብት አተገባበር ረገድ የገንዘብ ዋጋ የሚኖረው ወሳኝ ሚና ናቸው:: በዚህ ውስጥ ያለው ሐቅ ሁሉም አገሮችና ማህበራዊ ተቋሞች በማህበራዊው ተቋም ውስጥ ለሚኖረው ንግድ፣ የዕቃ ልውውጥ እና የንግድ ግብይት የሚያገለግል የመገበያያ ገንዘብ መፍጠርና መጠበቅ የሚገባቸው መሆኑ ነው:: ይህ የገንዘብ ምጣኔ ሀብት በአገሪቱ በሥልጣን ላይ ባለው መንግሥት የሚመሰረትና በየዕለቱ ለሚከናወነው ተግባራዊ እንቅስቃሴና መረጋጋት ወሳኝ ክፍል በመሆን የሚያገለግል ነው:: ይህ የጋራ የመገበያያ ገንዘብ ከሌለ በስተቀር እንደ አገር ለመኖር የማይቻል ነገር ይሆናል:: ያለ ገንዘብ ምንም ነገር ሊፈጸም አይችልም፤ ስለሆነም በማህበራዊው መዋቅር ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ሰው ይህ ገንዘብ እንዲኖረው ማሰብና ማግኘቱንም ማረጋገጥ አለበት::

ሰማያዊው መንግሥትም ደግሞ፣ ምንም እንኳን በዓይን የማይታይ ቢሆንም፣ አገር ነው፤ ሰማያዊ መንግሥትም ለንግድና ለመገበያያ በሚያገለግል ገንዘብ የሚሠራ ነው:: የሰማያዊው መንግሥት ባሕል ፍቅር ነው፤ ድባቡ (ሁኔታው) ተስፋ ነው፤ የጋራ የመገበያያ ገንዘቡ እምነት ነው:: የሰማያዊ መንግሥት ገንዘብ እምነት ነው:: እምነት በምድር ላይ ላለው የሰማያዊ መንግሥት ሕይወት የሚኖረው ታላቅ አስፈላጊነት፣ ቀዳሚነትና



ጥቅም በመንግሥቱ ውስጥ ስለሚኖረው ሚና በራሱ በንጉሡ በተሰጡት መግለጫዎች ተረጋግጧል:: ይህ መንግሥት ያለ እምነት ሊሠራ አይችልም:: ከዚህ የሚከተሉትን ልብ ይሏል፦

... እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ ... (ማቴዎስ 9፥29-30):: ባለማመናቸውም ምክንያት ብዙ ተአምራትን በዚያ አላደረገም ... (ማቴዎስ 13፥58)::

... አንቺ ሴት እምነትሽ ታላቅ ነው እንደ ፈለግሽው ይሁንልሽ... (ማቴዎስ 15፥28) እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "እምነታችሁ በማነሱ ምክንያት ነው፤ እላችኋለሁ፣ የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል እምነት ቢኖራችሁ፣ ይህንን ተራራ ከዚህ ተነሥተህ ወደዚያ ሂድ ብትሉት ይሄዳል፣ የሚሳናችሁም ነገር አይኖርም" (ማቴዎስ 17፥20)::

ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "እውነት እላችኋለሁ፣ እምነት ቢኖራችሁ ባትጠራጠሩ በበለሷ ዛፍ ላይ የሆነውን ማድረግ ብቻ ሳይሆን ይህንን ተራራ ከዚህ ተነቅለህ ባሕር ውስጥ ግባ ብትሉት እንኳ ይሆናል፤ እምነት ካላችሁ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ" (ማቴዎስ 21፥21-22)::

ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን "አንተ ልጅ ኀጢአትህ ተሰርዮልሃል!" አለው (ማርቆስ 2፥5)

ባለማመናቸውም ተደነቀ (ማርቆስ 6፥6)::

እላችኋለሁ፣ ፈጥኖ ይፈርድላቸዋል፣ ነገር ግን የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆንን? (ሉቃስ 18፥8)፡፡

... የአብርሃም እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት ብለናል (ሮሜ 4፥9)

ስለዚህ ተስፋው በእምነት መጥቶአል ... (ሮሜ 4፥16)

ደግሞም ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሁሉ እግዚአብሔር መኖሩንና ከልብ ለሚሹትም ዋጋ እንደሚሰጥ ማመን አለበት (ዕብራውያን 11፥6)፡፡

በወንጌል የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጦአልና፤ ጽድቁም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በእምነት የሆነ ነው፤ ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደ ተጻፈ (ሮሜ 1፥17)

ጻድቅ ግን በእምነት ይኖራል ወደ ኋላ ቢያፈገፍግ ነፍሴ በእርሱ ደስ አይላትም (ዕብራውያን 10፥38)

እነዚህ መግለጫዎች በምድር ላይ ላለው የሰማያዊው መንግሥት ሥርዐትና ማህበረሰብ አሠራር የእምነትን አስፈላጊነት የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ የዚህ መንግሥት ገንዘብ መሠረታዊ ባሕርይ (ፍሬ ነገር) እርሱ እውነት መሆኑን "ማመን" እና መቀበልም የአንተ የዜግነት መብት መሆኑን "መጠባበቅ" ከሌለ በስተቀር ምንም ዐይነት ልምምድ ወይም ተግባራዊነት አለመኖሩን የሚያመለክት ነው፡፡ መንግሥቱ የሚንቀሳቀሰው እርሱ (መንግሥቱ)



ተጨባጭ፣ ፋይዳ ያለውና ሕያው መሆኑን በማመን ነው፡፡ የመንግሥቱን አገዛዝና ሕገ መንግሥታዊ ተስፋዎቹን ማመን፣ እንዲሁም በአሁንና በወደፊት ሕይወትህ የሚሠራ ስለመሆኑ ሙሉ እምነት ሊኖር ይገባል፡፡

ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ "በእግዚአብሔር እመኑ" (ማርቆስ 11፥22)፡፡

የሂሳብ መዝገብህ በተትረፈረፈ እምነት የተሞላ ይሁን፤ በየዕለቱ ኑሮህም እምነትን ተግባራዊ በማድረግ መጠቀም ይሁንልህ፡፡

# መግቢያ

"በጥርጥር ላይ ስትሆን ... እምነት ይኑርህ።"

ግዙፍ የሆነው የ747 ጄት አውሮፕላናችን ጉማ የግብፅን አየር ማረፊያ ማኰብኰቢያ ሥፍራ ገጨት አደረገና መሬት ነካ፤ ይህም ሰላማዊ ከሆኑት የዓለም ጉዞዎቼ መካከል አንድ ሌላ በሰላም የማረፍ ሁኔታ አስመዘገበ። ይህ ወደ ካይሮ የመጀመሪያው ጉዞዬ ነበር። የዚህች ጥንታዊት ከተማ የበረሃ ሙቀት እኔንና ባለቤቴን እንደ ሞቀ ብርድ ልብስ ተገናኘን። ከዚያም በቅጽበት በዘመናት ድር አማካይነት ወደ ታሪክ ውስጥ የገባሁ መሆኔ ተሰማኝ። ከልጅነቴ ጀምሬ ስለዚህ ሩቅ አገር ያነበብኳቸውና የተማርኳቸው ታሪኰች ሁሉ በቅጽበት በአእምሮዬ ውስጥ ፈነዱ፤ ስለዚህ አሁን ምድሪቱ ሕይወት እንዳለው ፍጡር ሆና ለምርምር በፊት ለፊቴ ተዘረጋች።

ወደ 70 አገሮችን የሚሸፍን በሺህ የሚቆጠር ኪሎሜትር ተጉዤ የብዙ ከተሞችን፣ ባሕሎችን፣ የአየር ፀባዮችን እና የማህበራዊና ሃይማኖታዊ ልማዶችን ተሞክሮ አግኝቼአለሁ፤ ይሁን እንጂ እያንዳንዱ ዐዲስ ሥፍራ እንደማይታወቅ ምስጢራዊ የታሪክ መጽሐፍ ያልተነበቡትን ገጾች እንዳነብ እኔን እየጋበዘ እንደ ሕፃን ልጅ የሆነ ጉጉትን በውስጤ አቀጣጠለ። ካይሮ እንደዚህ ዐይነት ከተማ ነበረች። የታላቁ መሪና የነፃ አውጪው የሙሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጽሑፎች፣ ዐምስቱ የብሉይ ኪዳን መጽሐፎች፣ በዚህች በባሕል በበለፀገች ምድር በተከናወኑ ሁነቶች የተሞላ የታሪክ መዝገብ አስቀምጠልናል። ለሰባት ቀናት ያህል ቆይተን በመላው አገሪቱ ውስጥ በመጓዝ የካይሮንና የሉክሶርን ከተሞችና ዝናቸው በዓለም የታወቀውን ጥንታዊውን የግብፅ ፈርዖኖችን መቃብሮች ማለትም ፒራሚዶቹን ጐብኝተናል።



በሉክሶር በሚገኙት ጥንታውያን የፈረሱ ግንቦች መካከል ስራመድ የነበረኝን የሚያስጥም የስሜት ማዕበል አስታውሳለሁ። በዚያም አንገቴን እየጠመዘዝሁ በቤተ መቅደሱ ያሉትን ግዙፍ ዐምዶችና ግዙፍ ቅርጻ ቅርጾች እንዲሁም ትናንት የተጻፉ ይመስል በሚያስደንቅና ውብ በሆነ ሁኔታ የተጠበቁትን የግብፅ የሄሮግሊፊክ ጽሑፎችን ተመለከትሁ።

የዛሬውንም ዘመን አእምሮ የሚያስገርመውን የሥልጣኔ ማስረጃ በምመለከትበት ጊዜ ባልታወቀው ምስጢር ውስጥ ያለው ኃይል በስሜቴ መምጣቱ አይቀሬ ሆነ። ብዙ ጥያቄዎች አእምሮዬን ሞሉት! እነዚህ ታላላቅ ሕንጻዎች የተገነቡት እንዴት ነበር? ከእኛ ሊምንት ሰብአዊ አካል በላይ የቆሙትን ግዙፍ ድንጋዮች ያጓጓዙትና ያነሱት እንዴት ነበር? በእነዚህ የተቀደሱ አዳራሾች ውስጥ ምን ዐይነት ሥነ ሥርዐቶች ተካሂደው ነበር? እነዚህ ሰዎች ምን ዐይነት ነበሩ? ለዚህስ ሥራ ያነሳሳቸው ምክንያት ምን ነበር?

በቀጣዩ ቀን ለረጅም ጊዜ በጉጉት ወደ ጠበቅነው ወደ ፒራሚዶቹ ዘንድ በደረስን ጊዜ ያልተመለሱ ጥያቄዎቼ የባሰ ገነኑብኝ። በልጅነቴ ጊዜ ከነበሩኝ ከብዙ የታሪክ መጻሕፍት ገጾች፣ እነዚህ ምን እንደሚመስሉ ገምቼ ነበር፤ ሆኖም ግምቴ በዚያ ቀን በዓይኔ ላየሁት ነገር ሊያዘጋጀኝ አልቻለም። በዚያ በሚያቃልጠው የበረሃው የፀሐይ ሙቀት ውስጥ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ለማየት የሚናፍቁትን አየሁ፣ ያየኋቸው ሦስቱ ዋና ዋና የጥንት ግብፃውያን ነገሥታትና ፈርዖኖች ፒራሚዶች ነበሩ። የጐብኝቱ መሪያችን የነበረው ሰው ወደ መጀመሪያው ተቋም በወሰደን ጊዜ በአንድ ስዕላዊ የሞዴል ዓለም ውስጥ ያለሁ መሰለኝ። በግንቡ ውስጥ የተካተቱትን የድንጋዮች መጠን ባየሁበት ጊዜ በመገረም ተሞላሁ - እያንዳንዳቸው እኔ ካየኋቸው አውቶሞቢሎች ወይም አውቶቡሶች የበለጡ ነበሩ። ከዚያም

የጠቅላላው ግንብ ግዙፍ ከፍታው ነበር:: ከዚህም ጋር ወደ ጠራው ሰማይ የተዘረጋው ፍጹም ትክክል የሆነው ማዕዘን ይታያል::

ከዚያም ግምቴ ጭራሽ ዋጋ ቢስ የሆነው በአንድ ወቅት ቅዱስ ወደነበረው ወደ ገናናዎቹ የግብፅ መሪዎች የመቃብር ሥፍራ በበሩ በኩል የገባንበት ጊዜ ነበር:: ንጉሥ ቱት የተባለውን ፈርዖን (ልጅ - ፈርዖን ነበር) ውብ የሆነ የቅርጽ ቅሪት ባየሁ ጊዜ ሥልጣኔው በሕይወቴ ላይ ሲፈስስ ተሰማኝ:: በዚያም በዚህ ሰፊ ክፍል ባሉ መስተዋቶች ወስጥ የጥንታዊቷ ግብፅ ቅርሳ ቅርሶች ይታያሉ:: በዚህ ጊዜ እኔም ሆንኩ ባለቤቴ እንዲሁም በዚያ አብረውን የቆሙት ጐብኚዎች ፍጹም ተሸንፈን ነበር ለማለት እችላለሁ::

ጥያቄዎች በአእምሮዬ ውስጥ እንደ ማዕበል ጐረፉ:: የዚያን ዕለት ጉዞ ፍጻሜም እንደ ጅማሬው ሆነ ይኸውም ከመልሱ ጥያቄው በለጠ - ድምዳሜውም የሕይወት ተጨባጭነት የሚገኘው በራሱ ምስጢሮች ውስጥ ነው የሚል ነው:: ለሁሉም ነገር መልስ አይኖርህም! ሁሉን ነገር ፈጽሞ አታውቅም! ሁሉን ችግር ፈጽሞ ለመፍታት አትችልም:: ሁሉን ግራ የመጋባት ሁኔታ ለመቋጨት አትችልም:: ልትገልጻቸው የማትችላቸው ነገሮች በሕይወት ውስጥ ሁልጊዜ ይኖራሉ:: አንዳንድ ጊዜ ማብራሪያ የሌለውን ሕይወት መኖርን ልንቀበለው የምንገደደው ተግዳሮት ነው:: ትልቅ ግራ መጋባትን የሚያስከትሉት በሕይወት ልምምድ ውስጥ ያሉት ባዶ ሥፍራዎች ናቸው:: ፈጽሞ ልንረዳቸው (ልናውቃቸው) የማንችላቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ:: ምን ማድረግ እንዳለብህ ግራ በሚገባህ ጊዜ ምን ታደርጋለህ? በዚያን ጊዜ ማመን ይኖርብሃል:: የሕይወት ድብቅ ነገሮች (ምስጢሮች) ሁልጊዜ ለእምነት ሥፍራ ይሰጣሉ::





## እምነታችሁ የት አለ?

*"እምነት ሁሉንም ነገር ያስችላል ... ፍቅር ሁሉንም ነገር ቀላል ያደርጋል"::*

ሕይወት በምስጢሮች የተሞላ ነው:: በሕይወት ባሕርይና ትርጉም ላይ ያሉ ጥያቄዎች በእያንዳንዱ ባሕልና ትውልድ ውስጥ የሚገኙና በየትም ያሉ ናቸው:: እያንዳንዱ ሰው በአንድ ወይም በሌላ ደረጃ የሕይወትን ዐላማ አተኩሮ ያሰላስላል:: እንደ ቀደሙት የጥንት አባቶቻችን ሁሉ እኛም ከዋክብት በሚያበሩበት ሌሊት ወደ ሰማይ እየተመለከትን "ከየት ነው የመጣሁት?" "እዚህስ የምኖረው ለምንድነው?" በማለት እንጠይቃለን:: "የጣቶችህን ሥራ ሰማያትህን ስመለከት፣ በስፍራቸው ያኖርሃቸውን ጨረቃንና ከዋክብትን ሳይ፣ በሐሳብህ ስፍራ ትሰጠው ዘንድ ሰው ምንድነው? ትጠነቀቅለትም ዘንድ የሰው ልጅ ምንድን ነው?" (መዝ 8፥3-4) በማለት ከጻፈው ከጥንቱ ዘመን መዝሙረኛ ጋር የጋራ ትስስር አለን:: ዐዲስ የተወለደውን የሕፃን ፊት እየተመለከትን የዐዲስ ሕይወትን ምስጢርና ግርማ እናደንቃለን:: ትልቅ ይሁን ወይም ትንሽ የዕለት ከዕለት ኑሮአችን በምስጢር የተሞላ ነው:: ሌላው የጥንት ፀሐፊ እንዲህ በማለት በሚገባ ገልጾታል፦ "እጅግ የሚያስደንቁኝ ሦስት ነገሮች አሉ፤ የማላስተውላቸውም አራት ናቸው፤ የንስር መንገድ በሰማይ፣ የእባብ መንገድ በቋጥኝ፣ የመርከብ መንገድ በባሕር፣ የሰውም መንገድ ከሴት ጋር ናቸው" (ምሳሌ 30፥18-19):: እኛ በምስጢር የተከበብን ነን:: ምስጢር፣ ሕይወትን ልንኖርበት የተገባ እንዲሆን የሚያደርግ አንድ ክፍል ነው::

ይሁን እንጂ፣ ብዙ ሰዎች በዚህ ዐይነት አይመለከቱትም:: እነርሱ የሚፈልጉት ሕይወት በቀላሉ ለመጉረስ ያመች ዘንድ በአፍ ጉርሻ መጠን ተቆራርጦ እንዲቀርብላቸው ነው:: በምስጢር ነገር ምቾት ስለማይሰማቸው የሕይወት ትርጉም እንደሚፈልጉት አንዳች ግራ መጋባት፣ ማወላወልና እንዲሁም የዕድል ጉዳይ ሳይኖርበት በሠንጠረዥና በእርሳስ ጫፍ ተጠቁሞ እንዲቀርብላቸው ይፈልጋሉ:: ችግሩ ግን፣ ሕይወት ፈጽሞ የዚህ ዐይነት ስላልሆነ በዚህ ነገር ተስፋ መቁረጥ ይገጥማቸዋል::

ዐላማና ትርጉም ያለው የተሟላና የተረጋጋ ሕይወት ለመገንባት ከፈለግን፣ ምስጢርን ለመቀበል ፈቃደኞች መሆን አለብን:: ለማወቅ ብንፈልግም ሁሉን ነገር ፈጽሞ ለማወቅ የማንችል የመሆኑን ሐቅ መቀበል አለብን:: አንዳንድ ነገሮች ሁልጊዜ የማይደረስባቸው ናቸው፤ አንዳንድ ሁኔታዎች ለዘላለም ከዕውቀታችን ውጪ ናቸው:: ይህም ማለት ሕይወትን

ጤናማ በሆነ ትህትና በመቅረብ ሁሉንም ነገር እንደማናውቅና ለማወቅም እንደማንችል ማመን ይገባናል፡፡ የእኛ ሁኔታ ልክ እንደዳዊት "እግዚአብሔር ሆይ ልቤ አልታበየም፣ ዐይኔ ከፍ ከፍ አላለም፤ ሐሳቤ ለዐጉል ትልቅነት አልተነሣሣም፣ ከዐቅሜ በላይ አልተንጠራራሁም፡፡ ነገር ግን ነፍሴን ጸጥ፣ ዝም አሰኘኋት፤ ጡት የጣለ ልጅ ዐርፎ እናቱ ላይ እንደሚቀመጥ፣ ነፍሴ ጡት እንዳስተውት ሕፃን በውስጤ ጸጥ አለች፡፡ እስራኤል ሆይ ከአሁን ጀምሮ ለዘላለም በእግዚአብሔር ተስፋ አድርግ" (መዝ. 131፥1-3) የሚል መሆን አለበት ትህትናና እምነት የሕይወትን ምስጢር ለመቋቋም ይረዱናል፡፡

## የሕይወት ምስጢሮች

ሕይወት በጨለማው በኩል ሲመታህ ምን ታደርጋለህ? ያልተጠበቀው ነገር ሲፈጸም ምላሽህ ምን ዐይነት ይሆናል? ዐዲስ የተጋባችሁት የትዳር ጓደኛ ሲሞት ምን እንደምታስቡ ገምቱ፡፡ አባትህ የራሱን ሕይወት ያጠፋል፤ እናትህ ከ30 ዓመት በኋላ ወላጅ አለመሆንዋን ትረዳለህ፡፡ እህትህ ዝሙት አዳሪ ናት፡፡ አባትህ ግብረ ሰዶማዊ የመሆኑን ምስጢር ይገልጻል፤ ዐዲስ የሠራኸው ቤት ይቃጠላል፡፡ ጤናማ ልጅህ በድንገት ይሞታል፤ ወይም የመጀመሪያው እርግዝናሽ ይጨነግፋል፡፡ በአንድ ኩባንያ ወይም ተቋም ውስጥ በሕይወትህ ሙሉ ያጠራቀምከው ገንዘብ ይጠፋል፡፡ የቤተሰብህ አባል በአውሮፕላን አደጋ ይሞትና የምታሳድጋቸው ሕፃናት ይኖራሉ፡፡ እነዚህን አሰቃቂ አደጋዎች የምትገልጻቸው ወይም የምትረዳቸው በምን ዐይነት ነው?

እነዚህ በሕይወት ውስጥ ፈጽሞ ልንመልሳቸው የማንችላቸው ጥያቄዎች ናቸው፡፡ አንዳንድ ሰዎች ለሁሉም ነገር መልሱን ማወቅ አለብን ብለው በግትርነት ያስባሉ፡፡ ከሰው መረዳት ውጪ የሆነ ምንም ዐይነት የእውቀት ክልል የለም ብለው ያስባሉ፡፡ ከዚህ የተነሣ፣ አንድ ነገር ሲያደናቅፋቸው ይተከዛሉ፡፡ ለእውቀትና ለመረዳት ያለን የማይረካ ጥማት በተወሰነ ደረጃ በትክክል ተፈጥሮአዊ ነው፡፡ ፈጣሪያችን ስለራሳችንና ስለምንኖርበት ዓለም ተመራማሪዎች እንድንሆን ዐቅዶ ፈጥሮናል፡፡ ዋናው ነገር እያንዳንዱን ነገር በተገቢው አመለካከት ማስቀመጥ ነው፡፡  እኛ ፈጽሞ ልንረዳቸው የማንችላቸው አንዳንድ ነገሮች መኖራቸውን መገንዘብ የዚያ አመለካከት አንዱ ክፍል አካል ነው፡፡

አንዳንድ ጊዜ እኔ ለምን እንደማልተከዝና እንደማላዝን ሰዎች ይጠይቁኛል፡፡ እኔ ፈጽሞ ልመልሳቸው የማልችላቸው ጥያቄዎች



መኖራቸውን ከ30 ዓመት በፊት የተረዳሁ መሆኔ አንዱ ምክንያቴ ነው፡፡ እስከምችለው ድረስ መልሶችን እፈላልጋለሁ፣ ከዚያም ከዐቅሜ በላይ ስለሆኑ (ሁልጊዜም ይሆናሉ) አልፋቸዋለሁ፡፡ ፈጽሞ ለመመለስ የማንችላቸው አንዳንድ ጥያቄዎች አሉ፡፡ ይህንን ሐቅ መረዳት ሕይወትን በጣም ቀላል ያደርገዋል፡፡

*በሕይወት ውስጥ ፈጽሞ ልንገልጻቸው የማንችላቸው ነገሮች አሉ፡፡* በሕይወት ውስጥ የምናያቸው ወይም የምንለማመዳቸው አንዳንድ ነገሮች በምርምር የተደረሰበት መግለጫ የማይገኝላቸው ናቸው፡፡ እነርሱን ዝም ብሎ መቀበል ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ሕይወትን ይበልጥ ትደሰትበታለህ፡፡ የአእምሮ ህክምና ተራ ክፍሎች የማይገለጸውን ለመግለጽ በሚጥሩ በተሰበሩ ሰዎች የተሞሉ ናቸው፡፡ ልትገልጻቸው የማትችላቸው አንዳንድ ነገሮች መኖራቸውን አሁኑኑ ተቀበል፡፡ ያለበለዚያ፣ ሁልጊዜ ትተከዛለህ፡፡

*በሕይወት ውስጥ ፈጽሞ ልንለውጣቸው የማንችላቸው ነገሮች አሉ፡፡* ምንም ነገር ይሁን ምን ዛሬ በሕይወቴ የምደሰተው እኔ ልለውጣቸው የማልችላቸው አንዳንድ ነገሮች መኖራቸውን ከ30 ዓመት በፊት ስለተረዳሁ ነው፣ ስለዚህም መሞከሩ ጥቅም የለውም፡፡ ሕይወት ከያዛቸው ነገሮች ውስጥ 90 በመቶ የሚሆነውን ልንለውጣቸው የማንችላቸው ናቸው ተብሏል፡፡ ብዙዎቻችን ልንለውጣቸው የምንችላቸውን 10 በመቶ ነገሮችን መመልከት ትተን ልንለውጣቸው የማንችላቸውን 90 በመቶ የሆኑትን እያሰብን በመናደድና በመጨነቅ ጊዜያችንን እናጠፋለን፣ ተስፋ በመቁረጥ ውስጥ የምንሆነውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ሚዛናዊነት ስለጐደለው ሕይወት ማልቀስ፣ መጨነቅና ማዘን፣ ምናልባት የደም ግፊትን ከማትረፍ በስተቀር የሚለውጣው ነገር የለም፣ ስለዚህ በዚህ ወጥመድ ውስጥ አትግባ፡፡

*በሕይወት ውስጥ እኛ ልንቆጣጠራቸው የማንችላቸው ነገሮች አሉ፡፡* አንዳንድ ሰዎች በቁጥጥር አሳብ የተሞሉ ናቸው፣ ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን፣ በአካባቢያቸው ላሉትም ጭምር እያንዳንዱን የሕይወት ክፍል መቆጣጠር ይፈልጋሉ፡፡ ሁላችንም እንዲህ ያለውን አንድ ሰው እናውቃለን፡- ያ ሰው የሥራ አለቃ፣ ወላጅ፣ ልጅ፣ የትዳር ጓደኛ ሊሆን ይችላል፡፡ ብዙዎቻችን አንድ አምባገነናዊ ሰው በሌሎች ሕይወት ላይ የሚያደርሰውን አስደንጋጭ ውጤት አይተናል ወይም ተለማምደናል፡፡

ይሁን እንጂ፣ ዞሮ ዞሮ፣ ማንኛችንም ብንሆን፣ ለእኛ ቅርበት ያላቸውን ሰዎች እንኳን፣ ሌላ ማንም  ሰው የሚያደርገውን ነገር ለመቆጣጠር አንችልም፡፡ ጥቅማችንን እናስተምራቸዋለን፣ ምኞታችንን ልንገልጽላቸው እንችላለን፣ ሕጉንም ልንደነግግላቸው እንችላለን፣ ዳሩ ግን፣ የራሳቸውን

ምርጫ በማድረግ ለምርጫቸው ኃላፊነትን ይወስዳሉ፡፡ እኛም ይህንኑ እናደርጋለን፡፡ ምናልባት የትዳር ጓደኛህ ልትተውህ ወስና ይሆናል፡፡ በዚህ ምክንያት ልትለምን፣ ልትደራደር፣ ልታለቅስ፣ ልታባብል፣ ልትፀልይም እንኳ ትችላለህ፤ ዳሩ ግን እርስዋ ለመለየት ከቆረጠች የምታደርገው ምንም ነገር የለም፡፡ ምናልባት አንዱ ዘመድህ ወይም ወንድ ወይም ሴት ልጅህ በሀሽሽ ሱስ ሊጠመድ ይችላል፡፡ አንተም ልትጮህ፣ ልትደነቅ፣ ልትሰብክ፣ ልትጨቃጨቅ ትችላለህ፤ ዳሩ ግን እርሱ ወይም እርስዋ በሚያደርጉት ምርጫ ላይ ምንም ቁጥጥር የለህም፡፡ ይህንን እንጋፈጠው፣ ምንም ያህል ብንሻም፣ በሕይወት ውስጥ ልንቆጣጠራቸው የማንችላቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ፡፡ ይህንን ሐቅ ተቀበል፡፡

*በሕይወት ውስጥ እኛ ልናግዳቸው የማንችላቸው ነገሮች አሉ፡፡* በባቡር ሐዲድ ላይ ብትቆምና ባቡሩ በሙሉ ፍጥነቱ ወደ አንተ እየገሠገሰ ሲመጣ ብታይ ሁለት ምርጫ አለህ፣ ወይ መንገዱን መልቀቅ ወይም መጨፍለቅ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሕይወትም እንደዚህ ነው፡፡ ወደ አንተ የሚመጡ አንዳንድ ነገሮች ሊገቱ የማይችሉ ናቸው፤ ስለዚህ እነርሱን እንዴት እንደምታሳልፋቸው ዝግጅት ማድረግን መማር አለብህ፡፡ እየበረረ በሚመጣ በፈጣን ባቡር ፊት ለፊት እጁን አንስቶ እንደሚቆም ሰው በመንገዱ ላይ ብትቆምና እርሱን ለማቆም ብትሞክር እርሱ ወደ መድረሻው መንጐዱን ይቀጥላል፤ አንተ ግን በሂደቱ ውስጥ ትጠፋለህ፡፡

*በሕይወት ውስጥ በኃላፊነት ተጠያቂ የማንሆንባቸው ነገሮች አሉ፡፡* ልጆቻችንን ምንም ያህል በመልካም ሁኔታ ብናሳድጋቸው፣ አስከፊ የሆኑ ውጤቶችን የሚያስከትሉ የሞኝነት ውሳኔዎችን ወይም ስህተቶችን ሊፈጽሙ ይችላሉ፡፡ ለድንገተኛ ወጪ ምንም ያህል በጥንቃቄ ብንዘጋጅ ገንዘብን፣ ጤንነትን፣ የጡረታ ዘመንን፣ ወዘተ በሚመለከት ፍጹም ካልተጠበቀ አቅጣጫ ችግር ሊመጣና ሊደመስሰው ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የተቻለንን ሁሉ ብናደርግም መጥፎ ነገሮች ይከሰታሉ፡፡ ለእነዚያ ነገሮች ኃላፊነት የለብንም፡፡ የእኛ ኃላፊነት ለእነዚያ ነገሮች ምን ዐይነት ምላሽ እንደምንሰጥና ባለን ጊዜና ሀብት ምን እንደምናደርግ መወሰን ብቻ ነው፡፡

*በሕይወት ውስጥ ልናልፋቸው የማንችላቸው ገደብ ያላቸው ነገሮች አሉ፡፡* አንዳንድ ሰዎች ገደባቸውን አያውቁም፤ አንዳንዶች ደግሞ ምንም ዐይነት ገደብ ለመቀበል አይፈልጉም፡፡ እንዲህ ያለው አዝማሚያ ትዕቢትና ሞኝነት ነው፡፡ ሁላችንም ገደብ አለን፤ እነዚያንም ገደቦች ብንቀበል በጣም ደስተኞች እንሆናለን፡፡ በሕይወት ውስጥ ሰላምን የሰጠኝና የምወደው አንድ አረፍተ ነገር አለ፡- እርሱም “እኔ አላውቅም” የሚለው ነው፡፡ ይህ



ማንኛችንም በሕይወታችን ልንፈጽም ከምንችላቸው ኃይለኛና ኃይል ሰጪ መግለጫዎች መካከል አንዱ ነው፡፡

ከብዙ ዓመታት በፊት ሬይንሆልድ ኔቡር በተባለ አሜሪካዊ ቄስና የሥነ መለኮት ምሑር የተጻፈው ጸሎት በሕይወት ውስጥ ስላሉት ምስጢሮች ሊኖረን የሚገባውን ዝንባሌ በትክክል የሚያንፀባርቅ ነው፤ የጸሎቱ የመጀመሪያው ክፍል በብዙዎቻችን ዘንድ የታወቀ ነው፤ የሁለተኛው ክፍል ግን ፋይዳ ያለው ድምዳሜ ነው፡-

> እግዚአብሔር ሆይ፣ ልለውጣቸው የማልችላቸውን ነገሮች ለመቀበል የሚያስችል ሰላምን ስጠኝ፣ ልለውጣቸው የምችላቸውን እንድለውጥ ድፍረትን፣ እንዲሁም ልዩነቱን ለማወቅ የሚያስችል ጥበብን ስጠኝ፡፡
>
> አንድን ቀን በአንድ ጊዜ እንድኖር፤
>
> አንዱን ጊዜ በአንድ ጊዜ እንድደሰትበት፤
>
> ችግሮች ወደ ሰላም የሚወስዱ መንገዶች መሆናቸውን እንድቀበል፤
>
> ይህ ኀጢአተኛ ዓለም እኔ እንደፈለግሁት ሳይሆን እርሱ እንዳደረገው እንዳለ እንድቀበል፤
>
> ለእርሱ ፈቃድ ብገዛ እርሱ ሁሉንም ነገር እንደሚያስተካክል በመተማመን፣
>
> በዚህ ሕይወት በአግባቡ እንድደሰትና በቀጣዩም ለዘላለም ከእርሱ ጋር በከፍተኛ ደረጃ እንድደሰት፡፡
>
> አሜን፡፡

## ሕይወትን በተሳካ ሁኔታ መጋፈጥ

በሕይወት ውስጥ ይህን ያህል ምስጢርና ግራ መጋባት ካለ ሕይወትን በልበ ሙሉነት ለመጋፈጥ አንዳች ተስፋ ሊኖረን የሚችለው እንዴት ነው? ይህን ያህል ነገር ከእኛ የተሰወረ ከሆነ በሕይወት ውስጥ ስኬትን የምናረጋግጠው እንዴት ነው? የስኬት ምስጢር እውቀት ነው፡፡ ይህ ለሌላ ተግባር (ጥረት) እውነት የመሆኑን ያህል ለሕይወትም እውነት ነው፡፡ ለስኬታማ ኑሮ ቁልፉ አራት ነገሮችን ማወቅ ነው፡፡

በመጀመሪያ፣ *ገደባችንን ማወቅ አለብን::* ብናምን ከሆንነው በላይ እንደምንሆን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፤ ከዚያም ጥበብን ካጣን ከተላላ ሰው የከፋ እንሆናለን፡- “ራሱን እንደ ጠቢብ የሚቆጥረውን ሰው አይተሃልን? ከእርሱ ይልቅ ለተላላ ተስፋ አለው” (ምሳ 26፥12):: ተላላ ለሚለው ቃል በዋናው የዕብራይስጥ ቃል “ደደብ” ወይም “ጅል” ማለት ነው:: በሌላ አነጋገር፣ በዓለም ላይ የመጨረሻ ደደብ ሰዎች የሚባሉት ራሳቸውን ከመጠን በላይ ከፍ የሚያደርጉት ናቸው ማለት ነው:: እያንዳንዱ ሰው ገደብ አለው፣ እኛም ጠቢብ ከሆንን የራሳችንን ገደብ እናውቃለን:: መስመሩ የት እንደሆነና የት ማቆም እንዳለብን ማወቅ ይገባናል:: ልንደርስበት ከሚገባን ቦታ መድረሳችንን ማወቅ አለብን::

እግዚአብሔር በራሳችንን ኃይል ከገደባችን በላይ እንድንሄድ አይጠብቅብንም:: ይሁን እንጂ እርሱ በሚጠይቀን ጉዳይ፣ ምንም እንኳ ለእኛ የማይቻል ቢሆን፣ እንድንፈጽመው እርሱ ኃይልን ይሰጠናል:: እኛ ገደብ አለን፣ እግዚአብሔር ግን የለውም:- “ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና” (ሉቃስ 1፥37):: ገደባችንን ማወቅ በእግዚአብሔር ወሰን የሌለው ችሎታ ለመራመድና ለመኖር ነፃነትን ይሰጠናል:: የእርሱን ወሰን የለሽነት ስንቀበል “የማይቻለውን ለማድረግ የምንችለው” በዚያን ጊዜ ነው::

ሁለተኛ፣ *ኃላፊነት የምንወስድበትን ነገር ማወቅ አለብን*: ለምሳሌ በየቀኑ ለምናደርገው ውሳኔ ኃላፊነት አለብን:: ዛሬ ብዙ ሰዎች ራሳቸው ላደረጉት ምርጫና ተግባር ኃላፊነትን ለመቀበል እምቢ በማለት “የማሳበብ ጨዋታን” ይጫወታሉ:: በዚህ ፈንታ፣ የአካባቢያቸው፣ የአስተዳደጋቸው፣ ወይም የሌሎች ሰዎች ባሕርይ ሰለባ መሆናቸውን ይገልጻሉ:: ይህ ጨዋታ ከኤደን ገነት የጀመረ ነው፤ በዚያ አዳምና ሄዋን በእግዚአብሔር ላይ በፈጸሙት አለመታዘዝ እርስ በርሳቸው ተወነጃጀሉ:: በእውነት ለመናገር፣ እኛ ለምንወስነው ውሳኔና ውሳኔው ለሚያስከትለው ውጤት ራሳችንን እንጂ ሌላ ማንንም መንቀፍ አንችልም:: ኃላፊነት ያለብን ለራሳችን ውሳኔ ብቻ አይደለም፣ አንዳንድ ጊዜ ሕይወት በመንገዳችን ለሚያመጣው መከራ ለምንሰጠው ምላሽም ኃላፊነት አለብን:: የሚደርስብንን ነገር ብዙ ጊዜ ልንቆጣጠረው አንችልም፤ ዳሩ ግን መከራው በሕይወታችን ላይ ተጽእኖ የሚያደርግበትን መንገድ ልንቆጣጠር እንችላለን፤ የእኛ ኃላፊነት እዚህ ላይ ነው::

ሦስተኛ፣ *ኃላፊነት የማንወስድበትን ነገር ማወቅ አለብን::* ይህ የሁለተኛውን ነጥብ ያህል አስፈላጊ ነው:: ለአንዳንድ ነገሮች ኃላፊነት ያለብን ሲሆን ለአንዳንድ ነገሮች ደግሞ ኃላፊነት የለብንም:: ለምሳሌ፣ ለራሳችን ድርጊት ኃላፊነት ያለብን ሲሆን ለሌሎች ሰዎች ድርጊት ኃላፊነት



የለብንም:: የእኛ ነፃ ፈቃድ በራሳችን ቁጥጥር ሥር ነው፤ የሌሎች ነፃ ፈቃድ ግን አይደለም:: እግዚአብሔር እንኳ ለእኛ ነፃ ፈቃድ ኃላፊነት አይወስድም:: ምርጫችንን እንድናስተካክል የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል፤ ዳሩ ግን ምርጫዎችን በእኛ ፈንታ ለእኛ አይመርጥልንም:: ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ሲል በመስቀል ላይ ሞቶአል:: እኛ የኀጢአትን ይቅርታ እንድናገኝና የአባቱ መንግሥት የዘላለም ዜጎች እንድንሆን ለእኛ በነፃ ሕይወቱን ሰጥቶ ደሙን አፈሰሰ:: ከዚያም ወደ እርሱ የሚመለሱ የዘላለም ሕይወት ስለማግኘታቸው ዋስትና እንዲሆናቸው ከሞት ተነሣ:: ኢየሱስ ይህን ሁሉ አድርጐአል፣ ይሁን እንጂ ያለ እኛ ፈቃድ አያድነንም:: እርሱ ገደቡን ያውቃል፤ ይህ የራሱ ውሳኔ ነው:: እርሱ ወደ ነፃ ፈቃዳችን ለመግባት መስመሩን አይሻገርም:: እኛ ኃላፊ የማንሆንባቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ፤ ስኬታማ ኑሮ ማለት እነዚህ ወሰኖች የት እንደሆኑ ማወቅ ነው::

አራተኛ፣ *ለማድረግ የማንችለውን ነገር ማወቅ አለብን::* በመሠረቱ፣ ይህኛው ሌሎቹን ሦስቱን ያጠቃልላል:: ስኬታማ ሕይወት ማለት ከእኛ ቁጥጥር ውጪ በሆኑ ሁኔታዎች ወይም ውጤቶች ምክንያት በበደለኝነት ስሜት አለመጓዝን መማር ነው:: ብዙ ወላጆች በልጆቻቸው የሞኝነት ውሳኔ ምክንያት ከዓመት ወደ ዓመት ራሳቸውን ሲወቅሱ ይኖራሉ:: በዚያን ጊዜም ሆነ አሁን ልንለውጣቸው በማንችላቸው ጉዳዮች “እንዲህ ቢሆን ኖሮ” በሚል ፀፀት የምንያዝ ስንቶቻችን ነን? በዚህ ዐይነት መኖር የለብንም:: እኛ ልንለውጣቸው በማንችላቸው ነገሮች ራሳችንን መኰነን አንችልም:: በሕይወት ውስጥ እርካታና ስኬት የሚገኙት ልናደርጋቸው የማንችላቸው አንዳንድ ነገሮች መኖራቸውን ስናውቅ ነው:: የእኛ ትልቁ ድክመት ከገደባችን የወሰን መስመር አጠገብ ስንደርስ ነው::

## ያነሳሳህ ምንድን ነው?

በሕይወት ውስጥ ያሉትን ምስጢሮችና የማይታወቁትን ነገሮች ከተገነዘብንና ገደቦቻችንንም አውቀን ከተቀበልን በኋላ ምን ይቀረናል? በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ በስኬት መኖር እንዴት እንችላለን? አንድ መንገድ ብቻ አለ፡- እምነት:: የሰው ልጅ የተፈጠረውና የታቀደው እምነት በተባለው በዚህ እጅግ አስፈላጊ መርሕ እንዲኖር መሆኑን በሙሉ ልቤ አምናለሁ:: ለሰው መንፈስ ኃይልን የሚሰጠው፣ በማይታየው ማመንና በማይታወቀው ተስፋ ማድረግ ነው:: የመላው ዓለም ንጉሥ የሆነው የእኛ ፈጣሪ በራሱ አምሳል ከፈጠራቸው ሰዎች ዘንድ ጠንካራ እምነትን ይፈልጋል፤ እርሱንም ባገኘ ጊዜ የበለጠ ያጠነክረዋል፡- “በፍጹም ልባቸው የሚታመኑበትን ለማበርታት የእግዚአብሔር ዐይኖች በምድር ሁሉ ላይ ይመለከታሉና”

(2ዜና 16፥9)። በአንድ ወቅት ኢየሱስ ራሱ “ነገር ግን የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆንን?” በማለት ጠይቆአል (ሉቃስ 18፥8)። እግዚአብሔር ጠንካራ እምነትን ይፈልጋል። እርሱ እምነትን ብቻ እንጂ ኃይልን፣ ሥልጣንን፣ ሀብትን፣ ዝናን፣ ሃይማኖትን፣ ፓለቲካን፣ ንግድን፣ ትምህርትን፣ ወይም ባሕልን አለመፈለጉ የሚገርም ነገር ነው። ምናልባት እምነት በምድር ላይ ከሁሉም በላይ አስፈላጊ ነገር መሆኑን ስላየ ይሆናል።

የእምነትህ ጥንካሬ በፈተና ውስጥ ለማለፍ በሚችልበት መጠን ብቻ ነው። ጥንካሬህ ምን ያህል ነው? አስተማማኝ ነው እንዲባል ከተፈለገ ጥንካሬህ መፈተን ይኖርበታል። የአንተ ጥንካሬ ልታነሣው በምትችለው ክብደት መጠን ነው፤ ስለዚህ አስቀድመህ ካልፈተንኸው በስተቀር በጥንካሬህ ከመጠን በላይ አትኩራ።

በዓለም ዙሪያ ካደረግኋቸው ጉዞዎች መካከል በአንዱ አውሮፕላን ውስጥ ከአንድ መካከለኛ ዕድሜ ካለው ሰው አጠገብ ተቀመጥሁ። ወደ ሎንዶን ለምናደርገው የአሥራ አንድ ሰዓት በረራ እንደተዘጋጀን መደበኛ ሥራው ምን እንደሆነ ጠየቅሁት። እርሱም “የፍተሻ ነጂና አውሮፕላን ነጂ (ፓይለት) ነኝ” አለኝ። እኔም ወዲያው ጉጉት አደረብኝና የመኪና ፍተሻን ጥበብ በሚመለከት የኰሌጅ ትምህርት ወደ ሆነልኝ ብርሃን ሰጪ ውይይት ተሸጋገርሁ። ከዚያም እርሱ በሥራው ውስጥ ስለ አሉት ዐላማዎች፣ ዝግጅቶች፣ ከህሎቶችና ደስታዎች ለእኔ ማስተማሩን ቀጠለ። ከዚያም እኔ ትልቁን ጥያቄ ጠየቅሁት፦ ዐዲስ መኪናን ወይም የአውሮፕላንን ሞተር መፈተሽ ለምን ያስፈልጋል? አልሁት። የእርሱም መልስ ሕይወቴን ለወጠው! ማንኛውም ታማኝ የሆነ አምራች ምርቱን በሚመለከት እነርሱ የሚሰጡት መግለጫ እውነት መሆኑን ለማረጋገጥና ዋስትና ለመስጠት በፍተሻ ላይ ትልቅ ትኩረት ያደርጋሉ አለኝ። ለደንበኛህ ለምትሰጠው የተስፋ ቃል ታማኝነትህን ለማረጋገጥ ፍተሻ አስፈላጊ ነው አለኝ። በአጠቃላይ ፍተሻ የአስተማማኝነት ቅድመ ሁኔታ ነው። በዐጭር አነጋገር ፍተሻ ቃልን ያረጋግጣል።

ብዙ አማኞች ብዙ ቃል እየተናገሩ እግዚአብሔርንም እያወደሱና እያመለኩ እርሱ ምን ያህል መልካም እንደሆነላቸውና ምን ያህል እንደባረካቸው ይመሰክራሉ፦ ዳሩ ግን እምነታቸው በተጨባጭ ፈጽሞ አልተፈተነም። ነገሮች በተስተካከሉበት ጊዜ “እግዚአብሔር መልካም ነው” ማለት ቀላል ነው። ዳሩ ግን በመጥፎ ጊዜስ እንዴት ነው? የቤት ኪራይህን ወይም የመብራት ዕዳን ለመክፈል በማትችልበት ጊዜ፣ ወይም ያለህን ሥራ በምታጣበት ጊዜ እንዴት ነው? በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ “እግዚአብሔር



መልካም ነው” ለማለት ትችላለህን? በኢዮብ እንዳደረገው ሁሉ እኛም ጥንካሬአችን ምን ያህል እንደሆነ እንድናውቅ እግዚአብሔር እምነታችን እንዲፈተን ይፈልጋል። እግዚአብሔር ኢዮብን እጅግ ባርኮት ነበር፣ ይሁን እንጂ ሰይጣን ለኢዮብ ያለውን ሁሉ እንዲወስድበት ፈቀደለት፦ ቤተሰቡን፣ ሀብቱን፣ ጤንነቱን ወሰደበት። ይህም የኢዮብ እምነት በፈተና ውስጥ ለማለፍ የሚችል መሆኑን ለማወቅ ነበር። “እግዚአብሔርን አምናለሁ” ብለህ ብትናገር ተዘጋጅ፣ ምክንያቱም አንተና ሌሎችም ሰዎች እምነትህ እውነተኛ መሆኑንና አለመሆኑን እንዲያዩ እግዚአብሔር እምነትህ እንዲፈተን ይፈቅዳል። የእርሱ ዐላማ አንተን ለማዋረድና በውሸት ለማጥመድ ሳይሆን አንተ እንድታድግ ለመርዳት ነው፣ ምክንያቱም ያልተፈተነ እምነት ብቁ እምነት እንዳልሆነና ብዙ እንደማይጠቅም ስለሚያውቅ ነው።

የእምነታችን መፈተን የሚያገለግለው የእምነታችንን ጥንካሬ ለማሳየት ብቻ ሳይሆን ዳሩ ግን ከእምነታችን በስተጀርባ ያለውን አነሳሳሽ ምክንያት ለመግለጽም ነው። “በእግዚአብሔር ላይ እደገፋለሁ” ብለህ ብትናገር በእግዚአብሔር ላይ የምትደገፈው ለምንድነው? በማንነቱ ምክንያት ነው ወይስ ከእርሱ ለማግኘት ተስፋ በምታደርገው ነገር ምክንያት ነው? ኢዮብ እግዚአብሔርን የተከተለው እግዚአብሔር ስለባረከው ነው ብሎ ሰይጣን ኢዮብን ከሰሰው። ስለዚህ እግዚአብሔር ኢዮብ እንዲፈተን ፈቀደ። እርሱም ከኢዮብ እምነት በስተጀርባ ያለውን መነሻ ምክንያት ለመግለጥ ፈለገ፤ ይህም ኢዮብ ሁሉንም ነገር ቢያጣ እንኳን እግዚአብሔርን የሚከተል መሆኑንና አለመሆኑን ለመግለጥ ነበር። በእግዚአብሔር መንግሥት በማንኛውም አገር ውስጥ እንደሚሆነው ሁሉ፣ በአገሪቱ ሕገ መንግሥታዊ የተስፋ ቃሎችና መብቶች ላይ ያለህ እምነት የሚረጋገጠው ሁኔታዎች መዋቅሩን እንድትጠይቅ በሚያስገድዱበት ጊዜ ነው። በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የእምነትህ መፈተን የሚከሰተው በምድር ላይ ባለው ሰማያዊ መንግሥት የፖለቲካ፣ የምጣኔ ሀብት፣ የማህበራዊና የባሕል መዋቅር ላይ ያለህን እምነት ለማረጋገጥ ዕድል የሚሰጡ ሁኔታዎች በሚፈጠሩበት ጊዜ ነው።

## የአንቀሳቃሽ ምክንያትና የእምነት ኃይል

ስለ አንድ አሳዛኝ ግድያ ወይም አሰቃቂ አደጋ መግለጫ ሲሰጥ ተመልከተህ ከሆነ ባለሥልጣኖቹ የሚጠይቁት የመጀመሪያው ትልቅ ጥያቄ “መነሻ ምክንያቱ ምን ነበር?” የሚል መሆኑን ስትሰማ ተደንቀህ ታውቃለህን? ለዚህ ምክንያቱ ለሰው ፀባይ ከሁሉ የሚበልጠው ኃይል መነሻ

ምክንያት ስለሆነ ነው! እኛ የምናደርገው ማንኛውም ነገር ከአንድ የመነሻ ምክንያት የሚመነጭ ነው:: መነሻ ምክንያት ምንድነው? መነሻ ምክንያት ሲባል አንድን ድርጊት የሚጀምረው፣ የሚያፀናውና የሚያረጋግጠው የተሰወረ ምክንያት ወይም ምኞት ነው:: ማንኛውም የሰው ድርጊት፣ ምንም እንኳ እኛ ተቃራኒውን ብንናገር፣ የመነሻ ምክንያት ውጤት ነው:: መነሻ ምክንያት በውስጣችን የተረጋገጠ ምክንያት ነው:: እንደ እውነቱ ከሆነ፣ የመነሻ ምክንያት አለመኖር የሞት ምልክት ነው:: ሕይወት ራሱ ትርጉም ይኖረው ዘንድ በመነሻ ምክንያት ላይ ይመሠረታል:: መነሻ ምክንያት በሌለበት ሥፍራ መነሳሳትም ሆነ ኃይል የለም:: ሁላችንም ማንኛውንም ነገር የምናደርገው በአንድ ምክንያት ነው:: እኛን የሚያንቀሳቅሰን መነሻ ምክንያት ነው:: እኛ የአንቀሳቃሽ ምክንያት ሰለባዎች ነን፤ ስለሆነም እንዳይጋለጡ እንጠብቃቸዋለን::

መነሻ ምክንያት ለእምነት ጉዳይ በጣም አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድነው? መነሻ ምክንያት ከጽኑ እምነታችን የሚመነጭ ነው::

እግዚአብሔርን ለመከተል መነሻ ምክንያትህ ምንድነው? ለዚህ ጥያቄ መልሱ የሚገኘው በሕይወት ማዕከል ውስጥ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ጌታህ አድርገህ ለመቀበልና በመንግሥቱ ውስጥ ለመግባት ያለህ መነሻ ምክንያት ምንድነው? እነዚህ ዋና ጥያቄዎች ናቸው፤ ምክንያቱም የእምነትህን መነሻ ምክንያት ስለሚፈትሹ ነው:: የዮሐንስ ወንጌል ስድስተኛ ምዕራፍ፣ ኢየሱስ 5000 ሰዎችን በዐምስት እንጀራና በሁለት አሣዎች መመገቡን በመግለጽ ይጀምራል:: ከዚያ በኋላ ደቀመዛሙርቱ በገሊላ ባሕር ላይ በጀልባ ወደ ሌላው ጠረፍ ሲሻገሩ ኢየሱስ ብቻውን ለመሆን ወደ ኮረብታ ሄደ:: በኋላም በዚያው ሌሊት በባሕሩ ላይ እየተራመደ እነርሱ ወደአሉበት ጀልባ መጣ:: በቀጣዩ ቀን በተኣምር የመገባቸው ብዙ ሰዎች ኢየሱስን ፈልገው ሲመጡ ሊያገኙት አልቻሉም::

> ሰዎቹም ኢየሱስ ወይም ደቀ መዛሙርቱ በዚያ አለመኖራቸውን እንዳወቁ ኢየሱስን ፍለጋ በጀልባዎቹ ወደ ቅፍርናሆም ሄዱ:: ከባሕሩ ማዶ ባገኙትም ጊዜ "ረቢ፣ መቼ ወደዚህ መጣህ?" አሉት:: ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፣ የምትፈልጉኝ እንጀራ ስለ በላችሁና ስለ ጠገባችሁ እንጂ ታምራዊ ምልክቶችን ስላያችሁ አይደለም:: ለሚጠፋ እንጀራ አትሥሩ፣ ነገር ግን የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር ምግብ ሥሩ:: ለዚህም እግዚአብሔር አብ ማረጋገጫ ማህተሙን በእርሱ ላይ አትሞልና (ዮሐንስ 6፥24-27)::



ሰዎቹ ኢያሱስን የፈለጉት ስለ ማንነቱ ሳይሆን እርሱ ስለሚያደርግላቸው ነገር ነው:: እርሱ ሊመግባቸው ይችላል፤ ሥጋቸውንም ሊፈውስ ይችላል፤ ከሕይወታቸው አጋንንትን ሊያስወጣ ይችላል:: መነሻ ምክንያታቸው ራሳቸውን ማገልገል ነበር፤ ኢየሱስም ይህን አውቆታል:: በዚህም ምክንያት እንደዚህ አላቸው፤ "እዚህ ለምን እንደመጣችሁ አውቃለሁ፤ የምትፈልጉት እኔን አይደለም፣ እናንተ የምትፈልጉት በረከት ነው፤ እናንተ የምትፈልጉት ተጨማሪ ነፃ አሣና እንጀራ ነው":: መነሻ ምክንያታችሁ የእምነታችሁን ዐይነትና ባሕርይ የሚደብቅና የሚገልጥ ነው::

እግዚአብሔር ሲባርከን እንወድምን? እርሱ እንደሚባርከን ተስፋ ሰጥቶናል:: ነገሮችን እንደሚጨምርልን ተስፋ ሰጥቶናል:: ነገር ግን በረከቶች ኢየሱስን ለመከተል አንቀሳቃሽ ምክንያት መሆን የለባቸውም:: እርሱ ዛሬ ባይባርከንስ? ዛሬ ምንም ነገር ባይጨምርልንስ? ከዚያስ? ሸሽተን ወደ ሌላ ልንሄድ ነውን? ወይስ ባይባርከንም ኢየሱስን መከተላችንን እንቀጥላለን? አንቀሳቃሽ ምክንያታችን ምንድነው? ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ጥያቄ ነው:- "በጨለማ እንኳ ቢሆን ብርሃኑን ትከተላለህን?"

ኢየሱስ "ለሚጠፋ እንጀራ አትሥሩ፣ ነገር ግን የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር ምግብ ሥሩ" አለ:: በሌላ አነጋገር፣ እምነታችንን በማግሥቱ በሚጠፉ ነገሮች ላይ ማባከን የለብንም:: ይልቁንስ እምነታችንን ማሳረፍ ያለብን እግዚአብሔር አብ ማረጋገጫ ማህተሙን ባተመበት የሰው ልጅ" ላይ ነው:: በሕይወት ውስጥ ማህተም ያለበትና ዋስትና ያለው ክርስቶስ ብቻ ነው:: እምነታችንን የምናሳርፍበት ታማኝና መመኪያ እርሱ ብቻ ነው:: የእርሱ በረከቶች፣ የእርሱ መግቦት፣ የእርሱ ፈውሶች ሳይሆኑ ኢየሱስ ራሱ ነው:: የእግዚአብሔር በረከቶች ጊዜያዊ ስለሆኑ፣ በእነርሱ ላይ እምነታችንን ማሳረፍ የለብንም::

**በክርስቶስ ማመን:- የእግዚአብሔር ሥራ::**

ጥንት በቅፍርናሆም ብዙ ሰዎች ኢየሱስን እንደፈለጉት ዛሬም ብዙ ሰዎች እርሱን ለበረከቶቹ ሲሉ ይከተሉታል:: እግዚአብሔር ሰዎችን ሲፈውስ ትታመንበት ይሆናል፣ ነገር ግን አንድ ሰው ባይፈወስና እንዲያውም ቢሞት አሁንም በእርሱ መታመንን ትቀጥላለህን? እግዚአብሔር ለኪራይ ገንዘብ ቢሰጥህ ትታመንበታለህ፣ ነገር ግን ኪራይ የመክፈያህ ጊዜ ደርሶ ገንዘቡ ባይገኝ በእርሱ መታመንን ትቀጥላለህን? እግዚአብሔር ልጆችህን ቢጠብቅልህ ትታመንበታለህ፣ ነገር ግን አንዱ ልጅህ የሀሺሽ ሱሰኛ ቢሆን ወይም ከመንግሥት ሕግ ጋር ችግር ቢኖረው በእርሱ መታመንን ትቀጥላለህን? እምነትህ ያለው የት ነው? በክርስቶስ ላይ ነው ወይስ እርሱ

በሚያደርግልህ ነገር ላይ ነው? በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ እምነታችን በእግዚአብሔር ውጤቶች (በረከቶች) ላይ ከመሆን ይልቅ በይበልጥ በእግዚአብሔር ባሕርይ ላይ ነው::

በዚያን ዕለት ለእነዚያ ለፈለጉት ሰዎች ኢየሱስ የሰጣቸው ምላሽ ፀጉራቸውን ሳያቆመው አልቀረም፣ ምክንያቱም ከዚያ በኋላ የሚገዳደሩ ጥያቄዎችን ጠይቀው ነበር:-

> እነርሱም፣ "ታዲያ የእግዚአብሔን ሥራ ለመሥራት ምን ማድረግ አለብን?" አሉት::
>
> ኢየሱስም፣ "እርሱ በላከው ታምኑ ዘንድ፣ ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው" ሲል መለሰላቸው::
>
> ስለዚህ እንዲህ ብለው ጠየቁት፣ "አይተን እንድናምንህ ምን ታምራዊ ምልክት ታደርጋለህ? ምንስ ትሠራለህ? ይበሉ ዘንድ ከሰማይ እንጀራን ሰጣቸው ተብሎ እንደተጻፈ አባቶቻችን በምድር በዳ መና በሉ"::
>
> ኢየሱስም እንዲህ አላቸው "እውነት እላችኋለሁ፣ ከሰማይ እንጀራ የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም እውነተኛውን እንጀራ ከሰማይ የሚሰጣችሁ ግን አባቴ ነው:: የእግዚአብሔር እንጀራ እርሱ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነውና" (ዮሐንስ 6፥28-33)::

ሰዎቹ ግራ ገብቶአቸው ነበር:: በዐጭር አነጋገር፣ ለኢየሱስ እንዲህ አሉት፤ "እሺ እንግዲህ ለእንጀራ ወይም ለአሣ፣ ወይም ከአንተ ለምናገኘው ለሌላ ለማንኛውም ነገር የማንከተልህ ከሆነ ታዲያ ምን ማድረግ ይኖርብናል?"

ኢየሱስም መልሶ "ቀላል ነው፣ አብ በላከው እመኑ" አላቸው:: በሌላ አነጋገር፣ በእንጀራው አትመኑ፣ በአሣው አትመኑ፣ በተአምራት አትመኑ፣ በእግዚአብሔር ድርጊቶች ላይ እምነታችሁን አታሳርፉ፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር እናንተ እንደምትጠብቁት ላያደርግ ይችላል:: ይህ ማለት ግን እርሱ የማይታመን ወይም እምነት ሊጣልበት የማይገባ ነው ማለት አይደለም:: በዐጭሩ የእርሱ ዕላማና ፈቃድ ሁልጊዜ ውስን በሆነው በእኛ አመለካከት ሙሉ በሙሉ የማይታዩ ናቸው ማለት ነው:: የእግዚአብሔር ዕላማ ሁልጊዜ ከማንኛውም የእኛ የግል አመለካከትና ሁኔታ የላቀ ነው:: ይህም በሥራዎቹ ላይ ሳይሆን በእርሱ ላይ እንድንተማመን የሚፈልገው በዚህ ነው:: መነሻ ምክንያታችንን ከነገሮች ላይ ወደ እርሱና ወደ ባሕርዩ



ይቀይረዋል፣ ምክንያቱም ነገሮች ስለሚለዋወጡ ነው:: ነገሮች ይበላሻሉ፣ ነገሮች ይዝጋሉ፣ ይሰበራሉ ወይም ያረጁና ይጠፋሉ:: ነገሮች ጊዜያዊ ስለሆኑ እምነት ልንጥልባቸው የሚገቡ አይደሉም:: እግዚአብሔር ያህዌና የእርሱ ክርስቶስ ዘላዓለማዊ ናቸው፣ ዘላቂነት ያለውም ለእርሱ ጥበቃ የተሰጠ ነገር ብቻ ነው::

በተአምራቱ ቀን በኢየሱስ ዙሪያ የነበሩት ሰዎች የራሳቸውን እንጀራና አሣ የመመገብ ልምምድን መና (እንጀራ) ከሰማይ ወርዶላቸው ከበሉት ከእስራኤላውያን ልምምድ ጋር ለማወዳደር ሞከሩ:: ምናልባት እነርሱ ሙሴን የተከተሉት በተአምራቱ ምክንያት ስለመሆኑ ኢየሱስን ለማሳመን ፈልገው ሊሆን ይችላል፣ ይኸውም ሙሴን የተከተሉት በመናው፣ ከግብፅ ባርነት ነፃ በማውጣቱ፣ የቀይ ባሕር በመክፈሉ ነው ለማለት ፈልገው ይሆናል:: ኢየሱስም መናው የመጣው ከእግዚአብሔር እንጂ ከሙሴ አይደለም በማለት መለሰ:: በተአምራት ላይ መተማመን አደገኛ ነው:: ምክንያቱም ተአምራት ጊዜያዊ በመሆናቸው ነው:: የወለድ ክፍያ ጊዜያዊ ነው፤ የመኪና ክፍያ ጊዜያዊ ነው፤ እግዚአብሔር አሳቡን ካልገለጸ በስተቀር እርሱ ምን እንደሚያስብ ለማወቅ ፈጽሞ አንችልም:: እርሱ የወለድ ክፍያን ወይም የመኪና ክፍያን ሊሰጥ ይችላል፣ ወይም ምንም እንኳ ክፍያን ባናገኝ ከእርሱ ጋር በሰላም መቀጠላችንን ለማረጋገጥ ሊፈትነን ይችላል::

ኢየሱስም እምነታችንን በአምላክ ነገሮች ላይ ሳይሆን በነገሮቹ አምላክ ላይ እንድናሳርፍ የነገረን በዚህ ምክንያት ነው:: እርሱም "እውነተኛውን እንጀራ ከሰማይ የሚሰጣችሁ ግን አባቴ ነው፤ የእግዚአብሔር እንጀራ እርሱ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነውና" አላቸው:: በዚህ ውስጥ የተጠቀሰው ሁለት ዐይነት እንጀራ ነው፡ የመጀመሪያው እንደ መና ወይም ኢየሱስ ሕዝቡን ለመመገብ እንደሰጣቸው እንጀራ ያለ የበረከት እንጀራ ነው:: ሁለተኛው ዐይነት እንጀራ ከሰማይ የወረደው "እውነተኛ እንጀራ" ወይም የእግዚአብሔር "እንጀራ" ነው:: የበረከቱ እንጀራና እውነተኛው እንጀራ ሁለቱም ከአንድ ሥፍራ ከሰማይ የመጡ ናቸው:: ነገር ግን የበረከቱ እንጀራ ጊዜያዊ ነው:: በእርሱ መርካት የለብንም:: የበረከቱ እንጀራ ዐላማ እውነተኛውን እንጀራ እንድንራብ ፍላጐታችንን መቀስቀስ ነው:: የእውነተኛው እንጀራ ባሕርይስ ምንድነው? ከሕዝቡ ጋር የተካሄደው የዚህ ንግግር መርሕ ከሀብቱ ይልቅ ምንጩ ይበልጥ ዋና ነገር መሆኑን፣ እንዲሁም ከምርቱ ይልቅ አምራቹ ይበልጥ ዋና ነገር መሆኑን ሊያስተምረን ነው:: ይህ ወሳኝ ነገር ነው፤ ምክንያቱም ሀብቱ አላቂ ሲሆን ምንጩ ግን ቋሚ ስለሆነ ነው:: እምነታችንን በምንጩ ላይ እንጂ በሀብቱ ላይ ማድረግ ፈጽሞ የለብንም:: ኢየሱስም እንዲህ አለ፤

እነርሱም “ጌታ እንግዲያውስ ይህን እንጀራ ሁልጊዜ ስጠን አሉት። ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፣ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፣ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔም የሚያምን ፈጽሞ አይጠማም፤ ነገር ግን እንደ ነገርኋችሁ አይታችሁኝም እንኳ አታምኑም” (ዮሐንስ 6፥34-36)።

በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ዋናው ጉዳይ ምን ያህል እምነት እንዳለህ ሳይሆን ነገር ግን እምነትህ ያረፈው በምን ላይ ነው? የሚል ነው። የምትከተለው ኢየሱስን ነው? ወይስ ምልክትንና ድንቅን እንዲሁም ብልጽግናን ነው? እምነትህ “የሕይወት እንጀራ” በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው፣ ወይስ በበረከቱ እንጀራ ረክተሃል? መንፈስህን ለማርካት ትፈልጋለህ? ወይስ ሆድህን ለመሙላት ብቻ ጥረት ታደርጋለህ? እውነተኛ እርካታ በማይሰጡት ነገሮች ላይ ትተማመናለህ? ወይስ ለዘላለም በሚያረካው በእየሱስ ላይ ትተማመናለህ? እኔ ያገኘኋቸው ብዙ ሰዎች እምነታቸውን የሚያሳርፉት በጋጋሪው ላይ ሳይሆን በእንጀራው ላይ ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት መርሕ ሀብትን ሳይሆን ምንጩን መተማመን ነው።

የእግዚአብሔር መንግሥት እያንዳንዱን ፍላጐታችንን ሙሉ በሙሉ ያረካል፣ ይህን አትሳሳቱ። ዳሩ ግን መተማመን ያለብን ፍላጐታችንን በሚያረኩት ነገሮች ላይ ሳይሆን በሰጪው በንጉሡ ላይ መሆን የሚኖርበት በዚሁ ምክንያት ነው። የመንግሥቱ ዜጋ እንደመሆናችን መጠን የእኛ ተግባር ንጉሡን መተማመን፣ ለእርሱ መታዘዝና እርሱን ማገልገል ነው። የእርሱ ተግባር እኛን መንከባከብ ነው፤ ኢየሱስ ከዚህ የሚከተለውን ሲናገር ይህንኑ ማለቱ ነው፤

> ስለዚህ ምን እንበላለን? ምን እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ አሕዛብ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ለማግኘት ይጨነቃሉና፤ የሰማዩ አባታችሁም እነዚህ ሁሉ ለእናንተ እንደሚያስፈልጓችሁ ያውቃል። ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን እሹ፣ እነዚህ ሁሉ ይጨመሩላችኋል (ማቴዎስ 6፥31-33)።

እግዚአብሔርን የምንከተለው ከእርሱ ለምናገኘው ነገር አይደለም፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት በንጉሡ ላይ ያለ እምነት እንጂ በንጉሡ ሊጋስ ስጦታ ላይ አይደለም። በእርሱ ላይ ያለ እምነት ነው እንጂ በስጦታው ላይ አይደለም።



**እምነት በአስቸጋሪ ሁኔታ ሲከበብ**

ዕድሜዬን ሙሉ በካሪቢያን ውብ በሆኑት በባሃማስ ደሴቶች ውስጥ ስኖር እንደ መስተዋት የጠራውን ውቅያኖስ፣ የተትረፈረፈ የባሕር ምግብ፣ በዓመት በአማካይ 75 ዲግሪ የሆነውን የአየር ሙቀት መጠን፣ ብዙዎች በአገራችን እንዲቀኑ ያደረጋቸውን የምጣኔ ሀብትና የፖለቲካ መረጋጋት፣ ለዓመታት ዐምስት ሚሊዮን ቱሪስቶችን ወደ ጠረፋችን የሳበውን የሕዝባችንን የሞቀ መንፈስ ስደሰትበት ቆይቻለሁ። ይሁን እንጂ ሕይወት በየቀኑ እንደ ሕልም የሆነበት ይህ የደሴት ገነት ደግሞ በዓመታዊው አውሎ ነፋስ ወይም ዝናብ አዘል አውሎ ንፋስ ባለበት መስመር ላይ የተዘረጋ ነው። በእነዚህ ውብ ደሴቶች ውስጥ በምኖርበት ዘመን የተፈጥሮን፣ የሕንፃዎችንና የሰዎችን ዘላቂነት የሚፈታተኑ ብቻ ሳይሆን፣ በእነዚህ አስፈሪ ማዕበሎች ውስጥ በሚመራን የመንግሥት አስተዳደር መዋቅር ላይ ያለንን አመኔታ ጭምር የሚፈታተኑ ብዙ ታላላቅ አውሎ ንፋሶችን አሳልፈናል። እንደዚሁም ሁሉ፣ የእግዚብሔር መንግሥት እምነት የታቀደው ለመልካም ጊዜ ብቻ ሳይሆን ለአስቸጋሪ ጊዜም ነው። ልጅ ሳለሁ እንዲሁም ዛሬ ጐልማሳ ሆኜ፣ ቤተሰባችን በአንድነት በሬዲዮ ዙሪያ ተሰብስቦ መንግሥት በብሔራዊው የሬዲዮ ማሠራጫ ኮርፖሬሽን በየደቂቃው የሚሰጠውን የማዕበሎቹን መግለጫ እናዳምጥ እንደ ነበር አስታውሳለሁ። በሰዓት 130 ማይልስ የሚበርረው ንፋስ ሲተምምና ዛፎች በአካባቢያችን ሲወድቁ የቤታችን ጣራ ሲነቃነቅ ነበር፤ የመብረቁን ጩኸትና ብልጭታ ስንሰማ መዳናችንን እንድንጠራጠር ያደርገን ነበር።

የእኛ መላው አመኔታችን የተመሠረተው በመንግሥት ባለሥልጣኖችና እኛን እንዲጠብቁና ደህንነታችንን እንዲያረጋግጡ በተሰጡት የሕንፃ ግንባታ ደንቦች (ኰድስ) ላይ ነበር። የአገራችን የመንግሥት የሕንፃ ግንባታ ደንቦች የተወሰኑት ቤታችን በአውሎ ንፋሱ አካባቢ በመሆኑና ደንቦቹንም በመከተል እንዲሁም የቤታችንን መሠረት በዚሁ ደንብ በመሥራታችን ነበር። ይህ ከሆነ ቤቱ ማዕበሉን ሊቋቋም ስለመቻሉ መንግሥት ዋስትና ይሰጣል። ይህንን ረቂቅ በምጽፍበት ጊዜ በትልቅ ማዕበል ወቅት ቤታችን በላያችን ላይ ወድቆ የማያውቅ መሆኑን ስገልጽ ደስ ይለኛል። በዐጭሩ፣ የመንግሥት የሕንፃ ደንቦች አገሪቱን ለማይቀረው ፈተና የሚያዘጋጁ ናቸው። እኛ ለደንቦቹ ያለን ታዛዥነት በማዕበሎቹ ውስጥ ሰላምንና ልበ ሙሉነትን በመስጠት ፍርሃትንም ይቀንሳል።

በምድር ላይ ቅኝ ግዛት የመሠረተው መንፈሳዊ ልዕለ ተፈጥሮአዊ የሆነው የመንግሥተ ሰማያት አገርም ከዚህ የተለየ አይደለም። ሰማያዊው መንግሥትና የእርሱ ሕገ መንግሥታዊ የተስፋ ቃሎች ለዜጐቹ የደህንነት

ዋስትናን ይሰጣሉ፤ ስለሆነም ለመንግሥቱ ማህበረሰብ በሕይወት ውስጥ ለሚደርሱ ማዕበሎች የታቀዱ የግንባታ ደንቦችን ያዘጋጃል:: ብዙ የመንግሥቱ ዜጎች በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ በሚያልፉበት ጊዜ 'በቂ እምነት የለንም ማለት ነው' ብለው ያስባሉ:: ነገሩ እንደዚህ አይደለም፣ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ከችግር ነፃ አያወጣንም፣ ነገር ግን በችግሩ ውስጥ ያፀናናል፣ ይጠብቀናልም:: አሁንም እንደገና ቁልፉ እምነታችንን የምናሳርፍበት ቦታ እንጂ የእምነታችን ብዛት አይደለም:: በአንድ ወቅት ሰማያዊው ንጉሥ በመንግሥቱ የግንባታ ደንብ ውስጥ ይህንኑ የእምነት ጉዳይ ጠቅሶአል:-

> እንግዲህ ይህን ቃሌን ሰምቶ በተግባር የሚያውል ቤቱን በዐለት ላይ የሠራን ብልህ ሰው ይመስላል:: ዶፍ ወረደ፣ ጐርፍም ጐረፈ፣ ነፋስም ነፈሰ፣ ይንን ቤት መታው፣ በዐለት መሠረትም ላይ ስለ ተመሠረተ አልወደቀም:: ይህን ቃሌን ሰምቶ በተግባር የማያውለው ግን ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራን ሞኝ ሰው ይመስላል:: ዶፍ ወረደ ጐርፍም ጐረፈ፣ ነፋስም ነፈሰ ያንን ቤት መታው ቤቱም ወደቀ አወዳደቁም የከፋ ሆነ (ማቴዎስ 7፥24-27)::

በምድር ላይ ባለው የመንግሥቱ ዜጋ ሕይወት ውስጥ የፈተና፣ የመከራና የማዕበል ጉዳይ እንግዳና ያልተጠበቀ ነገር ሳይሆን ነገር ግን በልበ ሙሉነትና በእምነት የሚጠበቅ ነገር ነው:: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ማዕበልን በማቀፍ በመከራ ውስጥ ያለውን ጥቅም ያረጋግጣል:: የዚህ መንግሥት ንጉሥ በሌላ ወቅት ይህንን አሳብ ለዜጎቹ ሲገልጽ እንዲህ ብሎአል:-

> በእኔ ሰላም እንዲኖራችሁ ይህን ነግሬአችኋለሁ:: በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ:: ነገር ግን አይዞአችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ (ዮሐንስ 16፥33)::

ለእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች ዋስትና የሚሰጠው ሌላው መንግሥታዊ የተስፋ ቃል እንዲህ በማለት ነው:-

> እንግዲህ እባቡንና ጊንጡን እንድትረግጡ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣንን ሰጥቻችኋለሁ፣ የሚጐዳችሁም አንዳች ነገር አይኖርም (ሉቃስ 10፥19)::

አንድ ሰው፣ "ደህና፣ እግዚአብሔር መልካም ከሆነ ይህ ነገር በአንተ ላይ ለምን ይደርሳል?" በማለት ጠይቆህ ያውቃልን? ኢየሱስ በዚህ ውስጥ ይህን ጥያቄ ይመልሳል:: ምናልባት አስቸጋሪ ሁኔታዎች ለምን እንደሚያጋጥሙህ



ትጠይቅ፣ ወይም የመንግሥቱ ንጉሥ የአንተን ሁኔታ አያውቅ ይሆናል በማለት ትደነቅ ይሆናል:: ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት መከራን፣ ፈተናን፣ ተግዳሮትንና ሀዘንን በሚመለከት በእኛ ላይ ከሚደርሰው ነገር ጋር ምንም ግንኙነት የለውም:: ጌታ የመንግሥቱ ዜጐች በመሆናችን ብቻ በሕይወት ውስጥ ከሚደርሱ ችግሮች አያድነንም:: በተቃራኒው ግን እምነታችንን ለመፈተሽ፣ ለማጠንከርና ለማጥራት ሲል መከራ እንዲያገኘን ይፈቅዳል:: በችግር ውስጥ መጽናትን መማር ባሕርያችንን በመቅረጽ በሳል እንዲሆን ያደርገዋል::

ይህንን አሳብ ለመቀበል የሚከብድህ ከሆነ የዳንኤልን ልምምድ ተመልከት:: አንተ በዳንኤል ቦታ ብትሆንና ለእግዚአብሔር በታማኝነት በመታዘዝህ የተራቡ አንበሶች በሞሉበት ጉድጓድ የምትጣል መሆኑ ቢነገርህ ምን ይሰማሃል? ምናልባት ዳንኤል ጸልዮ መልአክ እንዲመጣለት ጠብቆ ይሆናል:: ምንም መልአክ ብቅ አላለም:: ከዚያም ምናልባት ዳንኤል በልዕለ ተፈጥሮአዊ ሁኔታ ተለውጬ በንጉሡ በዳርዮስና በተከታዮቹ ፊት ወደ ላይ እነጠቃለሁ ብሎ ዐስቦ ሊሆን ይችላል:: ምንም መነጠቅ (መለወጥ) አልተፈጸመም::

ዳንኤልን በሰንሰለት አሥረው ወደ አንበሶች ጉድጓድ ሲወስዱት እግዚአብሔር በአዳራሹ ውስጥ በመንገድ ላይ ይዞኝ ሰንሰለቱን አውልቆ ነፃ ይለቅቀኛል በማለት ዐስቦ ሊሆን ይችላል፣ ይህም አልሆነም:: ዳንኤል አንበሶቹ ሲያገሱ በሚሰማበት ጊዜ እግዚአብሔር የት አለ በማለት ሳይደነቅ አይቀርም:: በጉድጓድ ውስጥ በተጣለና በተራቡት አንበሶች በተከበበ ጊዜ እግዚአብሔር የት እንዳለ አወቀ - ይኸውም በዚያው በጉድጓድ ውስጥ ከእርሱ ጋር ነበር! እግዚአብሔር በአገልጋዩ ላይ ምንም ጉዳት እንዳይደርስበት ከዳንኤል በፊት የአንበሶቹን አፍ እንዲዘጋ መልአኩን ልኮ ነበር:: ዳንኤልን አዳነው፣ ነገር ግን ያዳነው አስቀድሞ ውጤቱን ሳያውቅ በአንበሶቹ ጉድጓድ መከራ ውስጥ ከገባ በኋላ ነበር:: እግዚአብሔር የት ነበር? ዳንኤል እምነቱን በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ከማድረግ ይልቅ በራሱ በእግዚአብሔር ላይ አደረገ (ሙሉውን ታሪክ ከዳንኤል ምዕራፍ 6 ይመልከቱ)::

ዛሬ በሃይማኖታዊው ማህበረሰብ የዳንኤል ዐይነት ጥራት ያለው የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት በጣም ብርቅ ነው:: ምክንያቱም በዘመናችን ያሉት አስተምህሮዎችና የእምነት ዘዴዎች በሚፀናና በሚያሸንፍ እምነት ላይ ከማተኮር ይልቅ ግልብ በሆነ "በመሸሸ እምነት" ላይ ይበልጥ ስለሚያተኩር ነው:: ይህም ዘለዓለማዊ የሆነውን የመንግሥትን ኃይል የሚያረጋግጡትን እነዚህን ጊዜያዊ ዕድሎች ከመጋፈጥ፣ ከመጽናትና

ከማሸነፍ ይልቅ ችግሮች፣ መከራዎችንና ፈተናዎችን በመሸሽ ላይ የተመሠረተ እምነት ነው:: ለዛሬዋ ዓለማችን መመለስ የዳንኤል ዐይነት እምነት ያስፈልገናል::

የእነ ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጐም ሁኔታ ተመሳሳይ ነው፣ እነርሱም ትድግናቸውን ከማግኘታቸውና እግዚአብሔር በእሳቱ ውስጥ ከእነርሱ ጋር መሆኑን ከማወቃቸው በፊት በሚነደው እሳት ውስጥ መግባት ነበረባቸው (ዳንኤል ምዕራፍ 3 ይመልከቱ):: የእነዚህ ሦስት ዕብራውያን ወጣቶች ታሪክ ታላቅ የሆነ የመጽናናት ምንጭና ጉልህ የሆነ እውነተኛ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ምሳሌ ሊሆን ይገባዋል:: እንግዲህ እነርሱ ከሌላ አገር መንግሥት ጋር ያደረጉትን የፊት ለፊት ፍጥጫ እንጥቀስና የእግዚአብሔር አሳብ ለእነርሱ ጥቅም ያንቀሳቀሰውን የእምነታቸውን ገንዘብ ከፍተኛነት እንመልከት፦

> ከዚያ በኋላ ንጉሡ የቤተ መንግሥቱን ጃንደረቦች አለቃ አስፋኔዝን ከንጉሣዊው ቤተሰብና ከመሳፍንቱ ዘር የሆኑትን እስራኤላውያንን እንዲያመጣ አዘዘው፤ እነርሱም የአካል ጉዳት የሌለባቸው መልከ መልካሞች፣ ማንኛውንም ትምህርት የመማር ችሎታ ያላቸው ዕውቀት የሞላባቸው፣ ሁሉን ነገር በፍጥነት መረዳት የሚችሉትን በንጉሡም ቤት ለማገልገል ብቃት ያላቸው ወጣት ወንዶች ናቸው የባቢሎናውያንን ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ እንዲያስተምራቸውም አዘዘው ንጉሡም በየዕለቱ የሚበሉትን ምግብና የሚጠጡትን የወይን ጠጅ ከንጉሡ ማዕድ ድርጐ እንዲሰጣቸው አደረገ:: ለሦስት ዓመት ከሠለጠኑ በኋላ በንጉሡ አገልግሎት ላይ የሚሠሩ ናቸው::
>
> ከነዚህም መካከል ከይሁዳ የመጡት ዳንኤል፣ አናንያ፣ ሚሳኤልና አዛርያ ነበሩ፤ የጃንደረቦቹ አለቃም ዐዲስ ስም አወጣላቸው፣ ዳንኤልን ብልጣሶር፣ አናንያን ሲድራቅ፣ ሚሳኤልን ሚሳቅ፣ አዛርያን አብድናጐ ብሎ ጠራቸው (ዳንኤል 1፥3-7)::
>
> ከዚህም በላይ በዳንኤል አሳሳቢነት ንጉሡ ሲድራቅን፣ ሚሳቅንና አብድናጐን የባቢሎን አውራጃ አስተዳዳሪዎች አድርጐ ሾማቸው ዳንኤል ግን በቤተ መንግሥት ተቀመጠ (ዳንኤል 2፥49)::



> ... እነዚህንም ሰዎች በንጉሡ ፊት አቀረቧቸው:: ናቡከደነፆርም እንዲህ አላቸው፣ ሲድራቅ ሚሳቅና አብድናጐ ሆይ፣ እኔ ላቆምሁት ምስል አለመስገዳችሁ አማልክቴንም አለማገልገላችሁ እውነት ነው? አሁንም ቢሆን የመለከቱንና የእምቢልታውን የመሰንቆውንና የክራሩን፣ የበገናውንና የዋሽንቱን፣ የዘፈኑንም ሁሉ ድምፅ ስትሰሙ እኔ ላቆምሁት የወርቅ ምስል ተደፍታችሁ ለመስገድ ዝግጁ ከሆናችሁ መልካም! ባትሰግዱለት ግን ወዲያውኑ ወደሚንበለበለው እቶን እሳት ውስጥ ትጣላላችሁ፤ ታዲያ ከእጄ ሊያድናችሁ የሚችል አምላክ ማን ነው?
>
> ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጐ ለንጉሡ እንዲህ ብለው መለሱ፣ ናቡከደነፆር ሆይ፣ በዚህ ጉዳይ ስለ ራሳችን መልስ መስጠት አያስፈልገንም፣ ንጉሥ ሆይ፣ በሚንበለበለው የእቶን እሳት ውስጥ ብንጣል የምናመልከው አምላክ ሊያድነን ይችላል፤ ከእጅህም ያድነናል፤ ነገር ግን ንጉሥ ሆይ ባያድነንም እንኳ፣ አማልክትህን እንደማናገለግል ላቆምኸውም የወርቅ ምስል እንደማንሰግድ ዕወቅ (ዳንኤል 3፥13 -18)::

በእነዚህ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጐች እምነት ውስጥ አስገራሚ የሆነው ነገር እግዚአብሔር ባያድናቸው እንኳ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደፀና የሚቆይ መሆኑን የገለጹበት እምነት ነው:: ይህ እውነተኛ የመንግሥት እምነት ስለሆነ እኛም በመንግሥቱ ውስጥ ሳለን በየዕለቱ ኑሮአችን ውስጥ ይህ እምነት መገኘት አለበት:: እኛ ስለ እግዚአብሔር ዕቅድ ያለን አስተሳሰብ ግቡን በማይመታበት ጊዜ እንኳ የፀና እምነት ያስፈልገናል፤ ይህም እምነት ዘላለማዊነቱን ለማረጋገጥ በእሳት ውስጥ ለመቃጠል ፈቃደኛ የሚሆን እምነት ነው:: ሐዋርያው ጴጥሮስ የእግዚአብሔር መንግሥት አምባሳደር እንደመሆኑ መጠን እንዲህ አለ፤

> አሁን በብዙ ዓይነት ፈተና ውስጥ ሆናችሁ ለጥቂት ጊዜ መከራን ብትቀበሉም እንኳ በዚህ እጅግ ደስ ይላችኋል:: እነዚህ ነገሮች በእናንተ ላይ የደረሱት በእሳት ተፈትኖ ቢጠራም ጠፊ ከሆነው ወርቅ ይልቅ እጅግ የከበረው እምነታችሁ እውነተኛ መሆኑ እንደተረጋገጠና ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ምስጋናን፣ ክብርንና ውዳሴን እንዲያስገኝላችሁ ነው (1ጴጥሮስ 1፥6-7)::

እምነትህ ይበልጥ በተፈተነ መጠን በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ ያለህ ልበ ሙሉነት ይበልጥ ያድጋል፡፡ ይህም እኔ በምኖርበት በካሪቢያን የአውሎ ነፋስ ልምምድ ውስጥ ተመሳሳይ የሆነ ነገር ነው፡፡ ከአንድ ታላቅ አውሎ ነፋስ በምንተርፍበት ጊዜ የሚቀጥለውን ለመጋፈጥ ያለን ፍርሀትና ጠባሳ ይቀንሳል፣ በመጨረሻም በአካባቢያችን እንደ ተለመደ የሕይወት ክፍል እንመለከተውና እንዲያውም እንዲህ ያለው የተፈጥሮ ክስተት ያለውን ጥቅም ማመስገን እንጀምራለን፡፡ አውሎ ነፋሶች በመንግሥት ደንብ መሠረት ያልተሠሩ ቤቶችን ያስወግዳሉ፣ የበሰበሱ ዛፎችን ይደመስሳሉ፣ በአየር ውስጥ ያለ ብክለትን ያጠራሉ፤ ብሎም ዐዲስ እድገትንና ዐዲስ ጅማሬን ያነሳሳሉ፡፡

ጳውሎስና ሲላስ የክርስቶስን ወንጌል በመስበካቸው በፊልጵስዮስ ከተማ በእስር ቤት ውስጥ ተጥለው በግንድ ተጠርቀው ነበር፤ በሁኔታቸው በማልቀስና በማዘን ፈንታ በዚያው በእስር ቤቱ ውስጥ እግዚአብሔርን ያመልኩና መዝሙር ይዘምሩ ነበር፤ እግዚአብሔርም እስረኞቹን በሙሉ ያስለቀቀ የመሬት መናወጥ ሰደደ፣ ከዚህም የተነሣ የወህኒው ጠባቂ ከመላው ቤተሰቡ ጋር ወደ ክርስቶስ ተመለሰ (የሐዋ 16፥16-34 ይመልከቱ)፡፡

እምነታችን በእግዚአብሔር ላይ ከሆነ በአካባቢያችን ምንም ነገር ቢፈጸም ልዩነት የለውም፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር የፀና ነው፡፡ እርሱ አይለወጥም ወይም ሥፍራውን አይለቅም፣ እርሱ ትናንት፣ ዛሬም፣ ለዘላለምም ያው ነው (ዕብ 13፥8)፡፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ "ሥጋዬን ብሉ፣ እኔ የምሰጣችሁን ነገር አትብሉ፣ እኔን ብሉ፣ ደሜን ጠጡ፣ የሕይወትን በረከቶች አትጠጡ፣ እኔን ጠጡ፣ ይህ ከሆነ ሕይወት ይኖራችኋል" (ዮሐንስ 6፥53-57 ይመልከቱ)፡፡ እምነታችን በእርሱ ላይ ከሆነ ማንኛውንም ነገር እንችላለን፣ ምክንያቱም በራሳችን ሳይሆን በእርሱ ኃይል ስለምንተማመን ነው፡፡ ደግሞም እርሱ ከምንችለው በላይ እንድንፈተን ስለማይፈቅድ ነው፡- "በሰዎች ሁሉ ላይ ከደረሰው የተለየ ፈተና አልደረሰባችሁም፣ እግዚአብሔር ታማኝ ነው፣ ስለዚህ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አይተዋችሁም፤ ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን መታገስ እንድትችሉ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል" (1ቆሮንቶስ 10፥13)፡፡

ጥንካሬህ ምን ያህል ነው? የጥንካሬህ መጠን እምነትህ ከአንድ ፈተና በሚተርፍበት መጠን ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ሁልጊዜ ይፈተናል፡፡ ጥንካሬው የሚያድገውም በዚህ ሁኔታ ነው፡፡ ጡንቻዎቻችን በሥራ ላይ ሲውሉ እንደሚጠነከሩ ሁሉ እምነታችንም በሥራ ላይ ሲውል ይበልጥ ይጠነክራል፡፡ ታላላቆቹ የእምነት ፈተናዎች ከዚህም የተነሣ ታላላቆቹ የእድገት እምቅ ኃይሎች ከችግር ወቅቶች የሚገኙ ናቸው፡፡ ስለዚህ በጌታ የምትተማመን ከሆነ ለእነዚህ ፈተናዎች ተዘጋጅ፣ የፈተና ቀን እየደረሰ



ነው፤ ሥራህን ወይም ቤትህን ብታጣ፣ ወይም ልጅህ ቢታመምና ጸሎትህም ተጨባጭ ውጤት ባይኖረው ሁሉን አዋቂ በሆነው በእግዚአብሔር መልካምነት ማመንህን ትቀጥላለህን? በአንተ የሕይወት ጉዳይ እንደ ዣንጥላ ከለላ በሆነው ሰማያዊ መንግሥት ልበ ሙሉነት ይሰማሃልን? ያ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ነው!

## ፈተናውን ታልፋለህን?

በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ብዙ ዜጎች ንጉሡን የሚከተሉት ለመልካም ጊዜዎችና ለመልካም ነገሮች ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ በክርስቲያን ሃይማኖት ማህበረ ሰብ ያገኘኋቸው አብዛኞቹ ሰዎች በአገሩ ውስጥ እንደ ዜጋ በመኖር በኃላፊነት፣ በግዴታዎች እንዲሁም ለሕጉ ለመታዘዝ፣ ሕብረትን ለመጠበቅና በመንግሥቱ ህብረተ ሰብ መርሕ መሠረት ለመሥራት ከመትጋት ይልቅ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት በግል ጥቅም ላይ የተመሠረተ ይመስላል፡፡ ብዙ ሃይማኖተኛ አማኞች እግዚአብሔርን የሚመለከቱት የግል ምኞታቸውን እንዲያሟላላቸው እንደ ፈለጉት የሚጠመዝዙት በጠርሙስ ውስጥ እንዳለ እንደ አንድ ማሙሽ አድርገው ነው፡፡ በቅፍርናሆም መንደር የነበሩት ሰዎች የነፃ እንጀራና አሣ ከመገባቸው በኋላ ኢየሱስ በጐበኛቸው ጊዜ የነበራቸው ዝንባሌ ይኸው ነበር፤ ያንን ግንኙነት እንደገና እንመልከተው፡-

> ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፣ "እውነት እላችኋለሁ፣ የምትፈልጉኝ እንጀራ ስለ በላችሁና ስለ ጠገባችሁ እንጂ ታምራዊ ምልክቶችን ስላያችሁ አይደለም፣ ለሚጠፋ እንጀራ አትሥሩ፣ ነገር ግን የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር ምግብ ሥሩ፤ ለዚህም እግዚአብሔር አብ ማረጋገጫ ማህተሙን በእርሱ ላይ አትሞአልና፡፡ እነርሱም ታዲያ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ምን ማድረግ አለብን? አሉት ኢየሱስም እርሱ በላከው ታምኑ ዘንድ ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው" ሲል መለሰላቸው (ዮሐንስ 6፥26-29)፡፡

በእርሱ ግምገማ መሠረት እርሱን ለመከተል የነበራቸው መነሻ ምክንያት ከእርሱ ለሚያገኙት ነገር ነበር፡፡ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ዜግነትና ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ መንግሥቱን ለማገልገል ስላለባቸው ግዴታ ምንም ግንዛቤ አልነበራቸውም፡፡ "ለሚጠፋ እንጀራ አትሥሩ" የሚለው የንጉሡ አነጋገር በእግዚአብሔር ላይ ያለን እምነት ከዚያ ግንኙነት በምናገኘው

ጥቅም ላይ የሚመሠረት ሳይሆን ዜጐቹን በሚያፈቅረው በንጉሡ ጠባይና ባሕርይ ላይ የሚመሠረት መሆን እንዳለበት ያመለክታል፡- ኢየሱስ ንግግሩን በሚቀጥልበት ጊዜ እነዚህን ቃላት ተመልከቱ፡-

> እውነት እላችኋለሁ፣ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት አለው፤ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ፤ ይሁን እንጂ ሞቱ፡፡ ነገር ግን ሰው እንዳይሞት ይበላው ዘንድ ከሰማይ የሚወርድ እንጀራ ይህ ነው፡፡ ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ ማንም ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፡፡ ይህም እንጀራ ለዓለም ሕይወት እንዲሆን የምሰጠው ሥጋዬ ነው (ዮሐንስ 6፥47-51)፡፡

እርሱ የእምነታቸውን ጥራትና ዐላማ እየፈተሸና ያለ ቦታው የተቀመጠ ትኩረታቸውን እያስተካከለ ነበር፡፡

በዚያን ቀን በቅፍርናሆም ከኢየሱስ ጋር ከተነበሩት ሰዎች ብዙዎቹ የእምነትን ፈተና ወድቀዋል፡፡ በአጠቃላይ ለእግዚአብሔር መንግሥት እምነት የሚፈለገው ጥሪ ተግዳሮትን መጋፈጥ፣ እንቅፋትን ማሸነፍና በችግሮች ላይ ድልን መቀዳጀት ነው፡፡ ነገር ግን ብዙ ሰዎች ይህን ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኞች አይደሉም፡፡ ይህም በርግጠኝነት ኢየሱስ ሥጋውን ስለመብላትና ደሙን ስለመጠጣት ባደረገው ጥሪ በተሰናከሉት በአብዛኛዎቹ በቅፍርናሆም ሰዎች ዘንድ እውነት የሆነ ነገር ነበር፡፡

> ከደቀመዛሙርቱ ብዙዎች ይህን ሲሰሙ፣ "ይህ የሚያስጨንቅ ቃል ነው፣ ማንስ ሊቀበለው ይችላል?" አሉ፡፡
>
> ከዚህም በኋላ ከደቀመዛሙርቱ ብዙዎች ወደ ኋላ ተመለሱ፣ ከዚያም ወዲያ አልተከተሉትም፡፡ ኢየሱስም ዐሥራ ሁለቱን "እናንተም ደግሞ መሄድ ትፈልጋላችሁ?" አላቸው፡፡
>
> ስምዖን ጴጥሮስም እንዲህ ሲል መለሰለት "ጌታ ሆይ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ፣ አንተ አንድያ የእግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆንህ አምነናል ዐውቀናልም" (ዮሐንስ 6፥60፤66-69)፡፡



ሰዎቹ የኢየሱስን ቃሎች "የሚያስጨንቅ ቃል" እንደሆነ የገመቱት ለምን ነበር? ለዚህ ምክንያቱ ምንም አሣና እንጀራ ለመመገብ ተስፋ ሳይሰጣቸው እንዲከተሉት ጥሪ ያደረገላቸው መሆኑን በመገንዘባቸው ነበር፡፡ በእርሱና በእርሱ ብቻ እንዲረኩ ጥሪ አደረገላቸው፣ በቅድሚያ ውጤቱን ሳያውቁ እንዲከተሉት ጥሪ አደረገላቸው፣ የወደፊቱን በእርሱ እጅ በመተው እንዲረኩ ነበር፡፡

በዚህም እንደገና ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጐ በንጉሡ በናቡከደነፆር ፊት ይህን ዐይነት እምነት በተግባር አሳዩ፣ እነርሱ እርሱ ላቆመው ታላቅ ምስል ባለመስገድ የንጉሡን ትእዛዝ በመተላለፋቸው በእቶን እሳት ውስጥ እንዲገቡ ተፈርዶባቸው ነበር፡፡ ትዕቢተኛው ንጉሥ ምን ዐይነት አምላክ ከእጁ ሊያድናቸው እንደሚችል ለማወቅ ፈለገ፡-

> ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጐ ለንጉሡ እንዲህ ብለው መለሱ፤ ናቡከደነፆር ሆይ በዚህ ጉዳይ ላይ ስለራሳችን መልስ መስጠት አያስፈልገንም፡፡ ንጉሥ ሆይ፣ በሚንበለበለው የእቶን እሳት ውስጥ ብንጣል የምናመልከው አምላክ ሊያድነን ይችላል፣ ከእጅህም ያድነናል፡፡ ነገር ግን ንጉሥ ሆይ፣ ባያድነንም እንኳ አማልክትህን እንደማናገለግል፣ ላቆምኸውም የወርቅ ምስል እንደማንሰግድ ዕወቅ (ዳንኤል 3፥16-18)፡፡

ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ነው፡፡ ይህም እምነት ቢባርከም ባይባርከም፣ ቢታደግም ባይታደግም፣ ቢፈውስም ባይፈውስም በእግዚአብሔር ላይ የሚተማመን እምነት ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ምንም ሆነ ምን በክርስቶስ ላይ ይተማመናል፣ ምክንያቱም እርሱ የዘላለም ሕይወት ቃል ያለው መሆኑን ስለሚያወቅ ነው፡፡ ደግሞም ንጉሥ ዳዊት "ምሕረትህ ከሕይወት ይበልጣልና ከንፈሮቼ ያመሰግኑሃል" (መዝ 63፥3) በማለት የገለጸውን እውነታ ስለሚገነዘብ ነው፡፡

በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ምን ማድረግ እንዳለብህ ግራ በገባህ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ተማመን! ዳዊት በሌላ መዝሙር እንዲህ አለ፡- "እግዚአብሔር ዐለቴ፣ መጠጊያዬና ታዳጊዬ ነው፣ አምላኬ የምሸሸግበት ዐለቴ እርሱ ጋሻዬ የደህንነቴ ቀንድና ዐምባዬ ነው (መዝ 18፥2)፡፡ በዐለቱ ላይ መልሕቅን ከጣልህ ማዕበሉ ችግር የለውም፡፡ እምነትህ በሕያው እግዚአብሔር ላይ ከሆነ በአካባቢህ ምንም ነገር ቢሆን ታሸንፋለህ፣ ብዙዎቹ የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ግን እርሱን ከመከተል ወደኋላ ተመለሱ፡፡ ዛሬም ብዙ ሰዎች እንደዚሁ አድርገዋል፤ ለምን? እነርሱ የአሣ ሳንድዊች ደቀመዛሙርት ነበሩ፡፡ እነርሱ ወደኋላ የተመለሱት ኢየሱስ አሣቸውንና

እንጀራቸውን ወስዶ በምትኩ ሥጋውንና ደሙን ስለሰጣቸው ነው:: እነርሱ ግን እርሱን አልፈለጉትም:: እርሱ ስጦታዎቹን ወስዶ ሰጪውን ሰጣቸው፣ እርሱን አልፈለጉትም እርሱ ድነትን ወስዶ አዳኙን ሰጣቸው፤ እርሱን አልፈለጉትም:: እርሱ በረከቶቹን ወስዶ ባራኪውን ሰጣቸው፣ እነርሱ እርሱን አልፈለጉትም:: በመንግሥት ውስጥ ንጉሡ ከመንግሥቱ ይበልጣል፤ ምክንያቱም መንግሥቱ ሕጋዊነቱን የሚያገኘው ከንጉሡ ስለሆነ ነው:: መንግሥቱ ንጉሡን ንጉሥ አያደርገውም፣ ነገር ግን ንጉሡ መንግሥቱን መንግሥት ያደርገዋል::

በዚህ በምድር ላይ ያለነው አሣና እንጀራ ለማግኘት ብቻ አይደለም:: እኛ በዚህ ያለነው ዓለምን ሕያው እንጀራ በመመገብ ለመለወጥ ነው:: እምነታችሁ ያለው የት ነው? በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ነው ወይስ በሚሠራው አምላክ ላይ ነው? አንተ "የአሣና የእንጀራ ክርስቲያን" ነህ? ወይስ "የሥጋና የደም" አማኝ ነህ? ለዚህ የምትሰጠው መልስ እምነትህ ፈተናውን የሚወድቅ ወይም በማንኛውም ማዕበል ውስጥ ፀንቶ የሚቆም መሆኑን ይወስናል:: የሞቃታማውን ገነት የሕይወት ውበትና ጥራት በምንደሰትበት በዚህ በባሃማስ ከአውሎ ነፋስ፣ ከማእበል፣ ወይም ከሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች ለመዳን መንግሥት ዋስትና አይሰጥም፣ ነገር ግን እንደ አስፈላጊነቱ ለጥበቃ፣ ለአቅርቦት፣ ለሀብትና ለተሃድሶ ዋስትና ይሰጣል:: የሰማያዊውም መንግሥት አገርና ቅኝ ግዛት ከዚህ የተለየ አይደለም:: ንጉሡ ኢየሱስ ክርስቶስ ከፈተናና ከመከራ ነፃ ለመሆን ዋስትና አይሰጥም:: እንደ እውነቱ ከሆነ፣ እነርሱ እንደሚመጡ ዋስትና ይሰጣል:: ኢየሱስ እንዲህ አለ፤

> እንግዲህ ይህን ቃሌን ሰምቶ በተግባር የሚያውል ቤቱን በዐለት ላይ የሠራን ብልህ ሰው ይመስላል:: ዶፍ ወረደ፣ ጐርፍም ጐረፈ፣ ነፋስም ነፈሰ፣ ያንን ቤት መታው፤ በዐለት መሠረትም ላይ ስለ ተመሠረተ አልወደቀም:: ይህን ቃሌን ሰምቶ በተግባር የማያውለው ግን ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራን ሞኝ ሰው ይመስላል፤ ዶፍ ወረደ፣ ጐርፍም ጐረፈ፣ ነፋስም ነፈሰ፣ ያንን ቤት መታው፣ ቤቱም ወደቀ፣ አወዳደቁም የከፋ ነበር (ማቴዎስ 7፥24-27)::

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ማዕበሎችን፣ ፈተናዎችንና መከራዎችን አይፈራም፣ ምክንያቱም ዜጐቹ ቤታቸውን የሠሩት በሰማያዊው መንግሥት የግንባታ መመሪያ መሠረት ስለሆነ ነው:: በዚህም ምክንያት የእነርሱ መሠረት እንደ ንጉሡ ቃል፣ ባሕርይና ተስፋ የማይነቃነቅ ጽኑ ዐለት ነው:: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት በዐለቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ መልሕቁን የጣለ ነው:: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ማዕበሉን



የሚጋፈጥና ማዕበሉም ካለፈ በኋላ ፀንቶ የሚቆም ነው:: የእናንተ እምነት ያለው የት ነው?

## የእግዚአብሔር መንግሥት መርሆች

- የእምነትህ ጥንካሬ የሚለካው ለማለፍ በሚችለው ፈተና መጠን ነው::
- የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ጥያቄ፦ "በጨለማ ቢሆንም እንኳ ብርሃኑን ትከተላለህን?"
- በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያለው ጉዳይ ምን ያህል እምነት አለህ? የሚል ሳይሆን እምነትህ ያረፈው በምን ላይ ነው? የሚል ነው::
- የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት መርሕ ሀብቱን ሳይሆን ምንጩን መተማመን ነው::
- በእግዚአብሔር መንግሥት ምን ማድረግ እንዳለብህ ግራ ሲገባህ በእግዚአብሔር ተማመን!

ምዕራፍ ሁለት

## እምነት፡- የእግዚአብሔር መንግሥት ባህል

*"እምነት ማለት ከአመክንዮ ኃይል በላይ የሆነውን ነገር ማመን ነው"፡፡*

የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ስለ ሃይማኖት፣ ስለ ወንድማማችነት፣ ስለ ቀብር ማህበር፣ ወይም ስለ ጸሎት ሥነ ሥርዓት ማህበራዊ ክበብ ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ቃል እውነተኛና ያልተዛባ አመለካከት ካለን ይህ በዘመናት የተፈተነ መጽሐፍ የሚገልጥልን ስለ ንጉሥና ስለ መንግሥት ንጉሥ፣ ጌታ፣ የበላይነት፣ ሉዓላዊነት፣ ንጉሣዊ፣ ግዛት፣ ግርማ፣ አምልኮ፣ ማወደስ፣ ክብር፣ ዙፋን፣ ዘውድ፣ አገዛዝ፣ መታዘዝ፣ እና መስገድ የሚሉት ቃላት በዴሞክራሲ ወይም በሪፑብሊክ ባሕል ወይም መዝገበ ቃላት የሚገኙ አይደሉም፡፡ እነዚህ አስተሳሰቦች በዛሬውም ዘመን ሕብረተሰብ ተሞክሮ ውስጥ የሚገኙ አይደሉም፤ ምናልባትም በዘመናችን ባሕል ውስጥ ለብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳትና ለማመስገን አስቸጋሪ የሆነባቸው በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም፡፡

እኔ የተወለድሁት በ1954 ሲሆን ይህም ደሴቶቻችንን ከ200 ዓመት በላይ በገዛው በንጉሣዊ አገዛዝ ሥር ነው፡፡ የባሃማስ ደሴቶች የታላቋ ብሪታንያ ቅኝ ግዛቶች በመሆን ይታወቁ ነበር፡፡ ታላቋ ብሪታንያም (እንግሊዝ) በካሪቢያን አካባቢ እንደ ጃማይካ፣ ባርባዶስ፣ ትሪኒዳድና ቶባጐ፣ የእንግሊዝ ቨርጂን ደሴቶች፣ ግራናዳ፣ ብሪቲሽ ጉያና እና የመሳሰሉትን ሌሎች ብዙዎችን ገዝታለች፡፡

ንጉሣዊ ግዛት ምንድነው? በመርሕ ደረጃ ንጉሣዊ ግዛት የንጉሥ ሉዓላዊ መንግሥትና በግዛቱ ላይ ያለው የአገዛዝ ተጽእኖ ሲሆን እርሱም ዐላማው፣ ፈቃዱ፣ ባሕርዩ፣ ሕጐቹ፣ እሴቶቹ፣ ግብረ ገብነቱና ባሕሉ በዜጐቹ ውስጥ እንዲንፀባረቁ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ ንጉሣዊ ግዛት በንጉሥ የሚገዛ መንግሥት ወይም አገር ሲሆን የግዛቱ ባሕልና ሕብረተ ሰብ የንጉሡን የግል ባሕርይ የሚያንፀባርቅበት ነው፡፡

አንድ መንግሥት በሩቅ ወደሚገኝ ግዛት የመንግሥቱ ተፅዕኖ ሲያስፋፋ፣ ይህ ሂደት ቅኝ አገዛዝ ይባላል፡፡ የቅኝ አገዛዝ ግብ የግዛቱን ሕጐች፣ እሴቶችና ባሕል ወደዚያ ሩቅ ግዛት ማስፋፋትና የንጉሡን ክብር በዚያ ግዛት ውስጥ መግለጥ ነው፡፡ ግዛቶች ሁሉ ከዚህ የሚከተሉትን ያካትታሉ፡- ንጉሥ፣ ጌታ፣ ክልል፣ የጋራ ቋንቋ፣ ንጉሣዊ ሕገ መንግሥት፣ ንጉሣዊ ሕጐች፣ ልማድና እሴቶች፣ ግብረ ገብነት፣ ንጉሣዊ የሥነ ምግባር ደንብ፣ ንጉሣዊ



ፕሮቶኰል፣ ምጣኔ ሀብት፣ የጋራ ደህንነት፣ እና የንጉሡን ባሕርይ የሚያንፀባርቅ ልዩ ባሕል ናቸው፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስም መልእክትና ኃላፊነት ባሕርይ ይህ ነው፤ የንጉሣዊ ግዛትና የእርሱ መመሪያ ጽሑፍ፣ ዐላማ፣ ትርጓሜና ትግበራ ከዚህ ዐውድ ውጪ ግንዛቤ ሊያገኝ አይችልም፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስን መልእክትና ቅደም ተከተል በቀላሉ ብንመለከት ይህንን ሐቅ የሚያንፀባርቅ ሆኖ እናገኘዋለን፡-

> ከዚያ ጊዜ አንሥቶ ኢየሱስ "ንስሓ ግቡ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና እያለ መስበክ ጀመረ" (ማቴዎስ 4፥17)፡፡
>
> አየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥራች ቃል እየሰበከ፣ በሕዝቡ መካከል ማንኛውንም ደዌና ሕመም እየፈወሰ በመላው ገሊላ ይዘዋወር ነበር (ማቴዎስ 4፥23)፡፡
>
> በመንፈስ ድኾች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፣ መንግሥተ ሰማይ የእነርሱ ናትና (ማቴዎስ 5፥3)፡፡
> እናንተ ግን እንዲህ ብላችሁ ጸልዩ፣ በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ስምህ ይቀደስ፣ መንግሥትህ ትምጣ፣ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን (ማቴ 6፥9-10)፡፡
>
> ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን እሹ፣ እነዚህ ሁሉ ይጨመሩላችኋል (ማቴዎስ 6፥33)፡፡
>
> ኢየሱስ በምኩራቦቻቸው እያስተማረ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥራች እየሰበከ፣ እንዲሁም ደዌንና ሕመምን ሁሉ እየፈወሰ በከተሞችና በመንደሮች ዞረ (ማቴዎስ 9፥35)፡፡
>
> ሄዳችሁም መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች ብላችሁ ስበኩ፤ በሽተኞችን ፈውሱ፣ ሙታንን አስነሱ፣ ለምጻሞችን አንጹ፣ አጋንንትን አስወጡ፣ በነጻ የተቀበላችሁትንም በነጻ ስጡ (ማቴዎስ 10፥7-8)፡፡

ነገር ግን እኔ አጋንንትን የማስወጣው በእግዚአብሔር መንፈስ ከሆነ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ መጥታለች (ማቴዎስ 12፥28)።

እርሱም እንዲህ አላቸው፣ ለእናንተ የመንግሥተ ሰማይን ምስጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፣ ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም (ማቴዎስ 13፥11)።

እንግዲህ የዘሪውን ምሳሌ ስሙ:- የእግዚአብሔርን መንግሥት ቃል ሰምቶ ከማያስተውል ከማንኛውም ሰው ልብ ውስጥ ክፉው መጥቶ የተዘራውን ዘር ይነጥቃል። ይህ እንግዲህ በመንገድ ዳር የተዘራው ዘር ነው (ማቴዎስ 13፥18-19)።

አሁንም ሌላ ምሳሌ እንዲህ ሲል ነገራቸው፣ መንግሥተ ሰማይ ሴት ወስዳ ሊጡ በሙሉ እስኪቦካ ድረስ በሦስት መስፈሪያ ዱቄት ውስጥ በመደባለቅ የሸሸገችውን እርሾ ትመስላለች (ማቴዎስ 13፥33)።

የመንግሥተ ሰማይን መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ በምድር ያሰርኸው ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የፈታኸው ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል (ማቴዎስ 16፥19)።

ለሕዝብ ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበከል፤ ከዚያም መጨረሻው ይመጣል (ማቴዎስ 24፥14)።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ከኢየሱስ መልእክት መካከል ጥቂት ምሳሌዎች ብቻ ሲሆኑ እነዚህም እርሱ በምድር ላይ ላለው ተልእኮ የመንግሥቱን አስተሳሰብ ቅደም ተከተል የሚዘረዝሩ ናቸው። ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣው የሰማያዊውን መንግሥት ቅኝ ግዛት በምድር ላይ ለመመለስ ሲሆን ይህም እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የነበረው የመጀመሪያ ዐላማና ዕቅድ ነበር። የሰው ልጆች ውድቀት በምድር ላይ የነበረውን የሰማያዊውን መንግሥት አገዛዝ እንዲጠፋ አደረገ፤ ፈጣሪ እግዚአብሔር ንጉሡን ልጁን ወደ ቅኝ ግዛቱ እንዲልክ ያነሳሳው የሰማያዊውን መንግሥት ተጽእኖዎች፣



ሕጐች፣ እሴቶች፣ የኑሮ ዘይቤና ባሕል ወደ ምድር እንዲመልስ ነበር። የሰማያዊው መንግሥትና ባሕል በዜጐቹ ውስጥ በተግባር ላይ የሚውለው በእምነት ገንዘብ አማካይነት ብቻ ነው። እንደ ንጉሡ አሳብ በመንግሥቱ ሕይወት ውስጥ ያሉት ተስፋዎችና መብቶች ሊንቀሳቀሱ የሚገባቸው በእምነት ጥራት ነው። ከመንግሥቱ የመርሕ ቁልፎች መካከል አንዱ እምነት ነው።

... እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ (ማቴዎስ 9፥29)።

በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ካሉት አስተሳሰቦች መካከል እጅግ የተበላሸው፣ በተሳሳተ መንገድ በጥቅም ላይ የዋለውና የተሳሳተ ግንዛቤ ያለው እምነት ነው። በታሪክ (በዘመናት) ሁሉ በሃይማኖት ውስጥም ሆነ ከሃይማኖት ውጪ እምነት በብዙ ልዩ ልዩ መንገዶች ታይቷል። በእምነት ካባ፣ ወንዶች ሴቶችን አስገድደው ደፍረዋል፣ ዘርፈዋል፣ በዝብዘዋል፣ ጨቁነዋል፣ እንዲሁም በጅምላ ጨፍጭፈዋል። ባለፉት 100 ዓመታት ውስጥ ስለእምነታቸውና በእምነት ስም የተገደሉት ከዚያ በፊት የነበረው የምዕት ዓመታት ታሪክ ተደምሮ ይበልጣሉ። አብዛኛውን ጊዜ፣ ግድያውን የሚፈጽሙት ሰዎች ይህን የሚያደርጉት እግዚአብሔርን እንደሚያገለግሉ በማመን ነው።

በቤተክርስቲያን እንኳ እምነት ብዙውን ጊዜ በመበላሸቱና በተሳሳተ መንገድ ለግል ጥቅም በሥራ ላይ በመዋሉ እምነትን በማይረዱት ሰዎች እየተተቸ በንቀት ዓይን ታይቷል። በተመሳሳይ ምክንያት እምነት ከብዙ አማኞች ልምምድ ውስጥ በሞላ ጐደል ተወግዶአል ለማለት ይቻላል። እውነተኛ እምነት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፣ መጽሐፍ ቅዱስም የእግዚአብሔርን ስጦታ ለግል ጥቅም ማዋልን በሚመለከት ብዙ ማስጠንቀቂያዎችን ይሰጣል።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የ“እግዚአብሔር መንግሥት እምነት” የሚለው ሐረግ ከአጠቃላዩ የእምነት ትርጉም ለመለየት ታስቦ በበቂ ምክንያት የተመረጠ ነው። “የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት” ከእውነተኛ እምነት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፣ ይህም እምነት በ“ሃይማኖት” ውስጥ ያለውን ሕይወት ሳይሆን በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያለውን የሚገልጽ ነው። ይህም በመንግሥቱ ውስጥ ባሉ በእውነተኛ ዜጐች ውስጥ ያለ የጋራ ባሕል ነው።

አሁንም ደግሜ የማሰምርበት፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ሃይማኖት አይደለም፤ ክርስትና ሃይማኖት ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት አገር ነው። ኢየሱስ በአደባባይ የማስተማር አገልግሎቱን ሲጀምር ዐዲስ ሃይማኖትን ለማስተዋወቅ እየሰበከ አልነበረም፣ ዳሩ ግን እርሱ ለአባቱ

መንግሥት እንደ አምባሳደር ሆኖ ይናገር ነበር። እርሱ "እነሆ እኔ ዐዲስ ሃይማኖትን እነግራችኋለሁ" አላለም። አይደለም፣ በመጀመሪያ የተመዘገቡት የኢየሱስ ቃላት፦ "ንስሓ ግቡ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና" የሚሉ ናቸው (ማቴ 4፥17)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብሉይም ሆነ በዐዲስ ኪዳን፣ የእግዚአብሔር መንግሥት መልእክት ስለ አንድ አገር መልእክት ነው። በውስጠኛው ልባችን፣ እያንዳንዱ ሰው አሁን ከምንኖርባት ምድር ሌላ የተሻለ አገር ይፈልጋል። ሁሉም ሰብአዊ መንግሥታት ጉድለት አለባቸው። በጣም የተሻሉና ጠቃሚ ናቸው የተባሉት እንኳ የውስጠኛውን ፍላጐታችንን ማርካት ይሳናቸዋል። የተሻለ አገር መፈለጋችን በትክክል ተፈጥሯዊ ነው፤ አዳምና ሄዋን በኤደን ገነት በወደቁ ጊዜ ያጣነው ሃይማኖትን አይደለም፦ ያጣነው አገርን ነው። ግዛትን አጣን። መንግሥትን አጣን። ባሕልን አጣን። የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ያጣነውን የምንመልስበት ቁልፍ ነው። ስለዚህ "የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት" የሚለውን ቃል በምጠቀምበት ጊዜ በአገር ዐውድ ውስጥ ስላለው እምነት መናገሬ ነው።

## የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ባሕል

እያንዳንዱ አገር ባሕል አለው፤ የእግዚአብሔርም መንግሥት ከዚህ የተለየ አይደለም። ባሕል አንድን መንግሥት ወይም የሕዝብ ወገን ልዩ የሚያደርጉትን ልዩ እምነቶች፣ ግብረ ገባዊ እሴቶች፣ ማህበራዊ ልማዶችና የአኗኗር ዘይቤዎች የሚያመለክት ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት የመንግሥት ዜጐች መለያ ባሕርይ ስለሆነ እምነት የእግዚአብሔር መንግሥት ባሕል ነው ለማለት እንችላለን። እግዚአብሔር ገና ከመጀመሪያው የእርሱ መንግሥት ዜጐች ባሕል የሆነው እምነት እንዲኖራቸው ዐቅዶአል። ዳሩ ግን ይህ ምን ማለት ነው?

በመጀመሪያ ደረጃ፣ እምነት የእግዚአብሔር መንግሥት ገንዘብ ነው ማለት ነው። ገንዘብ በአንድ አገር ውስጥ ለሕጋዊ ጨረታ የሚያገለግልን ማንኛውንም ነገር ያመለክታል። የትኛውም አገር ያለ ገንዘብ ሊሠራ አይችልም። በአንድ አገር ውስጥ ለመኖር፣ ለመነገድ፣ ለመግዛት፣ እና ለመሸጥ የዚያን አገር ገንዘብ ማግኘት አስፈላጊ ነው። አንተ ትክክለኛውን ገንዘብ ካላገኘህ ምን ይሆናል? ምንም ነገር ለመግዛት አትችልም፤ ምግብ፤ መጠጥ፣ መጠለያ፣ ሸቀጦች ለመግዛት ወይም አገልግሎት ለማግኘት አትችልም። በኪስህ ምንም ያህል ገንዘብ ቢኖርህና አንተ ባለህበት አገር የማያገለግል ገንዘብ ከሆነ አንተ ዋጋ የለህም። ትክክለኛው ገንዘብ ከሌለህ



እንዲሁ ለመቀመጥ ብቻ ካልሆነ በስተቀር ምንም ነገር ልትሠራ አትችልም፤ አንዳንድ ጊዜ ይህም እንኳ የማይቻል ይሆናል።

ምንም ገንዘብ የሌላቸውን ሰዎች ምን ብለን እንጠራቸዋለን? ድሆች እንላቸዋለን። በምድራዊ ባሕል ድሆች ሰዎች ምንም ገንዘብ የሌላቸው ናቸው። ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር መንግሥት ድህነት የሚለካው በገንዘብ እጦት ሳይሆን በእምነት እጦት ነው። እምነት የሌላቸው ሰዎች፣ ምንም ያህል ገንዘብ በባንክ ቢኖራቸው፣ በእግዚአብሔር መንግሥት ድሆች ናቸው። አንድ ባለጠጋ ሰው የዘላለም ሕይወት ለማግኘት ምን ማድረግ እንዳለበት ኢየሱስን ቢጠይቀው ኢየሱስ እንዲህ ሲል መለሰለት፤ "ፍጹም ለመሆን ከፈለግህ ሄደህ ንብረትህን ሁሉ ሸጠህ ገንዘቡን ለድሆች ስጥ፣ በሰማይም ሀብት ታገኛለህ፣ ከዚያም መጥተህ ተከተለኝ" (ማቴዎስ 19፥21)።

በመሠረቱ ኢየሱስ ለሰውዬው የተናገረው፣ "በሀብትህ ላይ አትተማመን፤ በእኔ ላይ ተማመን። ከዚያ በኋላ እውነተኛ ሀብት ታገኛለህ" የሚል ነበር። ምድራዊ ሀብት ዘላቂ አይደለም። እውነተኛ ሀብት የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ነው። እምነት ከምድራዊ ብልጽግና የሚበልጠው ለምንድነው? በ2008 እና በ2009 በዓለም ዐቀፍ የምጣኔ ሀብት ቀውስ እንደተከሰተው ሁሉ ሀብት ሁልጊዜ ጊዜያዊ ነው፤ ሊሰረቅ፣ ሊጠፋ ወይም ዋጋው ሊቀንስ ይችላል። የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ግን ገደብ በሌለው በሰማያዊው የጋራ ብልጽግና ክምችት ውስጥ መግቢያ "በር" ስለሆነ ፈጽሞ ሊያልቅ አይችልም። ገንዘብህን ብታጣ ትንሽ ብቻ ልትቀንስ ትችላለህ። እምነትህን ብታጣ ግን ሙሉ በሙሉ ትሸነፋለህ።

ዲያብሎስ ገንዘብህን አይፈልግም። እርሱ ቤትህን፣ ልብስህን፣ ልጆችህን፣ ወይም ሌላ ማንኛውንም እርሱ ይፈልጋል የምትለውን ነገር አይፈልግም። እርሱ የሚፈልገው አንድ ነገር ነው፦ ያውም እምነትህን ነው። እርሱ እምነትህን ከሰረቀህ፣ በመንፈስ ድሀ እንደምትሆን ያውቃል። እምነት ተስፋን ይሰጠናል፤ ስለዚህ እምነት ከጠፋ ተስፋ በነፋስ እንደሚጠረግ ጉም በንኖ ይጠፋል። እምነተ ቢስነት ወደ ተስፋቢስነት ይመራል፤ ይህም ወደ ተስፋ መቁረጥ ይመራል። ሕይወት ትርጉም የሌለውና ዋጋቢስ ይሆናል። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ አብዛኛዎቹ የዓለም ሰዎች ተስፋ መቁረጥ የሚታይባቸው ናቸው ለማለት እንችላለን። በምድር ላይ እጅግ ደሀ የሆነው ሰው እምነት የሌለው ሰው ነው።

በማንኛውም አገር ለጥሩ ሕይወት ገንዘብ አስፈላጊ ነው። ያለህ ገንዘብ መጠን በህብረተሰብ ውስጥ የምትሠራውን ሥራ መጠን ይወስናል። እምነትም የእግዚአብሔር መንግሥት ገንዘብ ነው። ያለ እርሱ ምንም

ልታገኝ ወይም ምንም ልታደርግ አትችልም:: እምነት ከሌለህ የእግዚአብሔር መንግሥት ሕይወትና ሀብት ለአንተ የተዘጉ ናቸው::

ይህ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እምነት ባሕል ወደ ሁለተኛው ነጥብ ያመጣናል:- በመንግሥቱ ውስጥ ሁሉም ነገር የሚገኘው በእምነት ነው:: ስንት ነገር? ሁሉም ነገር:: ይህን ለመረዳት ከባድ ነውን? እንግዲያው ነገሩን ዘወር እናድርገው:: በመንግሥቱ ውስጥ ምንም ነገር ያለ እምነት አይገኝም:: ይህ በወሳኝነት ዋና ነገር ነው:: ያለ ገንዘብ ምንም ለማድረግ አትችልም:: እንደ እውነቱ ከሆነ ከንግድና ከገንዘብ መሠረታዊ መርሆች አንዱ፣ ገንዘብ ለማግኘት ወይም ገንዘብ ለማጠራቀም ገንዘብ ሊኖርህ ይገባል የሚል ነው:: ከባንክ ብድር ብትፈልግ የብድሩን መጠን 10 ወይም 20 በመቶ ከራስህ እንደ ቀብድ ይዘህ ካልሄድህ በስተቀር ባንኩ ብድር የማይሰጥህ ለዚህ ነው:: የኢየሱስን ጥያቄ ተመልከት:- "ነገር ግን የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆንን?" (ሉቃ 18፥8):: ኢየሱስ በሚመለስበት ጊዜ ምድር ሁሉ ከሁሉም በላይ እጅግ አስፈላጊ በሆነው ገንዘብ ድሀ ሆና ትገኝ ይሆንን? በመንግሥቱ ውስጥ ማንኛውም ነገር የሚገኘው በእምነት ነው፣ በዚህ በመንግሥቱ ውስጥ ያለ እምነት ምንም ነገር አይገኝም::

እምነት የመንግሥቱ ገንዘብ ከሆነ፣ እንግዲያውስ በመንግሥቱ ውስጥ ለመኖርም እምነት አስፈላጊ ነው ማለት ነው:: አስቀድሜ እንዳልሁት፣ እምነትን ካጣን በመንፈሳዊ ጉዳይ ድሆች እንሆናለን፤ ይህ ከሆነ ለእግዚአብሔር መንግሥት ሕይወት ያልታጠቅንና ጨርሶ የማንስማማ እንድንሆን ያደርገናል ሰይጣን የሚዋጋው እምነታችንን ለመስረቅ ብቻ ነው:: ይህንን በኢዮብ ላይ ሞክሮአል፣ ስለዚህ በአንተና በእኔ ላይ እንዴት አያደርገውም? ሰይጣን ቤትህ እንዲቃጠል የሚያደርገው ለምንድነው? በእግዚአብሔር ላይ መተማመንህን እንድትተው ነው:: በአካልህ ላይ ሕመምን የሚያመጣውና በበሽታ የሚያጠቃህ ለምንድነው? እግዚአብሔር ፍላጐትህን ለማሟላት የሚችል መሆኑን እንዳታምን ለማድረግ ነው:: ሰይጣን የሚፈልገው እምነታችንን ነው፣ ምክንያቱም በአገራችን ውስጥ የምንኖረው በእርሱ መሆኑን ስለሚያውቅ ነው:: በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ለማንኛውም ነገር በእምነት እንጠቀማለን:: በዚህ ዐይነት ነው የምንኖረው::

በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ እምነት አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም ያለ እምነት የመንግሥቱ መርሆች ሊንቀሳቀሱ አይችሉም:: እያንዳንዱ አገር ሕገ መንግሥት አለው:: በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ሕገ መንግሥቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው:: ሕገ መንግሥቱ አገሪቱ የምትመራበትን ደንብ የያዘ ነው:: ለአገሪቱ ዜጐች ስኬታማ በሆነ መንገድ ለመሥራትና በዜግነታቸው



ጥቅሞች እንዲደሰቱ ከተፈለገ የአገራቸውን ሕጐችና ሕጐቹ እንዴት እንደሚሠሩ ማወቅ ያስፈልጋቸዋል:: በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ሕጐቹን የሚያንቀሳቅሰው እምነት ነው:: ያለ እምነት በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የምናነበው ሁሉ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም:: ያለ እምነት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ያሉት ሕጐች የተስፋ ቃሎችና መገለጦች ሁሉ በወረቀት ገጽ ላይ ያሉ ቃላት ብቻ ይሆናሉ:: የእምነት መንፈስ በልባችን ውስጥ ሲያነቃቃቸው እምነት ሕይወትን ይሰጣቸዋል:: አንዳንድ አማኞች ያልሆኑ ሰዎች እንኳ መጽሐፍ ቅዱስን ሊያነቡት ሊያጠኑትና እንደ አንተና እንደ እኔ ሊጠቅሱት የሚችሉት ለዚህ ነው፤ ይሁን እንጂ በሕይወታቸው ላይ ውጤት አይኖረውም ምክንያቱም ሕጉን የሚያንቀሳቅሰው እምነት ስለሆነ ነው:: የመንግሥቱን ተስፋዎችና መርሆች የሚያንቀሳቅሰው ገንዘብ እምነት ነው:: እምነትን በሚገባ ካልተረዳንና ካልተጠቀምንበት በስተቀር እውነተኛውን የእግዚአብሔር መንግሥት ሕይወት ለመኖር አንችልም::

ለማጠቃለል ያህል፣ የእግዚአብሔር መንግሥት የአኗኗር ዘይቤ እምነት ነው:: በሌላ አነጋገር፣ እምነት የምንኖርበት፣ እንደ ልብስ የምንለብሰው ዘይቤ ነው:: እርሱም የእግዚአብሔር መንግሥት ባሕል የምንገልጥበት መንገድ ነው:: እምነት ሕያው ያደርገናል::

### እምነት ሲተረጐም

እምነት የተባለው ቃል በሕይወት ውስጥ ብዙ አስተሳሰቦችን ለመግለጽ ይጠቅማል:: ለምሳሌ "እምነት" የሚለው ቃል መደበኛ የሆኑ እምነቶችን ወይም እንደ የክርስትና እምነት የመሳሰሉ የተመሠረቱ ሃይማኖቶችን ያመለክታል:: "እምነትን መጠበቅ" ማለት የእምነትህን መዋቅር ወይም የሃይማኖትህን ቃል ኪዳን በጥብቅ መያዝ ማለት ነው:: "የእምነት እንቅስቃሴ" የሚለው ሐረግ የእምነትን ኃይል በአስተምህሮ ደረጃ የሚያጐላውን የእምነት መዋቅር የሚያመለክት ነው:: እነዚህ ሁሉ በዘመናት በሚሊዮን በሚቆጠሩ ሰዎችን የግልም ሆነ የሕብረት ልምምዶችን ለመተርጐም የሚያገለግሉ ሕጋዊ መግለጫዎች ናቸው::

የእምነት አስተሳሰብ በታሪክ ውስጥ፣ በተለይም ላለፉት 40 ዓመታት ታላቅ ትኩረትን የሳበ ጉዳይ ነው:: እርሱም ታላላቅ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎችንና ድርጅቶችን የፈጠረ የአስተምህሮ ምርምር ርዕስ ጉዳይ ሆኖ ቆይቶአል:: በምዕራቡ ዓለም የእምነት እንቅስቀሴ በመባል የሚታወቀው በእምነት ላይ ትኩረት ያደረገው እንቅስቃሴ በዓለም ዙሪያ በሚሊዮን በሚቆጠሩ ሰዎች ሕይወት ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ አሳድሮአል::

በምዕራቡ ዓለም ሃይማኖታዊ ልምምድ ውስጥ እንደ አንድ ትልቅ ክፍል አድርጐ እምነትን እንደገና የማግኘት ጉዳይ የሰው ልጆች ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት ውስጥ ብዙዎችን ወደ እምነት ቁም ነገር አምጥቶአቸዋል። እኔም ከዚህ ትኩረት ብዙ ተጠቅሜአለሁ።

ይሁን እንጂ፣ ከዚህ አጽንኦት አዎንታዊ ያልሆኑ ተጽእኖዎች ደግሞ ነበሩ። ለብዙዎች ሰዎች እምነት አንድ የተለየ የተናጠል አስተምህሮ ሲሆን ይህም "ትክክለኛው እምነት የሌላቸው" የተባሉትን በመንፈሳዊ ጉዳይ ብቃት የሌላቸው እንደ ሆኑ እንዲሰማቸው የሚያደርግ ልዩ የአማኞች ክበብ መፍጠር ማለት ነው። ይህም በሚሊዮን በሚቆጠሩ ሰዎች ዘንድ አስደንጋጭ የሆነ ውጤትን ያስከተለ ሲሆን ብዙዎችም የበደለኝነት፣ የሀዘን፣ የትካዜና የዝቅተኝነት ሕይወት እንዲኖሩና ብሎም "ከእምነቱ" ጭራሹን እንዲያፈገፍጉ ያደረገ ጉዳይ ነው። በተቃራኒው የሚያስገርመው ነገር እምነት እነዚህኑ አጥፊ ሁኔታዎችን ለማስወገድ የታቀደ መሆኑ ነው። ተስፋን ለመፍጠር የታቀደው እምነት፣ በዚህ ፈንታ የጉድለትን ስሜት ፈጠረ ማለት ነው።

ትልቁ ችግር እምነት ራሱን የቻለ አንድ አስተምህሮ ወይም የተለየ መልእክት እንዲሆን የተቃደ አለመሆኑ ነው። ይልቁንስ በዚህ ፈንታ እርሱ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ባለው ሰፊ ስዕል ውስጥ የተካተተ ተፈጥሮአዊ ልምምድ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ እምነትን አንድ የተለየ ክፍል አድርጐ አላስተማረም፣ ይልቁንስ እርሱ ያስተማረው እምነትን ዋናው መልእክት፣ ማለትም በእግዚአብሔር መንግሥት ዐውድ ውስጥ በማድረግ ነው። የእርሱ አቋም እምነት በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ትክክለኛ የሕይወት ክፍል እንደሆነ ይመስላል። በዐጭሩ፣ የእምነት አስተሳሰብ ከመንግሥቱ ዐውድ ተለይቶ መታየት የለበትም፤ እምነት በምድር ላይ ያለውን የሰማያዊ መንግሥት ተስፋዎች ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ሙሉ ውጤት ይኖረዋል።

ዳሩ ግን እምነት በተጨባጭ ምንድነው? ትርጉም ባለው መንገድ እርሱን የምንገልጸው እንዴት ነው? በዐዲስ ኪዳን ውስጥ የዕብራውያን ፀሐፊ እንዲህ በማለት ተርጉሞታል፦ "እምነት ተስፋ ያደረግነው ነገር እንደሚፈጸም ርግጠኛ የምንሆንበት፣ የማናየውም ነገር እውን መሆኑን የምንረዳበት ነው" (ዕብራውያን ፲፩፥፩)። በዕብራይስጥ ቋንቋ ለእምነት ያለው የተለመደ ቃል "አማን" ሲሆን በግሪኩ ቋንቋ በዐዲስ ኪዳን ብዙ ጊዜ የሚነገረው ቃል "ፒስቲስ" የሚለው ነው። ፒስቲስ ማለት በባሕርዩ እምነት ማለት ሲሆን ዳሩ ግን ከአእምሮአዊ እውቀት ወይም አቀባበል በላይ ነው። ፒስቲስ ሙሉ የልብ መሰጠትን ወይም በጥልቀት የተያዘ እምነትን የሚያመለክት ነው። ደግሞም "መግባባት" ማለት ነው። የፒስቲስ እምነት ያለው አንድ ሰው ስለ አንድ ነገር እውነት መሆኑን ጥልቅ በሆነ የልብ መሰጠት በመግባባት የተቀበለ ሰው ነው።



ፒስቲስ ማለት በሌላ አገላለጽ በልበ ሙሉነት የሚጠባበቅ እምነት ማለት ነው። ዕብራውያን ፲፩፥፩ የሚለው ይህንን ነው። በልበ ሙሉነት መጠባበቅ ማለት "ተስፋ ያደረግነው ነገር እንደሚፈጸም ርግጠኛ የምንሆንበት፣ የማናየውም ነገር እውን መሆኑን የምንረዳበት ነው"። እውነተኛ እምነት ኖሮን አንድ ነገር እንደሚፈጸም ሳንጠባበቅ አንቀርም። የፒስቲስ እምነት ካለን፣ ምንም እንኳ አንድ ነገር ሲፈጸም በዓይናችን ለማየት ባንችልም እግዚአብሔር ለእኛ ጥቅምና ለእርሱ ክብር አንድ ነገር እንደሚያደርግ በልበ ሙሉነት እየተጠባበቅን በትእግሥት እንቆያለን።

ደግሞም እውነተኛ እምነት ማለት "የተረጋገጠ ተስፋ" ማለት ነው። ዳሩ ግን ይህ እርስ በርሱ የሚቃረን አይደለምን? በመጽሐፍ ቅዱስ ዕይታ ግን አይደለም። ተስፋ አንድ የምንመኘው ዳሩ ግን ለመቀበል ርግጠኛ የማንሆንበት ነገር ነው ብለን እናስባለን፦ "ያንን ዐዲስ ሥራ ለማግኘት ተስፋ አደርጋለሁ" እንላለን። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተስፋ ከዚህ የተለየ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተስፋ የተረጋገጠና እውነተኛ ነው፤ ምክንያቱም በእግዚአብሔር እውነተኛነትና በእርሱ የተስፋ ቃሎች ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ነው። ገና ላናየው እንችላለን፣ ነገር ግን እንደሚመጣ እናውቃለን፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ብሏልና ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ተስፋ እንዲህ አለ፤ "በዚህ ተስፋ ድነናል። ተስፋው የሚታይ ከሆነ ግን ተስፋ አይደለም የሚያየውንማ ማን ተስፋ ያደርገዋል? ነገር ግን ያላየነውን ተስፋ ብናደርግ በትዕግሥት እንጠብቃለን" (ሮሜ 8፥24-25)። እንደገናም የዕብራውያን ፀሐፊ እንዲህ ይላል፤ "እኛም የነፍስ መልሕቅ የሆነ ጽኑና አስተማማኝ ተስፋ አለን፤ ይህም ተስፋ ከመጋረጃው በስተጀርባ ወዳለው ውስጠኛ መቅደስ ይገባል። ይህም ስፍራ ኢየሱስ ስለ እኛ ቀድሞ የገባበት ነው" (ዕብ 6፥19-20)። ተስፋ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ዋናው ክፍል ነው። ደግሞም በማይዋሸውና በማይለወጠው በእግዚአብሔር ላይ በጥብቅ የተመሠረተ ስለ ሆነ በእጃችን እንደያዝነው ያህል ለእኛ ርግጠኛ ነው።

የፒስቲስ እምነት እንደዚህ ባለው ተስፋ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ በተጨማሪ "መወሰን" የሚል ትርጉም ሊኖረው ይችላል። "መወሰን" ማለት ስለ አንድ ነገር ወደ አንድ የታወቀ ውሳኔ ወይም መደምደሚያ መድረስ ማለት ነው። መወሰን፣ "እግዚአብሔር ቃሉን እንደሚጠብቅ አውቃለሁ። እንዴት፣ መቼ፣ ወይም የት እንደሚያደርገው አላውቅም፣ ግን አንድ ነገር አውቃለሁ፤ እርሱ ያደርገዋል!" ይላል።

በዛሬይቱ ቤተክርስቲያን ትልቁ አሳዛኝ ነገር የብዙ አማኞች እምነት ወደዚህ ደረጃ አለመድረሱ ነው:: የአንተስ እንዴት ነው? የምትተማመነው በሀብት፣ በሁኔታዎች ወይም በዓይንህ በምታያቸው ነገሮች ነው ወይስ እምነትህ የተመሠረተው በማይዋሸውና "ትናንት፣ ዛሬም፣ ለዘላለምም ያው በሆነው" (ዕብ 13፥8) በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ነው?

ይህ እንዴት እንዲሚሠራ እንመልከት:: ዝናብ እንደሚዘንብ የምትጠባበቅ ከሆነ ምን ታደርጋለህ? ዣንጥላ ትይዛለህ:: ሰማዩ የጠራና ፀሐያማ ይሆናል፣ ነገር ግን የአየር ትንበያው ካፊያ ይኖራል ካለና አንተም ካመንህበት ለዝናብ ተዘጋጅተህ ከቤትህ ትወጣለህ:: ሰዎች ብሩህ በሆነ በጠራራ ፀሐይ ዣንጥላ ይዘህ ሲያዩህ ምናልባት ቀውስ ነህ ሊሉ ይችላሉ:: ነገር ግን አንተ እነርሱ የማያውቁትን አንድ ነገር ታውቃለህ፣ ለዚህም ተዘጋጅተሃል:: እምነት ካለህ ለምላሹ በቅድሚያ ትዘጋጃለህ፣ ምክንያቱም እንደሚመጣ ስለምታውቅ ነው:: አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር እንደሚጠብቃቸው ማመናቸውን ይናገራሉ፣ ነገር ግን ለወደፊቱ ወይም መምጣቱ ለማይቀረው ማዕበል ራሳቸውን ለማዘጋጀት ምንም ነገር አያደርጉም። ይህ እምነት አይደለም፤ ይህ ራስን ማታለል ነው:: ደግሞም ሞኝነት ነው::

እምነት ወደ ተግባር የሚወስድህ የተረጋገጠ ተስፋ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስም ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው የሚለው ለዚህ ነው (ያዕቆብ 2፥26 ይመልከቱ):: ተግባሮች ወይም መልካም ሥራዎች እምነትን አይተኩም:: እውነተኛ እምነት የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ተግባርንና መልካም ሥራን ያስከትላል:: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት መልካም ሥራን ያስከትላል፣ በተቃራኒው ግን አይሆንም:: የዚህ መጽሐፍ ዐላማ በዋነኛነት በእምነት ትርጉም ላይ ማተኮር አይደለም፤ ይህ ከብዙ ምንጮች ከሚመጡ ከብዙ መጻሕፍትና ከብዙ ጥናቶች ሊገኝ የሚችል ነው:: በዚህ መጽሐፍ የእኔ ዋና ዐላማ በሰማያዊው መንግሥትና እርሱም በምድር ላይ ባደረገው መስፋፋት ሰፊ ስዕል ዐውድ ውስጥ እምነትን መልሶ መትከል ነው፤ ደግሞም እምነትን ከጽንፈኛ ተናጠልነት አጥርቶ በእግዚአብሔር መንግሥት አኗኗር ባሕልና ባሕርይ ውስጥ መልሶ ማስቀመጥ ነው:: አከስጂን (አየር) ለሰው ልጅ፣ ገንዘብ ለምጣኔ ሀብት፣ ውሀ ለአሣ እንደሆነ ሁሉ እምነትም ለእግዚብሔር መንግሥት ነው:: እርሱ አስፈላጊ ነው፣ ግን ትርፍ ነገር አይደለም:: ያለ እምነት በሰማያዊው መንግሥት አገዛዝ ውስጥ ምንም ዓይነት ሥራ ልትሠራ አትችልም:: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት መርሕ ቀላል ነው:- "የማታምነውን ነገር ለመቀበል አትችልም፤ የማትጠባበቀውን ነገር ልታይ አትችልም" የሚል



ነው:: ያለ ገንዘብ በአገርህ ምጣኔ ሀብት ውስጥ ልትኖር እንደማትችል ሁሉ በእግዚአብሔር መንግሥትም ውስጥ ያለ እምነት ልትኖር አትችልም::

**የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት በተግባር::**

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ወዳሉት መብቶች፣ ዕድሎችና ጥቅሞች ውስጥ ያስገባናል፤ እነዚህ ሁሉ በሕገ መንግሥቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተስፋ የተሰጡ ናቸው:: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት የኑሮ ዘይቤ እንደሆነ እና መሆንም እንዳበት መረዳት የሚያስፈልገን ለዚህ ነው:: ትክክለኛው ገንዘብ ያላቸው ሰዎች መንግሥቱ የሚያቀርበውን ማንኛውንም ነገር ለማግኘት ይችላሉ:: እነርሱ ማድረግ ያለባቸው መጠየቅ ብቻ ነው:: ከዐዲስ ኪዳን አንድ ምሳሌ እንመልከት::

> ኢየሱስም ከዚያ እንደ ሄደ ሁለት ዐይነ ስውሮች "የዳዊት ልጅ ሆይ ማረን፣" በማለት እየጮኹ ተከተሉት::
>
> ዐይነ ስውሮቹም ኢየሱስ ወደ ገባበት ቤት ተከትለው ገቡ፤ ኢየሱስም "ዐይናችሁን ላበራላችሁ እንደምችል ታምናላችሁን? ሲል" ጠየቃቸው::
>
> እነርሱም "አዎን ጌታ ሆይ" ብለው መለሱለት::
>
> ከዚያም ኢየሱስ ዐይናቸውን ዳስሶ "እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ" አላቸው:: (ማቴዎስ 9፥27-30)

በእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ምንም ዓይነት ምስጢር የለም:: እርሱ ቀጥተኛ፣ ተግባራዊና እንዲሁም ከሃይማኖት ወይም ከሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓት ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ነው:: እነዚህ ሁለት ዐይነ ስውራን ሰዎች የዐይናቸውን ብርሃን ፈልገው ወደ ኢየሱስ በመጡ ጊዜ እርሱ የሃይማኖት ጥያቄ አልጠየቃቸውም:: ደግሞም ምን ያህል ጸሎት እንደጸለዩ ወይም ለቤተ መቅደስ ምን ያህል ገንዘብ እንደሰጡ አልጠየቃቸውም:: እርሱ የጠየቀው አንድ ቀላልና ሃይማኖታዊ ያልሆነ ጥያቄ ነው:- "ዐይናችሁን ላበራላችሁ እንደምችል ታምናላችሁን?" የሚል ነበር:: በቃ ይኸው ነበር:: በዐጭሩ ኢየሱስ የጠየቃቸው፣ "የዐይናችሁን ብርሃን ለማግኘት ዋጋውን ትከፍላላችሁን" በማለት ነበር:: እምነት ገንዘብ (ዋጋ) ነው፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ገንዘብ መሆኑን ልብ በሉ:: እነዚህ ሁለት ዐይነ ስውራን ከእግዚአብሔር መንግሥት ጥቅም ፈልገዋል - ሙሉ አካል - ነገር ግን ትክክለኛው ገንዘብ ያስፈልጋቸዋል:: ያም ገንዘብ እምነት ነው:: በሌላ አነጋገር፣ ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጠየቃቸው፣ "የዐይናችሁን ብርሃን

ትፈልጋላችሁ? ገንዘባችሁን አሳዩኝ"፡፡ እነርሱም እንዲህ አሉ፡- "ይኸው ጌታ ሆይ እናምናለን" ኢየሱስም አለ፡- "እሺ ይበቃል"፡፡ ከዚያም ብርሃናቸውን መለሰላቸው፡፡ እነርሱም የእግዚአብሔር መንግሥትን ጥቅም በእግዚአብሔር መንግሥት ገንዘብ ገዙና የሚፈልጉትን አገኙ፡፡

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት የመንግሥቱ ዜጐች በቃሉ ሕገ መንግሥት ውስጥ ያሉትን የመንግሥት ሕጋዊ የተስፋ ቃሎች ከማመንና በሕጉ ውስጥ ያለውን መብታቸውን ከመጠየቅ የተለየ ነገር አይደለም፡፡ ሁለቱ ዐይነ ስውራን ኢየሱስን ምን ብለው እንደጠሩት ልብ በሉ፡፡ በመጀመሪያ "የዳዊት ልጅ" አሉት፣ ይህም ኢየሱስ ከዳዊት ንጉሣዊ የትውልድ ሐረግ ስለ መጣ እርሱ ንጉሥ ለመሆኑ እውቅና መስጠታቸው ነው፡፡ ደግሞም "የዳዊት ልጅ" የሚለው ሐረግ በኢየሱስ ዘመን ለእስራኤል ተስፋ የተሰጠውን ንጉሥና አዳኝ የሆነውን መሲሑን የሚያመለክት እንደሆነ የሚታወቅ ነበር፡፡ ደግሞም ዐይነ ስውራኑ ኢየሱስን "ጌታ" ብለው ጠሩት፣ ይህም "ባለቤት" ማለት ነው፡፡ ይህንን ማዕረግ መስጠታቸው ኢየሱስ በርግጥ ንጉሥ ለመሆኑና ራሳቸውን ጨምሮ የሁሉም ነገር ባለቤት ለመሆኑ እውቅና መስጠታቸው ነበር፡፡ ኢየሱስን ጌታ ብለው የመጥራታቸው ውጤት "አንተ የእኛ ባለቤት ነህ፣ እኛም ዐይነ ስውራን ነን፣ ስለዚህ አንተ የዐይነ ስውርነትም ባለቤት ነህ" ማለታቸው ነበር፡፡ ይህም በኢየሱስ ላይ ጫና አሳደረበት፣ ምክንያቱም የንጉሥ መልካም ስም የሚያርፈው በሕዝቡ የሕይወት ደህንነትና ጥራት ላይ ስለሆነ ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ሰዎች መንግሥታዊ መብታቸው የሆነውን ጤንነታቸውን ለመጠየቅ ከመጡ በኋላ ገንዘባቸውን (እምነት) ከፈሉና ጤናማ ሆነው ተመለሱ፡፡

አንዳንድ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር የሚመጡት አንዳንድ ነገር ለማግኘት ነው፣ ነገር ግን እግዚአብሔር የእነርሱ ባለቤት እንዲሆን አይፈልጉም፡፡ "ጌታ ሆይ ባርከኝ፣ ነገር ግን በሕይወቴ ውስጥ ጣልቃ አትግባ፡፡ ግንኙነቶቼን አትንካ፡፡ በሥራዬ ውስጥ ጣልቃ አትግባ" ይላሉ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ "ቆይ እስኪ፣ እኔ ማን ነኝ? ከማንስ ጋር ትመስለኛለህን" ይህ ወሳኝ ጥያቄ ነው፡፡ ለአንተስ እግዚአብሔር ማነው? "ለሃይማኖታዊ" እምነት ሰዎች እግዚአብሔር አንዳንድ ነገሮች ለማግኘት ወደ እርሱ የሚሄዱበት ሰማያዊ የገና አባት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለእግዚአብሔር መንግሥት እምነት፣ እግዚአብሔር ጌታና ንጉሥ፣ እንዲሁም ሉዓላዊ ፈጣሪና የሁሉም ነገሮች ባለቤት ነው፡፡

ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ "ስለዚህ በጸሎት የምትለምኑትን (የምትሹትን) ሁሉ እንደ ተቀበላችሁት አድርጋችሁ ብታምኑ ይሆንላችኋል" (ማርቆስ 11፥24)፡፡ ብዙ ሰዎች ይህንን ጥቅስ በተሳሳተ መንገድ ይረዱታል፣ በራስ



ወዳድነት እነርሱ የሚፈልጉትን ማንኛውንም ነገር ከእግዚአብሔር መጠየቅ እንደሚችሉ መናገሩ ነው ብለው ተሳስተዋል፡፡ ደግሞም ቅዱስ መጽሐፍ በኢየሱስ ስም መጠየቅ እንዳለብን ይገልጻል (ዮሐንስ 14፥13 ይመልከቱ)፤ ይህም እንደ እርሱ ባሕርይ ማለት እና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መጠየቅ አለብን ማለት ነው (1ዮሐንስ 5፥14 ይመልከቱ)፡፡ ተራ ፍላጐት "ከፈለግህ ውሰደው ወይም ተወው" የሚል ዝንባሌ ያለው ሲሆን መሻት ግን የጋለ ፍላጐት መኖሩን የሚያመለክት ነው፡፡ መሻት "ካላገኘሁት አልተውም" የሚል ውስጣዊ ግፊት ያለበት ነው፡፡ ኢየሱስ ሁለቱን ዐይነ ሰውራን "ዐይናችሁን ላበራላችሁ እንደምችል ታምናላችሁ?" ብሎ ጠየቃቸው፡፡ ያልተጠየቀ፣ ነገር ግን በውስጠ ታዋቂነት ያለው ሌላ ጥያቄ "ምን ያህል ትፈልጉታላችሁ?" የሚል ነው፡፡ በመንግሥቱ ውስጥ (አንድን ነገር) የምንቀበልበት መጠን በእምነታችን መጠን የሚወሰን ነው፡፡ ይበልጥ ባመንን መጠን (ይበልጥ ገንዘብ በከፈልን መጠን)፣ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ሕይወት ያለን ልምምድ ይበልጥ ሙሉ ይሆናል፡፡ እምነት ከሌለን ከእግዚአብሔር መንግሥት ምንም ነገር አናገኝም፡፡ ሰይጣንም እምነታችንን የሚፈልገው (የሚከታተለው) ለዚህ ነው፡፡

## የእምነት ጠላቶች

ሰይጣን እምነታችንን ለማጥፋት በሚያደርገው ያልተቋረጠ ዘመቻ፣ ሁለት ኃይለኛ የጦር መሣሪያዎችን፣ ሁለት አውዳሚ የእምነት ጠላቶችን ይጠቀማል፡- እነርሱም ፍርሀትና ጥርጥር ናቸው፡፡ ፍርሀትና ጥርጥር የተዛመዱ ናቸው፡፡ አንዱ ብቅ ሲል ሌላውም ይከተላል፡፡ ሰይጣን እምነትን ከሚሰርቅባቸው መንገዶች አንዱ በሕይወታችን ውስጥ ፍርሀትን መዝራት ነው፡፡ እርሱ እኛ እንድንፈራ ለማድረግ ማናቸውንም ከባድ ነገሮች ያደርጋል፣ እንዲሁም በመንገዳችን ላይ ማናቸውንም ዓይነት ችግር ያመጣል፣ ምክንያቱም እርሱ ፍርሀት ባለበት ቦታ እምነት እንደማይኖር ስለሚያውቅ ነው፡፡ ፍርሀት ስቃይን ያመጣል፣ ስቃይም ተስፋ ቢስነትን ይቀሰቅሳል፣ ይህም ከዚህ ስቃይ መውጫ መንገድ የለም የሚል ስሜት ነው፡፡ ለስቃይ ሌላው ተለዋጭ ቃል ጭንቀት ነው፡፡ የተራዘመና ያልተወገደ ጭንቀት ማናቸውንም የጤና ችግር ያስከትላል፡፡ እንዲያውም ከሞላ ጐደል የእያንዳንዱ በሽታ የመጀመሪያ መሠረት ጭንቀት ነው፡፡ ስለዚህ ፍርሀት በአካላችን በሽተኞች ሊደርገን ይችላል፡፡ በሕይወት ውስጥ ጭራሽ የማንፈልገው ነገር ቢኖር ለፍርሀት እጅ መስጠት ነው፡፡ በፍርሀት መኖር እምቅ ኃይላችንን በማጥፋት እምነታችንንም ይደመስሰዋል፡፡

በሌላም በኩል፣ በእምነት መኖር ሙሉ ወደ ሆነው እምቅ ኃይላችን እንድንደርስና፣ እንዲያውም የማይቻለውን እንድናደርግ ጥንካሬን ይሰጠናል። ከዕለታት አንድ ቀን፣ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ተጨባጭ ትምህርት ለመስጠት ፍሬ የሌላትን አንዲት የበለስ ዛፍ ረገማት። በቅጽበትም ዛፍዋ ደረቀች። ደቀመዛሙርቱም በመደነቅ ይህ እንዴት ሊሆን እንደቻለ ጠየቁት፦

> ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "እውነት እላችኋለሁ፣ እምነት ቢኖራችሁ ባትጠራጠሩ በበለሷ ዛፍ ላይ የሆነውን ማድረግ ብቻ ሳይሆን ይህንን ተራራ ከዚህ ተነቅለህ ባሕር ውስጥ ግባ ብትሉት እንኳ ይሆናል። እምነት ካላችሁ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ" (ማቴዎስ 21፥21-22)

በዚህ ዓለም ውስጥ በእግዚአብሔር መንግሥት ባሕል ሥር እስከኖርን ድረስ ሁልጊዜ በእምነትና በፍርሀት መካከል ጦርነት እናካሂዳለን። የእኛ ኃላፊነት እምነት ማሸነፉን ማረጋገጥ ነው። ፍርሀት ከተራራው እንድንሸሽ ያደርገናል፣ እምነት ተራራውን ያንቀሳቅሰዋል። ምንም እንኳ ይህ ሊሆን ቢችልም ኢየሱስ ስለ ግዙፍ ተራራ እየተናገረ አይመስለኝም። እርሱ ይናገር የነበረው ለእኛ ተራራ ስለሚመስልን ስለ ማንኛውም ነገር፣ የማይታለፍ ስለሚመስለን ስለ ማንኛውም ነገር፣ እድገታችንን የሚገታ ስለሚመስለን ስለ ማንኛውም ነገር ነበር። የእግዚአብሔር መንግስት እምነት ማንኛውንም እንቅፋት ያስወግዳል። እንቅፋቶቹ በአንድ ጊዜ ላይ ጠፉ ይችላሉ፤ በመጨረሻው ግን እምነት ያሸንፋል። ዓለምን የሚያሸንፈው እምነት ነው።

እኛ ጸሎትን ከባድ እንዲሆን እናደርገዋለን፣ ነገር ግን ጸሎት በእግዚአብሔር መንግሥት ባሕል የመጨረሻ ቀላል ነገር መሆን ይኖርበታል። የኢየሱስን ንግግር ቀላልነት ተመልከቱ፦ "እምነት ካላችሁ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ" አለ። ከዚህ የበለጠ ቀላል ነገር ምን አለ? ይህ ቀጥተኛና ትክክለኛ ነገር ነው። ለጸሎት ውጤታማነት የሚፈለገው ብቸኛ ነገር እምነት ነው። ብታምን፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት እምነት ብትለማመድ፣ ሰይጣንም ሆነ መላው የገሃነም ኃይላት ሊቋቋሙህ አይችሉም፤ ፍርሀት በእምነት ፊት ሊቆም አይችልም። በእምነት እግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነና እኛንም እንደሚወደን እናውቃለን። እምነት እግዚአብሔርን እንድንወድ ያስተምረናል፣ ይህም የፍቅር ግንኙነት ካደገ ፍርሀት ይሸሻል፣ ምክንያቱም ፍቅር ፍርሀትን አውጥቶ ይጥላል፤ ምክንያቱም "በፍቅር ፍርሀት የለም። ፍጹም ፍቅር ግን ፍርሀትን አውጥቶ ይጥላል፤ ፍርሀት ከቅጣት ጋር የተያያዘ ነውና። የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም" (1ዮሐንስ 4፥18)።



የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ጥርጥርንና ፈተናዎችን ማሸነፍ አለበት። በምድር ላይ እያንዳንዱ ሰው በፈተና ውስጥ ያልፋል። መከራዎችና ችግሮች ለሰው ልጆች የተለመዱ ዕጣ ፈንታዎች ናቸው። ለማንኛችንም ነጻ አይደለንም፤ ማንኛችንም ከዚህ ውጪ አይደለንም። ፈተናዎቹ መቼ የትና እንዴት እንደሚመጡ ለመቆጣጠር ባንችልም ለእነርሱ ምን ዐይነት ምላሽ እንደምንሰጥ ልንቆጣጠር እንችላለን። ፈተናዎች እምነታችንን ይገነባሉ ወይም ያፈርሳሉ። ግልጽ ለማድረግ ያህል፣ ፈተናዎች ምን ዐይነት እምነት እንዳለን ያስረዳሉ ወይም ይገልጣሉ። በዓለቱ በክርስቶስ ላይ የተተከለ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ፀንቶ ይቆማል፤ ሌላ ዓይነት እምነት ግን አይቆምም። አንድ ዓይነት ችግር ባጋጠመን ጊዜ በእምነትና በፍርሀት መካከል ምርጫ ማድረግ አለብን። ኢየሱስ ይህንን ይረዳል፣ ብዙ ጊዜም "አትፍሩ" ያለው ለዚህ ነው።

ከዕለታት አንድ ቀን ኢያኢሮስ የተባለ የምኩራብ አለቃ በሕመም ላይ የነበረችውን ልጁን እንዲፈውስለት ኢየሱስን ጠየቀው። በመንገድ ላይ ሳሉም መልእክተኞች መጡና ልጅቷ መሞቷን ነገሩአቸው። ኢያኢሮስንም ኢየሱስን ማድከም እንደሌለበት ተናገሩ። ኢየሱስ የተለየ አሳብ ነበረውና "ኢየሱስ ግን ሰዎቹ የተናገሩትን ችላ በማለት የምኩራቡን አለቃ እመን ብቻ እንጂ አትፍራ" አለው (ማርቆስ 5፥36)። ከዚያም ወደ ኢያኢሮስ ቤት ገብቶ ልጅቱን ከሞት አስነሳት።

እምነታችሁን በጥንቃቄ ጠብቁ። ሰዎች በከርከር እምነታችሁን ሊያስጥሉአችሁ ይሞክራሉ። ፍርሀትና ጥርጥር ሁለት ታላላቅ ጠላቶች ናቸው፤ እነርሱ ሁልጊዜ ከበር ውጭ እያደቡ ለመግባት ይዘጋጃሉ። እኔም እንደማንኛውም ሰው ፍርሀትንና ጥርጥርን አውቃቸዋለሁ፣ ምን ያህል ኃይለኛም እንደሆኑ አውቃለሁ። ሐኪም በሽታህ ካንሰር መሆኑን ይነግርሃል እንበል። የሥራ አለቃህ ከሥራ መቀነስህን ይነግርሃል እንበል። ቤትህ ይቃጠልና ሁሉንም ነገር ታጣለህ። እንዲህ ያለ ነገር ይከሰታል፣ መሬትም ከእግርህ ሥር ይከዳሃል። ዓለምህ በመላው ይበታተንብሃል። ገና ሳታስብበት ፍርሀት በውስጥ ይነግሥና ሊደመስስህ ይቃጣዋል። በዚህ ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ ይላል፣ "ይገባኛል። እንደፈራህ አውቃለሁ። አትፍራ። በእኔ እመን ፍርሀትህን ወደ እምነት ለውጥ።" በማንኛውም የቀውስ ሁኔታ ውስጥ ሁልጊዜ ምርጫ አለ፦ ይኸውም ፍርሀት ወይም እምነት ነው። እምነትን ምረጥ። ይህ ሁልጊዜ ቀላል አይሆንም ምክንያቱም ፍርሀት በጥርሱና በጥፍሩ ይዋጋሃል፣ ነገር ግን አትሸነፍ። ተዋጋ፤ የእምነትን ገድል ተጋደል።

## የእምነት ገድል (ውጊያ)

በሕይወት ውስጥ እኛ ያለን እውነተኛና ብቸኛ ገድል (ውጊያ) በእምነትና በፍርሀት መካከል ያለ ገድል ነው:: ዲያብሎስንም እንኳ አንዋጋውም፣ ሰይጣን ግን እርሱን የምንዋጋው እንዲመስለን ለማድረግ ይሞክራል:: ሐዋርያው ጳውሎስ ለወጣቱ ተከታዩ ለጢሞቴዎስ "የእምነትን ገድል" እንዲጋደል ነገረው (1ጢሞ 6፥12):: ጳውሎስ ደግሞ የሚሰብከውን ሆኗል፤ በተግባር ላይ አውሏል:: ጳውሎስ በሕይወቱ መጨረሻ አካባቢ ለጢሞቴዎስ እንዲህ ሲል መስከረለት፣ "መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፣ ሩጫውን ጨርሻለሁ፣ ሃይማኖትንም ጠብቄአለሁ" (2ጢሞቴዎስ 4፥7):: የተጋድሎውን ዐይነት በሚመለከት ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጻፈ፤ "ምክንያቱም ተጋድሎአችን ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን ከዚህ ከጨለማ ዓለም ገዦች ከሥልጣናትና ከኃይላት እንዲሁም በሰማያዊ ስፍራ ካሉ ከርኩሳን መናፍስት ሰራዊት ጋር ነው" (ኤፌ 6፥12):: መንፈሳውያን ጠላቶች መንፈሳዊ የጦር መሣሪያ ያስፈልጋቸዋል:-

> የምንኖረው በዚህ ዓለም ቢሆንም የምንዋጋው በዚህ ዓለም ስልት አይደለም ደግሞም የምንዋጋበት የጦር መሣሪያ የዚህ ዓለም መሣሪያ አይደለም:: ይሁን እንጂ ምሽግን ለመደምሰስ የሚችል መለኮታዊ ኃይል ያለው ነው:: በእግዚአብሔር ዕውቀት ላይ በትዕቢት የሚነሣውን ክርክርና ከንቱ ሐሳብ ሁሉ እናፈርሳለን:: አእምሮንም ሁሉ እየማረከን ለክርስቶስ እንዲታዘዝ እናደርጋለን (2ቆሮንቶስ 10፥3-5)::

እዚህ ላይ ጳውሎስ የሚገልፀው ምሽግ አእምሮአዊ ምሽግ ሲሆን የተጋድሎአችንን ባሕርይና የጠላቶቻችንን ማንነት በሚመለከት ዲያብሎስ እኛን ለማሳሳት የሚጠቀምበት ስውር የሆነ የአስተሳሰብ መንገድ ነው:: በሕይወት ላይ የሚደርሱ መከራዎች - በሽታ፣ የሥራ ማጣት፣ የገንዘብ ድህነት፣ አመፀኞች ልጆችና የመሳሰሉት - የእኛ ጠላቶች አይደሉም:: የእኛ ጠላቶች ተስፋችንን ለማስቆረጥ በመከራችን በመጠቀም በልባችን ውስጥ ፍርሀትንና ጥርጥርን የሚዘሩ የጨለማው ዓለም መንፈሳውያን ኃይላት ናቸው:: እነዚህን ምሽጎች ለማፍረስና እነርሱንም በእምነት መሠረት ላይ በተገነቡ በዐዲስ ዐይነት አስተሳሰቦች ለመተካት መለኮታዊ ኃይል - የክርስቶስ ኃይል -የሚያስፈልገንም ለዚህ ነው::

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት እጅግ ኃይለኛ ከመሆኑ የተነሣ የሞትን ፍርሀት እንኳን ያስወግዳል:: መጽሐፍ ቅዱስና ከዚያም በኋላ ያለው



ታሪክ ሞትን ያለ ፍርሀት፣ በልበ ሙሉነትና እንዲያውም በደስታ በተጋፈጡ ሰዎች ምስክርነት የተሞሉ ናቸው:: ምክንያቱም እነርሱ ሞት መጨረሻ (ማክተሚያ) ሳይሆን የሕይወት መጀመሪያ መሆኑን ስላወቁ ነው:: ለእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ ሥጋዊ ሞት ምንም ማለት አይደለም፤ እርሱ ወደ ሌላው ወገን ማለትም፣ ፍጹም ሙላት ወዳለው ሕይወት መግቢያ በር ብቻ ነው:: አማኞች እንደ መሆናችን መጠን ብንሞት የምናጣው ነገር የለም፤ እንዲያውም እናሸንፋለን:: አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔርን በዚህ ምድር መለኪያ እንለካውና በሌላው ወገን (በመንግሥተ ሰማያት) ከዚህ የበለጠ ታላቅ መሆኑን እንረሳለን:: ጳውሎስ ይህ እውነት መሆኑን ስለ አወቀ ፍፁም በሆነ ሰላም እንዲህ በማለት ጻፈ፤ "ለእኔ መኖር ክርስቶስ ነው፣ ሞትም ማትረፍ ነው" (ፊሊጵ 1፥21):: ንጹህ፣ ሙሉና አጠቃላይ ወደ ሆነ ድነት የሚመራው ድል እምነት ነው:: ፍርሀትና ጥርጥር ሕይወትህን እንዲገዙ አትፍቀድላቸው፤ እነርሱ የእምነት ቀማኞች ናቸው::

ብዙ ሰዎች ከእምነት ጋር ችግር ያለባቸው አንዱ ምክንያት የእውቀት ተቃራኒ ስለሚመስል ነው፤ አመክንዮአዊ አስተሳሰብን የሚቃረን መስሎ ስለሚታይ ነው:: ዓለም ውጫዊ ገጽታዎችንና ሁኔታዎችን እንዳለ የመቀበል ዝንባሌ አለው:: ይሁን እንጂ ብዙ ጊዜ ውጫዊ መልክ አሳሳች ነው:: አንድን ሁኔታ ከእግዚአብሔር እይታ አንፃር ካላየነው በስተቀር ፈጽሞ እውነቱን ለማወቅ አንችልም:: ለዚህም እምነት ያስፈልጋል:: እምነት ለዓለም ምንም ስሜት አይሰጥም፣ ምክንያቱም ተፃራሪ ነገር ያለበት ስለሆነ ነው:: ተፃራሪ ማለት ተቃራኒ የሚመስል ግን እውነት የሆነ መግለጫ ነው:: የእግዚአብሔር መንግሥት ሕይወት በተፃራሪ ነገሮች የተገነባ ነው:- ኋለኞች ፊተኞች፣ ፊተኞችም ኋለኞች ይሆናሉ (ማቴ 19፥30 ይመልከቱ):: በመንግሥቱ ውስጥ ታላቅ የሚሆነው የሁሉም አገልጋይ ነው (ማቴ 23፥11):: ትህትና የታላቅነት መንገድ ነው (ማቴ 18፥4):: ነፍሱን ስለ ክርስቶስ የሚያጠፋ ያድናታል (ማቴ 16፥25 ይመልከቱ):: እምነትም ደግሞ ተፃራሪ ነገር ነው:: ዕብራውያን 11፥1 እንደሚነግረን እምነት ተስፋ ያደረግነው ነገር እንደሚፈጸም እርግጠኛ የምንሆንበት፣ የማናየውም ነገር እውን መሆኑን የምንረዳበት ነው:: በሌላ አነጋገር ለማስቀመጥ፣ ጥርጥር ሲገጥምህ፣ እምነት ይኑርህ የምታደርገውን ስታጣ እመን:: ምንም ነገር ስሜት ሳይሰጥህ ሲቀር፣ ተማመን::

በምዕራፍ አንድ ውስጥ እንዳየነው፣ እምነታችንን የምናሳርፍበት ሥፍራ ወሳኝ ነው:: ኢየሱስ "በእግዚአብሔር እመኑ" አለ (ማርቆስ 11፥22):: በነገሮች ላይ ወይም በሰዎች ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ተማመኑ:: እርሱ ብቻ የማይነቃነቅ ነው:: ሰዎች ይረሱአችኋል:: ዕቅዶች ይከሽፋሉ:: የምድር

ሥርዓቶች ይፈርሳሉ፡፡ ሥራ ይታጣል፡፡ እምነትህን በእግዚአብሔር ላይ ጣል፡፡ የእርሱ መንግሥት ከቶ አይወድቅም፡፡ እግዚአብሔር ከቶ አይጥልህም፡፡ እርሱ ቋሚ ነው፡፡ እርሱ ጽኑ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለዘላለም ነው፡፡

## ምልክት ሳይሆን እምነት

እስከ አሁን እንዳየነው በእግዚአብሔር ማመን ማለት በስጦታዎቹ ላይ ሳይሆን በእርሱ ላይ መተማመን ነው፡፡ እርሱ በሚያደርገው ነገር ላይ ሳይሆን በማንነቱ ላይ ማመን ነው፡፡ ሁልጊዜ ምልክትን የሚፈልግ እምነት ያልበሰለ እምነት ነው፡፡ ልብ አድርግ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት የሚያምነው ተስፋ የምናደርገውንና ገና የማናየውን ነገር ነው፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ሰው ወደ ኢየሱስ መጥቶ ተአምር እንዲያሳየው ቢጠይቀው ኢየሱስ የሚያስገርም ምላሽ ሰጠው፡-

> ኢየሱስም ውሀውን የወይን ጠጅ ወዳደረገበት በገሊላ ወደምትገኘው ወደ ቃና ከተማ ዳግመኛ መጣ፡፡ በቅፍርናሆምም ልጁ የታመመበት አንድ የቤተ መንግሥት ሹም ነበረ፡፡ ይህም ሰው ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ መምጣቱን በሰማ ጊዜ ወደ እርሱ ሄደና በሞት አፋፍ ላይ የነበረውን ልጁን መጥቶ እንዲፈውስለት ለመነው፡፡
>
> ኢየሱስም "መቼውንም እናንተ ምልክቶችንና ድንቅ ነገሮችን ካላያችሁ አታምኑም" አለው (ዮሐንስ 4፥46-48)፡፡

ይህ ከባድ አይመስልምን? የፈራና ልቡ የተሰበረ ሰው በሞት አፋፍ ላይ ለነበረው ልጁ ፈውስን ፈልጎ ወደ ኢየሱስ ቢመጣ "ኢየሱስ ምልክቶችንና ድንቅ ነገሮችን ካላያችሁ አታምኑም" ይለዋል፡፡ 'ይህ ችግረኛ ሰው ነው፣ ኢየሱስ ሊያዝንለት ይገባው ነበር' ብለህ ታስብ ይሆናል፡፡ በዚህ ፈንታ እርሱ ሁልጊዜ ምልክት ለማየት የሚፈልግን እምነት ይነቅፋል፡፡ በርግጥም ኢየሱስ በዙሪያው የሚሰበሰቡ ሰዎች የነበራቸውን የእምነት ጉድለት በማየት ብዙ ጊዜ ሳያዝን አልቀረም፡፡ አንዳንድ ነገሮችን ለማግኘት ብቻ ወደ እርሱ በመምጣታቸው የተሰላቸ መሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ ነገር ግን በዚህ ውስጥ ሌላም ነገር አለ፡፡ ኢየሱስ ከእርሱ ረድኤትን ፈልጎ የመጣውን ሰው እምነቱንና መነሻ ምክንያቱን እየፈተነ ነበር፤ ሰውዬው ፈተናውን አለፈ፡፡

> ሹሙም "ጌታዬ ልጄ ከመሞቱ በፊት እባክህ ድረስልኝ" አለው፡፡



> ኢየሱስም "ልጅህ በሕይወት ይኖራልና ሂድ" አለው፡፡
>
> ሰውዬውም ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አምኖ ሄደ፡፡ በመንገድ ላይ እንዳለም አገልጋዮቹ አግኝተውት ልጁ በሕይወት መኖሩን ነገሩት፡፡ እርሱም ልጁ በስንት ሰዓት እንደ ተሻለው ሲጠይቃቸው "ትኩሳቱ የለቀቀው ትናንት በሰባት ሰዓት ላይ ነው" አሉት፡፡
>
> አባትዮውም ሰዓቱ ኢየሱስ "ልጅህ በሕይወት ይኖራል" ያለበት ሰዓት መሆኑን ተገነዘበ፡፡ እርሱና ቤተሰቡም ሁሉ አመኑ (ዮሐንስ 4፥49-53)፡፡

የዚህ የሀዘንተኛ አባት ብቸኛ ጭንቀት በሞት አፋፍ ላይ የነበረው ልጁ ሕይወት ነበር፡፡ እርሱ አንፀባራቂ ትርኢት ወይም አስገራሚ ተአምር አልፈለገም፡፡ እርሱ የፈለገው ልጁ እንዲድንለት ብቻ ነበር፡፡ አሁን ኢየሱስ በአዘኔታ መለሰለት፡፡ ፈተናው አለቀ፡፡ ሰውየው ወደ ቤቱ እንዲሄድ ልጁም እንደሚፈወስ ነገረው፡፡ ሰውዬው የኢየሱስን ቃል አምኖ እንደሄደ ተመልከቱ፡፡ የእርሱ የመጀመሪያው ጥያቄ ኢየሱስ መጥቶ ልጁን እንዲፈውስለት ነበር፡፡ በዚህ ፈንታ ኢየሱስ "ሂድ ልጅህ በሕይወት ይኖራል" አለው፡፡ ለሰውዬው ይህ በቂ ነበር፡፡ የኢየሱስን ማረጋገጫ ተቀብሎ በልበ ሙሉነት መሄዱ የእርሱ እምነት በተአምሩ ላይ ሳይሆን በተአምሩ አምላክ ላይ መሆኑን ያሳያል፡፡ ልጁ ኢየሱስ በተናገረበት ትክክለኛ ሰዓት የመፈወሱ ማረጋገጫ የሰውዬውን እምነት ከማጠናከሩ የተነሣ እርሱና መላው ቤተሰቡ ተለወጡ፡፡ እንደ ሁለቱ ዐይነ ስውራን ይህም ሀዘንተኛ አባት የእግዚአብሔር መንግሥት ንግድ በእግዘኢ.ብሔር መንግሥት ገንዘብ - በእምነት - ተለዋወጠና የመንግሥትን ጥቅም አገኘ፡፡

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ለእምነታችን እንድንዋጋ ይፈልጋል፤ ምክንያቱም ለእምነታችን መዋጋት እምነታችንን ያጠነክረዋል፡፡ በረከቶች ሁልጊዜ እኛ ስንፈልጋቸው አይመጡም፤ ፈውሶች ሁልጊዜ በእኛ የጊዜ ሰሌዳ አይፈጸሙም፤ ችግሮች ሁልጊዜ እኛ በምንፈልግበት ፍጥነት አይወገዱም፡፡ እግዚአብሔር እነዚህን ወቅቶች እምነታችንን ለመፈተን ይጠቀምባቸዋል፡፡ እርሱ እንዲህ ሲል ይጠይቃል፡- "በምንም ሁኔታ ውስጥ በእኔ ትተማመናለህን? አንተ የምትፈልገውን በምትፈልግበት ጊዜ ወይም በምትፈልግበት መንገድ ባታገኝ እንኳ ታምናለህን?" እርሱ እምነታችን በተግባር ላይ ሲውል ማየት ይፈልጋል፡፡ እኛም እምነት የሚሠራ መሆኑን እንድናይ ይፈልጋል፡፡

እኛን የሚጠብቁን ተአምራት አይደሉም፤ የሚጠብቀን የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ሕመምተኛ ልጅ የነበረው ሰው በኢየሱስ ቃል አመነ፤ ተአምሩንም ተቀበለ፡፡ የእርሱ እምነት በክርስቶስ ላይ እንጂ ክርስቶስ በሚያደርገው ነገር ላይ አልነበረም፡፡ ልብ በሉ፣ በረከቶች ጊዜያዊ ናቸው፡፡ ተአምራት ጊዜያዊ ናቸው፡፡ ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት አስነሳው፣ ነገር ግን አልዓዛር በኋላ እንደገና ሞተ፡፡ ምልክቶችና ድንቅ ነገሮች ጊዜያዊ ናቸው፡፡ እግዚአብሔር ግን ቋሚ ነው፡፡

እግዚአብሔር በአንተ ሕይወት ውስጥ ሊያደርግ የሚፈልገውን ነገር ያለ እምነት አያደርግም፡፡ ያለ አንዳች ምልክት በእርሱ ብቻ ማመን አለብህ፡፡ እርሱ እምነትህን ለማረጋገጥና ለማጠናከር ይፈትነዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ወደ ጫፍ ላይ ይወስድህና “ዝለል” ይልሃል፡፡ ለውጤቱ በእርሱ ላይ በመተማመን ቃሉን ብቻ አምነህ ትዘልላለህ? ወይስ ወደኋላ ተመልሰህ “ጌታ ሆይ በመጀመሪያ ምልክት አሳየኝ!” ትላለህ? እርሱ ለመዝለል የሚያበቃ እምነት እንዳለህ ለማወቅ ይፈልጋል፡፡ ከዚህም በላይ አንተ ለመዝለል የሚያበቃ እምነት ያለህ መሆኑን እንድታውቅ ይፈልጋል፡፡ እርሱ ከመያዙ በፊት እስከ መሬት ድረስ እንድትወርድ ሊተውህ ይችላል፤ ግን ይይዝሃል፡፡ ከዚያም በኋላ፣ “ጥሩ አደረግህ! እንደምታደርገው አውቄ ነበር፣ አንተ እውነትም የእኔ መንግሥት ልጅ ነህ!” ይልሃል፡፡

እምነት የእግዚአብሔር መንግሥት ገንዘብ ነው፡፡ በልግስና (ያለመቈጠብ) ተጠቀምበት፣ ከዚያ ሁሉም ነገር ክፍት ይሆንልሃል፡፡ እምነትህን በእግዚአብሔር ላይ ጣል፡፡ በእርሱ እመን፣ ከዚያም ሁሉ ነገር ይቻላል፡፡



## የእግዚአብሔር መንግሥት መርሆች

- እምነት የእግዚአብሔር መንግሥት ገንዘብ ነው፡፡
- በመንግሥቱ ውስጥ እያንዳንዱ ነገር የሚገኘው በእምነት ነው፡፡
- ያለ እምነት የመንግሥቱ መርሆች ሊንቀሳቀሱ አይችሉም፡፡
- የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት መርሕ ቀላል ነው፤ የማታምነውን ነገር ልታገኝ አትችልም፣ የማትጠባበቀውን ነገር አታይም የሚል ነው፡፡
- የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት፣ የመንግሥቱ ዜጎች በቃሉ ሕገ መንግሥት ውስጥ ያሉትን የመንግሥታቸውን ሕጋዊ የተስፋ ቃሎች ከማመንና በሕጉ ውስጥ ያሉትን መብቶቻቸውን ከመጠየቅ የተለየ ነገር አይደለም፡፡
- ጥርጥር ሲገጥምህ እምነት ይኑርህ፤ የምታደርገውን ስታጣ እመን፤ ምንም ነገር ስሜት ሳይሰጥህ ሲቀር ተማመን፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት የተፈተነ እምነት ነው

*"የምትጨብጠው እርሱ ብቻ እስካልሆነ ድረስ እምነትህ እምነት አይደለም"::*

የእግዚአብሔር መንግስት እምነት የተፈተነ እምነት ነው:: የተፈተነም እምነት የበሰለ እምነት ነው:: ልብ አድርግ፣ የእምነታችን ጥንካሬ ሊያልፍ የሚችለውን ፈተና ያህል ነው:: ይህ እስካልሆነ ድረስ አታምንም ማለት ነው፤ የእምነታችን ጥንካሬ በእግዚአብሔር መንግሥት ሕይወት ምን ያህል በሙላት እንደምንሠራበትና እንደምንደሰትበት ይወስናል:: እምነት የእግዚአብሔር መንግሥት ገንዘብ ነው፣ የመንግሥቱ ምጣኔ ሀብትም ከቶ ድቀትን አያውቅም:: የዋጋ ግሽበትም የለበትም:: የመንግሥቱ ምጣኔ ሀብት ሁልጊዜ የተረጋጋ፣ ሁልጊዜ አስተማማኝ፣ ሀልጊዜ ዋስትና ያለው ነው:: ገንዘባችንን (እምነታችንን) በመንግሥቱ ምጣኔ ሀብት ላይ በምናውልበት ጊዜ፣ "በደለበ" ገበያ ውስጥ ማዋላችን ነው::

ስለ እምነት ብዙ መናገር አንድ ነገር ነው፤ ነገር ግን እምነታችንን በሥራ ላይ ማዋል - "ገንዘባችንን አፋችን በተናገረበት ላይ ማዋል" ሌላ ነገር ነው:- ይኸውም በሀዘንና በፈተና ጊዜ ማለት ነው:: እውነተኛ የብስለት ደረጃችን የሚገለጠው በዚህ ጊዜ ነው:: ብስለታችን የሚለካው ጫናን፣ ትካዜን እንዲሁም የግራ መጋባትንና የማዕበልን ወቅት በምናስተናግደበት ሁኔታ ነው:: ብስለት የሌላቸው ሰዎች በትካዜ ጊዜ ተዝለፍልፈው ይወድቃሉ:: ጫና ሲደርስባቸው ይሸነፋሉ:: ነገሮች ሲጠንከሩ ትተው ይሸሻሉ:: የአንተ ብስለት ምን ያህል ነው?

ለስኬታማ ኑሮ ቁልፉ የሚጠበቀውንና የማይጠበቀውን ነገር ለማስተናገድ ያለን አቅምና ችሎታ መጠን ነው:: ለብዙ ሰዎች የሚጠበቀውን ነገር ማስተናገድ በጣም ከባድ አይደለም፣ ምክንያቱም በቀላሉ ሊዘጋጁበት ስለሚችሉ ነው፤ ነገር ግን የማይጠበቀውስ ሁኔታ እንዴት ነው? አንድ ያልተጠበቀ ነገር በድንገት ሲከሰት ምላሽህ ምን ዐይነት ነው? ላልተጠበቀው ነገር የምትሰጠው ምላሽ አንተ ምን ዐይነት እንደሆንህ በግልጽ የሚያሳይ ምልክት ነው:: የበሰሉ ሰዎች ላልተጠበቀው ነገር ይዘጋጃሉ:: እነርሱ ያልተጠበቀውን ስለሚጠባበቁ ለእርሱ በቅድሚያ ይዘጋጃሉ:: ያልበሰሉ ሰዎች ግን ይህን ስለማያደርጉ ውጤቱን ያገኙታል:: በጥንታዊው ምሳሌ አባባል፤ "አስተዋይ ሰው አደጋ ሲያይ መጠጊያ ይሻል፤



ብስለት የጐደለው ግን በዚያው ይቀጥላል መከራም ያገኘዋል" (ምሳሌ 22፥3)::

ብስለትና ስኬት የተያያዙ ናቸው:: ስኬት የሚለካው በመከራ ጊዜ የራስህን ሚዛን በምትጠብቅበት ሁኔታ ነው:: ለብዙ ዓመታት በእርሱ የኖርሁበት አንድ አባባል አለኝ:- "እኔ ስለማልጨነቅ አንተ ተጨነቅልኝ":: አስቀድሞ ስለ እያንዳንዱ ነገር የሚጨነቁ በቂ ሰዎች አሉ:: ስለዚህ እኔ ለምን እጨምራለሁ? የበሰሉ ሰዎች በመከራ ጊዜ እንኳ ሚዛናቸውን ይጠብቃሉ:: ሚዛንን መጠበቅ ማለት የምናየውን ነገር ከማመን ይልቅ እግዚአብሔር የሚናገረውን ማመን ነው:: ውጫዊ መልክ አሳሳች ሊሆን እንደሚችል ልብ በል በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እውነቱን ለማወቅ በእግዚአብሔር ዓይን መመልከት አለብን:: ለማየትም በእምነት ዓይን መጠቀም አለብን:: በሕይወት ውስጥ ትልቁ መገለጥና እንዲሁም ትልቁ የእድገት ዕድል የሚመጣው ባልተጠበቀው የችግርና የፈተና ወቅት ነው:: እግዚአብሔር በትኩስና በዐዲስ መልክ ራሱን የሚገልጥልን በዚህ ጊዜ ነው:: ዐዲስ ሁኔታን ማስተናገድ ስለሚያስፈልገን ዐዲስ እምነትን ይሰጠናል:: ነገር ግን ያለንን እምነት በሥራ ላይ ማዋል አለብን::

ፈተናዎች በሳልና ሚዛናዊ ወደ መሆን እንድናድግ ይቀርጹናል:: ብስለትህ የሚለካው በአደጋና በትርምስ ጊዜ በተሳካ ሁኔታ ምላሽ ለመስጠት ባለህ ችሎታ መጠን ነው:: ትርምስን የምታስተናግደው እንዴት ነው? በአካባቢህ ሁሉም ነገር በድንገት በሚፈርስበት ጊዜ ምን ታደርጋለህ? በዚያ ወቅት የምታደርገው ነገር ብስለትህ ምን ያህል እንደሆነ ይገልጣል:: ሁልጊዜ የአንድን ሰው ብስለት፣ ጫናዎችን በሚያስተናግድበት ሁኔታ ልትረዳ ትችላለህ:: በሌላ አባባል፣ በጭንቀት ጊዜ የእርሱን ወይም የእርሷን ባሕርይ እስካላየን ድረስ አንድን ሰው በትክክል ለማወቅ አንችለም:: ጫና ብስለትን ብቻ አይገልጥም፤ ባሕርይንም ይገልጣል:: ላልተጠበቀው፣ ለትርምሱ እንዲያውም ለአስከፊው አደጋ ተዘጋጅተሃልን? እምነትህ በሕይወት ፈተናዎች ውስጥ የሚፀናና የሚያድግ ነውን? ወይም አንተ ሕይወትን በጥሩ ሁኔታ ለማስተናገድ እንድትችል የአንተ ዓለም ንጹህ፣ የተስተካከለና ያልተጐሳቆለ መሆን ይጠበቅበታልን? ፈተናዎችን አትፍራ እነርሱ ያጠነክሩሃል:: አንተ የሚጠበቅብህ በእምነትህ ጸንተህ መቆም ነው:: ከዚያም ብስለትንና ሚዛናዊነትን አግኝተህ ታልፋለህ::

በእምነታችን ጸንተን ለመቆም የሚያዳፋፍረን አንዱ ነገር፣ ከቶ የማይወድቅ ወይም የማይወገድ መንግሥት ዜጐች የመሆናችን ሐቅ ነው:: የእግዚአብሔር መንግሥት ዘላለማዊ መንግሥት ሲሆን እርሱም የመጨረሻው ሰብአዊ መንግሥት ከፈረሰና አቧራ ላይ ከወደቀ በኋላ

ለዘመናት በሙሉ ኃይሉና ክብሩ ጸንቶ የሚቆም ነው። እስኪ ከቅዱስ መጽሐፍ ድፍረትን እንቀበል፦

> "ስለዚህ ከቶ የማይናወጥ መንግሥት ስለምንቀበል እግዚአብሔርን እናመስግን ደግሞም ደስ በሚያሰኘው መንገድ በአክብሮትና በፍርሀት እናምልከው፣ አምላካችን የሚያጠፋ እሳት ነውና" (ዕብ 12፥28-29)።

ሰማያዊው አገርና እርሱ የሚወክለው መንግሥት ሊናወጡ አይችሉም። አንዳንድ ጊዜ ይህ መንግሥት እስከ አሁን ድረስ በምን ውስጥ እንዳለፈና አሁን በእኛ የሕይወት ዘመን በማለፍ ላይ ካለበት በባሰ ሁኔታ ውስጥ እንዳለፈ እንረሳለን። በዘመናት ሁሉ ብዙ ሰዋዊ ግዛቶችና መንግሥታት የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማጥፋት ሞክረዋል። የእግዚአብሔርን ሕዝብ አሳድደዋል፣ ገድለዋልም። የእግዚአብሔርን መጽሐፍ፣ መጽሐፍ ቅዱስን፣ አግደዋል፣ አቃጥለዋልም። የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማርን ሕገ ወጥ አድርገውታል። በሌሎችም በብዙ መንገዶች የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመርገጥ፣ ለማጣመምና ዋጋ ቢስ ለማድረግ ሞክረዋል። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር መንግሥት አሁንም በጽናትና በማይናወጥ ሁኔታ ፀንቶ ሲቆም እነዚያ መንግሥታት ግን አንድ በአንድ ወድቀዋል፤ ከገጸ ምድርም ጠፍተዋል። የእግዚአብሔር ቃል እኛ በምንገምተው በማንኛውም ነገር ውስጥ ዐልፎ በአሸናፊነት ወጥቶአል፤ ሁልጊዜም ያሸንፋል። እያንዳንዱ ትውልድ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት የሚገዳደሩ ዐዳዲስ ኃይላት ወይም መንግሥታት ሲነሱ ያያል፤ ዛሬም በዓለማችን ተገዳዳሪዎችን እናያለን። ይህ የሚጠበቅ ነው፤ ምክንያቱም ሰይጣን ተስፋ አይቆርጥም። ነገር ግን የእግዚአብሔር መንግሥት ሁሉንም ዐልፎ ይሄዳል። ስለዚህ ልበ ሙሉ ለመሆን በቂ ምክንያት አለን።

## የተፈተነ እምነት ጽናትን ይገነባል

በየቀኑ ተግዳሮት በሞላበት ዓለም ውስጥ ስኬታማ ኑሮ ለመኖር እንዴት መጽናት እንደሚቻል የሚያውቁ ጠንካራ ሰዎችን ይጠይቃል። የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ጽናትን ይገነባል፤ ይህም ፈተናዎችንና ችግሮችን በመሸሽ ወይም በማምለጥ ሳይሆን በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል ፊት ለፊት በመጋፈጥ ነው። የእግዚአብሔር ቃል በፈተና ውስጥ በእምነትና በጽናት መካከል ግልጽ የሆነ ተያያዥነት መኖሩን ይገልጻል፦

> ወንድሞች ሆይ፣ እምነታችሁ በየጊዜው እያደገ በመሄዱና የእርስ በርስ ፍቅራችሁም እየጨመረ በመምጣቱ ስለ



> እናንተ እግዚአብሔርን ሁልጊዜ በሚገባ ማመስገን አለብን። ስለዚህ በደረሰባችሁ ስደትና መከራ ሁሉ በመጽናታችሁ እኛ ራሳችን ስለ ትዕግሥታችሁና ስለ እምነታችሁ በእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ እንመካለን።
>
> ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ፍርድ ቅን መሆኑን የሚያመለክት ነው። ከዚህም የተነሣ መከራን ለምትቀበሉለት ለእግዚአብሔር መንግሥት የበቃችሁ ሆናችሁ ትቆጠራላችሁ (2ተሰሎንቄ 1፥3፥5)።

በተሰሎንቄ ከተማ የነበሩ ክርስቲያን አማኞች በስደትና በመከራ ውስጥ እያለፉ ነበር። ጳውሎስ እንደሚለው እነርሱ መከራን የሚቀበሉት ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ነበር። ታዲያ መከራ የመቀበላቸው ውጤት ምን ነበር? እነርሱ እየተማረኩ፣ ወይም እየሸሹ ወይም እየተሸነፉ ወይም እምነታቸውን እየተው ነበርን? አይደለም። በተቃራኒው እነርሱ እየጸኑ ነበር። እምነታቸውም በየጊዜው እያደገ ነበር። የእርስ በርሳቸውም ፍቅር እየጨመረ ነበር። ይህ ሁሉ የሆነው በስደትና በመከራ ውስጥ ነበር። እነዚህ አማኞች የእምነትና የጽናት መልካም ስምን እያዳበሩ ነበር። ሰዎች አንተ የሸሸህበትን ነገር ሳይሆን ያለፍህበትን ነገር ቢያውቁ ታላቅ ነገር አይደለምን? በመከራ ውስጥ በፀጋና በልበ ሙሉነት ብንጸናና ጥንካሬን አግኝተን ብንወጣ ሰዎች ባጋጠማቸው ፈተና እንዲጸኑ ልናደፋፍራቸውና ልናነቃቃቸው እንችላለን። ከዚህም በላይ የእኛ ጽናት በእርሱ ኃይል ጽናትን ወደምናገኝበት ወደ ኢየሱስ ይመራቸዋል።

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት መከራን እንድንችል ያስታጥቀናል። ደግሞም ይህ እምነት እኛ በምናልፈው በእያንዳንዱ ፈተና ጥንካሬን ያገኛል። ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ባሕርይ ነው፤ እርሱ በችግር ጉድጓድም ውስጥ ያብባል። የሕይወትን መከራና ፈተና ለመሸሽ አንችልም፣ ነገር ግን በጌታ መገኘትና ኃይል በፈተና ላይ ድልን እናገኛለን። በዚህም ወቅት የውስጥ ሰላምን እንለማመዳለን። ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ "በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ ይህን ነግሬአችኋለሁ። በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ" (ዮሐንስ 16፥33)።

በአጠቃላይ ሰዎች እኛ በመልካም (በስኬት) ጊዜ - ባለን እምነት አይደነቁም። ነገሮች በጥሩ ሁኔታ ሲሄዱ ማንም ሰው ማመን ይችላል። ሁኔታዎች አስቸጋሪ ሲሆኑ እኛ የምናደርገውን ለማየት ይጠባበቃሉ።

ባለህበት ቦታ በሕይወትህ ላይ ምንም ነገር ይሁን ቢከሰት ኢየሱስን ልታንፀባርቀው (ልታሳየው) ትችላለህን?

ከዓመታት በፊት በአክላሆማ ግዛት፣ በቱልሳ፣ ከኮሪ ቴንቡም ጋር ምሳ የበላንበትን ቀን አስታውሳለሁ። ኮሪ ቴን ቡም፣ ከሌሎች የቤተሰብዋ አባላት ጋር በመሆን በትውልድ አገራቸው በሆላንድ በአባታቸው የእጅና የግድግዳ ሰዓት ሱቅ ውስጥ ይሠሩ በነበረበት በ2ኛው የዓለም ጦርነት ወቅት አይሁዶችን ከናዚዎች እየደበቁ ከአገር እንዲወጡ የሚረዱ ነበሩ። በመጨረሻም እነርሱ ራሳቸው በጀርመኖች ተማርከው ወደ ማጐሪያ ጣቢያ ተላኩ። የኮሪ ቴን ቡም አባትና እህቷ ቤጺ ሁለቱም በማጐሪያው ጣቢያ ውስጥ ሞቱ። ይሁን እንጂ ቤጺ ከመሞቷ በፊት ከእህቷ ጋር በመሆን ራቬንስብሩክ በሚገኘው የማጐሪያ ጣቢያ አብረዋቸው ለታሠሩት ሴቶች የክርስቶስን ፍቅርና ፀጋ ብርሃን አበሩላቸው። ኮሪ በተሳካ ሁኔታ ዘበኞቹን በማሳለፍ በድብቅ ባስገባችው ትንሽ መጽሐፍ ቅዱስ በመጠቀም ማታ ማታ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብና የጸሎት ስብሰባ በጣቢያው ውስጥ ያካሂዱ ነበር። ሰማያዊው የእውነት ብርሃን የምድር ገሃነም በመሰለው በማጐሪያው ሥፍራ እንዲበራ አደረጉ። ብዙ ሰዎችም ዘላለማዊ ለውጥን አገኙ።

ኮሪ ቴን ቡም በእርስዋ ዕድሜ ያሉት ሴቶች ወደ ጋዝ ማቃጠያው ክፍል ከመላካቸው ከአንድ ወር በፊት ከራቬንስብሩክ ማጐሪያ ጣቢያ "በኃላፊዎች ስህተት" ተለቅቃ በዓለም ውስጥ በመዳዝ የቀረውን ረጅም ዕድሜዋን ስለ እግዚአብሔር ፀጋና ፍቅር በማስተማርና በመመስከር አሳለፈች። ኮሪ፣ "የእግዚአብሔር ፍቅር አልፎ የማይወርድበት የጉድጓድ ጥልቀት የለም" ትል ነበር። እርስዋ አወቀች፣ ኖረችበትም። የእርስዋ እምነት የእህትዋ የቤጺ ጭምር - ከመቼውም ይበልጥ በራቬንስብሩክ ተፈተነ፣ እነርሱም አሸነፉ።

ኮሪ ስለ ተሞክሮአቸው "የመደበቂያ ሥፍራ" (ዘ ሃይዲንግ ፕሌስ) የተሰኘ መጽሐፍ የጻፈች ሲሆን ጽሁፍዋ ከጊዜ በኋላ ጥሩ ተንቀሳቃሽ ፊልም ሆኖ ተሠርቷል። በፊት እንዳልሁት ከእኚህ ሴት ጋር ዐብሮ ምሳ የመብላት የተባረከ ዕድል አግኝቼአለሁ። በዚያን ጊዜ 87 ዓመት ዕድሜ የነበራት ቢሆንም ለጌታ ገና ጠንካራ ነበረች። በምግብ ላይ ሳለን እንዲህ በማለት ጠየቅኋት፤ "ሚስስ ቴን ቡም፣ ለአንድ ወጣት የሚረዳውን አንድ ነገር የምትነግሪው ካለ ምን ትነግሪኛለሽ?"

የእርስዋ መልስ ሕይወቴን ለወጠው። እርስዋም "ማይልስ፣ በተተከልህበት ሥፍራ ማደግን ብቻ አስታውስ" አለችኝ። እኔም በ1980 የባሃማስን የእምነት አገልግሎት ቤ/ክ ከመሠረትሁ ጀምሮ ያደረግሁት



ይህንኑ ነው፤ አሁንም ከ30 ዓመታት በኋላ እዚሁ ነኝ። ሰዎች ይመጣሉ፣ ይሄዳሉ፣ የተለመደ ነው፣ እኔ ግን አሁንም እዚሁ ነኝ። ከእኔ ጋር የሚያገለግሉት አንዳንድ ሰዎችም ከመጀመሪያ ጀምሮ እዚሁ ናቸው። በተተከልህበት ሥፍራ እደግ። እግዚአብሔር ባስቀመጠህ ሥፍራ ለምልም። በባሃማስ የእምነት አገልግሎት በነበርንበት በዘመናት ውስጥ ማንኛውንም ማዕበል፣ ስደትና መከራ አሳልፈናል። ለምን? ምክንያቱም ስለተተከልን ነው። እዚህ ያለነው ነገሮች መልካም ወይም መጥፎ ስለሆኑ አይደለም። እዚህ ያለነው እግዚአብሔር ስለተከለን ነው። በተተከልህበት ቦታ እደግ። ጳውሎስ የተሰሎንቄን ሰዎች እንዲህ ሲል አመሰገናቸው፣ "... ስለዚህ በደረሰባችሁ ስደትና መከራ ሁሉ በመጽናታችሁ እኛ ራሳችን ስለ ትዕግሥታችሁና ስለ እምነታችሁ በእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ እንመካለን" (2ተሰሎ 1፥4)። ባለፈው ስለ አሳለፋችሁትና አሁንም በማሳለፍ ላይ ስላላችሁት መከራ አስቡ። ጳውሎስ ስለ ጽናታችሁና ስለ እምነታችሁ ይመካልን? ከዚህም በላይ እግዚአብሔር ይመካልን?

ደግሞም ጳውሎስ እምነታችን በፈተና ውስጥ ጸንቶ ሲቆም ለእግዚአብሔር መንግሥት የበቃችሁ ሆናችሁ ትቆጠራላችሁ አለ (2ተሰ 1፥5)። ለእግዚአብሔር መንግሥት ያለን ብቃት ችግርን ከማሳለፍ፣ በመከራም ከመጽናት ችሎታችን ጋር የተሳሰረ ነው። ይህንን በማሳብ ፈተናዎችን በደስታ መቀበል አለብን፣ ፈተናዎቹ ቀላል ስለሆኑ አይደለም፤ ብዙ ጊዜ እነርሱ ቀላል አይደሉምና ነገር ግን እነርሱ ወደ ብስለትና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሙላት የሚያሳድጉን መሆኑን ስለምናውቅ ነው። የጌታ ወንድም ያዕቆብ እንዲህ በማለት አስቀምጦታል፤

> ወንድሞቼ ሆይ፣ ልዩ ልዩ መከራ ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት፣ ምክንያቱም የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ ታውቃላችሁ። ምንም የማይጐድላችሁ ፍጹማንና ምሉኣን እንድትሆኑ ትዕግሥት ሥራውን ይፈጽም (ያዕቆብ 1፥2-4)።

በችግር ውስጥ በምታልፉበት ጊዜ ሁሉ ጥንካሬና ብስለት በውስጣችሁ ያድጋሉ። በሌላ አነጋገር፣ በሂደቱ ውስጥ መጥፎ ሁኔታችሁ እየቀነሰ፣ እናንተ ግን እያሸነፋችሁ ትሄዳላችሁ። ብዙ ጊዜ በመልካም ጊዜያት አናድግም። እግዚአብሔር በሕይወትህ ለሌላ እድገት ያዘጋጀህ መሆኑን የምታውቀው በመንገድህ ላይ እንዲገጥሙህ በሚፈቅዳቸው ፈተናዎች ነው። ትንሽ አስቸጋሪ በሆነ ወቅት ውስጥ የሚያሳልፍህ ወደ ሌላ ደረጃ ከፍ ሊያደርግህ ሲፈልግ ነው። ስለዚህ በመንገድህ ላይ በሚደቀንብህ ነገር በጽናት ቁም፣ በእምነት ተጋፈጠው፣ ከዚያም በአሸናፊነትና በጥንካሬ ትወጣለህ። ሰዎች

ስለ አንተ ምን ለማለት እንደሚችሉ ገምት፣ ከዚህም በላይ ኃይልን የሚሰጥህ እግዚአብሔር ምን እንደሚል ገምት።

በአካባቢህ ያሉ ሰዎች ምን ዐይነት እምነት እንዳለህና ምን ዐይነት አምላክ እንደምታገለግል ለማየት ይጠባበቃሉ። የምትናገረው ታሪክ መልካም ብቻ ከሆነ እነርሱ እግዚአብሔር ሰማያዊ የገና አባት (ሳንታክላውስ) ከመሆን የበለጠ አይደለም ከሚል ድምዳሜ ላይ ይደርሳሉ። ነገር ግን በገሃነም ውስጥ ስታልፍና አንዳች የጭስ ሽታ ሳይኖርብህ በፈገግታ ስትወጣ ሲያዩህ "ይህን ዐይነት አምላክ እኔም እፈልጋለሁ" ይላሉ። በሚጠባበቀን ዓለምና በእግዚአብሔርም መንግሥት ዘንድ ከበሬታን የሚያስገኝልን የምንሸሽበት ሳይሆን የምንጸናበት ነገር ነው።

## ፈተናውን ያለፉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጀግኖች እምነት

ጠንካራ እምነት ያለው ሰው እንድትሆን የሚያስችልህ ነገር እንዳለህ የምትጠራጠር ከሆነ፣ ወይም ያለፈው አጠያያቂ ሕይወትህ ተስፋ የሚያስቆርጥህ ከሆነ፣ ፈተናውን ያለፉትን እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ተመልከት። እነርሱ እንደ አንተና እንደ እኔ ተራ ሰዎች ነበሩ፤ እነርሱም ከአንዱ (ከኢየሱስ) በስተቀር ሁሉም በአንድ ወይም በሌላ መንገድ አንዳንዶቹም በከፍተኛ ደረጃ ወድቀው ነበር። ይሁን እንጂ እነርሱ ለእግዚአብሔር መንግሥት ተገቢ መሆናቸውን በማረጋገጥ ወደ ድል ተሸጋግረዋል።

ሙሴ ግብፃዊውን ገደለ። ሙሴ ከራሱ ሕዝብ መካከል አንዱ የሆነውን ዕብራዊ ሲመታ ባየው ጊዜ ግብፃዊውን በጭካኔ ገደለው። ከዚህም የተነሣ ሙሴ ለሕይወቱ በመፍራት ሸሸና በምድረ በዳ ለ40 ዓመታት ያህል የበጐች እረኛ ሆነ። ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት እንዲያወጣ በእግዚአብሔር የተመረጠ ሰው ነበር። የሙሴ የግልፍተኝነት ተግባር የእግዚአብሔርን ዕቅድ የሚያሰናክል ነበርን? ምናልባት ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ለእግዚአብሔር ድንገተኛ ነገር አልነበረም። የሙሴ የ40 ዓመት ስደት ባሕርዩንና ብስለቱን ለመገንባት የጠቀመ ነገር ነበር፤ ከዚህም የተነሣ በእግዚአብሔር የተጠራበትን ሥራ ለመሥራት ዝግጁ ሆነ። ሙሴ ፈተናውን አለፈ።

አብርሃም ከሚስቱ አገልጋይ ጋር ተኛ። እግዚአብሔር ለአብርሃም ከሣራ ልጅ እንደሚሰጠው ቃል ገብቶለት ነበር፤ ነገር ግን ብዙ ዓመት ከጠበቁ በኋላ እግዚአብሔርን ለመርዳት ወሰኑ። አጋር የተባለችው የሣራ አገልጋይ ከአብርሃም አረገዘችና እስማኤል የተባለውን ወንድ ልጅ ወለደችለት። ይሁን



እንጂ እግዚአብሔር ከሣራ ልጅ እንደሚሰጠው የገባለትን የተስፋ ቃል አደሰለትና አብርሃምም በእግዚአብሔር አመነ። አብርሃም 100 ዓመት፣ ሣራም 90 ዓመት በሆናቸው ጊዜ ሣራ ይስሐቅን ወለደች። አብርሃም ፈተናውን አለፈ።

ኢያሱ ኢያሪኮን መጋፈጥ ነበረበት። አንድ ሰው ሙሴን ሊተካ የሚችለው እንዴት ነው? ይሁን እንጂ ኢያሱን የገጠመው ተግዳሮት ይኸው ነበር። እግዚአብሔር ኢያሱን ለማደፋፈር ከእርሱ ጋር እንደሚሆንና እርሱንና የእስራኤልን ሕዝብ በድል እንደሚመራቸው ቃል ገባለት። ሙሴ ከሞተ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ኢያሱ ሕዝቡን የዮርዳኖስን ወንዝ አሻግሮ ወደ ከነዓን ምድር አገባቸው። እግዚአብሔር ለሙሴ በቀይ ባሕር እንዳደረገው ሁሉ ሕዝቡ በደረቅ ምድር ይሻገሩ ዘንድ የወንዙን ውሀ በተአምር ለሁለት ከፈለው። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር እኛ ጉዞአችንን እንድንቀጥል ለመርዳት ተአምርን ያደርጋል። ይህንን እንደ ተጨማሪ ጥቅም ቁጠሩት። ብዙ ጊዜ እኛ የእምነትን ገድል መጋደል አለብን። እስራኤላውያን እግዚአብሔርን እያመለኩና እያወደሱ ዮርዳኖስን በልበ ሙሉነት ተሻገሩ። ከወንዙ ማዶ ሲደርሱ የተመሸገው የኢያሪኮ ከተማ በፊታቸው ገጠማቸው፤ ኢያሱ ጥቂት እረፍት የሚያገኙ መስሎት ሊሆን ይችላል፤ እግዚአብሔር ግን ከአንድ ፈተና ወደ ሌላ ፈተና ወሰዳቸው። እግዚአብሔር እንድናልፍበት በሚፈቅደው በእያንዳንዱ ፈተና ውስጥ ልናልፍ እንችላለን፤ ግን ከዚያስ ምን ይሆናል? ሌላ ፈተና ከፊት ለፊት አለ። ስለዚህ ከፈተና የምትሸሽ ከሆነ ለቀሪው የሕይወት ዘመንህ በሙሉ ስትሸሽ ትኖራለህ። ኢያሱ በእግዚአብሔር አመነና የኢያሪኮ ቅጥር ፈረሰ። ኢያሱ ፈተናውን አለፈ።

ዳንኤል በአንበሳ ጉድጓድ አንድ ሌሊት አሳለፈ። ዳንኤል በእግዚአብሔር የሚያምንና በእርሱ የሚተማመን ሰው ነበር፤ እርሱም በአረማዊ ንጉሥ የሞት ማስጠንቀቂያ ቢሰጠውም ለእግዚአብሔር ታዘዘ። ይሁን እንጂ ወደ አንበሳ ጉድጓድ ተጣለና አንዳች ጉዳት ሳይደርስበት በሕይወትና በጤንነት ሊወጣ ቻለ። እምነታችን ፈተናን አይከላከልልንም፤ እንዲያውም ወደ ውስጡ ያስገባናል። እግዚአብሔር በቃሉ አማካይነት የሰጠን እምነት ከሚገጥመን ከማንኛውም ሁኔታ የበለጠ ጥንካሬ እንዳለው ለማረጋገጥ ይፈልጋል። የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ መሆናችን ከፈተናና ከመከራ ነፃ አያደርገንም። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ የእግዚአብሔር መንግስት እምነት ፈተናንና መከራን ያበዛዋል፤ ይህም የያዝነው ነገር ንጹህ ወርቅ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው። ዳንኤል ፈተናውን አለፈ።

ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ዝሙት ፈጸመና ኃጢአቱን ለመሸፈን ሲል ምርጥ የጦር አዛዥ የነበረውን ባሏን ኦርዮን አስገደለ። ይሁን እንጂ ዳዊት እንደ

እግዚአብሔር ልብ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡ ለምን? ምክንያቱም ዳዊት ምንም እንኳ ብዙ ጉድለት ቢኖርበት ብዙ ጠንካራ ጐን ነበረው፡፡ ከእነዚያ ጠንካራ ጐኖች አንዱ እግዚአብሔርን በሙሉ ልቡ መውደዱ ነበር፡፡ ዳዊት ኀጢአቱን በተገነዘበ ጊዜ ተናዘዘ፤ ንስሐ ገባና ከእግዚአብሔር ይቅርታን አገኘ፡፡ ለማንኛውም የዳዊት ሕይወት የእምነት፣ የእውነተኝነትና የጽድቅ ሕይወት ነበር፡፡ ዳዊት ፈተናውን አለፈ፡፡

ኢዮብ ሁሉንም ነገር አጣ፡፡ ሰይጣን ኢዮብን እንዲፈትነው እግዚአብሔር ፈቀደለት፣ ምክንያቱም የኢዮብ እምነት እግዚአብሔር እስከ ባረከው ድረስ መሆኑን ሰይጣን ስለተናገረ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን ስለሚያውቅ ለኢዮብ ያለውን ሁሉ ሰይጣን እንዲወስድበት ፈቀደለት፡፡ ምንም እንኳ ኢዮብ ጻድቅ መሆኑን ቢገልጽና ለምን እንደሚሰቃይ ጥያቄ ቢያቀርብም አንድም ጊዜ እግዚአብሔርን አልረገመም፣ ወይም እምነቱን አልተወም፡፡ በመጨረሻም፣ እግዚአብሔር በፊት ከነበረው በላይ እጥፍ አድርጐ መለሰለት፡፡ ኢዮብ ፈተናውን አለፈ፡፡

ኢየሱስ ከወዳጆቹ በአንዱ ክህደት ደረሰበት፡፡ ሁልጊዜ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱብን ለእኛ ቅርብ የሆኑት ሰዎች ናቸው፡፡ በአንተ ላይ የማይተማመነውን ሰው ልትከደው አትችልም፡፡ ክህደት የሚፈጸመው መተማመን ሲኖር ነው፡፡ ከዐሥራ ሁለቱ የኢየሱስ ደቀመዛሙርትና የቅርብ ተከታዮች መካከል አንዱ የነበረው ይሁዳ ለጠላቶቹ አሳልፎ ሰጠው፡፡ ኢየሱስ ሥፍራውን ለቀቀ? ፈጽሞ አላደረገውም፡፡ ይሁዳ ግን ራሱን አጠፋ፡፡ ይሁዳ ይህንን እንደሚያደርግ ኢየሱስ አስቀድሞ ተናግሮ ነበር፡፡ ኢየሱስ የበደለኝነት ስሜት ሊኖረው አይገባም ነበርን? በፍፁም፡፡ ከዚህ የተነሣ ኢየሱስ ለይሁዳ "የምታደርገውን አድርግ፣ ለአንተ ውሳኔ እኔ ኃላፊነት የለብኝም" አለው፡፡ ኢየሱስ ወደፊት ቀጠለ፡፡ በሕይወትህ ውስጥ ጥሩ ጓደኛህን ልታጣ ትችላለህ፣ ነገር ግን ተነስተህ ጉዞህን ቀጥል፡፡ ኢየሱስ ፈተናውን አለፈ፡፡

ጳውሎስ ለብዙዎች የክርስቶስ ተከታዮች ሞት ተጠያቂ ነበር፡፡ ራሱ አማኝ ከመሆኑ በፊት ጳውሎስ የክርስቶስን ትምህርትና በእርሱም የሚያምኑነትን ለማጥፋት የጋለ ፍላጐት ነበረው፡፡ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ጳውሎስን ነካውና ለሚሲዮናዊነት ጠራው፤ ጳውሎስም ለዚህ ጥሪ ምላሽ በመስጠት በታሪክ ውስጥ ከኢየሱስ ቀጥሎ ለክርስቶስ ወንጌል እጅግ ከፍተኛ ኃይል ሊሆን ቻለ፡፡ ጳውሎስ ፈተናውን አለፈ፡፡

ጴጥሮስ ኢየሱስን ካደ፡፡ ጴጥሮስ ምንም እንኳ ኢየሱስን እንደማይከድ በችኰላ ቃል ቢገባም ፈተናው በመጣ ጊዜ ለፍርሃት እጁን ሰጠና ኢየሱስን ማወቁን ካደ፡፡ ኢየሱስም ከትንሣኤው በኋላ ጴጥሮስን እንደገና መለሰው፤



ጴጥሮስም ከዚያ በኋላ ፈጽሞ ጌታውን አልካደም፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ ክርስቶስን በድፍረት አወጀ፡፡ በክርስቶስ በማመኑ እስከ ሞት ድረስ ታመነ፡፡ ጴጥሮስ ፈተናውን አለፈ፡፡

ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት ግዞተኛ ሆነ፡፡ ከዐሥራ ሁለቱ የኢየሱስ ሐዋርያት የመጨረሻ የሆነው ዮሐንስ ከእምነቱና ለክርስቶስ ከነበረው ምስክርነት የተነሣ በሮማው ንጉሠ ነገሥት በፍጥሞ ደሴት ግዞተኛ ሆነ፡፡ በዚያም በጌታ ቀን በአምልኰ ላይ ሳለ፣ በኋላ የራዕይ መጽሐፍ የሆኑትን ራዕዮች በመለኰት ኃይል ተቀበለ፡፡ ዮሐንስ ፈተናውን አለፈ፡፡

እምነታችን ብቁ የሚሆነው በፈተና ውስጥ ነው፡፡ ጳውሎስ እኛ ለእግዚአብሔር መንግሥት ተገቢ የምንሆነው በስደት፣ በጽናት፣ በመከራና በፈተና መሆኑን ይናገራል፡፡ ስለዚህ ፈተናህን በጥሩ ሁኔታ ሥራና እግዚአብሔር በአደባባይ እንዲገልጥህ ዕድልን ስጠው፡፡ ለአንተ ስለሚያደርግልህ ነገር ብለህ እግዚአብሔርን አትመነው፣ ለአንተም ስለ ኣላደረገው ነገር እግዚአብሔርን አትናቀው፡፡ እግዚአብሔርን በማንነቱ እመነው፡፡

## መልካሙን ገድል ስለመጋደል

ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈው በመጀመሪያው መልእክት ወጣቱን እንዲህ በሚል ቃል አደፋፈረው፤

> የእግዚአብሔር ሰው ሆይ አንተ ግን ከዚህ ሁሉ ሽሽ (ከገንዘብ ፍቅር)፣ ጽድቅን፣ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትን፣ እምነትን፣ ፍቅርን፣ ትዕግሥትንና ገርነትን ተከታተል፡፡ መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል፡፡ በብዙ ምስክሮች ፊት በመልካም መታመን የመሰከርህለትንና የተጠራህበትን የዘላለም ሕይወት አጥብቀህ ያዝ (1ጢሞቴዎስ 6፥11-12)፡፡

ከዚህ በፊት እንዳየነው፣ የእኛ ውጊያ (ገድል) ከዲያብሎስ ጋር አይደለም፤ የእኛ ውጊያ ለእምነት ነው፡፡ ዲያብሎስ የሚዋጋው ሌላ ነገር ነው፡፡ እርሱ የሚያጠቃው የእምነታችንን መዋቅር ነው፡፡ ሰይጣን እንዳናምን ካደረገን፣ በእግዚአብሔር ላይ እንዳንተማመን ካደረገን፣ አሸነፈን ማለት ነው፡፡ ሰይጣን የእምነትህን መዋቅር እንዲነካ ከፈቀድህለት ሕይወትህን ያጠፋል፡፡ ጳውሎስ "መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል" ያለው ለዚህ ነው፡፡ እርሱም በሮሜ 10፥17 ላይ "እንግዲያስ እምነት የሚገኘው መልእክቱን

ከመስማት ነው፤ መልእክቱም በክርስቶስ ቃል ነው" ይላል:: እውነተኛ ውጊያ ባለበት እምነት አለ::

በእምነት ሕይወት ውስጥ ለመኖር ያለው ምኞት ፈተናዎችና መከራዎች እንደሚመጡ ያረጋግጣል:: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት የአደባባይና የግል ጉዳይ ነው:: የግል የሚሆነው እያንዳንዳችን ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን የግል ግንኙነት በሚመለከት ሁኔታ ነው:: የአደባባይ የሚሆነው አማኞች እንደመሆናችን በሌሎች ፊት እምነታችንን በምንመሰክርበት ሁኔታ ነው:: ጳውሎስ ጢሞቴዎስን "በብዙም ምስክሮች ፊት በመልካም መታመን የመሰከርህለትንና የተጠራህበትን የዘላለም ሕይወት አጥብቀህ ያዝ" በማለት መከረው:: ጢሞቴዎስ በክርስቶስ ያለው እምነት የአደባባይ ጉዳይ ነው:: እርሱም የእምነት ሰው ስለሆነ ወዲያውኑ እምነቱ እንደሚፈተን የተረጋገጠ ነበር::

እምነታችንን በአደባባይ በምንገልጥበት ጊዜ ራሳችንን ለፈተና ማስቀመጣችን ነው:: እግዚአብሔር የእምነታችን ምስክርነት እንዲፈተን የሚፈቅደው እኛ ራሳችንና የቀረውም ዓለም የእምነታችንን እውነተኛነት እንዲያውቅ ነው:: እግዚአብሔር በሥራህ እንዴት መልካም እንደሆነልህ ብትመሰክር፣ ሥራህን በሚመለከት ፈተና ስለሚመጣ ተዘጋጅ:: ጥቂት ተግዳሮት፤ ጥቂት ወደ ኋላ ማፈግፈግ፣ ጥቂት መቀዝቀዝ ሊመጣ ይችላል፣ እግዚአብሔር ግን "በእምነትህ ቀጥል፣ ነገሮች ጥቂት ስለጠነከሩብህ እምነትህን አትተው:: ነገሮች መልካም በሆኑበት ጊዜ ታምነኸለህ፤ አሁንም በአስቸጋሪው ጊዜ በእኔ እመን፣ በአደባባይ የመሰከርህለትን ነገር አጥብቀህ ያዝ" በማለት ያደፋፍርሃል::

እግዚአብሔር ፍላጐትህን ሁሉ እንደሚያሟላ አምነህ ትመሰክራለህ:: እርሱ ይህን ባያደርግልህና ገንዘብህም ቢያልቅብህ ምን ታደርጋለህ? እንደታመንከው ልትቀጥል ትችላለህን? ለጥቂት ጊዜ ቦርሳህ ባዶ ሲሆን በእግዚአብሔር ታማኝነትና ለጋስነት ላይ ያለህን አመኔታ ትቀጥላለህን? ሁኔታህ የፈተናውን ተግዳሮት ለመጋፈጥ ዕድል የሚሰጥ እንደሆነ አድርገህ በልበ ሙሉነት ትመለከተዋለህን? እግዚአብሔር እንደ ምንም አድርጎ እንደሚሞላው በማመን ምድጃህን አቀጣጥለህ ባዶውን ድስት በላዩ ላይ ትጥዳለህን? እምነትህን ተለማመድ፣ ከዚያም ሁሉም ነገር መልካም ይሆናል:: የእግዚአብሔር መንግሥት ገንዘብህን በተግባር ላይ አውለው፣ ከዚያም ሁሉም ነገር መልካም ይሆናል:: እግዚአብሔር በውስጡ ያሳልፍሃል፤ የምናመልከው አምላክ የመልካም ጊዜያት ብቻ ሳይሆን የመጥፎ ጊዜያትም አምላክ ነው:: ስለዚህ በሰዎች ፊት ስለ እምነትህ



በምትመሰክርበት ጊዜ ለፈተናው ተዘጋጅ:: የእምነት ምስክርነት ሁልጊዜ የእምነትን ፈተና ይጋብዛል::

**እስከምታሸንፍ ድረስ እመን::**

ጳውሎስ ስለ እምነት መጋደልን ከራሱ ልምምድ ተምሮአል:: በሕይወቱ መጨረሻ አካባቢ ለጢሞቴዎስ እንዲህ ለማለት በቃ፤

> መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፣ ሩጫውን ጨርሻለሁ፣ ሃይማኖትንም ጠብቄአለሁ:: ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፤ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ በዚያ ቀን ለእኔ ይሰጠኛል:: ደግሞም ለእኔ ብቻ ሳይሆን የእርሱን መገለጥ ለናፈቁ ሁሉ ነው (2ጢሞቴዎስ 4፥7-8)::

እምነት ለታላቅ ሽልማት የምንፈጽመው ተጋድሎና፣ የምንሮጠው እሽቅድድም ነው:: ሽልማቱ ፈተናውን ለሚያልፉ ሁሉ በመጨረሻ የተዘጋጀ የጽድቅ አክሊል ነው:: እሽቅድድሙ እስከ መጨረሻው ማመን ሲሆን ተጋድሎውም እስከታሸንፍ ድረስ ማመን ነው:: ወዳጆቼ፣ አድምጡኝ:: ዛሬ ብዙ ስለ መናገርህ አይደለም:: ጥያቄው፣ ከአሥር ዓመት በኋላም ታምናለህን? ነው:: ለእግዚአብሔር መንግሥት ብቁ የሚያደርጉህን ተግዳሮቶችን፣ መከራዎችን ችግሮችን በመፅናት አልፈህ አሁንም በአዎንታዊ አስተሳሰብ ልትቀጥል ትችላለህ?

የሚያጉረመርም ዜጋ ብስለት የሌለው ዜጋ ነው:: ብስለት ማለት መጥፎው ነገር እንደሚያጠነክረንና እንደሚያሻሽለን በማወቅ ከመልካሙ ነገር ጋር መጥፎውንም ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን ነው:: "ስቃይ ከሌለ ትርፍ የለም" የሚለው የተለምዶ አባባል ለእግዚአብሔር መንግሥትም የሚሆን ነው:: "ያለ መከራ አክሊል የለም" የሚለውም አባባል እንደዚሁ ነው:: ይህ ማለት ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት በመከራ ውስጥ መጓዝ አለብን ማለት አይደለም:: አክሊል የሚለው ቃል ሽልማትን እንጂ ድነትን የሚመለከት አይደለም:: በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ከእርሱ ጋር ወራሾች በመሆን ዐብሮ ለመሥራትና ለመግዛት የሚኖረን ተገቢነት በአብዛኛው የሚወሰነው ፈተናውን በማለፍ በምናረጋግጠው እምነት ነው:: ይህ የመንግሥቱ መርሕ ነው፤ ይበልጥ ስታሸንፍ ይበልጥ ትገዛዋለህ:: በተጽእኖ ውስጥ መጽናት ለእድገት ያዘጋጅሃል::

አማኞች እንደ መሆናችን መጠን ለገዥነት የተወሰንን ነገሥታትና ንግሥታት ነን፤ ነገር ግን አክሊላችንን ለማግኘት ጥቂት የፈተና ወቅት

ማሳለፍ ይኖርብናል፡፡ ስለዚህ መከራ በገጠመህ ጊዜ “ለአክሊሌ እየሠራሁ ነው!” በማለት ራስህን አሳምን፡፡ እኔ የገኸኘሁቴን የማዛት መጠን እያሰፋሁ ነው፡፡ በጽናት ቁም ከዚያም ንጉሡ ራሱ ለታማኝነትህ ሽልማት የሚሆን አክሊልን በራስህ ላይ ያስቀምጣል፡፡ ዋጋ አንድን ነገር ስትሠራ የምትቀበለው ነገር ነው፤ ሽልማት አንድን ነገር ከፍጻሜ ስታደርስ የምትቀበለው ነገር ነው፡፡ ሩጫውን ሩጥ፣ እሽቅድድሙን ፈጽም፤ መልካሙን ገድል ተጋደል፣ ተስፋ አትቁረጥ፣ ከዚያም የጽድቅን አክሊል ትሸለማለህ፡፡

አስቸጋሪ ሁኔታዎችን አንተን የተሻልክ ለማድረግና ለሽልማት ለማዘጋጀት እንደ መጡ ውድ ወዳጆች አድርገህ መቀበልን ተማር፡፡ መከራን በዚህ መንገድ እንድንመለከት ያዕቆብ ይመክረናል፤ ጴጥሮስም እንደዚሁ ይላል፡-

> የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ ይባረክ፤ እርሱ ከታላቅ ምሕረቱ የተነሣ በኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሣት ምክንያት ለሕያው ተስፋ በሚሆን አዲስ ልደት እንዲሁም በሰማይ ለማይጠፋ፣ ለማይበላሽና ለማይለወጥ ርስት እንደገና ወለደን፡፡ እናንተም በመጨረሻው ዘመን ሊገለጥ የተዘጋጀው ድነት እስኪመጣ ድረስ በእምነት አማካይነት በእግዚአብሔር ኃይል ትጠብቃላችሁ፡፡ አሁን በብዙ ዓይነት ፈተና ውስጥ ናችሁ ለጥቂት ጊዜ መከራን ብትቀበሉም እንኳ በዚህ እጅግ ደስ ይላችኋል፡፡ እነዚህ ነገሮች በእናንተ ላይ የደረሱት በእሳት ተፈትኖ ቢጠራም ጠፊ ከሆነው ወርቅ ይልቅ እጅግ የከበረው እምነታችሁ እውነተኛ መሆኑ እንደተረጋገጠና ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ምስጋናን፣ ክብርንና ውዳሴን እንዲያስገኝላችሁ ነው (1ጴጥሮስ 1፥3-7)፡፡

የምናልፍባቸው መከራዎች እምነታችንን ያጠራሉ፡፡ ዝገቱን ያቃጥላሉ፣ ማለትም በየቀኑ ሕይወታችን ሂደት ወደ እምነታችን የሚመጡትን ውሸቶችን፣ ኢ-ምንቶችንና የተሳሳቱ አመለካከቶችን፣ አሳቦችንና እምነቶችን ያቃጥላሉ፡፡ እውነተኛና አስፈላጊያችን የሆነውን ነገር ለማየት እንችል ዘንድ አመለካከታችንን የሚያጠራ አንድ ነገር በመከራዎች ውስጥ አለ፡፡ መከራዎች ቅደም ተከተላችንን እንድናስተካክል ይረዱናል፡፡ ነገሮች ምን ጊዜም ነገሮች እንጂ ዘላቂ እንዳልሆኑ ያስታውሱናል፡፡ ቋሚ የሚሆነው ከሰማይ የሆነው ብቻ ነው፣ ትኩረታችንም መሆን ያለበት በዚያ ነው፡፡

መከራዎች ለሰው ልጆች የተለመዱ ዕጣ ፈንታዎች ናቸው፡፡ ሁላችንም እንጋፈጣቸዋለን፣ ከእነርሱም ለመሸሽ አንችልም፤ ስለዚህ ማድረግ ያለብን



ከሁሉ የተሻለው ነገር፣ በውስጣችን ትዕግሥትንና ብስለትን ይገነቡ ዘንድ ለእኛ ጥቅም እንዲሠሩ መፍቀድ ነው፡፡ መልካሙን የእምነት ገድል መጋደል አለብን፡፡ እስከመጨረሻው መዝለቅ አለብን፡፡ ማንኛውንም ሁኔታ ማሸነፍ አለብን፡፡ ዋጋ ይጠብቀናል፣ ነገር ግን እኛ ለእርሱ መሥራት አለብን፡፡ በፈተናዎች መፅናት አለብን፡፡ ድል ይመጣል፣ ግን ብዙ ጊዜ ወዲያውኑ አይመጣም፡፡ የሚዘገይም መልስ ያው መልስ ነው፤ የሚዘገይም ድል ያው ድል ነው፡፡

ስለ መበለቲቱና ስለ አመፀኛው ዳኛ ኢየሱስ የተናገረው ነጥብ ይህንኑ የሚመለከት ነው፡-

> ደቀመዛሙርቱ ሳይታክቱ ሁልጊዜ መጸለይ እንደሚገባቸው ለማሳየት ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ነገራቸው፡፡ እንዲህም አላቸው፤ በ“አንዲት ከተማ የሚኖር እግዚአብሔርን የማይፈራና ሰውን የማያከብር አንድ ዳኛ ነበረ፡፡ በዚያችም ከተማ የምትኖር አንዲት መበለት ነበረች፡፡ እርሷ ‘ከባላጋራዬ ጋር ስላለብኝ ጉዳይ ፍርድልኝ’ እያለች ወደ እርሱ ትመላለስ ነበር፡፡
>
> ዳኛውም ለተወሰነ ጊዜ አልተቀበላትም ነበር፡፡ በኋላ ግን በልቡ እንዲህ አለ፣ ‘ምንም እግዚአብሔርን ባልፈራ ሰውንም ባላፍር ይህች መበለት ስለምትጨቀጭቀኝ እፈርድላታለሁ፣ አለበለዚያ ዘወትር እየተመላለሰች ታሰለቸኛለች!”
>
> ጌታም እንዲህ አለ፣ “አመፀኛው ዳኛ ያለውን ስሙ፡፡ እግዚአብሔር ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮኹ ምርጦቹ አይፈርድላቸውምን? ከመጠን በላይስ ችላ ይላቸዋልን? እላችኋለሁ ፈጥኖ ይፈርድላቸዋል፡፡ ነገር ግን የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆንን?” (ሉቃስ 18፥1-8)፡፡

እግዚአብሔር ችላ እንዳለህ ተሰምቶህ ያውቃልን? እኔ ተሰምቶኝ ያውቃል፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር መልሱን በሚያዘገይበት ጊዜ ወይ ትክክለኛውን ወቅት እየጠበቀ፣ ወይም ደግሞ እኔ ከጠየቅሁት የተሻለ ነገር ስላለው መሆኑን በዓመታት ውስጥ ተምሬአለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ በሁለቱም ምክንያት ይሆናል፡፡ ሁላችንም የምንመኘውን ነገር እያወቅን የማይደረስበት ሆኖ ስናይ የሚገጥመንን ናፍቆትና ሀዘን እናውቃለን፡፡ ወይም እየፀለይን ጫናው ለምን አይቆምም በማለት ግራ እንጋባለን፡፡ ከዚያም “ጌታ ሆይ

ለምን ይህን ያህል ጊዜ ትዘገያለህ?" በማለት እንጠይቃለን:: እኛ ለእርሱ የምንሠራ መሆናችንን ማስታወስ ያለብን በዚህ ጊዜ ነው፤ እርሱ ኃላፊ ስለሆነ የሚያደርገውን በትክክል ያውቃል:: እርሱ ለዘላለም አይዘገይም፤ መልሱም በመጣ ጊዜ፣ እኛን ወደ ብስለት ለማምጣትና ለእርሱም ክብርን ለማስገኘት በትክክለኛው ሰዓትና በትክክለኛው መንገድ እንደመጣ እናስተውላለን::

ብዙ አማኞች ሁልጊዜ ስኬት ወይም "ጥርመሳን" ያፈልጋሉ:: ትንሽ ቆዘም ሲሉ "የጥርመሳ" ትምህርት ወደሚሰጥበት ጉባኤ ይሄዳሉ፤ በሕይወታቸው የሚገጥማቸውን ችግር ለማጥፋት ስለሚፈልጉ ስለ ጥርመሳ የሚናገሩ መጻሕፍትን ያነባሉ:: ነገር ግን ሁልጊዜ ከደም ግፊት በስተቀር ምንም ለጥርመሳ ሳይሆኑ ይቀራሉ:: አብዛኛውን ጊዜ የእኛ ስኬት የሚመጣው ዘላቂ፣ ጠንካራና ጽኑ በሆነ እምነት በሕይወት ውስጥ የሚገጥሙ ፈተናዎችንና መከራዎችን እንደ አመጣጣቸው በመጋፈጥ ነው:: ሁልጊዜ የእኛ እምነትና ብስለት እያደጉ ይሄዱና ከረጅም ጊዜ በፊት በጥልቅ ስሜት የፈለግነው ስኬት እኛ እስከማናስታውስ ድረስ ቀስ በቀስ መምጣቱን በድንገት እንገነዘባለን::

እግዚአብሔር በሕይወትህ ውስጥ አንድ ነገር ያዘገየ ቢመስልህ፣ አታጉረምርም፤ በእርሱ መተማመንህን ብቻ ቀጥል፤ አንተ የተመኘኸውን ነገር ረዘም ላለ ጊዜ በማዘግየት በዚያ ነገር ብስለትን እንድታገኝ እምነትህን ለማሳደግ ይፈልግ ይሆናል:: ከዚያም እርሱ የፈለገውን እምነትና ብስለት ባገኘ ጊዜ "እሺ አሁን ልትወስደው ትችላለህ" ይልሃል::

መከራዎችና ፈተናዎች ለአንድ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ የየዕለት ሕይወቱ አካል ናቸው:: ማንም ሰው ከዚህ የተለየ ነገር ቢያምን ወይም ቢያስተምር የእግዚአብሔርን ቃል ይቃረናል:: የእግዚአብሔር ልጆች መከራ አይገጥማቸውም፤ አይሰበሩም፣ አይታመሙም፣ ሕይወት ቀላልና ከችግር ነፃ ነው - የሚለውን ትምህርት እየተማሩ ነገር ግን በየቀኑ የሚያጋጥማቸው ተጨባጭ ሁኔታ ከዚህ የተለየ በመሆኑ ብዙ ሰዎች ቤተክርስቲያንን ለቀው እንደሚወጡና እምነታቸውን እንደሚተው ስናይ እንገረማለን:: ሕይወት ለክርስቲያኖች ከችግር የነፃ ነው የሚለው መልእክት ሀሰት ነው:: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ከመከራ የሚሸሽ እምነት ሳይሆን በመከራ የተገነባ፣ የሚታገስና የሚያሸንፍ እምነት ነው:: የመንግሥቱ እምነት የተፈተነ እምነት ነው፣ ምክንያቱም እውነተኛ እምነት የሚገነባበትና የሚጠነከርበት ብቸኛው መንገድ በፈተና ውስጥ ስለሆነ ነው::



ለእግዚአብሔር መንግሥት ብቁ የሚያደርጉን የምናልፋቸው ፈተናዎች ናቸው:: ሉቃስ 18፥8 እግዚአብሔር እኛ በፍጥነት ፍትሕ ማግኘታችንን ለማረጋገጥ እንደሚሻ ይነግረናል:: በፍጥነት ማለት ዛሬ ወይም ነገ ጥዋት ማለት አይደለም:: በፍጥነት ማለት ትክክለኛው ጊዜ ሲደርስ ማለት ነው:: ትክክለኛው ጊዜ ሲደርስ ከች ነው! ስኬት በአንድ ሌሊት ይመጣል:: እውነተኛ ስኬት የሚባለው የእግዚአብሔር ጊዜ ሲደርስና እኛ እንኳ ሳንጠባበቃው ሲመጣ ነው:: እኛ ለስድስት ሳምንት ወይም ለስድስት ወር ወይም ለስድስት ዓመት እንፀልያለን፣ ከዚያም እግዚአብሔር በድንገት በስድስት ደቂቃዎች ውስጥ ያመጣዋል:: እግዚአብሔር የሚሠራው በዚህ መንገድ ነው:: የእርሱ ጊዜ ዘወትር የእኛ ጊዜ ላይሆን ይችላል፣ ነገር ግን የእርሱ ጊዜ ከቶ አይዘገይም::

የኢየሱስ ጥያቄ ዛሬ ለእኛ አስፈላጊ ነው፤ "የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆንን?" አለ:: እርሱ የሚፈልገው እምነትን ነው:: እርሱ የሚፈልገው ትልቅ ቤትን ወይም ቄንጠኛ መኪናን ወይም በባንክ ብዙ ገንዘብን ሳይሆን እምነትን ነው:: ሁልጊዜ ተአምራትን፣ ምልክቶችንና ድንቅ ነገሮችን የሚያሳድዱ ሰዎችን ሳይሆን የእምነትን ሰዎች ይፈልጋል::

ገድሉንም መጋደል የሚገባውና አሽቅድድሙንም መሮጥ የሚገባው፣ በመጨረሻው ሽልማቱ ታላቅ ስለሆነ ነው:: የዕብራውያን ፀሐፊ እንዲህ ይለናል፦

> እንግዲህ እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን ሸክም የሚሆንብንን ሁሉ፣ በቀላሉም ተብትቦ የሚይዘንን ኃጢአት አስወግደን በፊታችን ያለውን ሩጫ በጽናት እንሩጥ:: የእምነታችን ጀማሪና ፍጹም አድራጊ የሆነውን ኢየሱስን እንመልከት:: እርሱ በፊቱ ስላለው ደስታ መስቀሉን ታግሦ የመስቀሉንም ውርደት ንቆ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአል:: እንግዲህ ዝላችሁ ተስፋ እንዳትቆርጡ ከኃጢአተኞች የደረሰበትን እንዲህ ያለውን ተቃውሞ የታገሠውን እርሱን ዐስቡ (ዕብራውያን 12፥1-3)::

ድል በአየር ላይ ደርሶአል:: ስኬት እየመጣ ነው:: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት የተፈተነ እምነት ነው:: ስለዚህ ሩጫውን ሩጥ፤ አሽቅድድሙን ፈጽም መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል:: ልብ አድርግ፣ ሩጫው እስከ መጨረሻው ማመን ነው፣ መጋደሉ እስኪታሸንፍ ማመን ነው::

**የእግዚአብሔር መንግሥት መርሆች**

- ለስኬታማ ሕይወት ቁልፉ የተጠበቀውንና ያልተጠበቀውን ለመቆጣጠር ያለህ ችሎታና ብቃት ነው።
- ስኬት የሚለካው በችግር ወቅት የግል ሚዛንህን ለመጠበቅ ባለህ ችሎታ ነው።
- ብስለት የሚለካው በሀዘንና በትርምስ ጊዜ የተሳካ ምላሽ ለመስጠት ባለህ ችሎታ ነው።
- እምነትህ ብቃት የሚያገኘው በፈተና ውስጥ ነው።
- የእምነት ምስክርነት ሁልጊዜ ለዚያ እምነት ፈተና ይጋብዛል።
- ይበልጥ ስታሸንፍ፣ ይበልጥ ገዥ ትሆናለህ፤ በተጽእኖ ውስጥ መጽናት ለእድገት ያዘጋጅሃል።





## ዐሥሩ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ባሕርያት

*"እምነት ገና ጨለማ ሳለ ንጋት መምጣቱ እየተሰማት የምትዘምር ወፍ ናት"።*

የእስካንዲናቪያውያን አባባል

እንደ ማንኛውም ሌላ አገር ሰማያዊው መንግሥትም በተለያዩ ሕጎች የሚሠራ ነው። ከእነዚህ መካከል ዋነኛ የሆነው የእምነት ሕግ ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት የሚሠራው በእምነት ነው፤ ያለ እምነትም በመንግሥቱ ውስጥ ምንም ነገር አይሠራም። እምነት የእግዚአብሔር መንግሥት ባሕልና የሕይወት ዘይቤ መሆኑን ቀደም ብለን አይተናል፤ ደግሞም እምነት የመንግሥቱ ምጣኔ ሀብት ገንዘብ ነው። ስኬታማ የሆነ የመንግሥቱ ኑሮ ማለት በማየት ሳይሆን በእምነት መኖር ነው፤ በራሳችን ጥበብ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር መተማመን ነው።

ሰው የተፈጠረው በእምነት እንዲኖር ነው። ዘፍጥረት 1፥26 እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉና በመልኩ እንደ ፈጠረው ይናገራል። አምሳል ማለት ተፈጥሮ ወይም ባሕርይ ማለት ነው። ሰው የተፈጠረው በባሕርዩና በተፈጥሮው እግዚአብሔርን እንዲመስል ነው። ደግሞ እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ተፈጥሮአል። መልክ ሲባል ገጽታን ሳይሆን ተግባርን የሚመለከት ነው። በእግዚአብሔር መልክ መፈጠር ማለት ሰው እንደ እግዚአብሔር እንዲሠራ ተፈጠረ ማለት ነው። እግዚአብሔር በእምነት ይሠራል፤ ምክንያቱም እርሱ የእምነት አምላክ ስለሆነ ነው። ስለዚህ እኛም በእምነት እንድንሠራ ይፈለግብናል።

በመጀመሪያ አዳምና ሄዋን በሚያዩት ነገር ሳይሆን በሚያምኑት ነገር ይኖሩ ነበር። ለእግዚአብሔር ባለመታዘዛቸውና መልካምንና ክፉን ከምታስታውቀው ከተከለከለችው ዛፍ ፍሬን በመብላታቸው ምክንያት ሁኔታው ተቀየረ። ዓይናቸው ለክፉ ነገር ተከፈተ፤ የእምነት ችሎታቸው ግን ቀነሰ። ከዚህ በኋላ እምነት ለእነርሱ ተፈጥሮአዊ ሊሆን አልቻለም፣ ቀጣይ የሰው ልጆች ትውልድም የተቀነሰውን የእምነት ችሎታ ወረሰ። ዛሬም ለእኛ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ተፈጥሮአዊ አይደለም። የእግዚአብሔር መንፈስ በሕይወታችን ካልሠራ በስተቀር የመንግሥቱን እምነት ልናገኘው አንችልም፣ ያለ መንግሥቱ እምነትም የእግዚአብሔርን መንግሥት ከቶ ልናይ አንችልም። በዕብራውያን 11፥6 "ደግሞም ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሁሉ

እግዚአብሔር መኖሩንና ከልብ ለሚሹትም ዋጋ እንደሚሰጥ ማመን አለበት” ይላል::

ከተፈጠርንበት ዐላማ ውጪ በሆነ አካባቢ ወይም ፀባይ በምንሠራበት ጊዜ ከሥራ ውጪ እንሆናለን:: በአንዳንድ ሁኔታ ሊገድለንም ይችላል:: ለምሳሌ ያለ መተንፈሻ መሣሪያ በውሀ ውስጥ ለብዙ ጊዜ ከቆየህ ትሞታለህ:: አሣዎች በውሀ ውስጥ ለመኖር የተፈጠሩ ናቸው፤ እኛ ግን አይደለንም:: እኛ በእምነት ውስጥ ለመኖር ተፈጥረናል፤ ከዚያ ውጪ ከሆንን እንደሚገባ ልንሠራ አንችልም::

እምነት ከሌለ፣ ቀደም ብለህ እንዳነበብከው፣ በፍርሃትና በጥርጥር የሚሞላ ባዶ ሥፍራ ይፈጠራል:: ፍርሀትና ጥርጥርም የእምነት ተቃራኒ ወደ ሆነው ወደ ጭንቀት ይመራሉ:: በአካላችን ውስጥ ጭንቀትን ለማስተናገድ የታቀደ ነገር የለም:: እንደ እውነቱ ከሆነ የሳይንስ ምርምር እንደሚያመለክተው ጭንቀት በውስጣችን ያለውን ንጥረ ነገር ከመጠን በላይ በማመንጨት የደም ሥሮቻችንን ይዘጋል:: ይህም የደም ዝውውርን በመግታት የራስ ምታትን፣ የልብ በሽታን፣ መዝለፍለፍንና ሌሎች የልብና የደም ሥር በሽታዎችን ያስከትላል:: ስለዚህ “እስከ ሞት ድረስ ተጨንቄአለሁ” ብለህ ብትናገር ማጋነንህ አይደለም:: እግዚአብሔር የፈጠረህ በእምነት እንድትሠራ ነው:: ይህም በእምነት የማትሠራ ከሆነ ራስህን እያጠፋህ ነው ለማለት ይቻላል:: ያለ እምነት ከሆንህ ወደ ጭንቀት፣ ወደ መነጫነጭና ወደ አእምሮ መደበት ውስጥ እየገባህ ነው ማለት ነው:: ይህም በመጨረሻው ሕይወትህን ያጠፋል:: አንተ የተፈጠርኸው በእምነት እንድትኖር ነው::

እምነት የጭንቀትን ቦታ ያስለቅቃል:: እምነት፣ በማጣታችን ስለ ምንጨነቅባቸው ነገሮች፤ በየዕለቱ ለሚያስፈልገን መግቦትና ለወደፊቱ ሙሉ ተስፋ ያስጨብጠናል:: ኢየሱስም የሚከተለውን የተናገረው ይህንን ነጥብ ለመግለጽ ነበር፤

> ስለዚህ ምን እንበላለን? ምን እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ፣ አሕዛብ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ለማግኘት ይጨነቃሉና፤ የሰማዩ አባታችሁም እነዚህ ሁሉ ለእናንተ እንደሚያስፈልጓችሁ ያውቃል:: ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን እሹ፣ እነዚህ ሁሉ ይጨመሩላችኋል (ማቴዎስ 6፥31-33)::

በሌላ አነጋገር፣ ኢየሱስ “በየቀኑ በሚያስፈልጓችሁ ነገሮች አትጠመዱ:: የሰማዩ አባታችሁ፣ ንጉሡ፣ ስለ እነዚህ ነገሮች ያስባል:: በዚህ ፈንታ



በእግዚአብሔር መንግሥት ነገሮች ብትጠመዱ ይሻላል:: እናንተም የተፈጠራችሁት ለዚህ ነው” ማለቱ ነው::

## በእምነት መኖር

በእምነት መኖር ማለት ዓይናችሁ በሚያሳያችሁ ነገር ሳይሆን አእምሮአችሁ፣ ልባችሁና መንፈሳችሁ እውነት ነው ብሎ በሚመሰክርላችሁ ነገር መኖር ማለት ነው:: ቀደም ሲል እንዳነበባችሁት፣ እምነት “ተስፋ ያደረግነው ነገር እንደሚፈጸም እርግጠኛ የምንሆንበት፣ የማናየውም ነገር እውን መሆኑን የምንረዳበት” ነው (ዕብ 11፥1):: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት በእግዚአብሔር ፀባይና ባሕርይ ላይ የተመሠረተ የጽድቅ አካሄድ ነው:: የጽድቅ አካሄድ ማለትም ከእግዚአብሔር ጋር በተስተከከለ ሁኔታ መቆምና ከመንግሥቱ መርሆችና ሕጎች ጋር በመስማማት መኖር ማለት ነው:: የእግዚአብሔር ጽድቅ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በእምነት ለእኛ ተሰጥቶናል፤ “በወንጌል የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጦአልና፣ ጽድቁም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በእምነት የሆነ ነው፤ ‘ጻድቅ በእምነት ይኖራል’” ተብሎ እንደተጻፈው ነው (ሮሜ 1፥17)::

ከእግዚአብሔር ጋር በተስተካከለ ሁኔታ መቆማችንን ማመን አለብን:: ግዙፋዊ የሆነ “ማስረጃ” ስለሌለን እግዚአብሔርን በቃሉ መቀበል አለብን:: እርሱ “ኃጢአታችሁ በኢየሱስ ደም ተሰርዮላችኋል” ካለ ማመን አለብን:: ይህንን ካደረግን፣ ልባችን ካለ እግዚአብሔር መንፈስ አሠራር ሊገለጥ በማይችል ድፍረትና ደህንነት ይሞላል:: ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኝና ጌታ አድርገን ስንቀበል እግዚአብሔር ጽድቁን ለእኛ ያካፍለናል፤ ይህም የተረጋገጠ ሐቅ ይሆናል:: ከዚህ በኋላ በቀረው የሕይወት ዘመናችንና ለዘላለምም በእምነት በሚገኘው ጽድቅ እየኖርን እንደስተበታለን::

በምዕራፍ አንድ ውስጥ እንደ ጠቀስሁት የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ማለት ካልተረጋገጡትና ካልታወቁት ከሕይወት ምስጢሮች ጋር ዐብሮ መኖር ማለት ነው:: ጳውሎስ “የምንኖረው በእምነት እንጂ በማየት አይደለም” ብሎአል (2ቆሮ 5፥7):: በምናየው ነገር ላይ ሕይወታችንን መመሥረት አደገኛ ነው ምክንያቱም የምናየው ነገር ሙሉውን ስዕል የሚያሳይ አይደለም:: ሁኔታችንን ከሰማያዊ የዕይታ አንፃር ካላየን በስተቀር ውጫዊ መልክ አሳሳች ሊሆን ይችላል:: የእኛ የሥጋ ዓይን በእኛ ላይ ሊቀልድብን ይችላል፣ ነገሮችን በመንፈሳዊ የእምነት ዓይን ማየት ያለብንም ለዚህ ነው:: በማየት መኖር ሕይወታችንን እንደ ነፋስ ከሚለዋውጡት ከዕድልና ከሁኔታ ጋር ያጣምረዋል:: የዚህ ዐይነት ሕይወት መረጋጋት የለውም:: በሌላ በኩል፣ በእምነት መኖር ሕይወትህን በማይለወጠው

በእግዚአብሔር እውነት ላይ ይተከለዋል፤ ይህም የማይነቃነቅ መሠረት ነው::

የሕይወት ቁልፍ የሆነው እምነት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የተለመደ ፍሬ አሳብ ነው:: ዘፍጥረት 15፥6 "አብራም እግዚአብሔርን አመነ፤ እርሱም ጽድቅ አድርጐ ቆጠረለት" ይላል:: የእስራኤል ሕዝብ ከግብፅ ባርነት ተአምራዊ ትድግናን ካገኙና የእግዚአብሔርን መግቦት (የምግብና የውሀ አቅርቦት) ከተለማመዱ በኋላ የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግረው ተስፋ የተሰጣቸውን የከነዓንን ምድር ለመውረስ ለእግዚአብሔር አልታዘዙም:: እምነታቸውን በእግዚአብሔር ላይ በመጣል ፈንታ የሚያዩትን ነገር ማመንን መረጡ፡- ይህም ለማሸነፍ የማይችሉት የመሰላቸው ኃይለኛ ጠላት ነበር:: ካለማመናቸውም የተነሣ ያ ዐመፀኛ ትውልድ በሙሉ እስኪሞት ድረስ በምድረ በዳ ለ40 ዓመታት እንዲንከራተቱ አደረጋቸው:: የብሉይ ኪዳን በተደጋጋሚ ጥሪ የሚያደርገው ጌታን ስለ ማመን፣ በእርሱ ላይ ስለ መተማመንና ለእርሱ ስለ መታዘዝ ነው:: ዳዊት "እነዚህ በሰረገላ፣ እነዚያ በፈረስ ይመካሉ፤ እኛ ግን ትምክህታችን የአምላካችን የእግዚአብሔር ስም ነው" በማለት ጽፏል (መዝ 20፥7)::

በዐዲስ ኪዳንም ተመሳሳይ አጽንኦት ይገኛል:: ኢየሱስም፣ "ለሚያምን ሰው ሁሉም ነገር ይቻላል" ብሎአል (ማርቆስ 9፥23):: በእምነት የመኖር አስፈላጊነት ጳውሎስ ለአብያተ ክርስቲያናት በጻፋቸው መልእክቶች ውስጥ የዘወትር ፍሬ አሳብ ነው፡- "በወንጌል የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጦአልና፣ ጽድቁም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በእምነት የሆነ ነው:: "ጻድቅ በእምነት ይኖራል" ተብሎ እንደተጻፈው (ሮሜ 1፥17):: "የምንኖረው በእምነት እንጂ በማየት አይደለም" (2ቆሮ 5፥7):: ጻድቅ በእምነት ይኖራል ስለተባለ ማንም በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንደማይጸድቅ ግልጽ ነው:: ሕግ በእምነት ላይ የተመሠረተ አይደለም፤ ነገር ግን "ሕግጋትን የሚፈጽም ሰው በእነርሱ በሕይወት ይኖራል" ተብሎአል (ገላትያ 3፥11-12)::

ጻድቅ በእምነት ይኖራል:: በሁኔታዎች፣ ወይም በበረከቶች፤ ወይም በትንቢቶች፣ ወይም በፈውሶች፣ ወይም በሌላ በማንኛውም ነገር አይደለም፤ ግን በእምነት ብቻ ነው:: ማንኛውም ነገር ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው የእምነትህ ምንጭ እንዲሆን አትፍቀድ፤ ምክንያቱም ይህን ካደረግህ እነርሱ ሲወድቁ (መውደቃቸውም አይቀርምና) እምነትህም ዐብሮ ይወድቃል:: ስለዚህ በሕይወትህ የሚሆነው ማንኛውም ነገር ወይም የማይሆነው ማንኛውም ነገር በእግዚአብሔር ላይ ያለህን እምነት እንዲያቃውሰው አትፍቀድ:: አንተ ጻድቅ የመንግሥቱ ዜጋ ከሆንህ በእምነት መኖር ይጠበቅብሃል:: ይህም ማለት ትንሽ ጫና ወይም ችግር በገጠመህ ጊዜ ወደ ኋላ ማፈግፈግ ወይም እምነትህን መተው የለብህም ማለት ነው:: ከእምነት



ወደ ኋላ ማፈግፈግ ጌታን አያስደስተውም፡- "ጻድቅ ግን በእምነት ይኖራል፤ ወደ ኋላ ቢያፈገፍግ ነፍሴ በእርሱ ደስ አይላትም፤ እኛ ግን አምነው ከሚድኑት ወገን እንጂ ወደ ኋላ አፈግፍገው ከሚጠፉት አይደለንም" (ዕብ 10፥38-39)::

እምነት የእግዚአብሔር መንግሥትና የዜጐቹ መለያ ባሕርይ ስለሆነ በምድር ላይ ካሉት ከሌሎች ሰዎች እኛን መለየት አለበት:: ችግር ወይም ተግዳሮት ሲገጥማቸው ወደ ኋላ የሚያፈገፍጉ ልጆችን እግዚአብሔር አይፈልግም:: እርሱ የሚፈልገው በማዕበሉ ውስጥ ሊቆሙ የሚችሉ ልጆችን ነው፤ የምድር መናወጥን የሚቋቋሙ፣ የጭስ ሽታ ሳይኖርባቸው በእሳት ውስጥ የሚያልፉ ልጆችን ነው፣ "ለማለፍ ቻልሁ! ለምን? ምክንያቱም አምላኬ ታላቅ አምላክ ስለሆነ ነው!" ለማለት የሚችሉትን ልጆች ይፈልጋል:: ችግር ሲመጣ የሚወድቅ እምነት ጭራሽ እውነተኛ እምነት አይደለም:: እውነተኛ እምነት ማለትም የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ችግር እያለ ያምናል:: ችግር ወይም ተግዳሮት ሲመጣ ወደ ኋላ አያፈገፍግም:: ለስደት እጁን አይሰጥም፣ ወይም በሚደርስበት ጫና ምክንያት አያውላውልም:: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት በመከራና በችግር ጊዜ ያሸንፋል:: እምነታቸው የሚወድቅ ሰዎች የመጥፋት አደጋ ያጋጥማቸዋል:: እምነት ከጥፋት ይጠብቀናል::

ከዓመታት በፊት የኦራል ሮበርትስ ዩኒቨርስቲ ተማሪ ነበርሁ፣ በዚያን ጊዜ ኦራል ሮበርትስ የዮኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ነበረና አንድ ቀን በጸሎት ቤቱ ፈጽሞ የማልረሳውን አንድ ነገር ተናገረ:: "ተማሪዎች ሆይ ይህን አስታውሱ፤ ሁልጊዜ ሰላማችሁን ጠብቁ፤ ሰላማችሁን የምትጠብቁትስ እንዴት ነው? መልካሙን ተጠባበቁ፣ "ለመጥፎው ተዘጋጁ" አለ:: መልካሙን ተጠባበቁ፣ ለመጥፎው ተዘጋጁ:: ለመጥፎው የምንዘጋጅበት ብቸኛ መንገድ እምነት ነው፤ ምክንያቱም በአስቸጋሪ ጊዜ ሊያሻግረን የሚችለው እምነት ብቻ ስለሆነ ነው:: በእርግጥ አዎንታዊ አስተሳሰብም ያስፈልገናል! እግዚአብሔር ታላላቅ ነገሮችን እንደሚያደርግና እንደሚባርከን መጠባበቅ ይኖርብናል፤ ነገር ግን ምንም ዐይነት ማዕበል እንዲመጣ ፈቃዱ ሲሆን ለመቆም (ለመጽናት) መዘጋጀት አለብን:: በማዕበሉ ውስጥ እንድንጸና የሚያደርገን እምነት ነው::

ኢየሱስ በተያዘበት ሌሊት ለስምዖን ጴጥሮስ እንዲህ አለው፤ "ስምዖን ስምዖን ሆይ፣ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ:: እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ ጸለይሁ:: አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አበርታ" (ሉቃ 22፥31-32):: ምንም እንኳን ይህን እንደማያደርግ መሐላ ቢያወርድም፣ ከሰዓታት በኋላ ጴጥሮስ ጌታውን ሦስት ጊዜ ይክዳል:: ጴጥሮስ ያችን ልዩ ፈተና ወደቀ፤ እምነቱ ግን ተረፈ:: የእርሱ ስህተት በራሱ

**ጥንካሬ** ላይ ከመጠን በላይ መመካቱ ነበር። ከቅዱስ መጽሐፍ እንደምናውቀው ከሆነ፣ ጴጥሮስ ያንን ስህተት እንደገና አልፈጸመም። እምነቱን በራሱ ችሎታ ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ መመሥረትን ተማረ። ኢየሱስ ለጴጥሮስ እምነት ፀለየ፣ ይህም ጴጥሮስን እስከ መጨረሻ እንዲጸና ያደረገው ብቸኛ ነገር ነው።

በእምነት መኖር ማለት በሰዎች ወይም በፕሮግራሞች መታመን ማለት አይደለም፣ ነገር ግን፣ በእግዚአብሔር ብቻ መተማመን ማለት ነው፤ ደግሞም ከዕይታ ባሻገር በሥጋ ዓይን ወደማይታየው ወደ መንፈሳዊ እውነታ መመልከት ማለት ነው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ለደቀመዛሙርቱ ሲገለጥ ቶማስ ከእነርሱ ጋር አልነበረም። ሌሎቹ ስለዚህ ጉዳይ ሲነግሩት ቶማስ በራሱ ዓይን ካለየ በስተቀር እንደማያምን በእጽንዖት ተናገረ፣ ከአንድ ሳምንት በኋላ የማየት ዕድል አገኘ።

> ከስምንት ቀን በኋላም ደቀ መዛሙርቱ በቤት ውስጥ ነበሩ፤ ቶማስም ከእነርሱ ጋር ነበር። በሮቹ ተቆልፈው ነበር፤ ኢየሱስ ግን መጥቶ በመካከላቸው ቆመና "ሰላም ለእናንተ ይሁን!" አላቸው። ከዚያም ቶማስን "ጣትህን ወደዚህ አምጣ፤ እጆቼንም ተመልከት። እጅህንም ዘርጋና በጐኔ አስገባ። አትጠራጠር እመን" አለው።
>
> ቶማስም ጌታዬ አምላኬም አለው።
>
> ኢየሱስም አንተ ስላየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ግን ብፁዓን ናቸው አለው (ዮሐንስ 20፥26-29)

"ተአምር ካላየሁ በስቀር በእግዚአብሔር አላምንም" በማለት እንደ ቶማስ የሆንነው ስንቶቻችን ነን? ኢየሱስ ለቶማስ እንዳለው ለእኛም "አትጠራጠር እመን" ይለናል። እምነትህን እግዚአብሔር በሚያሳይህ ነገር ላይ አትመሥርት፤ በእግዚአብሔር ላይ መሥርተው፣ በቃ። ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ነው።

## የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ዋና ዋና ባሕርያት

እንደ ከለሳ አድርጌ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነትን በሚመለከት ዐሥር ዋና ዋና ባሕርያትን በዐጭሩ እተነትናለሁ። እነርሱንም ከኢዮብ፤ ከዕብራውያን መጽሐፍና ከሰምዖን ጴጥሮስ አንዳንድ አሳቦችን በመውሰድ አብራራለሁ።



### 1. የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት በማዕበል ውስጥ ጽኑና የተረጋጋ ነው።

ኢዮብ በተጽእኖ ሥር ላለ እምነት እንደ "ማስታወቂያ" የሚታይ ነው። ሰይጣን ኢዮብን እግዚአብሔርን የሚያምነው ለራሱ ጥቅም ነው በማለት በከሰሰው ጊዜ፣ ኢዮብ ያለውን ሁሉ በመውሰድ የኢዮብን እምነት እንዲፈትነው እግዚአብሔር ለሰይጣን ፈቀደለት። ኢዮብ ቤተሰቡን፣ ሀብቱንና ጤንነቱን ዐጣ፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት አላጣም። የስቃዩን ምክንያት በሚመለከት እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ፈለገ፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ላይ ጀርባውን አላዞረም። የኢዮብ ሦስት ወዳጆች እንኳ የኢዮብ ችግር በእርሱ ላይ ካለው ከእግዚአብሔር ፍርድ የተነሣ መስሎአቸው ኀጢአቱን እንዲናዘዝ በጨቀጨቁት ጊዜ ኢዮብ እምነቱንና ንጽህናውን አጽንቶ ያዘ፤

> ፍትሕ የነሣኝ ሕያው እግዚአብሔርን! ነፍሴንም መራራ ያደረጋት ሁሉን ቻይ አምላክን! በውስጤ የሕይወት እስትንፋስ በአፍንጫዬም ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ እስካለ ድረስ ከንፈሬ ኀጢአትን አትናገርም፤ አንደበቴም ሽንገላ አይወጣውም። እናንተን እንደ ቅኖች መቁጠር የማላደርገው ነገር ነው፤ ጨዋነቴንም እስከ ሞት ድረስ አልጥልም። ጽድቄን አጥብቄ እይዛለሁ፤ አልለቀውምም በዘመኔም ሁሉ ሕሊናዬ አይወቅሰኝም (ኢዮብ 27፥2-6)።

ኢዮብ ለምን እንደሚሰቃይ፣ ወይም እግዚአብሔር ይህን ለምን እንደፈቀደ ሊረዳ አልቻለም። ነገር ግን በማዕበሉ መካከል እያለ ማመኑን ቀጠለ፤ ቀድሞ ይኖር እንደነበረ በእውነተኛነት፣ በማይለወጥ አቋም፤ በታማኝነት፣ በግብረ ገባዊነትና በንጹህ ሕሊና መኖሩን ቀጠለ። ኢዮብ እምነቱ በሕያው እግዚአብሔር የተተከለ ስለነበረ ባለማወላወል የፈተናውን ወቅት በትእግሥት አሳለፈ። ኢዮብ በመልካም ጊዜና በመጥፎ ጊዜ እግዚአብሔር የሁለቱም ጌታ መሆኑን አመነ። እንደ እውነቱ ከሆነ ሁሉንም ነገር ካጣ በኋላ ስለ እምነቱ ተግዳሮት በገጠመው ጊዜ ኢዮብ እንዲህ በማለት ተቃወመ፤ "መልካሙን ነገር ከእግዚአብሔር ተቀበልን፤ ክፉውንስ አንቀበልምን?" አለ (ኢዮብ 2፥10)።

ነፋስንና ዝናብን እንደሚቋቋመው በዓለት ላይ እንደተመሠረተው ቤት ሁሉ (ማቴዎስ 7፥24-25 ይመልከቱ)፣ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነትም መሠረቱን በማይናወጠው በእግዚአብሔር ላይ የጣለ መሆኑን በማንኛውም የሕይወት ማዕበል ውስጥ በጽናትና በመረጋጋት ያስመሰክራል።

2. የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ሁሉን አዋቂ በሆነው በእግዚአብሔር እውቀት ላይ እንጂ በእኛ ውሱን እውቀት ላይ አይደለም፡፡

"የሕይወት ምስጢር" ብለን የምንጠራው ነገር መኖሩ ራሱ የእኛ እውቀት ውሱን መሆኑን ያመለክታል፡፡ ሆኖም እኛ ብዙ ጊዜ በንግግርም ሆነ በተግባር ሁሉን ነገር እንደምናውቅ እንገልፃለን፡፡ ሁኔታው ምንም ይሁን ምን በዓይናችን የምናየው ወይም በአእምሮአችን የምንረዳው የዚያ ነገር ሙሉ እውነታ ነው ብለን እናስባለን፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት የእኛ እውቀት ውሱን መሆኑን በትህትና በመቀበል የቀረውን በእግዚአብሔር እጅ ይተዋል፡፡ ኢዮብ ማስታወስ የሚገባው ይህንን ነበር፡፡ ምክንያቱም እንደ አብዛኞቻችን ሁሉ በስቃይ ውስጥ ስለ ተያዘ ስለ ሁኔታው ከእግዚአብሔር ይበልጥ የሚያውቅ መስሎት ነበር፡፡ ጌታም በፍጥነት አስተካከለው፤

> እግዚአብሔርም በዐውሎ ነፋስ ውስጥ ሆኖ ለኢዮብ መለሰለት እንዲህም አለው፤ "እውቀት በጐደለው ቃል ዕቅዴን የሚያጨልም ይህ ማነው? እስቲ እንደ ወንድ ወገብህን ታጠቅ፣ እኔ ልጠይቅህ፤ አንተም መልስልኝ፡፡ ምድርን በመሠረትሁ ጊዜ አንተ የት ነበርህ? በርግጥ የምታስተውል ከሆንህ ንገረኝ፡፡ ካወቅህ መጠኗን ለይቶ ማን ወሰነ? በላይዋስ መለኪያ ገመዱን የዘረጋ ማን ነው? የንጋት ከዋክብት ሲዘምሩ፣ መላእከትም እልል ሲሉ መሠረቶችም ምን ላይ ተተከሉ? የማዕዘን ድንጋይዋንስ ማን አቆመ? (ኢዮብ 38፥1-7)፡፡

> እግዚአብሔር ኢዮብን እንዲህ አለው፤ "ሁሉን ከሚችል አምላክ ጋር ተከራክሮ የሚረታው አለን? እግዚአብሔርን የሚወቅስ እርሱ መልስ ይስጥ!"(ኢዮብ 40፥1-2)፡፡

ከእኛ መካከል እንዲህ ያለውን ጥያቄ የሚመልስ ማነው? ኢዮብ አልቻለም፤ እኛም አንችልም፡፡ ዋናው ነጥብ ይኼ ነው፡፡ እግዚአብሔር ወሰን የሌለው ስለሆነ ከማንኛችንም በላይ ያውቃል፡፡ ለማንኛችንም ቢሆን እርሱ ራሱንም ሆነ ተግባሩን የመግለጽ ግዴታ የለበትም፡፡ ለመሆኑ ማን ለማን ተጠያቂ ነው? እኛ ለእግዚአብሔር ተጠያቂዎች ነን፤ በተቃራኒው አይሆንም፡፡ እኛ በመንግሥት እምነት የእውቀታችንን ውሱንነት በመቀበል ከሕይወት ምስጢሮች ጋር አብረን በመኖር እናርፋለን፤ ያልታወቀውን ነገር ደግሞ ሁሉን አዋቂ ለሆነው ለእግዚአብሔር እውቀት፣ በሁሉ ላይ ለሚሠለጥነው ኃይሉና ፍጹም ትክክል ለሆነው እቅዱ አሳልፈን እንሰጣለን፡፡



3. የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ከእኛ መረዳት በላይ ነው

እውቀታችን ውሱን በመሆኑ ከእኛ መረዳት በላይ የሆኑና ምን ጊዜም የሚሆኑ አንዳንድ ነገሮች አሉ፡፡ የእኛ ሰብአዊ ትምክህት ይህን ሐቅ ለመቀበል ስለማይፈልግ፣ አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ አስፀያፊ የሆኑ ነገሮችን እንድንናገር ወይም እንድናደርግ ይገፋፉናል፡፡ አንዳንድ ሰዎች፣ ሰው የሁሉም ነገር መለኪያ ስለሆነ ዞሮ ዞሮ ከሰው መረዳት ወይም ችሎታ በላይ የሆነ ምንም ነገር የለም ብለው ያምናሉ፡፡ የእኛ አእምሮአዊ፣ ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ ምጥቀት የእኛን ግብረ ገባዊ ሕሊና ራቁቱን በማስቀረት ማድረግ አለብን? ወይስ የሚለውን ጥያቄ ከግምት ውስጥ ሳናስገባ ማድረግ ስለምንችል ብቻ አንዳንድ ነገሮችን እንድናደርግ ይመራናል፡፡ የፅንሰ ሐዋሳት ምርምርና በሰው ሠራሽ ዘዴ በቤተ ሙከራ የሰውን ዘር የማዳቀል ምርምር ሁለት የዚህ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ የእግዚአብሔርን ታላቅነትና የእርሱን ወሰን የሌለው ጥበብና ኃይል በምናይበት ጊዜ ሁላችንም በእምነት ከተነሳሳው የኢዮብ ትህትና ትክክለኛ መጠን ለመጠቀም እንችላለን፡፡

> ኢዮብም እንዲህ ሲል ለእግዚአብሔር መለሰ፤ "አንተ ሁሉን ማድረግ እንደምትችል ዕቅድህም ከቶ እንደማይሰናከል ዐወቅሁ፡፡ አንተ 'ያለ ዕውቀት ዕቅዴን የሚያደበዝዝ ይህ ማን ነው?' አልኸኝ፣ በርግጥ ያልገባኝ ነገር የማላውቀውንና ላስተውለው የማልችለውን ጉዳይ ተናገርሁ፡፡ 'ስማኝ፣ ልናገር፤ እኔ እጠይቃለሁ፣ አንተ ትመልስልኛለህ' አልኸኝ፡፡ ጆሮዬ ስለ አንተ ሰምቶ ነበር፤ አሁን ግን ዐይኔ አየችህ፡፡ ስለዚህ ራሴን እንቃለሁ፣ በትቢያና በዐመድ ላይ ተቀምጬ ንስሓ እገባለሁ" (ኢዮብ 42፥1-6)

ኢዮብ እግዚአብሔርን በዐይኑ ባየ ጊዜ ራሱን በእውነተኛ ማንነቱ አየ፡፡ ከዚያም ለዚህ መገለጥ ፍጹም በሆነ ትህትና ምላሽ ሰጠ፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ ተመሳሳይ ልምምድ ነበረው፤

> ንጉሥ ዖዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔርን ከፍ ባለና በከበረ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት፤ የልብሱም ዘርፍ ቤተ መቅደሱን ሞልቶት ነበር፡፡ ሱራፌልም ከእርሱ በላይ ቆመው ነበር፤ እያንዳንዳቸውም ስድስት ክንፍ ነበራቸው፡፡ በሁለት ክንፍ ፊታቸውን ይሸፍኑ ነበር፤ በሁለት ክንፍ እግራቸውን ይሸፍኑ ነበር፤ በሁለቱም ክንፍ ይበሩ ነበር፡፡ እርስ በርሳቸው በመቀባበልም "ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ ምድር ሁሉ በክብሩ ተሞልታለች" ይሉ ነበር፡፡ ከድምፃቸው ጩኸት የተነሣ

> የመድረኩ መሠረት ተናወጠ፤ ቤተ መቅደሱም በጢስ ተሞላ።
>
> "እኔም ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው ነኝ፣ የምኖረውም ከንፈሮቹ በረከሱበት ሕዝብ መካከል ነው፤ ዐይኖቼም ንጉሡን የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔርን አይተዋልና ጠፍቻለሁ ወዮልኝ!" አልሁ (ኢሳይያስ 6፥15)።

እግዚአብሔር በሙሉ ግርማው ሲገለጥ ትክክለኛው ምላሽ ትህትና ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ይህንን ይገነዘባል፤ እኛ ፈጽሞ ልንረዳቸው የማንችል አንዳንድ ነገሮች የመኖራቸውንም ሐቅ አሜን ብሎ ይቀበላል። እግዚአብሔር ግን ይረዳል፣ ያ በቂ ነው።

4. የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ከፈተናዎች በኋላ ሽልማት ያገኛል።

ኢዮብ በስቃዩ መካከል ብቻ ሳይሆን ከሦስቱ ወዳጆቹ በደረሰበትም ክስ መካከል በእምነቱና በጽድቁ ግንዛቤ በጽናት ቆመ። ኤልፋዝ፣ በልዳዶስና ሶፋር የኢዮብን ችግር ከእግዚአብሔር ቁጣ ጋር አያያዙት። እነርሱ እግዚአብሔርን በተሳሳተ መንገድ ስለተረዱት እርሱን በተሳሳተ መንገድ ወከሉት። በመጨረሻም፣ እግዚአብሔር ኢዮብን ነፃ አወጣውና ሦስቱ ወዳጆቹ ባደረጉት ነገር እንዲጠየቁ አደረጋቸው፤

> እግዚአብሔር ይህን ለኢዮብ ከተናገረ በኋላ፣ ቴማናዊውያን ኤልፋዝን እንዲህ አለው፣ "እንደ አገልጋዬ እንደ ኢዮብ ስለ እኔ ቅን ነገር ስላልተናገራችሁ ቁጣዬ በአንተና በሁለቱ ባልንጀሮችህ ላይ ነዶአል። አሁን እንግዲህ ሰባት ወይፈኖችና ሰባት አውራ በጎች ይዛችሁ ወደ አገልጋዬ ወደ ኢዮብ ሂዱ። የሚቃጠል መስዋዕትም ስለ ራሳችሁ አቅርቡ። እንደ አሳፋሪ ተግባራችሁ እንዳላደርግባችሁ አገልጋዬ ኢዮብ ስለ እናንተ ይጸልያል፤ እኔም ጸሎቱን እቀበላለሁ። እንደ አገልጋዬ እንደ ኢዮብ ስለ እኔ ቅን ነገር አልተናገራችሁምና። ቴማናዊው ኤልፋዝ፣ ሹሐዊው በልዳደስና ናዕማታዊው ሶፋር እግዚአብሔር እንደ ተናገራቸው አደረጉ፤ እግዚአብሔርም የኢዮብን ጸሎት ተቀበለ" (ኢዮብ 42፥7-9)።

ኢዮብ ትክክለኛ መሆኑና ተመፃዳቂዎች ወዳጆቹ ስህተተኞች መሆናቸው ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ኢዮብ ስለ እነርሱ ያደረገውን ጸሎት ተቀብሎ እርሱን በተሳሳተ መንገድ ስለ ወከሉት ኀጢአታቸውን ይቅር በማለት የንስሓ



መስዋዕታቸውንም ተቀበለ። ይህም አልበቃ ብሎ እግዚአብሔር ለኢዮብ ከዚህ የበለጠ ነፃነት በመስጠት አረጋገጠ፤

> ኢዮብ ለወዳጆቹ ከጸለየ በኋላ እግዚአብሔር እንደገና አበለጸገው። ቀድሞ በነበረው ፈንታ ዕጥፍ አድርጐ ሰጠው ወንድሞቹና እህቶቹ ቀድሞም ያውቁት የነበሩ ሁሉ ወደ እርሱ መጡ በቤቱም ከእርሱ ጋር ምግብ በሉ። እነርሱም ሐዘናቸውን ገለጡለት፤ እግዚአብሔርም ካመጣበት መከራ ሁሉ አጽናኑት፣ እያንዳንዳቸውም ጥሬ ብርና የወርቅ ቀለበት ሰጡት (ኢዮብ 42፥10-11)።

ኢዮብ በፈተናው ሁሉ በጽናት ስለቆመ፣ በመጨረሻው የእግዚአብሔርን ዋጋ ተቀበለ። የነበረውን ሁሉ አጥቶ ነበር፣ እግዚአብሔር ግን ዕጥፍ አድርጐ መለሰለት። በሌላ አነጋገር ኢዮብ ከፈተናው በፊት ተባርኮ ነበር። ከፈተናው በኋላ ግን ዕጥፍ ተባረከ። የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ዋጋ ያስገኛል፤ አንዳንዶቹ ዋጋዎች በአሁኑ ሕይወት ሲሆኑ ከዚህ የበለጠው ደግሞ በሚመጣው ሕይወት ነው።

5. የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ዋጋ የሚቀበለው ከንጉሡ ነው።

ኢዮብ የተቀበለው ዋጋ በቀጥታ ከእግዚአብሔር እንደመጣ ልብ በሉ። በማንኛውም መንግሥት ዘንድ ከንጉሡ ተግባሮች አንዱ ለሕዝቡ መልካም ነገሮችን መለገስ ሲሆን፣ በተለይ ለታማኝ አገልግሎት ዋጋ መስጠት ነው። ኢዮብን በተመለከተ የእርሱ ዋጋ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ለጋስነትና ወሰን የለሽ ብልጽግና ብቻ አይደለም፤ በተጨማሪም እግዚአብሔር ታማኝነትን በሚባርክበት ጊዜ ግማሽ መለኪያን እንደማይጠቀም ያመለክታል።

> እግዚአብሔርም ከፊተኛው ይልቅ የኃለኛውን የኢዮብን ሕይወት ባረከ። እርሱም አሥራ አራት ሺህ በጐች ስድስት ሺህ ግመሎች አንድ ሺህ ጥማድ በሬዎች፣ አንድ ሺህ እንስት አህዮችም ነበሩት። ደግሞም ሰባት ወንዶችና ሦስት ሴቶች ልጆች ነበሩት ... እንደ ኢዮብ ሴቶች ልጆች የተዋቡ ሴቶች በምድሪቱ ሁሉ አልተገኙም፣ አባታቸውም ከወንድሞቻቸው ጋር ርስት ሰጣቸው።
>
> ከዚህ በኋላ ኢዮብ አንድ መቶ አርባ ዓመት ኖረ፤ ልጆቹንና የልጅ ልጆቹን እስከ አራት ትውልድ ድረስ አየ። በዚህ

> ሁኔታ አርጅቶ ዕድሜ ጠግቦ ሞተ (ኢዮብ 42፥12-13፡15-17)

በማዕበሉ ውስጥ በታማኝነት ለመጽናት ሌላው ምክንያት ይህ ነው፡- በፈተናው መካከል ተስፋ ከቆረጥህና ከሸሸህ በመጨረሻ የምትቀበለውን ዋጋ ታጣለህ፡፡ የኢዮብን ሚስት አስብ፤ የኢዮብ መከራ እንደተጀመረ፣ ልክ ሁሉንም ነገር ካጣ በኋላ፣ ሚስቱ "እግዚአብሔርን ርገምና ሙት አለችው" (ኢዮብ 2፥9)፡፡ ኢዮብም እንዲህ በማለት ገሰፃት፣ "አነጋገርሽ እንደማታስተውል ሴት ነው፤ መልካሙን ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ተቀበልን፤ ከፉውንስ አንቀበልምን" አላት (ኢዮብ 2፥10)፡፡ ከዚህ በኋላ ስለ ኢዮብ ሚስት ምንም የተሰማ ነገር የለም፡፡ አንድ ነገር ሳይደርስባት አልቀረም ብለን ለማሰብ እንችላለን፡፡ ኢዮብን ትታው ሄዳ ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲህ ከሆነ በመጨረሻው እርሱ ያገኘውን በረከት አጥታለች ማለት ነው፡፡ ኢዮብ በመጀመሪያ ከነበረው በረከት ዕጥፍ ማግኘቱ ብቻ ሳይሆን በሞቱ ልጆች ምትክ ሰባት ወንዶች ልጆችንና ሦስት ሴቶች ልጆችን አገኘ፡፡ ይህም በርግጥ ከመጀመሪያዋ ሚስቱ ይልቅ ከእርሱ ጋር በእምነት የምትመሳሰል ሌላ ሚስት ማግባቱን ያመለክታል፡፡ በርግጥ፣ ከዚህ አብዛኛው ግምት ነው፤ ነገር ግን ዋናው ነጥብ እምነትን ማጣት የመጨረሻውን ሽልማት ያሰጣል የሚል ነው፡፡ ንጉሡ በልግስና ይሸልማል፤ ነገር ግን እምነተ ቢስ የሆነውን ሰው አይሸልምም፡፡

6. የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት በንጉሡ የሚሰጥና የሚጸና ነው፡፡

ብዙ ሰዎች እምነት የሚመጣው ከሰው አእምሮ እንደሆነና በራሳችን ተነሳሽነት ለእግዚአብሔር የምናቀርበው ነገር ነው ብለው ያስባሉ፡፡ ምንም እንኳ የሰው ነፃ ፈቃድ የሚጫወተው ሚና ቢኖርም እምነት ራሱ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ነው፡፡ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ጽፎአል፤ "በእምነት በጸጋ ድናችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ በሥራ አይደለም፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀልንን መልካም ሥራ እንድንሠራ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርን የእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች ነን" (ኤፌ 2፥8-10)፡፡

እምነት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ላይ በሚያምፀው በኀጢአት ባሕርያችን ምክንያት ሙሉ በሙሉ በራሳችን ኃይል እውነተኛ እምነትን ልናመነጭ አንችልም፡፡ ኢየሱስም "የላከኝ አብ ካልሳበው በቀር ማንም ወደ እኔ መምጣት አይችልም" ብሎአል (ዮሐንስ 6፥44)፡፡ እምነት የእግዚአብሔር ስጦታ ስለሆነ እኛ ወደ ክርስቶስ ለመምጣት ምርጫ



ከማድረጋችን በፊት እርሱ ወደ ክርስቶስ ይስበናል፡፡ እምነት የሚመነጨው ከእግዚአብሔር መሆኑ ብቻ ሳይሆን የሚያጸናውና ወደ ፍፅምና የሚያመጣውም እርሱ ነው፤ ይህም እኛ በራሳችን ልንፈጽመው የማንችለው ነገር ነው፡፡ የዕብራውያን ፀሐፊም የሚከተለውን ቃል የተናገረውም ለዚህ ነው፡- "የእምነታችን ጀማሪና ፍጹም አድራጊ የሆነውን ኢየሱስን እንመልከት፤ እርሱ በፊቱ ስላለው ደስታ መስቀሉን ታግሦ የመስቀሉንም ውርደት ንቆ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአል" (ዕብራውያን 12፥2)፡፡

ንጉሡ እርሱ ለመረጠው ሰው እምነትን ይሰጣል፤ ያለ እርሱም ስጦታ ማንም ሰው ወደ እምነት አይመጣም፡፡ በእግዚአብሔር የእምነት ስጦታ አማካይነት ወደ ክርስቶስ እንቀርብና ለኀጢአት ይቅርታና በርሱ ላለው ዐዲስ ሕይወት በእርሱ እንተማመናለን፡፡ ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በውስጣችን እምነትን በማጽናትና ሙሉ በማድረግ ማንኛውንም ተግዳሮት ለመቋቋምና ማንኛውንም ፈተና ለማለፍ እንችል ዘንድ ያደርጋል፡፡ ከጅማሬ እስከ ፍጻሜው ድረስ እምነት የንጉሡ ሥራ ነው፡፡

7 የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ከደም (ከዝምድና) ይልቅ ጠንካራ ነው፡፡

የክርስቶስ አማኞችና ተከታዮች ከሆንን በዐዲስ ቤተሰብ ውስጥ፣ ማለትም በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ተወልደናል ማለት ነው፡፡ ይህም እምነታችን ከምድራዊ ቤተሰባችን የደም ትስስር ይበልጥ ጥንካሬ ያለው ትስስርን ይፈጥራል፡፡ ይህን ነጥብ የደቀመዝሙርነት ቀዳሚ ገጽታ መሆኑን ኢየሱስ በተደጋጋሚ ተናግሮአል፤

> ወደ እኔ የሚመጣ ሁሉ አባቱንና እናቱን ሚስቱንና ልጆቹን ወንድሞቹንና እህቶቹን የራሱንም ሕይወት እንኳ ሳይቀር በይጠላ ደቀመዝሙሬ ሊሆን አይችልም (ሉቃ 14፥26)
>
> ከእኔ ይልቅ እናቱን ወይም አባቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባም፤ ከእኔ ይልቅ ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባም (ማቴዎስ 10፥37)፡፡
>
> ኢየሱስ ለሕዝቡ ሲናገር ሳለ እናቱና ወንድሞቹ ሊያነጋግሩት ፈልገው በውጭ ቆመው ነበር፡፡ አንድ ሰውም "እነሆ እናትህና ወንድሞችህ ሊያነጋግሩህ ፈልገው በውጭ ቆመዋል" አለው፡፡

ኢየሱስም "እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነ ማን ናቸው?" ሲል መለሰለት በእጁም ወደ ደቀመዛሙርቱ እያመለከተ እንዲህ አለ፤ "እናቴና ወንድሞቼ እነዚህ ናቸው፤ በሰማይ ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ ወንድሜ፣ እህቴና እናቴም ነው" (ማቴዎስ 12፥46-50)::

ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ፣ "እውነት እላችኋለሁ፤ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ሲል ቤቱን ወይም ወንድሞቹን ወይም እህቶቹን ወይም እናቱን ወይም አባቱን ወይም ልጆቹን ወይም እርሻውን የተወ ሁሉ አሁን በዚህ ዘመን ከስደት ጋር ቤቶችን፣ ወንድሞችን እህቶችን፣ እናቶችን፣ ልጆችንና እርሻን መቶ ዕጥፍ የማይቀበል፣ በሚመጣውም ዓለም የዘላለም ሕይወትን የማይወርስ የለም (ማርቆስ 10፥29-30)::

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ከቤተሰብ የደም ትስስር ይበልጥ ጠንካራ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ከግል የደም መፍሰስ ፍርሀት የበለጠ ጥንካሬ አለው:- "እንግዲህ ዝላችሁ ተስፋ እንዳትቆርጡ ከኀጢአተኞች የደረሰበትን እንዲህ ያለውን ተቃውሞ የታገሠውን እርሱን (ክርስቶስን) ዐስቡ፤ ከኀጢአት ጋር ስትታገሉ ገና ደማችሁን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተቃወማችሁም" (ዕብ 12፥3-4):: ታሪክ በመከራና በስደት ውስጥ፣ እስከ ሞት ድረስ እንኳ፣ ታማኞች በሆኑ አማኞች ምሳሌ የተሞላ ነው:: የአንተስ እንዴት ነው? እምነትህ ምን ያህል ተፈትኖአል?

8. የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት የሚጠራው በፈተና ነው::

እምነት ካልተፈተነ ሊያድግ አይችልም:: በሕይወት ማጣሪያ ውስጥ ካልተፈተነ በስተቀር እምነት ብዙ ዋጋ የለውም:: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ከቃላት በላይ ነው፤ እርሱ በመልካም ሥራ ራሱን የሚገልጥና በመከራ በመጽናት ራሱን የሚያረጋግጥ ነው:: የእምነትህ ጥንካሬ በፈተና ለማለፍ የሚችለውን ያህል ነው:: የማንም ሰው እምነት በቃላት ብቻ የሚገለጥ ከሆነና በሕይወት ያልተደገፈ ከሆነ እምነት አይባልም:: የጌታ ወንድም የያዕቆብ ዳሰሳም ይህን የሚመለከት ነው:: እንዲህ ይላል፤

ወንድሞቼ ሆይ አንድ ሰው እምነት አለኝ ቢል ሥራ ግን ባይኖረው ምን ይጠቅመዋል? እንዲህ ያለው እምነት



ሊያድነው ይችላልን? አንድ ወንድም ወይም እንዲት እህት የሚለብሱት ልብስም ሆነ የሚመገቡት ምግብ አጥተው ከእናንተ መካከል አንዱ በሰላም ሂዱ፤ እይብረዳችሁ፤ ጥገቡ ቢላቸው ለሰውነታቸው ግን የሚያስፈልጋቸውን ባይሰጣቸው ምን ይጠቅማቸዋል? እንዲሁ ሥራ የሌለው እምነት በራሱ የሞተ ነው::

ነገር ግን አንድ ሰው:: "አንተ እምነት አለህ፤ እኔ ሥራ አለኝ? እምነትህን ከሥራ ለይተህ አሳየኝ እኔም እምነቴን በሥራዬ አሳይሀለሁ ይላል... ከመንፈስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ ከሥራም የተለየ እምነት የሞተ ነው( ያዕቆብ 2፥14-18:26)::

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ያላቸው ሰዎች ፈተናን በደስታ ይቀበላሉ፤ ምክንያቱም ፈተና እምነታቸውን እንደሚያጠራላቸውና ወደ ብስለት እንደሚያደርሳቸው ስለ ተገነዘቡ ነው:: ጴጥሮስ ለዚህ ሐቅ አጽንኦት ከሰጡት ከብዙ የዐዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች አንዱ ነው::

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ ይባረክ! እርሱ ከታላቅ ምሕረቱ የተነሣ በኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሣት ምክንያት ለሕያው ተስፋ በሚሆን አዲስ ልደት እንደዚሁም በሰማይ ለማይጠፋ፣ ለማይበላሽና ለማይለወጥ ርስት እንደገና ወለደን:: እናንተም በመጨረሻው ዘመን ሊገለጥ የተዘጋጀው ጽናት እስኪመጣ ድረስ በእምነት አማካይነት በእግዚአብሔር ኃይል ተጠብቃችኋል:: አሁን በብዙ ዐይነት ፈተና ውስጥ ሆናችሁ ለጥቂት ጊዜ መከራን ብትቀበሉም እንኳ በዚህ እጅግ ደስ ይላችኋል:: እነዚህ ነገሮች በእናንተ ላይ የደረሱት በእሳት ተፈትኖ ቢጠራም ጠፊ ከሆነው ወርቅ ይልቅ እጅግ የከበረው እምነታችሁ እውነተኛ መሆኑ እንደተረጋገጠና ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ምስጋናን፣ ክብርንና ውዳሴን እንዲያስገኝላችሁ ነው:: እርሱንም ሳታዩት ትወዱታላችሁ፤ አሁን ባታዩትም፣ በእርሱ ታምናላችሁ መግለጽ በማይቻልና ክብር በሞላበት ሐሴት ደስ ብሎአችኋል፤ የእምነታችሁን ፍጻሜ እርሱም የነፍሳችሁን ድነት እየተቀበላችሁ ነውና (1ጴጥሮስ 1፥3-9)::

አንተም ወደፊት ፈተና ባጋጠመህ ጊዜ ዐላማው የአንተን እምነት ለማጥራትና አንተን ጠንካራ ለማድረግ መሆኑን አስታውስ::

9. የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት መከራን አይፈራም::

በዛሬው ዘመን ስለ እምነት ያለው አብዛኛው ትምህርት በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ስለ እምነት ፈተና ለተጻፈው መግለጫ የሚመጥን አይደለም:: አብዛኛው የዛሬው የ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አማኝ እምነት በረከቶችን ለመቀበልና ለመጠባበቅ የሚጠቅም፣ እንዲሁም በመልካም ጊዜ ውስጥ እንዲያልፍ የታቀደ ነው:: ምናልባት ብዙዎች ለማንኛውም ችግራቸው ሰይጣንን የሚወቅሱትና የተቃውሞን ሁኔታ ለመሸሽ የሚሞክሩበት ምክንያት ለዚህ ይሆናል::

ይሁን እንጂ፣ እውነተኞች የእግዚአብሔር መንግስት ዜጐች የፈተና ዐላማና ጥቅሙ ለእምነታቸው ብስለት እንደሆነ ስለሚነገዘቡ ፈተናዎችን አይፈሩም:: እነርሱ በፈተናቸው ወቅት ክቡር የሆነውን የጌታን መገኘት መለማመድን ተምረዋል፤ በውስጡ የሚያልፉበት ችግር ፍጹም የተለየ አመለካከትን ይሰጣቸዋል፤ ይህም አመለካከት ሰማያዊ አመለካከት ነው:: ጴጥሮስ የመጀመሪያ መልእክቱን አንባቢዎች እንዲህ በማለት አደፋፈራቸው:-

> ወዳጆች ሆይ፣ እንደ እሳት የሚፈትን ብርቱ መከራ በመቀበላችሁ እንግዳ ነገር እንደ ደረሰባችሁ በመቁጠር አትደነቁ፤ ነገር ግን ክብሩ በሚገለጥበት ጊዜ ደስታችሁ ታላቅ እንዲሆን የክርስቶስ መከራ ተካፋዮች በመሆናችሁ ደስ ይበላችሁ:: ስለ ክርስቶስ ስም ብትሰደቡ የክብር መንፈስ የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ላይ ስለሚያርፍ ብፁዓን ናችሁ:: ከእናንተ ማንም መከራን የሚቀበል ቢኖር ነፍሰ ገዳይ ወይም ሌባ ወይም ወንጀለኛ ወይም በሰው ነገር ጣልቃ ገቢ ሆኖ መከራን አይቀበል:: ክርስቲያን በመሆኑ መከራ ቢደርስበት ግን ስለዚህ ስም እግዚአብሔርን ያመስግን እንጂ አይፈር (1ጴጥሮስ 4፥12-16)::

ጴጥሮስ የሚፈትን ብርቱ መከራ ለአማኞች የተለመደ ነው ይላል:: በኀጢአተኛና በወደቀ ዓለም ውስጥ ለሚኖሩ ለእግዚአብሔር መንግሥት ዜጐች የሕይወታቸው አካል ነው:: ከዚህም በላይ ጴጥሮስ የክርስቶስ መከራ ተካፋይ በመሆናችን እንድንደሰት ይመክረናል:: ለምን? ምክንያቱም የክርስቶስ መከራ ተካፋዮች በምንሆንበት ጊዜ በኋላ የእርሱ ክብርና



የሽልማት ተካፋዮች እንሆናለን:: በመከራ ውስጥ እንዴት እንደሰታለን? በሰው አመለካከት ይህ የማይቻል ነው:: ይህ የሚቻለው በሰማያዊ አመለካከት በእምነት ዓይን ሲታይ ነው::

10. የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት የወደፊቱን ለእግዚአብሔር ይሰጣል::

ሁሉም ሰው በወደፊቱ ነገር ላይ ትኩረት ያደርጋል:: መልካም ይሁን ክፉ ለእርሱ ለመዘጋጀት እንችል ዘንድ ነገ ወይም በሚቀጥለው ሳምንት ወይም በሚቀጥለው ዓመት የሚሆነውን ነገር ለማወቅ የማይፈልግ ማነው? ለመናፍስት ባለሙያዎችና ለኰከብ ቆጣሪዎች በየዓመቱ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ይወጣል:: ብዙ ሰዎች የሥራ ወይም የስፖርት ዜና እንደሚከታተሉ ሁሉ የኰከብ መቁጠሪያቸውንም በየቀኑ በታማኝነት ያነባሉ:: ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ብቸኛ የሆኑት ሕጋዊ ኰከብ ቆጣሪዎች የጥንታዊቱ እስራኤል ነቢያት ነበሩ:: እነርሱም ቢሆኑ ሁሉንም ነገር እንዲያዩ አልተፈቀደላቸውም የወደፊቱን በሙላት የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው:: እርሱም ለመረጣቸው ለተለዩ ሰዎች ለተለየ ጊዜ ወይም ለተለየ ሁኔታ "እንደ አስፈላጊነቱ" ጥቂት እዚህ ወይም ጥቂት እዚያ እየገለጠ በቅርብ ሆኖ ይጠብቀዋል::

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ያላቸው ሰዎች የወደፊቱን ለማወቅ በተለመደው ጥድፊያ ውስጥ አይያዙም:: እነርሱ ከሕይወት ምስጢር ጋር በመኖር እንደሚረኩ ሁሉ፣ የወደፊቱን ባለማወቃቸውም ይረካሉ፤ ምክንያቱም የወደፊቱን በእጁ የያዘውን ስለሚያውቁ ነው:: እነርሱ የአሁኑ ዘመን መከራ በወደፊቱ የእግዚአብሔር መንግሥት ሕይወት ከሚገኘው ክብር ጋር ሲወዳደር ምንም ነገር እንዳልሆነ ይረዳሉ:: ስለዚህ በትዕግሥት ፀንተው ይጠባበቃሉ:: ጴጥሮስ ከዚህ የሚከተለውን የጻፈው ይህን እያሰበ ይመስለኛል፤ ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መከራ የሚቀበሉ ሁሉ ነፍሳቸውን ለታመነ ፈጣሪ ዐደራ ሰጥተው መልካም ማድረጋቸውን ይቀጥሉ (1ጴጥ 4፥19)::

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ያላቸው ሰዎች የወደፊቱን ላያውቁ ይችላሉ፤ ነገር ግን የወደፊት ኑሮአቸው ዋስትና እንዳለው ያውቃሉ:: እነርሱ የእርሱ መንግሥት ዜጐች እንደመሆናቸው መጠን የወደፊቱን በእምነት ለንጉሡ ለእግዚአብሔር አሳልፈው ሰጥተዋል፤ የእርሱም መንግሥት ለዘላለም ጸንቶ የሚኖር፣ ወሰን የሌለው ኃይል፣ ውበት፣ ክብርና መልካምነት ያለው ነው::

**የእግዚአብሔር መንግሥት መርሆች**

- የመንግሥቱ እምነት በማዕበል ውስጥ የሚጸናና የተረጋጋ ነው::
- የመንግሥቱ እምነት ሁሉን አዋቂ በሆነው በእግዚአብሔር እውቀት እንጂ በእኛ ውሱን እውቀት ላይ አይደለም::
- የመንግሥቱ እምት ከእኛ መረዳት በላይ ነው::
- የመንግሥቱ እምነት ከፈተና በኋላ ሽልማት ያገኛል::
- የመንግሥቱ እምነት ሽልማትን የሚያገኘው በንጉሡ ነው::
- የመንግሥቱ እምነት የሚሰጠውና የሚፀናው በንጉሡ ነው::
- የመንግሥቱ እምነት ከደም (ከዝምድና) ይልቅ ጠንካራ ነው::
- የመንግሥቱ እምነት የሚጠራው በፈተና ነው::
- የመንግሥቱ እምነት መከራን አይፈራም::
- የመንግሥቱ እምነት የወደፊቱን ለእግዚአብሔር ይሰጣል::



ምዕራፍ ዐምስት

## እግዚአብሔርን እንደ አምላክነቱ

*"ፍርሀት በሩን አንኳኳ፣ እምነት መለሰ፣ ማንም አልነበረም"::*

የጥንት የእንግሊዞች ምሳሌ::

የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጐች በማየት ሳይሆን በእምነት ይመላለሳሉ፣ ይህ ግን እምነታችን ዕውር ነው ማለት አይደለም:: በተቃራኒው የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት በጨለማ ውስጥ መዝለል ሳይሆን ብሩህ በሆነው በሰማያዊ ብርሃን መራመድ ነው:: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ለቃሉ ታማኝ በሆነው በእግዚአብሔር ኃይለኛ ብርሃን በልበ ሙሉነት መዝለል ነው:: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት በዕድል ውስጥ የሚዋዥቅ እምነት ሳይሆን ነገር ግን በሰማያዊው ንጉሥና መንግሥት ታማኝነት ውስጥ ያለ የድፍረት ልባዊ እምነት ነው:: የመንግሥት እምነት በእርሱ ታማኝነት ላይ ያለ እምነት ነው::

በእምነት ስንራመድ ከማንኛውም ግዙፍ ከሆነው ዓለም ዕይታ ይበልጥ ሰፊና ሁሉን ዐቀፍ ከሆነው ከሰማያዊው የዕይታ አንፃር እንመለከታለን:: በሰው አቋም ብቻ ሊታዩ የማይችሉ ሁኔታዎችና እውነታዎች ለዕይታዎች ክፍት ይሆናሉ፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት በማየት ላይ ሳይሆን በራዕይ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ነው::

በእምነት ዓይን እያንዳንዱ ሰው አንድ ዐላማ ለመፈጸም የተፈጠረ መሆኑን እናስተውላለን:: እግዚአብሔር ለሚያደርገው ወይም ለሚፈቅደው ለእያንዳንዱ ነገር ምክንያት አለው:: ስለሆነም አንተና እኔ በዚህች ምድር ላይ የመኖራችን ሐቅ ድንገተኛ ነገር አይደለም:: ሕይወትና እስትንፋስ ያለህ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ለሕይወትህ ዕቅድና ዐላማ አለው፤ "ለእናንተ ያለኝን ዕቅድ እኔ አውቃለሁ ይላል እግዚአብሔር፤ ዕቅዱም ፍጻሜው ያማረና ተስፋ የሚሰጥ እናንተንም የሚጠቅም እንጂ የሚጐዳ አይደለም" (ኤር 29፥11):: በዚህ ውስጥ ተስፋ የሚለው ቃል የምኞት አስተሳሰብን የሚያመለክት አይደለም፤ ነገር ግን ምንም እንኳ ገና ባይታይም፣ በማይናወጠው በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል እውነተኝነት ላይ የተመሠረተ ርግጠኝነት ነው:: እኛ የወደፊቱን ለእግዚአብሔር ዐደራ አሳልፈን ለመስጠት እንችላለን፤ ምክንያቱም የእርሱ ቃል እውነት ስለሆነና እኛም በእምነት ስንራመድ እርሱ ለእያንዳንዳችን ካለው ዐላማ ጋር የተያያዘ ራዕይን ስለሚሰጠን ነው::

### የእግዚአብሔር መንግሥት መርሆች

- የመንግሥቱ እምነት በማዕበል ውስጥ የሚጸናና የተረጋጋ ነው::
- የመንግሥቱ እምነት ሁሉን አዋቂ በሆነው በእግዚአብሔር እውቀት እንጂ በእኛ ውሱን እውቀት ላይ አይደለም::
- የመንግሥቱ እምት ከእኛ መረዳት በላይ ነው::
- የመንግሥቱ እምነት ከፈተና በኋላ ሽልማት ያገኛል::
- የመንግሥቱ እምነት ሽልማትን የሚያገኘው በንጉሡ ነው::
- የመንግሥቱ እምነት የሚሰጠውና የሚፀናው በንጉሡ ነው::
- የመንግሥቱ እምነት ከደም (ከዝምድና) ይልቅ ጠንካራ ነው::
- የመንግሥቱ እምነት የሚጠራው በፈተና ነው::
- የመንግሥቱ እምነት መከራን አይፈራም::
- የመንግሥቱ እምነት የወደፊቱን ለእግዚአብሔር ይሰጣል::





## እግዚአብሔርን እንደ አምላክነቱ

*“ፍርሀት በሩን አንኳኳ፣ እምነት መለሰ፣ ማንም አልነበረም”::*

የጥንት የእንግሊዞች ምሳሌ::

የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች በማየት ሳይሆን በእምነት ይመላለሳሉ፣ ይህ ግን እምነታችን ዕውር ነው ማለት አይደለም:: በተቃራኒው የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት በጨለማ ውስጥ መዝለል ሳይሆን ብሩህ በሆነው በሰማያዊ ብርሃን መራመድ ነው:: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ለቃሉ ታማኝ በሆነው በእግዚአብሔር ኃይለኛ ብርሃን በልበ ሙሉነት መዝለል ነው:: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት በዕድል ውስጥ የሚዋዥቅ እምነት ሳይሆን ነገር ግን በሰማያዊው ንጉሥና መንግሥት ታማኝነት ውስጥ ያለ የድፍረት ልባዊ እምነት ነው:: የመንግሥት እምነት በእርሱ ታማኝነት ላይ ያለ እምነት ነው::

በእምነት ስንራመድ ከማንኛውም ግዙፍ ከሆነው ዓለም ዕይታ ይበልጥ ሰፊና ሁሉን ዐቀፍ ከሆነው ከሰማያዊው የዕይታ አንፃር እንመለከታለን:: በሰው አቋም ብቻ ሊታዩ የማይችሉ ሁኔታዎችና እውነታዎች ለዕይታዎች ክፍት ይሆናሉ፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት በማየት ላይ ሳይሆን በራዕይ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ነው::

በእምነት ዓይን እያንዳንዱ ሰው አንድ ዐላማ ለመፈጸም የተፈጠረ መሆኑን እናስተውላለን:: እግዚአብሔር ለሚያደርገው ወይም ለሚፈቅደው ለእያንዳንዱ ነገር ምክንያት አለው:: ስለሆነም አንተና እኔ በዚህች ምድር ላይ የመኖራችን ሐቅ ድንገተኛ ነገር አይደለም:: ሕይወትና እስትንፋስ ያለህ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ለሕይወትህ ዕቅድና ዐላማ አለው፤ “ለእናንተ ያለኝን ዕቅድ እኔ አውቃለሁ ይላል እግዚአብሔር፤ ዕቅዱም ፍጻሜው ያማረና ተስፋ የሚሰጥ እናንተንም የሚጠቅም እንጂ የሚጐዳ አይደለም” (ኤር 29፥11):: በዚህ ውስጥ ተስፋ የሚለው ቃል የምኞት አስተሳሰብን የሚያመለክት አይደለም፤ ነገር ግን ምንም እንኳ ገና ባይታይም፣ በማይናወጠው በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል እውነተኝነት ላይ የተመሠረተ ርግጠኝነት ነው:: እኛ የወደፊቱን ለእግዚአብሔር ዐደራ አሳልፈን ለመስጠት እንችላለን፤ ምክንያቱም የእርሱ ቃል እውነት ስለሆነና እኛም በእምነት ስንራመድ እርሱ ለእያንዳንዳችን ካለው ዐላማ ጋር የተያያዘ ራዕይን ስለሚሰጠን ነው::

የአንተ ዐላማ ለሕይወትህ ያለህ ራዕይ የተሰጠህ ሥራ ነው። ይህም ራዕይ የሚገለጠው በእምነት አማካይነት ነው። ብዙ ሰዎች በመላው የሕይወት ዘመናቸው ማን እንደሆኑና ምን ለማድረግ እንደተፈጠሩ ፈጽሞ አያውቁም። የእግዚአብሔር መንግሥት ሕይወት ማለት ካለማወቅ ጨለማ ወጥቶ ወደ ዐላማና ወደ ግንኙነት ብርሃን ውስጥ መግባት ነው፤ "እናንተ ግን ከጨለማ ወደ አስደናቂ ብርሃኑ የጠራችሁን የእግዚአብሔን ታላቅ ሥራ እንድታውጁ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ እግዚአብሔር ለራሱ የለያችሁ ሕዝብ ናችሁ። ቀድሞ የእርሱ ወገን አልነበራችሁም፤ አሁን ግን የእግዚአብሔር ሕዝብ ሆናችኋል፤ ቀድሞ ምሕረትን አላገኛችሁም ነበር፣ አሁን ግን ምሕረትን አግኝታችኋል" (1ጴጥ 2፥9-10)።

እኛ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጐች እና የእግዚአብሔር "የተመረጠ ትውልድ" እንደ መሆናችን መጠን የንጉሡ ንጉሣዊ ቤተሰብ ነን። የምድር ንጉሣውያን ቤተሰቦች ከመወለዳቸው ጀምሮ ማን እንደሆኑ፣ ምን ማድረግ እንዳለባቸውና እንደ ልዑላንና እንደ ልዕልታት እንዴት መመላለስ እንዳለባቸው ይሠለጥናሉ። የእግዚአብሔርም መንግሥት አሠራር በተመሳሳይ መንገድ ነው። አንተ ማን ስለመሆንህና እንድታደርገው ስለሚፈልገው ነገር እርሱ ራዕይን ይሰጥሃል። ያም ራዕይ ከንጉሥህና ከአባትህ የተሰጠህ የሕይወትህ የቤት ሥራ ነው። ያን ራዕይ መፈጸም የሕይወትህን ዐላማ የተሟላ ያደርገዋል። የመንግሥቱ እምነት ከአባትህ የተሰጠህን ራዕይ እንድታይና እንድትገነዘብ ይረዳሃል። እርሱ ለአንተ የሰጠህ ምን ዐይነት ራዕይ ነው?

ራዕይህ ምንም ዐይነት ቢሆን አንድ ነገር ርግጠኛ ነው፦ እያንዳንዱ ራዕይ ስለ እውነተኛነቱ ይፈተናል። ማንም ሰው ከሕይወት ፈተና ነፃ አይሆንም፤ ይህ በተለይ በእግዚአብሔር መንግሥት ዜጐች ዘንድ እውነት ነው። ለዚህ ብቸኛው የብቃት መመዘኛው መወለድ ነው። በአጠቃላይ አነጋገር፣ የሚገጥመን ፈተና ከተቀበልነው ራዕይ ጋር የተዛመደ ነው። ስለዚህ በሕይወትህ ውስጥ ከታላላቅ ፈተናዎች ለመሸሽ ያለህ ምቹ መንገድ ራዕይህን ላለመፈጸም መወሰን ነው። በሌላ አነጋገር፣ ራስህን ላለመሆን ወስን፣ ከዚያም በኋላ በሕይወትህ ብዙ ችግር አይገጥምህም። በርግጥ አንተ በዚህ ውሳኔህ ምንም ሳትሆን፤ ደግሞም ምንም ሳታደርግ ፍፃሜህ ይሆናል። ነገር ግን የተሰጠህን ሥራ ባወቅህና እርሱን ለመፈጸም ውሳኔ ባደረግህ ጊዜ ራስህን ለፈተና ታዘጋጃለህ።

ፈተና ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ የመሆንህ ምልክት ነው የሚለውን ውሸት ማመንን አቁም። ፈጽሞ አይደለም። ፈተና በእርሱ ፈቃድ ውስጥ የመሆንህ ምልክት ነው! ዲያብሎስ ወዴትም የማይሄደውን ሰው ለማቆም



በመሞከር ራሱን አያስጨንቅም። ለራዕይህ የተሰጠህ የቤት ሥራ ስለ እውነተኛነቱ ይፈተናል። ይህም ማለት እግዚአብሔር ሕይወትን ያቀደው አንተ "እግዚአብሔር እንዳደርገው የነገረኝ ነገር ነው" የምትለው ጉዳይ እውነት መሆኑን እስከታይ ድረስ እንዲፈትንህ ነው። ስለዚህ በከፍተኛ ደረጃ እንዳትፈተን ከፈለግህ ትናንሽ ነገሮችን አድርግ፣ ወይም ምንም አታድርግ። ልብ በል፤ ምንም ኢላማ ከሌለህ ሁልጊዜ እርሱን ትመታዋለህ። ግን ይህ ምን ዋጋ አለው? ማንም ሰው በሕይወት ውስጥ ሊወድቅ ይችላል። ስኬታማ ለመሆን ቁርጥ ውሳኔና እምነት ይጠይቃል። የተሟላ ሕይወት ማለት ራዕይህን መረዳት፣ ተግዳሮትን መቋቋም፣ ዐላማህን መከተልና ራዕይህ እውነተኛ መሆኑን ለማረጋገጥ እንደ መልካም ዕድል የሚመጡትን ፈተናዎች በደስታ መቀበል ነው።

ፈተና የሚመጣው ሊያጠፋህ ሳይሆን ራዕይህን ለመፈተን ነው። እስካልተፈተንህ ድረስ እውነተኛ ምንነትህን አታውቀውም። እግዚአብሔር በሕይወትህ ፈተና እንዲመጣ የማይፈቅደው ሊያጠፋህ ሲፈልግ ነው። ፈተና እንዲመጣ የሚፈቅደው አንተ ማን እንደሆንህ፣ በእግዚአብሔር ላይ ምን ያህል እንደምትተማመንና በተሰጠህ ሥራ ላይ ያለህ እምነት ምን ያህል ጥልቅ እንደሆነ ለማወቅ እንድትችል ነው።

አብርሃም የተፈተነው በዚህ ዓይነት ነበር። እግዚአብሔር ለአብርሃም ከመካን ሚስቱ ከሣራ ወንድ ልጅ እንደሚሰጠው ተስፋ ሰጥቶት ነበር። አብርሃምም ስለ ተስፋው ፍጻሜ ለ25 ዓመት ከጠበቀ በኋላ፣ በእርሱ አማካይነት እግዚአብሔር አብርሃምን ብዙ ሕዝብ ለማድረግ ቃል የገባለትን የይስሐቅን መወለድ በመጨረሻ አየ። ከዚያም ይስሐቅ ገና ወጣት፣ ምናልባትም ከዐሥር እስከ ዐሥራ ስምንት ባሉት ዓመታት ሳለ፣ አብርሃም ይስሐቅን ለሚቃጠል መስዋዕት እንዲያቀርበው በማዘዝ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው። አብርሃም እስከ መጨረሻ እንዲሄድ (እንዲሠዋው) የእግዚአብሔር አሳብ አልነበረም፤ ነገር ግን የአብርሃም እምነት እየፈተነ ነበር። አብርሃም ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ የሚሄደው እስከ ምን ድረስ ነበር ፈተናው ስለ አብርሃም ነበር፣ እግዚአብሔር በአብርሃም ልብ ውስጥ የነበረውን እምነት ያውቅ ነበር፤ አብርሃም ግን ማወቅ ነበረበት። አብርሃም የልጁን መስዋዕት ከመፈጸሙ በፊት እግዚአብሔር አስቆመውና ለአብርሃም ለመስዋዕት የሚሆን በግ አቀረበለት። እርሱም "እጅህን በብላቴናው ላይ አታሳርፍ፤ ምንም ጉዳት አታድርስበት፣ እነሆ እግዚአብሔርን እንደምትፈራ ተረድቻለሁ ልጅህን ያውም አንዱን ልጅህን ለእኔ ለመስጠት አልሳሳህምና አለው" (ዘፍ 22፥12)።

አብርሃም ቀድሞውንም ታላቅ እምነት የነበረው ሰው ቢሆንም ከዚያ ልምምድ ይበልጥ ጠንካራ የሆነ እምነትን እንዲሁም ስለ እግዚአብሔርና

እግዚአብሔር ስለሰጠው ተስፋ የተሻለ መረዳትን አገኘ:: የአብርሃም ራዕይ የዓለምን ሕዝብ የሚባርክ ከእርሱ የሚወጣ ትውልድ ነበር:: ስለዚህ አሁን እግዚአብሔር ያንን ነገር እንደሚፈጽመው ያለ ጥርጥር አወቀ:: የአብርሃም ፈተና ራዕዩን አረጋገጠና እምነቱን አጠነከረ::

የአንተ ፈተና እንደ አብርሃም ዐይነት ላይሆን ይችላል፤ ነገር ግን ምንም ዐይነት ቢሆን፣ የእምነትህን ሕይወትና የራዕይህን ማረጋገጫ በሚመለከት የዚያኑ ያህል ትልቅ ነገር ነው:: እግዚአብሔር ራዕይን የሰጠህ ከሆነ እርሱን ይፈትነዋል:: ፈተናውን አትፍራው በደስታ ተቀበለው::

**እግዚአብሔር አምላክ ነው፣ እኛ አይደለንም::**

ከእግዚአብሔር የተሻለ እናውቃለን የሚለውን አሳብ ወደ ጭንቅላታችን ውስጥ የምናስገባው እንዴት ነው? ምንም እንኳ ስህተቶችን ሁሉ ብንፈጽምም፣ ምንም እንኳ ብዙ ጊዜ የምናቃውስ ብንሆንም፣ ምንም እንኳ የሚታየው ብዙ ማስረጃ በተቃራኒው ቢሆንም፣ ሕይወታችንን እንደ ምንም ብለን ከእግዚአብሔር በተሻለ መንገድ እንመራለን ብለን በማመን እንጸናለን:: የዚህ ዐይነት አስተሳሰብ የሚመነጨው ከትምክህት ነው፤ አዳምንና ሄዋንን በኤደን ገነት በችግር ውስጥ ያስገባቸው ይኸው ትምክህት ነው::

እግዚአብሔርን እንደ አምላክነቱ ልናውቀው ይገባናል:: እርሱ አምላክ ነው፤ እኛ ግን አይደለንም:: ማንኛውንም ነገር ከታቀደለት በተቃራኒው መንገድ እንዲሠራ ብናስገድደው በተሳሳተ መንገድ ይሠራል:: እኛ እንደ እግዚአብሔር ለመሆን ብንሞክር፣ በሀዘንና በውድቀት ራሳችንን እናደክማለን:: ከዚህም በላይ ሕይወታችንን በአደጋ ውስጥ እንጥላለን፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ተቀናቃኞችን ስለማያቅፍ ነው:: ብቸኛው ትክክለኛ መንገድ፣ አደጋም የሌለበት ከመላእክት በጥቂት ያነስን (መዝ 8፥5) ፍጡራን የመሆናችንን ሥፍራ በትህትና መቀበልና እግዚአብሔርን እንደ አምላክነቱ መቀበል ነው:: ይህም ማለት እኛ ገደብ ያለን መሆናችንን መቀበልና እግዚአብሔር ግን ምንም ገደብ የሌለው መሆኑን ማወቅ ማለት ነው::

በምዕራፍ አንድ ውስጥ ገደባችንን ስለ ማወቅ ተናግረናል፤ ይህም ኃላፊነት ያለብንንና የሌለብንን እንዲሁም ለማድረግ የምንችለውንና የማንችለውን ማወቅ ማለት ነው:: አሁን ደግሞ በተቃራኒው ወገን እንመለከታለን:: ከሁሉ አስቀድሞ፣ *እግዚአብሔር ብቻ ሊሠራቸው የሚችል አንዳንድ ነገሮች አሉ::* መላውን ግዙፍ ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር ለማምጣት የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው:: እኛ ልናደርገው የምንችለው ከፍተኛው ነገር አስቀድሞ ከነበረ ጥሬ ዕቃ አንድ ነገር ማበጀት ነው::



ሕይወትን ለመፍጠር የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ሳይንቲስቶች የሕይወትን የግንባታ መሣሪያዎች በቤተ ሙከራ በማሰባሰብ ይህንን ለማባዛት ሞክረዋል:: ከዚያም ሕይወት በገዛ ራሱ ይፈጠራል ብለው በማሰብ ከሚሊዮን ዓመታት በፊት ነበሩ ብለው ያመኑባቸውን ሁኔታዎች እንደ ገና ለመፍጠር ሞክረዋል:: እነርሱ በዚህ አልተሳካላቸውም:: የሰውን ልብ ለመለወጥ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ቁጡ የሆነውን ዐመፀኛ ሰው ደስተኛ የእግዚአብሔር ልጅ በማድረግ የሚለውጥ እሱ ነው:: ሕክምና አንድን የተቸገረ ሰው ስለ ራሱ የተሻለ ስሜት እንዲኖረው ሊረዳ ይችል ይሆናል፤ ነገር ግን በዓለም ውስጥ ያለው ምክር አሰጣጥና ሥነ ልቡና ሁሉ ማዕከላዊ የሆነውን ችግር ሊያቃልል አይችልም:: ከኀጢአተኛ ልብ የሚመነጨው ትምክህት ስለሆነ ነው:: እግዚአብሔር ብቻ ኀጢአትን ይቅር ለማለት ይችላል:: እርሱ ብቻ ከምንጩ ከሰው ልብ ሊነቅለውና ሊያወጣው ይችላል:: እግዚአብሔር ብቻ ሊሠራቸው የሚችል አንዳንድ ነገሮች አሉ::

*እግዚአብሔር ብቻ የሚያውቃቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ::* ለሌላ ሰው ከምንነግራቸው በጣም እውነተኛና ነፃነት ከሚሰጡ ነገሮች መካከል አንዱ "እኔ አላውቅም" የሚለው ነው:: እኛ አላዋቂነታችንን ለመቀበል በጣም እንፈራለን፤ ሌሎች ሰዎች ደደብ ይሉናል ብለን በጣም እንፈራለን:: እኛ እንደተቆጣጠርን ለመሆን እንፈልጋለን፣ ወይም ቢያንስ ቢያንስ ሰዎች ስለእኛ ይህንን እንዲያስቡ እንፈልጋለን:: በዓለም ውስጥ ብዙ እርባና የሌለው ነገር ሊኖር የቻለው ብዙ ሰዎች በተለይም መሪዎችና "ባለሙያ ተብዬዎች" እውቀት እንደሌላቸው ሆነው በመታየት ወይም በሌሎች እንደዚህ በመታሰብ ዝናቸውን ላለመጉዳት አንዳንድ ነገር በመናገራቸው ነው:: መጽሐፍ ምሳሌ 1፥7 "እግዚአብሔርን መፍራት የዕውቀት መጀመሪያ ነው፤ ተላሎች ግን ጥበብንና ተግሳጽን ይንቃሉ" ይላል:: በሌላ አነጋገር፣ እግዚአብሔርን መፍራት እውነተኛ ዕውቀት የሚጀመርበት ሥፍራ ነው:: እያንዳንዱን ነገር እናውቅም ደግሞም አንችልም:: እግዚአብሔርን የመፍራት አንዱ ክፍል እግዚአብሔር ብቻ የሚያውቃቸው አንዳንድ ነገሮች የመኖራቸውን ሐቅ መቀበል ነው::

*እግዚአብሔር ብቻ የሚረዳቸው (የሚያውቃቸው) አንዳንድ ነገሮች አሉ::* በሕይወት ውስጥ የሚከሰተውን እያንዳንዱን ነገር ልንረዳው አንችልም:: አንዳንድ ነገሮች ፍጹም ከእኛ መረዳት ያለፉ ናቸው:: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት በጣም አስፈላጊ የሆነበት አንዱ ምክንያት ይህ ነው:: የመንግሥቱ እምነት ስሜት በማይሰጥ ዓለም ውስጥ ሰላምና ልበ ሙሉነት እንዲኖረን ይረዳናል:: እግዚአብሔር ሆይ፣ "አንተ ታውቃለህ፣ እኔ በእውነት ይህንን አልረዳውም አንተ ግን ትችላለህ፣ እኔም ማወቅ የሚያስፈልገኝ ይህንን ብቻ ነው" የምንልበት ጊዜ ይመጣል:: በማትረዳቸው

ነገሮች ሁሉ ግራ መጋባት ወይም ጭንቀት አለብህ? የአንተን የመረዳት ጉድለት ለእግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነት አሳልፈህ ስጥ። እርሱ ሁሉንም ነገር፣ ለአንተ ስሜት የማይሰጡህንም ነገሮች ጭምር፣ በቁጥጥሩ ሥር ማድረጉን በማረጋገጥ እረፍ።

*እግዚአብሔር ብቻ ሊገልጻቸው የሚችል አንዳንድ ነገሮች አሉ።* ብዙ አማኞች ወደ በሰለ እምነት እንዳያድጉ ከፍተኛ እንቅፋት ከሚሆኑባቸው ነገሮች አንዱ እግዚአብሔር በሕይወታቸው ላይ እንዲደርሱ ስለሚፈቅዳቸው ነገሮች መግለጫ ለመስጠት መብት እንደተሰጣቸው ማመናቸው ነው። በምዕራፍ አራት ውስጥ እንዳየነው፣ እግዚአብሔር ራሱንም ሆነ አሠራሩን ለማንኛችንም ቢሆን የመግለጽ ግዴታ የለበትም። ኢዮብ በማንኛውም ጊዜ ከኖረ ከማንኛውም ሰው ይልቅ በጥብቅ ተፈትኖአል፤ ነገር ግን ምንም እንኳ በተደጋጋሚ ለእግዚአብሔር ይግባኝ ቢያቀርብም፣ ለምን እንደተፈተነ ፈጽሞ ለማወቅ አልቻለም። በመጨረሻም እግዚአብሔር ለኢዮብ በተናገረው ጊዜ፣ ስለ ሕይወት በእግዚአብሔር ደረጃ ለመከራከር የነበረውን ዐጉል ድፍረት ለመገሰጽ ነበር። ኢዮብ እግዚአብሔርን በማንነቱ ካወቀ በኋላ ዐጉል ድፍረቱን ስለ ተገነዘበ በትቢያና በዐመድ ላይ ንስሓ ገባ (ኢዮብ 42፥6)። እግዚአብሔር ስለ ኢዮብ መከራ ምክንያቱን ፈጽሞ አልገለጠም፣ በመጨረሻም ከኢዮብ አንፃር ምንም ችግር አልነበረውም እግዚአብሔርን አምላክ በማድረጉ ረካ፤ ይህም እግዚአብሔር ብቻ የሚገልጻቸው አንዳንድ ነገሮች መኖራቸውንና እርሱም ይህን ለማድረግ ጊዜ ላይፈልግ የሚችል መሆኑን መቀበል ማለት ነው።

*የዚህም ፍሬ አሳብ እኛ ገደባችንን ማወቅ አለብን የሚል ነው።* እኛ የምንችላቸውን ነገሮች መለወጥን እንማር፣ ለመለወጥ የማንችላቸውን ነገሮች በፀጋ እንቀበል፤ በዚህ ሚዛን ሰላም ይኑረን። ሁሉም ነገር ለእግዚአብሔር ይቻለዋል። ስለዚህ ሊደረግ፣ ሊታወቅ፣ ሊደረስበትና ሊገለጽ የማይቻለው ሲያጋጥምህ የማይቻለውን ለሚችለው አምላክ ዐደራ አሳልፈህ ስጥ።

**ለፈተና መታቀድ**

*ዓለምን ለመረዳትና ለሕይወት ትርጉም ለማግኘት ያለን የመጨረሻና ብቸኛ መሣሪያ እምነት ነው።* አንዳንድ ነገሮች መግለጫ የሌላቸውና ከእኛ ሰብአዊ የመረዳት ችሎታ በላይ ናቸው። በእንዲህ ዐይነት ሁኔታ ውስጥ መሄድ ያለብን ወደ እምነት ብቻ ነው፤ ነገር ግን እምነታችን በሕያው እግዚአብሔርና በቃሉ እውነተኛነት ላይ ከሆነ የሚያስፈልገን እምነት ብቻ ነው ማለት ነው። እምነት ልበ ሙሉነትን ይፈጥራል። የልበ ሙሉነት ጉድለት የእምነት ጉድለት ምልክት ነው። አካባቢያዊ ሁኔታው ምንም ይምሰል ምን፤ በእምነት ከታጠቅን በየቀኑ በዓለም ውስጥ በልበ ሙሉነት



ለመራመድ እንችላለን። እምነት የአካባቢው ሁኔታ ምንም ዐይነት ቢሆን እኛ እንደምናሸንፍ የተረጋገጠ እውቀት ይሰጠናል። እንደሚገጥመን እርግጠኛ የሆንንበትን ፈተና በድል፣ እንደምናልፍ ያረጋግጥልናል።

እምነታችን በሚያጋጥመው ፈተና ይገለጣል። በሌላ አነጋገር፣ ፈተናዎች የእምነታችንን ባሕርይና ጥራት እንዲያውም እምነት መኖሩን ወይም አለመኖሩን እንኳ ይገልጣሉ። ከዚህ በፊት እንዳልሁት፣ የእምነታችን ጥንካሬ በሚያልፈው ፈተና ልክ ነው። እግዚአብሔር እምነታችን እንዲፈተን የሚፈቅደው ለዚህ ነው። እርሱ እምነታችን እንዳይጠፋ ብቻ ሳይሆን እንዲለመልም ይፈልጋል፣ ይህም የሚሆነው በፈተና ዐውድ ውስጥ ብቻ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ እግዚአብሔር እኛን ለፈተና ዐቅዶናል። ስለሆነም ፈተናዎች ትክክለኛ ፈተናዎች እስከሆኑ ድረስ ለእኛ መልካም ናቸው። እኛ በተደጋጋሚ በተሳሳቱ ነገሮች ራሳችንን እንፈትንና ሕይወታችን ለምን እንደሚመሰቃቀል እንደነቃለን። የእግዚአብሔር ፈተናዎች የታቀዱት ለታቀድንበት ነገር እንዲስማሙና እንዲሁም እኛን ለማጠንከርና ለመንግሥቱ ዝግጁ እንድንሆን ለማድረግ ነው።

በሰዓት 180 ማይል የሚነበብበት የፍጥነት መለኪያ ያለው መኪና ከገዛህ፣ የዚያ መኪና አምራች ያ መኪና በሰዓት 180 ማይል ለመሄድ እንደሚችል ማረጋገጫ መስጠቱ ነው። ምናልባት አንተ በዚያ ፍጥነት ነድተህ አታውቅም ይሆናል። የዚያንም የፍጥነት መለኪያ አሠራር ላታውቀው ትችላለህ። ያ መኪና ወደዚያ ፍጥነት እንደሚደርስ እንዴት ታውቃለህ? ለአምራቹ ያንን ማረጋገጫ ለመግለጽ መብት የሰጠው ምንድነው?

**መፈተን**

የአውቶሞቢል አምራቾች ዐዲስ ሞዴሎችንና ዕቅዶችን የሚፈትኑበትን መስመሮች (መንገዶች) ያዘጋጃሉ። የመፈተኛው መስመር የሩጫ መስመርን ይመስላል። ለምሳሌ አንድ ኩባንያ ዐዲስ ሞተር በሚያቅድበት ጊዜ እርሱን መሰል ሞተር ያዘጋጅና ያንን ነገር በመፈተኛ መኪና ላይ ይገጥመዋል። በኩባንያው የተቀጠረው የፈተና መኪናው ነጂ የመፈተኛውን መኪና ወደ መፈተኛ መስመር ይወስድና ዐዲሱን ሞተር በተመደበለት ፍጥነት ውስጥ ያስገባዋል። መሐንዲሶቹና የኩባንያው ሥራ አስኪያጆች ሞተሩ በታቀደለት መሠረት ሊሠራ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ ይፈልጋሉ። የፈተና መኪና ነጂው ሞተሩን እስከ መጨረሻው ድረስ እንበልና በሰዓት 180 ማይል በመጫን በዚያ ለተወሰነ ጊዜ እንዲቆይ ያደርገዋል። ይህ መሰል ሞተር ፈተናውን ከወደቀ እርሱን ይጥሉና እንደገና ሌላ ይጀምራሉ። ይሁን እንጂ ፈተናውን ካለፈ፣ በታቀደለት መሠረት ከሠራ "የዚህን ሞተር አምሳያ

በተስተካከለ ዝርዝር 300,000 ጊዜ አባዛው” የሚል ትእዛዝ ይወጣል:: እነርሱ እያንዳንዱን ሞተር አይፈትኑም፤ አንዱን ብቻ ይፈትኑና ከዚያ በኋላ በእርሱ መልክ 300,000 ያህል ያባዛሉ:: ከዚያም ኩባንያው ያ ሞተር ያለው መኪና ሁሉ በሰዓት 180 ማይል ለመሄድ እንደሚችል ማረጋገጫ ለመስጠት ይችላል:: ለምን? ምክንያቱም የተፈተነው ሞተር ፈተናውን ስላለፈ ነው:: የተፈተነውም ሞተር ፈተናውን ካለፈ በእርሱ መልክና አምሳል የተሠራው እያንዳንዱ ሞተር ደግሞ ይህን ለማለፍ የሚችል መሆን አለበት::

ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት በዋዜማው ሌሊት ለጴጥሮስ እንዲህ አለው፤ “ስምዖን ስምዖን ሆይ፣ እነሆ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፣ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ ጸለይሁ፣ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አበርታ” (ሉቃ 22፥31-32):: ጴጥሮስ ለፈተና እየተቃረበ ነበር፤ ከዚያም ጌታን በመካዱ ምክንያት ከደረሰበት መራራ ሀዘንና ጸጸት በኋላ፣ የጴጥሮስ እምነት በፊት ከነበረው ፈጽሞ በተለየ ሁኔታ ተመልሶ ይጠነክራል:: ከዚያም ፈተናውን ባለፈ ጊዜ ሌሎችን ለማበርታት ይችላል::

በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እያለፍህ ከሆነ እግዚአብሔር በሞዴልነት ሊጠቀምብህ እንደሚፈልግ ጥሩ ምልክት ነው:: ፈተናህን እለፍ፤ ባጋጠመህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በጽናት ቁም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ብዙ ሰዎችን በአንተ መልክ ለመሥራት ይፈልጋል:: እግዚአብሔር ከሕይወትህ ችግሩን እንዲያስወግድልህ ትጸልይ ይሆናል፤ እርሱ ግን በችግሩ ውስጥ እርሱን እንድታምን ይፈልግ ይሆናል:: ምክንያቱም የአንተ እምነት ውጥረትን ሁሉ ለማስተናገድ የሚችልና ከችግሩ ውስጥ በፈገግታ ለመውጣት የሚችል መሆኑን ለማየት የሚጠባበቁ አንዳንድ ሰዎች መኖራቸውን ስለሚያውቅ ነው:: በድካም ወይም በውጥረት ውስጥ የሚያልፈው የአንተ እምነት ሌሎችን ደግሞ በጽናት እንዲቆሙ ሊያጠነክርና ሊያበረታ ይችላል::

***መውጫ መንገድ***

በፈተና ስኬት የማግኛው ቁልፉ ጤናማ በሆነ የትሕትና መጠን የተቀመመ እምነት ነው:: በራስህ በጽናት ለመቆም ከመመካት የበለጠ ለውድቀት ፈጣን መንገድ የለም:: በመጽሐፈ ምሳሌ 16፥18 “ትዕቢት ጥፋትን፣ የእብሪት መንፈስም ውድቀትን ትቀድማለች” ይላል:: ጳውሎስ የቆሮንቶስ አማኞች ለማስጠንቀቅ ይህንኑ አደጋ ያሠምርበታል፤ “ስለዚህ ተደላድዩ ቆሜአለሁ የሚል እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ” (1ቆሮ 10፥12) ይላል:: በሌላ አነጋገር፣ ጳውሎስ እያለ ያለው ለራስህ ጠንካራ እንደሆንህ የምታስብ ከሆነ ተጠንቀቅ! ሁሉ ነገር እንዳለህ ብታስብ ተጠንቀቅ! ሌሎችን በስህተታቸውና በውድቀታቸው የምትነቅፍና የምትፈርድ ከሆነ አታድርገው



ምክንያቱም ቀጥሎ የአንተ ተራ ይሆናል ማለቱ ነበር:: ኢየሱስ “ምሕረት የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው፤ ምሕረትን ያገኛሉና” ብሎአል (ማቴ 5፥7):: በስፈሩት ቁና የመስፈር ሕግ ይህ ነው:- በወደቅህ ጊዜ ምሕረትን ለማግኘት ብትፈልግ ለወደቁ ለሌሎች ሰዎች ምሕረትን አድርግ:: ማንም ፍጹም የለም:: ከፈተና ነፃ የሚያደርግ ጠንካራ እምነት ያለው ማንም ሰው የለም::

እግዚአብሔር መውጫውን መንገድ የሚሰጠን ይህን ስለሚያውቅ ነው:: ጳውሎስ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፤ “በሰዎች ሁሉ ላይ ከደረሰው የተለየ ፈተና አልደረሰባችሁም እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤ ስለዚህ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አይተዋችሁም፤ ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን መታገሥ እንድትችሉ መውጫ መንገዱት ያዘጋጅላችኋል” (1ቆሮ 10፥13)::

የአንተ ችግሮች ከሰው የተለዩ እንደሆኑ ታስባለህን? አንተ በምታልፍበት ችግር ውስጥ ያለፈ ሰው እንደሌለ ታስባለህን? እኔ ልዩ ነኝ ብለህ ታስባለህን? እንደገና አስብበት:: ማንም ሰው ልዩ አይደለም:: ማንኛችንም ብንሆን ሌላ ማንም ሰው ያልገጠመው ልዩ ችግር ገጥሞኛል ለማለት አንችልም:: የአንተና የእኔ ፈተናዎች በሁሉም ሰው ዘንድ የተለመዱ ፈተናዎች ናቸው:: ኢየሱስ እንኳ ነፃ አልነበረም:: በዲያብሎስ በተፈተነበት በምድረ በዳ እየጾመ 40 ቀናትን አሳለፈ፣ ትኩረቱን በትክክለኛው ሥፍራ ላይ በማድረግ ፈተናውን አለፈ፤ ትኩረቱም በአባቱና አባቱ በሰጠው ተልእኮ ላይ ነበር:: ይህ ሊያደፋፍረን ይገባል:: ኢየሱስ ራሱ ፈተናን ስለተለማመደ ፈተና ምን እንደሆነ ያውቃል:: እኛ የምናልፍበትን ችግር ስለሚያውቅ ምሕረትን ይልክልናል:: የዕብራውያን ፀሐፊ ከዚህ የሚከተለውን የጻፈው ይህን ስለተገነዘበ ነበር፤

> እንግዲህ ወደ ሰማያት ያረገ ታላቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን እምነታችንን አጥብቀን እንያዝ:: በድካማችን የማይራራልን ሊቀ ካህናት የለንምና፣ ነገር ግን እንደ እኛ በማንኛውም ነገር የተፈተነ ሊቀ ካህናት አለን:: ይሁን እንጂ ምንም ኀጢአት አልሠራም:: እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበልና በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ (ዕብራውያን 4፥14-16)::

ኢየሱስ፣ እኛ ስንፈተን በምን ውስጥ እያለፍን እንደ ሆነ ስለሚረዳ ሊያበረታን ይችላል:: ይህም ሌላ ሰው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ በሚያልፍበት ጊዜ እኛ ካለን ልምምድ የተነሣ “በርታ ታልፋለህ!” ለማለት እንድንችል ነው:: እኛ ታማኞች ባንሆንም ጌታ ታማኝ ስለሆነ ከዚህ

ድፍረትን ልናገኝ እንችላለን። እኛ አናልፍበትም በምንልበት ጊዜ እንኳ እርሱ ሊያሳልፈን ይችላል፤ ይፈልጋልም። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ጻድቃን ሲጮኹ እግዚአብሔር ይሰማቸዋል፤ ከመከራቸውም ሁሉ ያድናቸዋል። የጻድቅ መከራው ብዙ ነው እግዚአብሔር ግን ከሁሉም ያድነዋል" ይላል (መዝ 34፥17፡19)።

እግዚአብሔር ለልጆቹ ታማኝ ከመሆኑ የተነሣ እኛ ከምንችለው በላይ እንድንፈተን አይፈቅድም። የመኪናን (የሞተርን) ችሎታ ከዐቀደውና ከሠራው ሰው በላይ የሚያውቅ ማነው? እግዚአብሔር እኛን ፈጠረን፣ የእኛን ችሎታ ከእርሱ በላይ የሚያውቅ ማነው? እኛ ራሳችን እንኳ ዕውቀታችን ውሱን ስለሆነ ሙሉ ችሎታችንን እግዚአብሔር የሚያውቀውን ያህል አናውቀውም። የማይታለፍ መስሎ የሚታይህ ፈተና በገጠመህ ጊዜ እንኳ እግዚአብሔር ልታሸንፈው ከምትችለው በላይ ሊፈትንህ እንደማይፈቅድ ቃል የገባልህ መሆኑን ብቻ አስታውስ። በሌላ አነጋገር፣ አንተን ሊያጠፋህ የሚችል ፈተና ወደ አንተ አይመጣም ማለት ነው፤ እግዚአብሔር አይፈቅድለትም።

ይሁን እንጂ፤ እግዚአብሔር መከራንና ፈተናን ከመንገዳችን ላይ እንደማያስወግድ እናስታውስ። ፈተና ይወገድ ከተባለ እኛን ከዓለም ውስጥ ማስወገድ ይኖርበታል። በዚህ ፈንታ ፈተናዎቻችንን እኛ በምንችለው መጠን ይገድባቸዋል። በዚህም እንኳ ፈተናውን "መታገሥ" እንድንችል "መውጫውንም" ያዘጋጅልናል። ስለዚህ መከራ በገጠመህ ጊዜ እግዚአብሔር "እንደምትቋቋመው አውቃለሁ፤ ስለዚህ ተቋቋመው! አትጩህ፣ አታጉረምርም፣ ደፋርና ልበ ሙሉ ሁን፣ እምነትህን ተለማመድ፣ የመንግሥት ገንዘብህን (እምነትህን) ወጪ አድርግና ቁም!" እያለህ ነው። የአንተ ፈተና እግዚአብሔር ለአንተ ያለው ልበ ሙሉነት ምልክት ነው። ጸንተህ ቁም፣ ከዚያም እርሱ የማምለጫውን መንገድ ያሳይሃል።

እግዚአብሔር የመውጫውን መንገድ ያዘጋጅልናል፣ ነገር ግን ከመንፈሱ ጋር ካልተባበርን ልናጣው እንችላለን። እኛ ብዙ ጊዜ ችግር ሲመጣ እግዚአብሔር እንዴትና መቼ እንደሚታደገን ለመገመት እንሞክራለን። እኛ በምንረዳው ሁኔታ እንዲሠራ እንፈልጋለን። ይሁን እንጂ፣ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር የሚሠራው ባልተጠበቀ ሁኔታ ነው። ከዚያም እግዚአብሔር እኛ በጠበቅነው ሁኔታ ሲሠራ በማናይበት ጊዜ ግራ እንጋባለን፣ እናዝናለን፣ እንፈራለን፣ እንዲያውም እርሱ እኛን ትቶናል እስከ ማለት እንደርሳለን።

ለዚህ ግራ መጋባት አንዱ ምክንያት የእግዚአብሔር አመለካከት ሰፊ ሆኖ እኛ በራሳችን ፍላጐትና አጀንዳ ላይ የማተኰር ዝንባሌ ስላለን ነው። እርሱ ይታደገናል፣ ነገር ግን ይህን የሚያደርገው የእርሱን ታላቅ ዐላማ እንዲያገለግል ባቀደው መንገድ ነው እንጂ በእኛ ጠባብ ፍላጐት አይደለም።



የዳንኤል መውጫ መንገድ በአንበሶች ጉድጓድ ውስጥ ነበር። የሲድራቅ፣ የሚሳቅና የአብድናጐ መውጫ መንገድ በዕቶን እሳት ውስጥ ነበር። ጳውሎስና ሲላስ በመሬት መናወጥ ትድግናን ከማግኘታቸው በፊት በፊልጵስዩስ ወህኒ ቤት በድብደባና በእሥራት ውስጥ ማለፍ ነበረባቸው። በእነዚህ በእያንዳንዳቸው ሁኔታዎች ውስጥ ትድግና የመጣው ከተጠበቀው በተለየ መንገድ ነው። በመጨረሻው ግን እግዚአብሔር ከበረ፣ የሰዎችም ሕይወት ተለወጠ።

ለምሳሌ የምትወደው በጣም የታመመ ሰው አለ እንበል። አንተም እግዚአብሔር ይህንን ሰው እንዲፈውሰው ዘወትር ትጸልያለህ። የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችን ትጠራና ዘይት ቀብተው እንዲጸልዩለት ወይም እንዲጸልዩላት ታደርጋለህ። የታመመው ሰው ልዩ ጸሎትና የእጅ መጫን እንዲደረግለት የፈውስ ፕሮግራም ወዳለበት ጉባኤ ትወስደዋለህ አንተ የምትችለውን ሁሉ ታደርጋለህ፣ ይሁን እንጂ የምትወደው ሰው ይሞታል። ከዚያስ ምን ይሆናል? እግዚአብሔር አሁንም አምላክ ነውን? ጸሎትህን መልሶአል ወይስ ችላ ብሎሃል? ኦራል ሮበርትስ የተባለ ሰው እግዚአብሔር በሁለት መንገድ በጊዜያዊነትና ለዘላቂነት እንደሚፈውስ ይናገር ነበር። በዚህ ሁኔታ፣ እግዚአብሔር አንተ የምትወደውን ሰው ወደ ዘላለም ቤቱ በመውሰድ በዘላቂነት ሊፈውሰው መርጦአል። እርሱ የመውጫውን መንገድ አዘጋጅቶአል፣ ነገር ግን አንተ ተስፋ ካደረግኸውና ከጠበቅኸው በተለየ መንገድ ነው።

ስለዚህ በምትፈተንበት ጊዜ በጽናት ቁምና የእግዚአብሔርን መውጫ መንገድ ተመልከት፤ ነገር ግን ይህን ስታደርግ ባልተጠበቀ ሁኔታ ወይም ካልተጠበቀ አቅጣጫ እንደሚመጣ ለማየት ተዘጋጅ። እግዚአብሔርን እንደ አምላክነቱ ተቀበል።

### ገደባችንን ማወቅ

እግዚአብሔር ባልተጠበቀ መንገድ እንዲሠራ መረዳት ገደባችንን በገሃድ ለመቀበላችን ሌላ ምክንያት ነው። እኛ ሁሉንም ነገር ማወቅ አለብን ወይም ማንኛውንም ነገር ለማድረግ መቻል አለብን ብለን የምናስብ ከሆነ፣ እግዚአብሔር በእኛ ዕቅድ መሠረት በማይሠራበት ጊዜ ዘወትር ተስፋ እንቆርጣለን። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ገደባችንን ማወቅ ነፃ የሚያወጣ ልምምድ ነው። ይህ ደግሞ ለእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ቁልፍ ከሆኑት ነጥቦች አንዱ ነው። በምዕራፍ ሁለት ውስጥ እንዳልሁት፣ በጥርጥር ጊዜ እምነት ይኑርህ፤ የምታደርገውን ስታጣ እመን፤ ምንም ነገር ስሜት ሳይሰጥህ ሲቀር ተማመን። ገደባችንን ማወቅ ከሌላ ከምንም ነገር በላይ ነፃነትን ይሰጠናል። እንዴት? ምክንያቱም የመንግሥት እምነት ገደቡን

ለማይገደበው አምላክ ስለሚያስረክብ ነው:: የእኛ ገደቦች በማይገደበው አምላክ እጆች ውስጥ ሲገቡ ጥንካሬዎች ይሆናሉ:: ጳውሎስ የእግዚአብሔር ኃይል በእኛ ድካም እንደሚፈጸም ገልጾአል፤ ከዚያ ቀጥሎም እንዲህ ይላል፦ "ስለ ክርስቶስ በድካም፣ በስድብ፣ በመከራ፣ በስደትና በጭንቀት ደስ የምሰኘው ለዚህ ነው፤ ስደክም ያን ጊዜ ብርቱ ነኝና" (2ቆሮ 12፥10)::

ገደባችንን ማወቅ ከራሳችን ይልቅ በእግዚአብሔር ብርታት፣ ጥበብና ኃይል ላይ እንድንመካ ያስገድደናል:: ጴጥሮስ በራሱ ብርታት ለክርስቶስ ለመቆም የሚችል መስሎት ነበር፤ ነገር ግን ለደህንነቱ የነበረው ፍርሀት ክርስቶስን ሦስት ጊዜ እንዲክድ ባደረገው ጊዜ የውርደት ውድቀት ደረሰበት:: ይሁን እንጂ ጴጥሮስ አንድ ጊዜ ድካሙን ካወቀና ለእግዚአብሔር ካስረከበ በኋላ የእምነት የኃይል ምንጭ በመሆን በድፍረት ክርስቶስን በነገሥታትና በንጉሠ ነገሥታት ፊት የሚያውጅ ሰው ለመሆን በቃ::

ገደብህን ለማይገደበው አምላክ አሳልፈህ ስጥ:: ሁሉንም ነገር ማወቅ አለብኝ ብለህ ግትር አትሁን:: አንተ ማወቅ የሚያስፈልግህ እርሱ ያስተምርሃል፤ ለማድረግ በማትችለው ነገር ምክንያት አትዘን:: ማድረግ የሚያስፈልግህን ነገር እግዚአብሔር እንድታደርገው በጠራህ ነገር ለማድረግ ኃይልን ይሰጥሃል:: እግዚአብሔርን እንደ አምላክነቱ ያዝ:: እርሱ ዝግጁነትህን በሚያውቀው መንገድ ይምራህ::

ዳዊት የተናገረውን ቃል ብናስብ መልካም ነው፦

> እግዚአብሔር ሆይ፣ ልቤ አልታበየም ዐይኔ ከፍ ከፍ አላለም ሐሳቤ ለዐጉል ትልቅነት አልተነሣሣም፤ ከዐቅሜ በላይ አልተንጠራራሁም:: ነገር ግን ነፍሴን ጸጥ፣ ዝም አሰኘኋት፤ ጡት የጣለ ልጅ ዐርፎ እናቱ ላይ እንደሚቀመጥ ነፍሴ ጡት እንዳስተውት ሕፃን በውስጤ ጸጥ አለች (መዝሙር 131፥1-2)

አስተውል፣ እነዚህ የአንድ ንጉሥ ቃሎች ናቸው:: ዳዊት በዘመኑ እጅግ ኃይለኛ ንጉሥ ነበር:: በደርዘን የሚቆጠሩ አገልጋዮች የእርሱን ምልክትና ጥሪ የሚጠብቁ ነበሩ:: በእጁ ምልክት ብቻ የሕይወትን ወይም የሞትን ጉዳይ ሊወስን የሚችል ሰው ነበር:: እርሱ የሚፈልገውን ነገር ሊነፍገው የሚችል ኃይል አልነበረም:: ይሁን እንጂ "ልቤ አልታበየም" ለማለት ችሎ ነበር:: ዳዊት ከየት እንደመጣ ያስተውል ነበር:: እረኛ የነበረ መሆኑን አልረሳም:: ዳዊትም ቀጠለና "ዐይኔ ከፍ ከፍ አላለም" አለ:: "ከፍ ከፍ" የሚለው ሐረግ በዕብራይስጡ ቋንቋ "ዐጉል ድፍረት" ማለት ይሆናል፤ ደግሞም በበላይነት ስሜት ሌሎችን ዝቅ አድርጎ ማየት ሊሆን ይችላል:: ሁለቱም አዝማሚያዎች ስህተቶች ናቸው:: ዳዊት ከሆነው በላይ ለመሆን



አልፈለገም:: እግዚአብሔር ለንጉሥነት ስለ መረጠው ብቻ ለመታበይና ራሱን ከሌሎች በላይ ለማድረግ አልሞከረም::

እኛም ይህን ማድረግ የለብንም:: የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጐችና የእርሱ የንጉሣዊ ቤተሰብ ልጆች በመሆናችን በሌሎች ላይ አፍንጫችንን የመንፋት መብት የለንም:: የመንግሥት እምነት ሚዛናችንን እንድንጠብቅ ይረዳናል:: የዚያም ሚዛን አንዱ ክፍል ማንና የት መሆናችንን በእርሱ የብርሃን መንግሥት ውስጥ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ብቻ ሳይሆን በተጨማሪም ማንና የት እንደነበርን - በሰይጣን የጨለማ ግዛት የታሠርን የኀጢአት ባሪያዎች የነበርን መሆናችንን መገንዘብ ነው::

ቀጥሎም ዳዊት፣ "ሐሳቤ ለዐጉል ትልቅነት አልተነሣሣም ወይም ከዐቅሜ በላይ አልተንጠራራሁም" ይላል:: ከዚህ በፊት እንዳየነው ለእኛ ከዐቅማችን በላይ የሆኑ አንዳንድ ነገሮች አሉ:: እነርሱን ለመረዳት አንችልም:: አሁን ልናውቃቸው የማንችላቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ:: እግዚአብሔር የራሱ ምክንያት ስላለው በእርሱ መተማመን ያስፈልገናል:: ኰሪ ቴን ቡም በ1974 በጻፉት ደብዳቤ፣ በልጅነታቸው የነበረውን ትዝታ ይገልጻሉ::

> ወደ አባቴ ሄድሁና፣ "አባዬ ለኢየሱስ ክርስቶስ ሰማዕት ለመሆን ጥንካሬ አይኖረኝም ብዬ እፈራለሁ" አልሁት:: አባቴም መልሰ እስኪ ንገሪኝ፣ ወደ አምስተርዳም በባቡር ለመሄድ በምትፈልጊበት ጊዜ የቲኬት መግዣውን ገንዘብ የምሰጥሽ መቼ ነው? ከሦስት ሳምንት በፊት ነውን?" አለኝ:: እኔም "አይደለም አባዬ የቲኬቱን ዋጋ የምትሰጠኝ ወደ ባቡሩ ልገባ ስል ነው" አልሁት:: አባቴም መልሶ "ልክ ነሽ፣ የእግዚአብሔርም ብርታት እንደዚሁ ነው:: የሰማዩ አባታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ሰማዕት ለመሆን ጥንካሬ መቼ እንደሚያስፈልግሽ ያውቃል:: የሚያስፈልግሽን ሁሉ በጊዜው ይሰጥሻል... "::

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት የእግዚአብሔርን ጊዜ በመጠበቅ ደስ ይለዋል:: በሕይወታችን አንዳንድ ሁኔታዎች በሚያጋጥሙን ጊዜ እግዚአብሔር ግድ የሌለው ወይም የእኛን ሁኔታ የማያውቅ የሚመስልበት ጊዜ አለ:: እግዚአብሔር ምንም የማይናገርበት ወይም ጸሎታችንን ችላ የሚል የሚመስልበት ጊዜ አለ:: የመንግሥቱ እምነት በእግዚአብሔር ዝምታ ውስጥ የሚኖረን ልበ ሙሉነት ነው::

**እግዚአብሔር የተሻለ ነገር አለው**

እኛ ስለ ዓለምና ስለምናልመው ሕይወት ያለን ግምት ምንም ያህል ብሩህና ውብ ቢሆን እግዚአብሔር ለእኛ ከዚያ የተሻለ ነገር አለው:: ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ በራሳችን ሕልም ላይ ከመጠን በላይ ትኩረት ስለምናደርግ ከዚያ የተሻለ ነገር መኖሩን አንገምትም:: የእኛ ራዕይና ዕውቀት የተገደቡ መሆናቸውን አትርሳ:: ሙሉውን ስዕል ለማየት ከፈለግን ነገሮችን ከእግዚአብሔር አንፃር መመልከት አለብን:: ኢሳይያስ 64፥4 "ከጥንት ጀምሮ በተስፋ ለሚጠባበቁት የሚደርስላቸው እንደ አንተ ያለውን አምላክ ያየ ዐይን፣ ያደመጠ ጆሮ ፈጽሞ" አልነበረም ይላል:: ጳውሎስ ለቆሮንቶስ አማኞች ይህንኑ ቃል ትንሽ ለየት ባለ መንገድ ጠቀሰላቸው:: "ይሁን እንጂ እንደተጻፈው፣ ዐይን ያላየውን፣ ጆሮ ያልሰማውን፣ የሰውም ልብ ያላሰበውን እግዚአብሔር ለሚወዱት አዘጋጅቶአል" ይላል (1ቆሮ 2፥9):: እግዚአብሔር ለእኛ ያቀደው ነገር ስፋቱና ውበቱ ከእኛ መረዳት በላይ ነው:: የመንግሥቱ እምነት አስፈላጊ የሚሆነውም ለዚህ ነው:: በደረጃ ሁለተኛ የሆነውን ነገር ይዘን በመቆየት ፈንታ ከእግዚአብሔር የሆነውን እጅግ የተሻለ እንድንጠብቅ ያስተምረናል:: ታማኞች ከሆንን እግዚአብሔር በራሱ ጊዜና በራሱ መንገድ "የተሻለውን ነገር" ይገለጽልናል:: የዕብራውያን ፀሐፊ እንደገለጸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት የእምነት ጀግኖች ምስክርነት ይህ ነበር፦

> እምነት ተስፋ ያደረግነው ነገር እንደሚፈጸም እርግጠኛ የምንሆንበት፣ የማናየውም ነገር እውን መሆኑን የምንረዳበት ነው:: አባቶችም የተመሰከረላቸው በዚሁ ነው (ዕብራውያን 11፥1-2)

አባቶች የተመሰከረላቸው ስለ እምነታቸው ነው:: ጸሓፊው የእነርሱን አዎንታዊ ምሳሌነት ሲጠቅስ የእነዚህን ታማኝ ሰዎች የስም ጥሪ ያስከትላል፦ አቤል፣ ሄኖክ፣ ኖሕ፣ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ፣ ሙሴ፣ ረዓብ፣ ጌዴዎን፣ ባርቅ፣ ሳምሶን፣ ዮፍታሔ፣ ዳዊት፣ ሳሙኤል እና ነቢያት ናቸው:: እነዚህ ሰዎች ምንም እንኳ ብዙ ትውልድን የሚወክሉ ቢሆኑም ቢያንስ አንድን ነገር የሚጋሩ ነበሩ፤ ይኸውም እነርሱን በግላቸው ለማየት በሕይወት ባይኖሩም በእርሱ ተስፋዎች ላይ እንዲጸኑ ያደረጋቸው በእግዚአብሔር ላይ የነበራቸው እምነት ነበር:: እንደገናም የዕብራውያን ጸሓፊ እንደዚህ ይላል፦

> እነዚህ ሁሉ የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል ሳያገኙ እምነታቸውን እንደ ጠበቁ ሞቱ:: ሆኖም ከሩቅ አይተው ሰላም አሉት፤ በዚህ ምድር ሲኖሩ መጻተኞችና እንግዶች መሆናቸውን ተገንዝበው ነበርና:: እንደዚህ የሚሉት ሰዎች የራሳቸው የሆነውን አገር እንደሚጠባበቁ ያሳያሉ:: ትተውት የወጡትን አገር ቢያስቡ ኖሮ ወደዚያ የመመለስ



> ዕድል ነበራቸው:: አሁን ግን ከዚህ የሚበልጠውን ሰማያዊ አገር ይናፍቃሉ:: ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካቸው ተብሎ ሊጠራ አላፈረም፤ ከተማን አዘጋጅቶላቸዋልና ... እነዚህ ሁሉ ስለ እምታቸው የተመሰከረላቸው ቢሆኑም ከእነርሱ ማንም የተስፋውን ቃል የተቀበለ የለም:: እግዚአብሔር ለእኛ የሚበልጥ ነገር ስላዘጋጀ ያለ እኛ ፍጹማን ሊሆኑ አልቻሉም (ዕብራውያን 11፥13-16፡ 39-40)

እነዚህን ሰዎች በአንድነት የሚያያይዛቸው ሌላው የጋራ የሆነ ነገር የታማኝነታቸው ዋጋ የሆነው በችግር ውስጥ የማለፋቸው ሁኔታ ነው:: ተፈተኑና ዐለፉ:: በማዕበሉ ውስጥ በእምነታቸው ፀንተው በመቆም በብቃት ተሻገሩ:: ለብዙዎቹ የመጨረሻው የእምነታቸው ዋጋ ሞት ነበር:: ነገር ግን የእነርሱ ሞት ወደ ዘላለማዊው የሕይወት ሙላት አስገባቸው፣ ይህም ምድራዊ ሕይወታቸውን የመሠረቱበት የተረጋገጠ ተስፋ ነበር::

እኛ በሸሸንበት ነገር ፈጽሞ አንታወቅም:: በወደቅንበት ፈተና ምክንያት በሰዎች ልንታወስ አንችልም (ሁልጊዜ መውደቅ ብቻ ካልሆነ በስተቀር):: ፈሪዎችን፣ በችግር ጊዜ የሸሹትን፣ ያልታወቁትንና በሕይወታቸው ውስጥ ምንም ነገር ያልሠሩትን ታሪክ አያስታውሳቸውም:: ምክንያቱም ምንም ነገር ስላልሞከሩ ነው:: አያስታውሳቸውም ታሪክ የሚያስታውሳቸው ባመኑበት ነገር የኖሩትን (እና የሞቱትን)፣ የቆሙለት ነገር ለፈተናው የሚመጥን መሆኑን ስላመኑበት በተቃውሞ ሁሉ ሳያወላውሉ የጸኑትን ነው::

ሰዎች የሚያስታውሱን በተጽእኖ ውስጥ ተረጋግተን በመቆየታችን፣ በትርምስ መካከል ፀጥ በማለታችንና በጥርጥር ጊዜ ልበ ሙሉ በመሆናችን ነው:: በሕይወት ውስጥ እንዲህ ዐይነት ሚዛናዊነት የሚሰጠን አንድ ነገር ብቻ ነው፣ እርሱም የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ነው:: ይህ እምነት፣ ሕይወት ትርጉም በማይሰጥበት ጊዜ እንኳ በእግዚአብሔር ላይ የሚደገፍ እምነት ነው:: ባለማወቃችን ረክቶ የሚኖር እምነት ነው:: ገዳባችንን የሚቀበል እምነት ነው:: በማዕበል ውስጥ ቢሆንም እንኳ እግዚአብሔር በመጨረሻው እንደሚሸልመን የሚተማመን እምነት ነው:: የአሁኑ ሁኔታ ምንም ዐይነት ቢሆን፣ የወደፊቱ ውብና ክቡር መሆኑን በማወቅ፣ እግዚአብሔርም በማዕበል ውስጥ የሚያጠራን በሙላት እንድንደሰት መሆኑን የሚያምን እምነት ነው:: እግዚአብሔርን አምላክ የሚያደርግ እምነት ነው::

## የእግዚአብሔር መንግሥት መርሆች

- የመንግሥቱ እምነት እግዚአብሔር ለቃሉ ታማኝ በሆነበት ኃይለኛ ብርሃን ውስጥ በልበ ሙሉነት መዝለል ነው::
- ዐላማህ በሕይወትህ ላለህ ራዕይ የተሰጠህ ሥራ ነው::
- ፈተና የታቀደው ሊያጠፋህ ሳይሆን ራዕይህን ሊያረጋግጥ ነው::
- እምነታችን የሚገለጠው በሚያጋጥመው ፈተና ነው::
- በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የምታልፍ ከሆነ፣ እግዚአብሔር በሞዴልነት ሊጠቀምብህ የሚፈለግ ለመሆኑ ጥሩ ምልክት ነው::
- በፈተና ውስጥ ስኬት የማግኛ ቁልፉ፣ ጤናማ በሆነ የትህትና መጠን የተቀመመ እምነት ነው::
- የመንግሥቱ እምነት ገደቡን ለማይገደበው አምላክ ያስረክባል::
- የመንግሥቱ እምነት በእግዚአብሔር ዝምታ ውስጥ በልበ ሙሉነት መቆም ነው::



# ምዕራፍ ስድስት

## የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ድፍረት

*"እምነት ያለ ማረጋገጫ ማመን ሳይሆን ያለ መቆጠብ መተማመን ነው"::*

ኤልቶን ትሩብለድ

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት፣ ደፋር እምነት ማለትም ተስፋ የማይቆርጥ እምነት ነው፣ ምክንያቱም የአሁኑ ሁኔታዎች ሙሉ የሆነውን ወይም የመጨረሻውን ተጨባጭ ሁኔታ የማይወክሉ መሆናቸውን ስለሚያውቅ ነው:: በቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ እምነት ይጠራል፣ ይህንንም ሲያደርግ ብዙ ጊዜ እምነትን ከድፍረት ጋር በማያያዝ ነው:: ድፍረት የፍርሀት አለመኖር ማለት አይደለም:: ድፍረት ማለት በፍርሀት ፊት ልበ ሙሉነትና ጽኑ እምነት ማለት ነው:: ድፍረት ማለት ከፍርሀት እንቅፋት ባሻገር (ወዲያ ማዶ) በሕይወት ማመን ነው::

ሙሴ ከሞተ በኋላ ወዲያውኑ እግዚአብሔር፣ የሙሴ ምትክ እንዲሆን የተመደበውን ኢያሱን፣ ለአብርሃምና ለዘሩ ቃል የገባላቸውን "የተስፋይቱን ምድር" ከነዓንን ይወርሱ ዘንድ ሕዝቡን እንዲያዘጋጅ አዘዘው:: ሙሴ ሕዝቡን በታላቅ ክህሎትና እጅግ ብዙ በሆኑ በእግዚአብሔር ኃይል ምልክቶች እየታገዘ ለ40 ዓመታት መርቶአቸው ነበር፣ እነዚያን እግሮች መተካት ከባድ ነበር:: በዚህ ተግዳሮት ላይ እስራኤላውያን ወደፊት የሚያገኙአቸው ከነዓናውያን በጦርነት ኃይለኞችና በምድሪቱ ተደላድለው የተቀመጡ መሆናቸው ሌላ ተጨማሪ ተግዳሮት ነበር:: ኢያሱ ዕጥፍ የሆነ ጠንካራ ተግዳሮት ገጠመው፤ ይህም የሙሴ ተተኪ እንደመሆኑ መጠን የእስራኤላውያኑን አመኔታና ከበሬታ ማትረፍ ብቻ ሳይሆን በተጨማሪም ዮርዳኖስን ተሻግረው ምድሪቱን እንዲወርሱ ማበረታታት ነበር፣ ይህ ጉዳይ ደግሞ የቀደመው ትውልድ ለመፈጸም ያልፈለገው ነገር ነበር::

ደግነቱ ግን በሥራው ላይ የነበረው ኢያሱ ብቻ አልነበረም:: ኢያሱ ብቻውን ሥራውን ሊሠራ እንደማይችል እግዚአብሔር ያውቅ ነበር:: ኢያሱ የሚሸከመው ኃላፊነትና የሚገጥመው ተግዳሮት ሚዛናዊ አስተሳሰብ ያለውን ማንኛውንም ሰው ወደ ኋላ እንዲያፈገፍግ የሚያደርግ ነበር:: እግዚአብሔርም ደግሞ ሕዝቡ አደጋ ሲገጥማቸው በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጡና ሁሉንም ነገር የሚተው መሆናቸውን ያውቅ ነበር:: ኢያሱ የሕዝቡ መሪ እንደመሆኑ መጠን ድፍረት ያስፈልገው ነበር፤ ሕዝቡም ደግሞ በመሪያቸው ምሳሌነት ድፍረትን ማግኘት ያስፈልጋቸው ነበር:: ስለዚህ

የከነዓንን ምድር ለማሸነፍ ዘመቻ ከመጀመሩ በፊት እግዚአብሔር ለሙሴ እንዳደረገው ለኢያሱም ተገለጠለት፤

> የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር የሙሴን አገልጋይ የነዌን ልጅ ኢያሱን እንዲህ አለው፤ እነሆ ባሪያዬ ሙሴ ሞቶአል፤ እንግዲህ አሁንም አንተና ይህ ሕዝብ ሁሉ ተነሡ፤ ለእስራኤላውያን ወደምሰጣቸው ምድር ለመግባት የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻገሩ:: ለሙሴ በሰጠሁትም ተስፋ መሠረት እግራችሁ የሚረግጠውን ቦታ ሁሉ እሰጣችኋለሁ:: የርስታችሁ ዳርቻ ከምድረ በዳው እስከ ሊባኖስ ከታላቁ ወንዝ ኤፍራጥስ አንሥቶ የኬጢያውያንን ምድር በሙሉ ይዞ በምዕራብ በኩል እስከ ታላቁ ባሕር ይደርሳል:: በሕይወት በምትኖርበት ዘመን ሁሉ ማንም አይቋቋምህም፤ ከሙሴ ጋር እንደነበርሁ ሁሉ ከአንተም ጋር እሆናለሁ፤ ከቶ አልጥልህም አልተውህም:: ጽና፣ ለቀደሙት አባቶቻቸው እሰጣችኋለሁ ብዬ የማልሁላችሁን ምድር እንዲወርሱ ይህን ሕዝብ የምትመራው አንተ ነህና በርታ:: አይዞህ፤ ብቻ አንተ በርታ:: ባሪያዬ ሙሴ የሰጠህን ትእዛዝ ሁሉ በጥንቃቄ ጠብቅ፤ በምትሄድበትም ሁሉ እንዲሳካልህ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል:: ይህ የሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፤ በውስጡ የተጻፈውን ሁሉ በጥንቃቄ እንድትፈጽመውም ቀንም ሆነ ሌሊት ከሐሳብህ አትለየው:: ይህን ካደረግህ ያሰብኸው ይቃናል፤ ይሳካልም:: በምትሄድበት ሁሉ እግዚአብሔር አምላክህ ከአንተ ጋር ነውና አይዞህ በርታ፣ ጽና፣ አትፍራ፣ አትደንግጥ ብዬ አላዘዝሁህምን?" (ኢያሱ 1፥1-9)::

በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሔር ኢያሱን ሦስት ጊዜ "አይዞህ፣ በርታ" ይለዋል:: ነገር ግን ምንም እንኳ እምነት የሚለው ቃል በምንባቡ ውስጥ ባይገኝም በውስጠ ታዋቂነት ታቅፎ ይገኛል:: እግዚአብሔር ለኢያሱ የሚሠራ ሥራ ይሰጠዋል፤ ከኢያሱ ጋር እንደሚሆን ያረጋግጥለታል፤ እንዲሁም በወደፊቱ ዘመቻ ድልን እንደሚሰጠው ቃል ይገባለታል:: ከዚያም ኢያሱ ጽኑና ብርቱ እንዲሆን ይነግረዋል:: ጽኑና ብርቱ የሚሆነው በምንድን ነው? እግዚአብሔርን በማመንና የእርሱን ትእዛዝ በመፈጸም ነው:: እግዚአብሔር የተናገረውን ለመፈጸም ሁልጊዜ ድፍረት ያስፈልጋል:: እምነትና ድፍረት አብረው የሚሄዱ ነገሮች ናቸው::



በእምነት ውስጥ ድፍረት አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በብዛት እንዳየነው የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት በፈተናዎች፣ በመከራዎችና በችግሮች የተሞላ ሕይወት ስለሆነ ነው፤ እነዚህንም ማዕበሎች ለመጋፈጥ ድፍረት ያስፈልጋል:: አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር እምነታችንን ለማደፋፈር ታላላቅና ተአምራዊ ሥራዎችን ይሠራል፤ ነገር ግን እኛ እምታችንን ያለቦታው እንዳናውል መጠንቀቅ ያስፈልገናል:: የእግዚአብሔር ሥራዎች ግብ፣ እምነታችንን በሥራዎቹ ላይ ሳይሆን በእርሱ ላይ እንድናደርግ ነው:: በዮሐንስ ወንጌል፣ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ማንነቱን ለመግለጽና እምነታቸውን ለማሳደግ ያደረጋቸውን የተለያዩ ተአምራት ወይም ምልክቶች ሐዋርያው ይገልጻል::

ከእነዚህ ምልክቶች በመጀመሪያ፣ ኢየሱስ በገሊላ ቃና በአንድ ሠርግ ላይ ተገኝቶ ውሀውን ወደ ወይን ለወጠ:: በኋላ ላይ፣ ዮሐንስ የዚህን ተአምር ዓላማ እንዲህ ሲል ይገልጻል፦ "ኢየሱስም ይህን የታምራዊ ምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ አውራጃ በቃና ከተማ አደረገ:: ክብሩንም ገለጠ፤ ደቀመዛሙርቱም በእርሱ አመኑ" (ዮሐንስ 2፥11):: የኢየሱስ ደቀመዛሙርት እምነታቸውን ያደረጉት ውሀውን ወደ ወይን ጠጅ በመለወጡ ላይ ሳይሆን በእርሱ ላይ ነበር:: ምክንያቱም እኛ እስከምናውቀው ድረስ ኢየሱስ ይህንን እንደገና አላደረገውም:: የአንድ ጊዜ ብቻ ተአምር ነበር::

እግዚአብሔር በሥራዎቹ፣ በተአምራቱና በበረከቶቹ ውስጥ ያለው ዐላማ እኛ እምነታችንን በሥራዎቹ ላይ ሳይሆን በእርሱ ላይ እንድናደርግ ነው:: በሌላ አነጋገር፣ እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ በሕይወታችን ውስጥ አስገራሚ ነገሮችን የሚያደርገው በእርሱ ላይ መተማመንን እንማር ዘንድ ነው:: በዚህ ፈንታ ግን እኛ ብዙ ጊዜ የምናደርገው እርሱ ባደረገው ነገር ላይ መተማመን ነው:: ከዚያም የዚያ ምልክት ወይም በረከት ከዓይናችን ሲደበዝዝ ሌላ ለማግኘት እንሮጣለን:: እግዚአብሔር ግን ሁል ጊዜ "እኔን እመኑ:: ተአምራትን፣ ምልክቶችና በረከቶችን ለማግኘት መሮጣችሁን ተውና እኔን እመኑ" ይለናል:: እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ተመሳሳይ ነገርን በተመሳሳይ መንገድ ሁለት ጊዜ አያደርግም፤ ወይም ለሁለት የተለያዩ ሰዎች በተመሳሳይ መንገድ አያደርግም:: ለምሳሌ ኢያሱ ምንም እንኳ የሙሴ ተተኪ እንዲሆን የተመደበ ቢሆንም እግዚአብሔር ለሙሴ እንዳደረገው በተመሳሳይ መንገድ ለኢያሱ አላደረገም:: ይሁን እንጂ የእኛ ዝንባሌ እግዚአብሔር ዛሬ ያደረገውን ነገር ነገም በተመሳሳይ መንገድ እንዲያደርግ መጠበቅ ነው፣ ወይም ለእኛ እንዳደረገው በተመሳሳይ መንገድ በሌላው ሰው ሕይወትም እንዲያደርግ ነው:: እግዚአብሔርን በእንደዚህ ዐይነት ሳጥን ውስጥ በምናስቀምጥበት ጊዜ ተስፋ እንቆርጣለን::

ስለዚህ እግዚአብሔር ለእኔ ወይም ለሌላ ሰው ባደረገው ነገር ላይ እምነታችሁን አታድርጉ:: እምነታችሁን በእግዚአብሔር ላይ አድርጉ፤ ከዚያም መንፈሳችሁን ዘና በማድረግ በራሱ ልዩ መንገድ ከእናንተ ጋር እንዲገናኝ ፍቀዱለት::

## መከራዎቹን የመጋፈጥ ድፍረት

የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጐችን የተለያዩ ዐይነት መከራዎች ብዙ ጊዜ ገጥመዋቸዋል፤ ይህም በመንፈሳዊ ሕዋሳችን ውስጥ ያለ ነው:: የኢየሱስን ቃሎች ልብ በሉ፡- "በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ:: ነገር ግን አይዞአችሁ! እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ" (ዮሐ 16፥33):: የጳውሎስን ቀጥተኛ አዋጅ ደግሞ ተመልከቱ፡- "በርግጥም በክርስቶስ ኢየሱስ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት መኖር የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ" (2ጢሞ 3፥12):: ጳውሎስ ይህንን በትክክል ያውቃል፤ ምክንያቱም ስደትን ከሁለቱም ወገን ሆኖ ስለሚያውቅ ነው:: ይኸውም በመጀመሪያ አማኞችን አሳዳጅ በመሆን ከዚያም የክርስቶስ ተከታይ ከሆነ በኋላ የክርስቶስ ወንጌል ታማኝ መልእክተኛ በመሆኑ ነው:: እንደ እውነቱ ከሆነ፣ በክርስቶስ በማመኑ ምክንያት መሞቱ በተመዘገበው በመጀመሪያ ሰው ስደት ውስጥ ጳውሎስ ቀንደኛ ተሳታፊ ነበር፤ ይህም ሰማዕት እስጢፋኖስ ይባላል::

የእስጢፋኖስ ታሪክ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በምዕራፍ ስድስትና ሰባት ውስጥ ይገኛል:: እርሱ ለመጀመሪያ ጊዜ የታየው በኢየሩሳሌም የነበረችው ቤተክርስቲያን በቤተክርስቲያኑ ሥር ለነበሩት ችግረኞች በየዕለቱ የሚፈጸመውን የማከፋፈል ሥራ በበላይነት እንዲቆጣጠሩ ከተመረጡት ሰባት ሰዎች መካከል አንዱ በመሆን ነው:: "በእምነትና በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ" (የሐዋ 6፥5) በሚል ቃል የተገለጸው እስጢፋኖስ በተጨማሪም ብርቱ የሆነ የክርስቶስ የአደባባይ ምስክር ነበር፤ ይህም ብዙ ሳይቆይ በችግር ውስጥ አስገባው፡-

> በዚህ ጊዜ እስጢፋኖስ ጸጋንና ኃይልን ተሞልቶ በሕዝቡ መካከል ድንቅ ነገሮችንና ታምራዊ ምልክቶችን ያደርግ ነበር:: "የነጻ ወጪዎች ምኩራብ" ተብሎ የሚጠራው ምኩራብ አባላት የሆኑ ከቀሬናና ከእስክንድርያ እንዲሁም ከኪልቅያና ከእስያ አውራጃዎች የመጡ ሰዎችም ተቃውሞ አስነሥተው እስጢፋኖስን ይከራከሩት ጀመር:: ይሁን እንጂ ይናገርበት የነበረውን ጥበብና መንፈስ መቋቋም አልቻሉም::



> ስለዚህ እስጢፋኖስ "በሙሴና በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል ሲሰነዝር ሰምተናል" የሚሉ ሰዎችን በስውር አዘጋጁ::
>
> በዚህ ሁኔታ ሕዝቡን፣ የአገር ሽማግሌዎቹንና የሕግ መምህራኑን በማነሣሣት እስጢፋኖስን አስይዘው በአይሁድ ሸንጎ ፊት አቀረቡት:: እንዲህ ብለው የሚመሰክሩ የሐሰት ምስክሮችንም አቆሙበት፤ "ይህ ሰው በዚህ በተቀደሰው ስፍራና በሕጉ ላይ የስድብ ቃል መናገሩን በፍጹም አልተወም፤ ምክንያቱም ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ ይህን ስፍራ እንደሚያጠፋና ከሙሴ የተቀበልነውን ወግ እንደሚለውጥ ሲናገር ሰምተነዋል":: በሸንጎው ተቀምጠው የነበሩትም ሁሉ እስጢፋኖስን ትኩር ብለው ሲመለከቱት ፊቱ የመልአክ ፊት መስሎ ታያቸው (የሐዋርያት ሥራ 6፥8-15)::

እስጢፋኖስ "እግዚአብሔርን ተሳድበሃል" በሚል ከፍተኛ ወንጀል ተከስሶ ወደ አይሁድ ሃይማኖታዊ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጐትቶ ከተወሰደ በኋላ በምዕራፍ 7 ውስጥ ለክርስቶስና ለመንግሥቱ በጽናት በመቆም ከሳሾቹ በንዴት አፋቸውን እንዲዘጉ ያደረገ እጅግ ረጅም ንግግር አደረገ፡-

> በሸንጎው ስብሰባ ላይ የነበሩትም ይህን በሰሙ ጊዜ እጅግ ተቆጡ፣ ጥርሳቸውንም አፋጩበት:: እስጢፋኖስ ግን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ ሲመለከት የእግዚአብሔርን ክብር፣ እንዲሁም ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየና "እነሆ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ" አለ::
>
> በዚህ ጊዜ በታላቅ ድምጽ እየጮኹ ጆሮአቸውን ደፍነው እርሱ ወደ አለበት በአንድነት ሮጡ፤ ይዘውም ከከተማው ውጭ ጣሉት፤ በድንጋይም ይወግሩት ጀመር:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ በዚያ የነበሩ ምስክሮችም ልብሳቸውን ሳውል (ጳውሎስ) በተባለ ጐልማሳ እግር አጠገብ አስቀመጡ::
>
> እስጢፋኖስም እየወገሩት ሳለ፣ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ ነፍሴን ተቀበላት" ብሎ ጸለየ:: ከዚያም ተንበርክኮ በታላቅ ድምጽ

"ጌታ ሆይ ይህን ኀጢአት አትቁጠርባቸው" ብሎ ጮኸ። ይህን ካለ በኋላም አንቀላፋ (የሐዋ ሥራ 7፥54-60)።

እስጢፋኖስ በቤተክርስቲያን እንደ አገልጋይ (መሪ) በመሆን የተመረጠው "በእምነት የተሞላ" ስለነበረ ነው። በክርስቶስ አካል ውስጥ ለመመረጥ በእምነት የተሞላህ መሆን አለብህ። ሰማያዊው መንግሥትና የእርሱ ወኪል የሆነችው ቤተክርስቲያን ተጽእኖ በመጣ ጊዜ ጥለው የሚሸሹ ደካሞች ዜጐችን ለማቀፍ አይችሉም። በመከራ ውስጥ የሚያቆምህ እምነት እንጂ ችሎታ (ብቃት) አይደለም። ሁሉም ነገር ሲወድቅብህ ጸንተህ እንድትቆም የሚረዳህ እምነት እንጂ ስጦታ አይደለም።

ይሁን እንጂ የእስጢፋኖስ እምነት በድንጋይ ከመወገር እንዳላዳነው ተመልከት። በእምነቱ ግን ጸንቶ ቆመ፤ ይህ የሕይወት ዋጋ አስከፈለው። እስጢፋኖስ ለክርስቶስ ባለው ምስክርነት ምክንያት በድንጋይ ተወግሮ የሞተ የመጀመሪያው ደቀመዝሙር ነው። መከራ ወይም ችግር በሚደርስብህ ጊዜ አንድ ሰው ይመጣና "እሺ እምነት ካለህ፣ ይህ ነገር ለምን ደረሰብህ?" ይልሃል። እስቲ እስጢፋኖስን ጠይቀው። "እግዚአብሔርን የምትከተል ከሆነ በድንጋይ እንዲወግሩህ እንዴት ሊፈቅድላቸው ቻለ?" ይህ የእግዚአብሔር ሥልጣን ነው። ለምን? ምክንያቱም እርሱ ንጉሥ ስለሆነና ለክብሩ ስለሚሠራ ነው። በመጨረሻም እስጢፋኖስ በእግዚአብሔር ክብር ራዕይ በመሞላትና ሕያው የሆነውን ክርስቶስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ እያየ፣ በፊቱ ላይ ፈገግታን በማሳየትና በከንፈሮቹ የይቅርታን ጸሎት በመጸለይ ሞተ።

ድንጋይ በላይህ ላይ እየወረደብህ በፈገግታ ልትሞት ትችላለህን? ደግሞስ ለሚገድሉህ ሰዎች ይቅርታ በማድረግ ትሞታለህን? እስጢፋኖስ ይህን አድርጐአል። የእርሱ እምነት ከድንጋይ የጠነከረ ነበር፤ ቤተክርስቲያንም የበዛችው ከእርሱ ሞት በኋላ ነበር። እግዚአብሔር የእስጢፋኖስን ሞት ለእያንዳንዱ ሰው የሕይወትን ዐላማ በመስጠት የተጠቀመበት ሲሆን፣ ይህም ለሁሉም ነገር የዓይን ምስክር ለሆነው ለጳውሎስም ጭምር ነበር። እስጢፋኖስ ለእምነቱ የሞተ ከሆነ እኛ ለእምነታችን መኖር አንችልምን?

### ሙሉው ታሪክ

የእግዚአብሔር መንግሥት ሕይወት አካል ስለሆኑት ስለ በረከቶች፣ ስለ ብልጽግናዎችና ስለ ሌሎችም መልካም ነገሮች የሚናገሩ ሰባኪዎች፣



የመጽሐፍ ቅዱስ መምህራንና ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሙሉውን ታሪክ እየተናገሩ አይደለም። የእግዚአብሔር መንግሥት ሕይወት እነዚህና ከእነዚህም በላይ ነው፤ በተጨማሪ የተግዳሮት፣ የመከራና የችግር ሕይወት ነው። ከመጀመሪያው እንደዚሁ ነበር፣ ደግሞም ክርስቶስ ዳግመኛ እስኪመጣ ድረስ እንደዚሁ ይሆናል። በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ በዐመፅ ባለ ዓለም መካከል የእግዚአብሔር መንግሥት ወኪሎች ሆነን ስንኖር ሳለን ሁኔታው እንዴት ሌላ ሊሆን ይችላል? የመንግሥቱ ዜጐች የመሆናችን ሐቅ ራሱ በተቃውሞና በተግዳሮት ፊት ያቆመናል።

በቤተክርስቲያን ቀደምት ዘመናት እንኳ ጳውሎስና ሌሎች የክርስቶስ ሐዋርያት፣ አማኞች በእምነታቸው ጸንተው እንዲቆሙ ማደፋፈርን አስፈላጊ ሆኖ አግኝተውታል፤ ምክንያቱም እምነታቸውን እንዲተው የሚያደርጓቸው ፈተናዎች በአካባቢአቸው ስለነበሩ ነው። በልስጥራ ከተማ ጳውሎስ ክርስቶስን በመስበኩ ቁጣ በሞላባቸው አይሁዶች በድንጋይ ተወግሮ ሞቶ ተብሎ ጥለውት ሄደው ነበር፤ ይህ ግን እርሱን አልገታውም፦

> አይሁድ ግን ከአንጾኪያና ከኢቆንዮን መጥተው ሕዝቡን አግባቡ። ጳውሎስንም በድንጋይ ከወገሩት በኋላ የሞተ መስሎአቸው ጐትተው ከከተማው ወደ ውጭ አወጡት። ሆኖም ደቀመዛሙርት ከበውት እንዳሉ ተነሣ፤ ወደ ከተማም ገባ። በማግስቱም ከበርናባስ ጋር ወደ ደርቤን ሄዱ።
>
> ጳውሎስና በርናባስ በደርቤን የምሥራቹን ቃል ሰብከው ብዙ ደቀመዛሙርትንም ካፈሩ በኋላ ወደ ልስጥራን፣ ወደ ኢቆንዮንና ወደ አንጾኪያ ተመለሱ፤ የደቀመዛሙርቱንም ልብ በማበርታትና በእምነታቸው ጸንተው እንዲኖሩ በመምከር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ ማለፍ አለብን አሏቸው። ከዚያም በየአብያተ ክርስቲያናቱ ሽማግሌዎችን ከሾሙላቸው በኋላ በጾምና በጸሎት ላመኑበት ጌታ ዐደራ ሰጧቸው (የሐዋ 14፥19-23)።

ጳውሎስ በድንጋይ ከተወገረ በኋላ ወደዚያው ከተማ መመለስ ብቻ ሳይሆን እርሱና ጓደኛው በርናባስ በየመንገዱ ባሉት ከተሞች አማኞችን እያበረታቱ ወደ አንጾኪያ ሲመለሱ ልስጥራንም ጐብኝተዋል። እነዚህን አማኞች ያበረታቱአቸው እንዴት ነበር? "ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ ማለፍ አለብን" ብለው በመንገር ነበር። ጳውሎስና በርናባስ መከራን ስደትንና ችግርን እንደ መንግሥቱ አምባሳደርነታቸው

የአገልግሎታቸው አካል አድርገው ተቀብለዋቸው ነበር፡፡ ለእኛም ከዚህ የተለየ አይደለም ደፋር እምነት የሚያስፈልገንም ለዚህ ነው፡፡

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ተግዳሮቶችን አይሸሽም፣ ነገር ግን የእምነት ሕይወት ዋነኛና አስፈላጊ አካል በማድረግ ይቀበላቸዋል፡፡ ጳውሎስ ይህንን እንደ ሌሎቹ እንዲያውም ከአብዛኞቹ በበለጠ ሁኔታ ተረድቶታል፡፡ በጳውሎስ ሕይወት የተፈጸመው ነገር እግዚአብሔር ለእኛ ጥቅምና ለእርሱ ክብር ሲል በችግር ውስጥ እንድናልፍ የሚፈቅድ መሆኑን በሚገባ ግልጽ ያደርግልናል፡፡ ሐዋርያው በእሥር ላይ እያለ በሮም ከተማ በቄሳር ፊት ይግባኝ ለማለት በመርከብ ሲሄድ በአድሪያቲክ ባሕር ላይ በማዕበል ተይዞ ነበር፡፡ ማዕበሉ እጅግ አስከፊ ከመሆኑ የተነሣ በመጨረሻው ብዙ ልምድ የነበራቸው መርከበኞች እንኳ ተስፋ ቆርጠው ነበር፡፡ ነገር ግን በዚያን ጊዜ ጳውሎስ ከጌታ ቃል አገኘ፡-

> ሰዎቹ እህል ሳይቀምሱ ብዙ ቀን ከቆዩ በኋላ ጳውሎስ በመካከላቸው ቆሞ እንዲህ አለ፤ እናንተ ሰዎች ሆይ የነገርኋችሁን ሰምታችሁኝ ቢሆን ኖሮ ከቀርጤስ ባልተነሣችሁና ይህ ጉዳትና ጥፋት ባልደረሰባችሁ ነበር፡፡ አሁንም ቢሆን አይዟችሁ፡፡ መርከቧ እንጂ ከእናንተ አንዲት ነፍስ እንኳ አትጠፋምና፡፡ በትላንትናዋ ሌሊት የእርሱ የሆንሁትና የማመልከው እግዚአብሔር የላከው መልአክ በአጠገቤ ቆሞ "ጳውሎስ ሆይ አትፍራ፡፡ በቄሳር ፊት መቆም ይገባሃል፤ ከአንተ ጋር የሚጓዙትንም ሰዎች ሕይወት እግዚአብሔር አትርፎልሃል፤" አለኝ፡፡ ስለዚህ እናንተ ሰዎች ሆይ፤ አይዟችሁ፣ እርሱ እንደነገረኝ እንደዚያው እንደሚሆን በእግዚአብሔር አምናለሁና፡፡ ይሁን እንጂ ወደ አንዲት ደሴት በነፋስ ተወስደን እዚያ መጣላችን አይቀርም (የሐዋ 27፥21-26)፡፡

ጳውሎስ በቄሳር ፊት እንደሚቆም እግዚአብሔር ለጳውሎስ ግልጽ አደረገለት፤ በዚያም ጳውሎስ ራሱን በሚከላከልበት ሂደት ውስጥ ለክርስቶስ ትልቅ ምስክርነትን ይሰጣል፡፡ በተጨማሪ ግልጽ መሆን ያለበት ነገር ጳውሎስ ወደ ሮም ከመድረሱ በፊት በባሕር ላይ በማዕበል ውስጥ ማለፉና የመርከቡ መሰበር የእግዚአብሔር ዐላማ መሆኑ ነው፡፡ እግዚአብሔር የጳውሎስን ጉዞ በሙሉ ሰላማዊ ሊያደርገው ይችል ነበር፤ ነገር ግን እርሱ ከዚህ ከፍ ያለ ዐላማ ነበረው፡፡ ይኸውም የጳውሎስ ጓደኞችና እንዲሁም በመርከቡ ላይ የነበሩት ወታደሮችና ተሳፋሪዎች የእግዚአብሔር የማዳኑ



ኃይል በተግባር ሲሠራ እንዲመለከቱና ለእርሱ ክብርን እንዲሰጡ ስለ ፈለገ ነበር፡፡

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ያላቸው ሰዎች ከችግሮች አይሸሹም፣ ምክንያቱም ችግሮች የመንግሥቱ ሕይወት ተፈጥሮአዊ አካል መሆናቸውን ስለሚያውቁ ነው፡፡ በረከቶች፣ ምልክቶችና ተአምራት፣ ምንም እንኳ አስደናቂ ቢሆኑም፣ የሙሉው ስዕል አንድ ክፍል ብቻ ናቸው፡፡

## እምነት ከሁሉ ነገር የበለጠ ይቆያል

የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች በበረከቶቻቸው ሳይሆን በፈተናዎቻቸው የሚታወቁት በዚህ ምክንያት ነው፡፡ በረከቶች ጊዜያዊ ናቸው፤ ምልክቶችና ድንቆች ጊዜያዊ ናቸው፤ እምነት ግን እስከ ዘላለም ይቆያል፡፡ የታማኞች ሰዎች ዝርዝር በሆነው በዕብራውያን ምዕራፍ 11 ውስጥ የተዘረዘሩት ቅዱሳን የተመሰከረላቸው በእምነታቸው ነው እንጂ በሀብታቸው ወይም በትምህርታቸው ወይም በስጦታቸው ወይም በችሎታቸው አልነበረም፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ዕብራውያን 11፥6 በግልጽ፡- "ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሁሉ እግዚአብሔር መኖሩንና ከልብ ለሚሹትም ዋጋ እንደሚሰጥ ማመን አለበት" ይላል፡፡ ኢየሱስም፣ "ነገር ግን የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆንን?" በማለት ጠይቋል (ሉቃ 18፥8)፡፡ የጠየቀው እምነትን እንጂ በረከቶችን ወይም ብልጽግናን አይደለም፡፡ ጳውሎስም "የምንኖረው በእምነት እንጂ በማየት አይደለም" ብሎአል (2ቆሮ 5፥7 ይመልከቱ)፡፡ በሌላ አነጋገር እኛ የምንኖረው በእግዚአብሔር ላይ ባለን እምነት መሠረት እንጂ በዓይናችን በምናያቸውና እርሱ በሚያደርግልን ነገሮች መሠረት አይደለም፡፡ ጳውሎስ በመልእክቶቹ ውስጥ በተደጋጋሚ የአንባቢዎቹን እምነት ያወድሳል፡-

> ከሁሉ አስቀድሜ እምነታችሁ በዓለም ሁሉ በመሰማቱ ስለ ሁላችሁም አምላኬን በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ (ሮሜ 1፥8)፡፡

> ስለ እናንተ በምንጸልይበት ጊዜ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እናመሰግናለን፤ ምክንያቱም በክርስቶስ ኢየሱስ ስላላችሁ እምነትና ለቅዱሳን ሁሉ ስላላችሁ ፍቅር ሰምተናል፡፡ ይህም የሆነው በሰማይ ተዘጋጅቶ ከተቀመጠላችሁ ተስፋ የተነሣ ነው፤ ስለዚህ ተስፋ በወንጌል የእውነት ቃል አስቀድማችሁ ሰማችሁ፣ ይህም ወደ እናንተ ደርሶአል፡፡ ይህንም ወንጌል

ከሰማችሁበትና የእግዚአብሔርን ጸጋ በእውነት ከተረዳችሁበት ቀን ጀምሮ በዓለም ዙሪያ እየሠራ እንዳለ ሁሉ በእናንተም ዘንድ ፍሬ እያፈራና እያደገ ነው (ቆላ 1፥3-6)።

በጸሎታችን እየስታወስናችሁ ሁልጊዜ እግዚአብሔርን ስለ ሁላችሁ እናመሰግናለን። ከእምነት የሆነውን ሥራችሁን፣ ከፍቅር የሆነውን ድካማችሁንና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ባላችሁ ተስፋ የተገኘውን ጽናታችሁን በአምላካችንና በአባታችን ፊት ዘወትር እናስባለን (1ተሰ 1፥2-3)።

ወንድሞች ሆይ እምነታችሁ በየጊዜው እያደገ በመሄዱና የእርስ በርስ ፍቅራችሁም እየጨመረ በመምጣቱ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ሁልጊዜ በሚገባ ማመስገን አለብን። ስዚህ በደረሰባችሁ ስደትና መከራ ሁሉ በመጽናታችሁ እኛ ራሳችን ስለ ትዕግሥታችሁና ስለ እምነታችሁ በእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ እንመካለን (2ተሰ 1፥3-4)።

እምነት እስከዚህ አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው? ምክንያቱም እምነት የጽድቅ ቁልፍ እግዚአብሔርን ለማየት፣ ወይም ወደ መንግሥቱ ለመግባት ብቸኛ መንገድም ነው። ጳውሎስ ለሮሜ አማኞች እንደዚህ ይላል፦

በወንጌል አላፍርም፣ ምክንያቱም ለሚያምን ሁሉ ለድነት የሚሆን የእግዚአብሔር ኃይል ነው፤ ይህም በመጀመሪያ ለአይሁድ፣ ቀጥሎም ለአሕዛብ ነው። በወንጌል የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጦአልና፤ ጽድቁም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በእምነት የሆነ ነው፤ "ጻድቅ በእምነት ይኖራል" ተብሎ እንደ ተጻፈው (ሮሜ 1፥16-17)።

የእግዚአብሔር መንግሥት ሕይወት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በእምነት የምንኖርበት ሕይወት ነው። እምነት በእግዚአብሔር መንግሥት ዜጐች አስተሳሰብ፣ ንግግር እና ፀባይ ውስጥ ዘልቆ የሚገባ ነው። እምነት ስለ ዓለም ያለንን አመለካከት የሚቀርጽና ውሳኔዎቻችንን የሚመራ ነው።



የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ብርቱ ነው፤ የሚገጥመውን የጦር መሣሪያ ሁሉ ዐልፎ ይሄዳል።

ተስፋ ሲጠፋ እንኳ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ጸንቶ ይቆያል፤ እግዚአብሔር ለአብርሃም በእርጅናው ወንድ ልጅ እንደሚሰጠው ቃል ገብቶለት ነበር፤ ተስፋው ሳይፈጸምለት ብዙ ዓመት ቢቆይም አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ። እርሱና ሚስቱ ሣራ ልጅ የመውለጃ ዕድሜአቸው ያለፈ ቢሆንም እርሱ በእምነቱ ጸና። የሰው ተስፋ ሲመነምን እምነት ብቻውን ጸንቶ ቆየ፤ ነገር ግን ያ በቂ ነው። ጳውሎስ እንዲህ አለ፦

የዓለምም ወራሽ እንዲሆን አብርሃምና ዘሩ ተስፋን የተቀበሉት በሕግ በኩል አልነበረም፤ ነገር ግን በእምነት ከሆነው ጽድቅ ነው።

ስለዚህ ተስፋው በእምነት መጥቶአል፤ ይኸውም ተስፋው በጸጋ እንዲሆንና ለአብርሃም ዘር ሁሉ ዋስትና ይሆን ዘንድ ነው፤ ይህም በሕግ የእርሱ ለሆኑት ብቻ ሳይሆን በእምነት የአብርሃም ለሆኑትም ነው። እርሱም (አብርሃም) የሁላችን አባት ነው።

ዘርህ እንዲሁ ይሆናል ተብሎ ለእርሱ በተነገረው መሠረት ምንም ተስፋ በሌለበት አብርሃም በተስፋ አምኖ የብዙ ሕዝብ አባት ሆነ። እርሱ የመቶ ዓመት ሰው ሆኖ ሳለ የራሱም ሰውነት ሆነ የሣራ ማሕፀን ምውት እንደነበር እያወቀ በእምነቱ አልደከመም። ይልቁንም በእምነቱ በመጽናት ለእግዚአብሔር ክብርን ሰጠ እንጂ የእግዚአብሔርን ተስፋ አልተጠራጠረም፤ እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ እንደሚፈጽም በሙሉ ልብ እርግጠኛ ነበር። ስለዚህ "ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት" (ሮሜ 4፥13፡ 16፡ 18-22)።

አብርሃም በተፈጥሮ ሁኔታ ልጅና ወራሽ የማግኘት ተስፋ ባልነበረው ጊዜ እምነቱ ከእርሱ ጋር ነበር፣ ስለዚህ በሌላ በምንም መንገድ የማያገኘውን በእምነት አገኘ። ስለዚህ የአንተም ሁኔታ ተስፋ የሌለው ከሆነ በእግዚአብሔር እመን። ካለህበት ችግር መውጫ ምንም መንገድ የማይታይህ ከሆነ፣ በጌታ ተማመን። ጭራሽ በማይጥለውና ለተስፋ ቃሉ ታማኝ በሆነው ጌታ በምትተማመንበት ጊዜ እምነት ያወጣሃል።

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ሞትን እንኳ ዐልፎ ይሄዳል:: በዘመናት ሁሉ ሞት፣ የማይበገርና በመጨረሻው ድል የሚያደርግ የሰው ልጆች ታላቅ ጠላት ሆኖ ቆይቶአል:: ከዚያም ክርስቶስ መጣና ሁሉንም ነገር ለወጠው:: ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ የሞትን ኃይል ሰበረ፣ በእርሱ በሚያምኑት ሰዎች ሕይወት ውስጥ ለዘላለም አሸነፈው:: ጳውሎስ ይህን አስገራሚ ሐቅ ስለተገነዘበ ለቆሮንቶስ ሰዎች እንዲህ በማለት ጻፈላቸው፤

> የሚጠፋው የማይጠፋውን፣ የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና:: የሚጠፋው የማይጠፋውን፣ የሚሞተውም የማይሞተውን በሚለብስበት ጊዜ "ሞት በድል ተዋጠ" ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸማል::
>
> እንዲሁም "ሞት ሆይ ድል መንሣትህ የት አለ?" ሞት ሆይ መንደፊያህስ የት አለ?
>
> የሞት መንደፊያ ኀጢአት ነው፤ የኀጢአትም ኃይል ሕግ ነው:: ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድልን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን (1ቆሮንቶስ 15፥53-57)::

በሕይወት ውስጥ ምንም ዐይነት ፈተና ቢገጥመን፣ የሞት ፈተና እንኳ ቢሆን የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት እኛን በማጽናት ድልን ይሰጠናል:: እምነት ካለን፣ ምንም ነገር ሊያሸንፈንና ከንጉሣችንና ከቡር ከሆነው ከእርሱ መንግሥት ሀብት ሊለየን የሚችል ነገር የለም:: እንደገና ጳውሎስ እንዲህ ይላል፣

> ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን ማን ነው? ችግር ወይስ ሥቃይ ወይስ ስደት ወይስ ረሀብ ወይስ ዕራቁትነት ወይስ አደጋ ወይስ ሰይፍ? ይህም "ስለ አንተ ቀኑን ሙሉ ከሞት ጋር እንጋፈጣለን፤ እንደሚታረዱ በጐች ተቆጠርን" ተብሎ እንደተጻፈ ነው::
>
> ምንም አይለየንም፣ በዚህ ሁሉ በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን:: ይህን ተረድቻለሁ፤ ሞትም ይሁን ሕይወት፣ መላእክትም ይሁኑ አጋንንት፣ ያለውም ይሁን የሚመጣው፣ ወይም ማንኛውም ኃይል፣ ከፍታም ይሁን ጥልቀት፣ ወይም የትኛውም ፍጥረት፣ በጌታችን



> ኢየሱስ ክርስቶስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም (ሮሜ 8፥35-39)::

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ድፍረትን ይሰጠናል፤ ምክንያቱም እኛን የሚቃወመንን ነገር ሁሉ ዐልፈን እንደምንሄድ ስለሚያረጋግጥልን ነው::

## እምነት ሁሉንም ነገር ያስችላል

በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የማይቻል ነገር የለም፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ገደብ ስለሌለው ነው:: እርሱ ሁሉን ዐዋቂ፣ ሁሉን ቻይና ለዘላለም የሚኖር እንዲሁም በማንኛውም ሥፍራ ያለው ማንኛውም ነገር የእርሱ ነው:: "ሁሉም ነገር በእምነት ይቻላል" በሚለው እምነት እንዲጸና፣ ለመንግሥቱ እምነት ድፍረትን የሚሰጠው ይህ የእግዚአብሔር ገደብ የለሽነት ጥልቅ ግንዛቤ ነው:: ኢየሱስ በዚህ ነጥብ ላይ ግልጽ ነበር:: ከዕለታት አንድ ቀን ኢየሱስ የእርሱ ደቀመዛሙርት ሊረዱት ያልቻሉትን፣ ልጁ በርኩስ መንፈስ የተያዘበትን አንድ አባትን አገኘው፤ እርሱም ይህን ዕድል ስለ እምነት ኃይል አንድ ትምህርት ለማስተማር ተጠቀመበት፤

> ከሕዝቡ መካከል አንድ ሰው እንዲህ አለው፣ "መምህር ሆይ፣ ርኩስ መንፈስ አድሮበት ዲዳ የሆነውን ልጄን ወደ አንተ አምጥቼዋለሁ:: በተነሣበት ጊዜ ሁሉ ይጥለዋል፤ አረፋ ይደፍቃል፣ ጥርሱንም ያፋጫል፣ ሰውነቱም ይደርቃል:: ርኩስ መንፈሱን እንዲያወጡት ደቀመዛሙርትህን ጠየቅኋቸው፤ እነርሱ ግን አልቻሉም"::
>
> ኢየሱስ መልሶ "የማታምን ትውልድ ሆይ፤ እስከ መቼ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ፣ እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ ልጁን ወደ እኔ አምጡት" አላቸው::
>
> ሰዎቹም ወደ እርሱ አመጡት:: ርኩስ መንፈሱም ኢየሱስን ባየው ጊዜ ልጁን ወዲያውኑ አንዘፈዘፈው:: እርሱም መሬት ላይ ወድቆ በመንፈራገጥም አረፋ ይደፍቅ ጀመር::
>
> ኢየሱስም የልጁን አባት፤ "ከያዘው ስንት ጊዜ ነው?" ብሎ ጠየቀው::

> እርሱም እንዲህ አለው "ከሕጻንነቱ ጀምሮ ነው:: ሊገድለው ፈልጐ ብዙ ጊዜ እሳትም ውስጥ ውሀም ውስጥ ይጥለዋል:: የሚቻልህ ከሆነ ራራልን ርዳንም::"
>
> ኢየሱስም "የሚቻልህ ከሆነ አልህ? ለሚያምን ሰው ሁሉም ነገር ይቻላል" አለው::
>
> ወዲያውኑ የልጁ አባት "አምናለሁ፣ አለማመኔን ርዳው!" በማለት ጮኸ::
>
> ኢየሱስም ሕዝቡ ወደዚያ እየተንጋጋ በሩጫ መምጣቱን ባየ ጊዜ "አንተ ደንቆሮና ዲዳ መንፈስ ከእርሱ ውጣ! ከእንግዲህም ተመልሰህ እንዳትገባበት አዝሃለሁ!" ብሎ ርኩሱን መንፈስ ገሠጸው::
>
> ርኩሱም መንፈስ እየጮኸ ክፉኛ ካንፈራገጠው በኋላ ከልጁ ወጣ፤ ብዙዎቹ! "ሞቶአል" እስኪሉ ድረስ ልጁ እንደ በድን ሆነ:: ኢየሱስ ግን እጁን ይዞ አስነሣው ልጁም ተነሥቶ ቆመ (ማርቆስ 9፥17-27)::

ኢየሱስ "ለሚያምን ሰው ሁሉም ነገር ይቻለዋል" ከማለት የበለጠ እንዴት ግልጽ ሊሆን ይችላል? ይህ ሀዘንተኛ አባት እምነት ነበረው፤ ነገር ግን ከእምነት ጋር የነበረውን ትግል ደግሞ አልደበቀም:: በልጁ መጥፎ ሁኔታ ለብዙ ዓመታት ተሰቃይቶአል፤ ምናልባትም ከአንድ ጊዜ በላይ በጸሎትና በሌላም መንገድ ፈውስን ለማግኘት ፈልጐአል:: የልጁ አባት፤ እርሱም የኢየሱስ ደቀመዛሙርት የጌታቸውን ያህል የፈውስ ኃይል አላቸው በሚለው ዜና ትንሽ የተስፋ ጭላንጭል አግኝቶ ነበር፤ ነገር ግን እነርሱ ልጁን ሊፈውሱለት ስላልቻሉ ተስፋው ተሟጠጠ:: አሁን እንግዲህ እምነቱ ተናጋ፣ ምክንያቱም እርሱ ምናልባት እምነቱን በኢየሱስ ማንነት ላይ ሳይሆን ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ በሚያደርጉት ነገር ላይ በማሳረፉ ሊሆን ይችላል:: ይሁን እንጂ ይህ አባት ኢየሱስን ባገኘው ጊዜ በትህትናና በግልጽነት ከእምነት ጋር የነበረውን ትግል አመነ፤ ከዚያም እንደገና እምነቱን በኢየሱስ ላይ አደረገና የማይቻለውን ነገር ለማግኘት ቻለ፤ ይኸውም የልጁ ፈውስ ነበር::

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ያሸንፋል፤ ምክንያቱም በሰው ዘንድ ከሚቻለው በላይ አሻግሮ ስለሚመለከት ነው፤ ይህ እምነት የሰውን



የመረዳት ገደብ፣ ትሩፋትና ችሎታ ዐልፎ ራሱን ሁሉን ለሚችለው በማስረከብ የማይቻለውን ነገር ያገኛል:: የመንግሥቱ እምነት በማይወሰነው ዕይታው ምክንያት፣ በሰው ወይም በግዙፍ አካል ለማይታሰቡት ጥቅሞችና ራዕዮች ምንጭ ይሆናል:: የኢየሱስ ደቀመዛሙርት በርኩስ መንፈስ የተያዘውን ልጅ እነርሱ ሊፈውሱት ለምን እንዳልቻሉ ሲጠይቁት ኢየሱስ እንደገና ወደ እምነት አመለከተ:-

> ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርቱም ለብቻቸው ወደ ኢየሱስ ቀርበው "እኛ ጋኔኑን ማስወጣት ያልቻልነው ለምንድን ነው?" ብለው ጠየቁት::
>
> እርሱም እንዲህ አላቸው "እምነታችሁ በማነሱ ምክንያት ነው:: እላችኋለሁ የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል እምነት ቢኖራችሁ 'ይህንን ተራራ ከዚህ ተነሥተህ ወደዚያ ሂድ ብትሉት ይሄዳል' የሚሳናችሁም ነገር አይኖርም" (ማቴዎስ 17፥19-21)::

የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል እምነት ተራራን ካስወገደች ከዚህ ከፍ ያለ እምነት ምን ሊያደርግ እንደሚችል ገምቱ! በምድር ላይ ባለው የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ አንዳንዶቹ ታላላቅ እንቅስቃሴዎች አገልግሎቶችና እርምጃዎች ሙሉ ተጨባጭነትን እስኪያገኙ ድረስ በእምነት የልምላሜ አፈር ውስጥ ባደገ የሐሳብ ዘር የተጀመሩ ናቸው:: የእግዚአብሔር መንግስት እምነት የሰው ራዕይ፣ ጥበብ ወይም አመክንዮ ይቻላል በሚሉት ነገር ላይ የተገደበ አይደለም:: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት በእግዚአብሔር ገደቦች ላይ የተወሰነ ነው:- እርሱ ደግሞ ምንም ገደብ የለውም::

እግዚአብሔር አፈጻጸሙን ሳይጨምር ለሰው ምንም ዐይነት ራዕይ ወይም ምንም ዐይነት ሕልም አይሰጥም:: ስለዚህ እግዚአብሔር በመንፈስህ ውስጥ አንድን ራዕይ ወይም በልብህ ውስጥ አንድን ሕልም አስቀምጦ ከሆነ ችላ አትበለው:: በአሁኑ ሁኔታህ አንፃር ሲታየው ፍጻሜው እጅግ የራቀ ወይም የማይመስል መስሎ ቢታይህ እንኳ የማይቻል ነው ብለህ አትሠርዘው:: ራዕይህን ለጌታ አሳልፈህ ስጥ:: የመንግሥትህን ገንዘብ የእምነትህን ዘር አውጣና በውስጥህ ያስቀመጠውን ራዕይ ወይም ሕልም እንዲፈጽመው ንጉሥህን እመነው:: ጥቂት ጊዜ ምናልባትም ዓመታት ሊወስድ ይችላል፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ትክክለኛ ጊዜ ይፈጸማል:: አስተውል፣ አብርሃም ይስሐቅን ለማግኘት 25 ዓመት ጠበቀ:: በዕብራውያን

ምዕራፍ 11 ውስጥ የተዘረዘሩት ቅዱሳን በሙሉ ያመኑበትን ነገር ሙሉ ፍጻሜውን ሳያዩ ሞቱ:: ይህ ግን እምነታቸው ያለ ቦታው ነበር ማለት አይደለም:: ይህም ባጭሩ እነርሱ እምነታቸውን ያሳረፉት ዕቅድና ዐላማው በቦታና በጊዜ በማይገደበው በርሱ (ባንድዬ) ላይ ነበር ማለት ነው::

## ወሳኙ ምርጫ

የእግዚአብሔር መንግሥት መልእክት የሚሰማውን ሰው ሁሉ ወሳኝ በሆነ ምርጫ ይገናኘዋል:- ይኸውም ካመንህ በሕይወት ትኖራለህ፣ ወይም ካላመንህ ትሞታለህ፤ ካመንህ ብልጽግናና ትርጉም ወዳለው ሕይወት ትገባለህ፣ ካላመንህ ትርጉም ወይም ዐላማ ወደ ሌለው ኑሮ ትወርዳለህ፤ ካመንህ ታሸንፋለህ፣ ካላመንህ ሽንፈትን ትቀበላለህ የሚል ነው::

የአስቆሮቱ ይሁዳ ይህ ምርጫ ቀርቦለት ነበር:: እርሱም ኢየሱስን ለጠላቶቹ አሳልፎ ከሰጠ በኋላ እንኳ ንስሐ ሊገባ ይችል ነበር:: ከሀደቱን መተው፣ ይቅርታን መፈለግና በጌታው ላይ እምነቱን ማደስ ይችል ነበር:: በዚህ ፈንታ ግን እርሱ ባለማመኑ ጸና፣ በጠፋው እምነቱ ምክንያት የሞላበት ተስፋ መቁረጥ ራሱን ወደ ማጥፋት መራው፤

> አሳልፎ የሰጠው ይሁዳም ኢየሱስ እንደተፈረደበት ባየ ጊዜ ተጸጸተ፤ የወሰደውን ሠላሳ ጥሬ ብር ለካህናት አለቆችና ለሕዝቡ ሽማግሌዎች መልሶ በመስጠት "ንጹሕ ሰው አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ" አለ::
>
> እነርሱም "ታዲያ እኛ ምን አገባን? የራስህ ጉዳይ ነው!" አሉት::
>
> ስለዚህ ይሁዳ ብሩን በቤተ መቅደስ ውስጥ ወርውሮ ወጣ:: ሄዶም ራሱን ሰቅሎ ሞተ (ማቴዎስ 27፥3-5)::

የይሁዳ ሕሊና ወዳጁ እያለ ይጠራው የነበረውን ንጹሕ ሰው በመክዳቱ ወደ ሐዘን መራው እንጂ ክርስቶስን የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ አድርጐ እንዲቀበል አላደረገውም:: የይሁዳ እምነት ያለ ቦታው ነበር:: ኢየሱስ መሆን ያለበትንና ማድረግ ያለበትን ነገር በሚመለከት ረገድ ይሁዳ የራሱን ራዕይ ተከተለ፤ ያም ራዕይ ባለመፈጸሙ እምነቱ ሊተርፍ አልቻለም:: ይሁዳ በኢየሱስ ላይ የነበረው እምነት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እምነት ደረጃ አልተሸጋገረም ነበር:: በአስቆሮቱ ይሁዳ ሕይወት የገጠመው አደጋ፣ እምነት ከጠፋ ሕይወት ትርጉም እንደሌለው ያሳየናል::



ስምዖን ጴጥሮስ ከይሁዳ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ምርጫ ቀርቦለት የነበረ ሲሆን ውጤቱ ከዚህ የተለየ ሆነ:: ጴጥሮስ ክርስቶስን ሦስት ጊዜ በገሃድ የካደ እንደመሆኑ መጠን በክህደት ጐዳና ሊያሽቈለቊልና እንደ ይሁዳ ሊሞት ይችል ነበር:: እርሱ ግን ይህን አላደረገም፤ ጴጥሮስ በክርስቶስ ላይ የነበረው እምነት የሚወላውል አልነበረም፤ የወላወለው ድፍረቱ ነበር፤ ፈተናውንም የወደቀው ባለማመኑ ሳይሆን በራሱ ብርታት ላይ ከመጠን በላይ ስለ ተማመነ ነበር:: በውድቀቱ ምክንያት ራሱን ዝቅ ስላደረገ (ይህም ጥበብ ነውና) ጴጥሮስ ከጌታው ጋር ያለውን ግንኙነት ለማደስ ዕድሉን ሞከረ:: በዚያ በገሊላ ባሕር ዳርቻ፤ ከሞት የተነሣው ክርስቶስ፣ ጴጥሮስ ለእርሱ ያለውን ፍቅር እንዲያረጋግጥ ሦስት ዕድሎችን ሰጠው፣ ይህም ለእያንዳንዱ የክህደት ቃል አንድ አንድ ዕድል ማለት ነው:: በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ እምነቱ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት መሆኑን በማሳየት ፈተናውን ዐለፈ፤ ይህ እምነት ዘላቂ የሆነ እምነት፣ የሚጸና እምነት፣ ትርጉምና ዐላማ ወዳለው ሕይወት ጠልቆ የሚገባ እምነት ነበር:: ጴጥሮስ በቀሪው የሕይወት ዘመኑ በድፍረት ሰበከ፤ ብዙ ችግርን አሳለፈ፤ እንዲሁም የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ብቻ ሊሰጠው በሚችል ድፍረት ማንኛውንም ተቃውሞ ተጋፈጠ::

እኛም እንደ ይሁዳና እንደ ጴጥሮስ፣ ወሳኝ የሆነ ምርጫ ለእያንዳንዳችን ቀርቦልናል:- ይህም የማመን ወይም የአለማመን ምርጫ ነው:: በሕይወት ፈተናዎችና መከራዎች በአሸናፊነት ለመውጣት ቁልፉ በእምነት መኖር ነው፤ ይህም ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር ተግባራዊና ገሃዳዊ መግለጫ ነው:: ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር የምናሳየው ለእርሱ በመታዘዝ ነው:: መታዘዝም ማለት እምነት በተግባር ሲታይ ነው:: ለእግዚአብሔር ባለን ፍቅር የተቀጣጠለ እምነት እኛን በተስፋ ይሞላናል፤ ይህም በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ለሚኖረን ዘላለማዊ ዜግነት ልበ ሙሉ የሆነ ማረጋገጫ ነው:: በመጨረሻውም ሁሉን ነገር ሲያልፍ እምነት፣ ተስፋ፤ ፍቅር፣ እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ:-

> ፍቅር ከቶ አይወድቅም ነገር ግን ትንቢት ቢሆን ይሻራል፤ ልሳንም ቢሆን ይቀራል፤ ዕውቀትም ቢሆን ይሻራል:: ምክንያቱም የምናውቀው በከፊል ነው፤ ትንቢት የምንናገረውም በከፊል ነው:: ነገር ግን ፍጹም የሆነው ሲመጣ በከፊል የነበረው ይሻራል .... እንግዲህ እምነት፣ ተስፋ፣ ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፤ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው (1ቆሮንቶስ 13፥8-10፥13)::

ይህ የእምነት፣ የተስፋና የፍቅር የሥስትዮሽ ኅብር በዓለም ላይ ያለንን አሸናፊነት የሚያረጋግጥ ድፍረትን ለሕይወታችን ያስገኝልናል፦

> ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዶአል፤ አባትንም የሚወድ ሁሉ ልጁንም እንደዚሁ ይወዳል። እግዚአብሔርን ስንወድና ትእዛዙቱን ስንፈጽም የእግዚአብሔርን ልጆች እንደምንወድ በዚህ እናውቃለን፤ እግዚአብሔርን መውደድ ትእዛዛቱን መፈጸም ነውና። ትእዛዛቱም ከባድ አይደሉም ምክንያቱም ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋል። ዓለምን የሚያሸንፈውም እምነታችን ነው። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ከሚያምን በስተቀር ዓለምን የሚያሸንፍ ማነው? (1ዮሐንስ 5፥1-5)።

እምነትን የሚኖረን ለምንድነው? ምክንያቱም እርሱ በስኬትና በውድቀት፣ በአሸናፊነትና በተሸናፊነት፣ በሰላምና በትርምስ፣ በልበ ሙሉነትና በፍርሃት፣ በድፍረትና በፈሪነት እንዲሁም በሕይወትና በሞት መካከል ያለ ልዩነት በመሆኑ ነው።

እምነት የሚኖረን ለምንድነው? ምክንያቱም እርሱ የእግዚአብሔር መንግሥት ገንዘብ ስለሆነና ያለ እርሱ ምንም ዐይነት መገበያያ ስለሌለ ነው።

እምነት የሚኖረን ለምንድነው? ምክንያቱም እርሱ ከመከራ በኋላ ሕይወት መኖሩን ስለሚያረጋግጥልን ነው!

### የእግዚአብሔር መንግሥት መርሆች

- ድፍረት የፍርሀት አለመኖር አይደለም። ድፍረት በፍርሀት ፊት ልበ ሙሉነትና ጽኑ እምነት ነው። ድፍረት ከፍርሀት እንቅፋት ባሻገር በሕይወት ማመን ነው።
- የመንግሥቱ እምነት ከተግዳሮቶች አይሸሽም፤ ነገር ግን ለእምነቱ ሕይወት ጠንካራና አስፈላጊ አካል እንደሆነ አድርጐ ይቀበላቸዋል።
- የመንግሥቱ እምነት ድፍረትን ይሰጠናል፤ ምክንያቱም እኛን የሚቃወመንን ዐልፈን እንደምንሄድ ስለሚያረጋግጥልን ነው።



- የመንግሥቱ እምነት የሚገደበው በእግዚአብሔር ገደቦች ነው፤ እግዚአብሔር ግን ምንም ገደብ የለውም።
- እግዚአብሔር ለፍጻሜው የሚረዳ ነገር ጨምሮ ካልሆነ በስተቀር ለሰው ምንም ዐይነት ራዕይ ወይም ሕልም አይሰጥም

## ምዕራፍ ሰባት

## እምነት ከፈተናው ባሻገር፣ ክፍል 1

*"እምነት ማለት እንቁላሎችህን ሁሉ በእግዚአብሔር ቅርጫት ውስጥ ማስቀመጥና፣ ከዚያም ሳይፈለፈሉ በፊት በረከቶችህን መቁጠር ነው"፡፡*

ሮማና ሲ.ካሮል

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ከፈተና ባሻገር ሕይወት መኖሩን ያረጋግጣል፡፡ ስለሆነም እምነት ለስኬታማ ኑሮ እኛ የሚኖረን እጅግ አስፈላጊ ኃይል ነው፡፡ ትምህርት በቂ አይደለም፡፡ የዶክተርነት ማዕርግ በትካዜ ጊዜ ብዙ አይረዳም፡፡ በመፈረካከስ ላይ ላለ ሕይወት የመጽሐፍ ትምህርት ብቻውን ብዙ ጠቃሚነት የለውም፡፡ በግርግርና በትርምስ ጊዜ ሊያድነን የሚችለው እምነታችን ብቻ ነው፡፡

እምነት በሕይወታችን ልበ ሙሉነት ይፈጥርልናል፤ የእኛ የልበ ሙሉነት ደረጃ ካለን የእምነት ደረጃ ጋር የተያዘ ነው፡፡ ልበ ሙሉነት የአዎንታዊ አቀራረብ ዝንባሌ ነው፡፡ አሉታዊ በሆነ አካባቢ፤ መሀል ሆኖ በአዎንታዊነት መጽናት እምነትን ይጠይቃል፤ ይህም አሉታዊ የሆኑት ነገሮች ጊዜያዊ ስለሆኑ ጠቅላላውን ሁኔታ የሚያንፀባርቁ አለመሆናቸውን መገንዘብ ነው፡፡ በአደጋ ፊት ፈገግታን ለማሳየት የሚችል የእምነት ሰው ብቻ ነው፡፡ በማዕበል ውስጥ ጸጥ ለማለት የሚችል የእምነት ሰው ብቻ ነው፡፡ በአሉታዊ ሁኔታዎች መሀል ውስጥ በመልካም አስተሳሰብ ለመጽናት የሚችል የእምነት ሰው ብቻ ነው፡፡

ስለዚህ፣ ከዚህ በፊት እንዳየነው እምነታችን የሚገለጠው በሚያጋጥመው ፈተና ውስጥ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ፈተና የእምነታችንን ጥራትና ጥልቀት ይገልጣል፡፡ ስለ እምነታችን በጉራ መናገር ማንንም አያስደንቅም፤ እምነታችን የሚረጋገጠው በተግዳሮት መሀል ውስጥ ነው፡፡ እግዚአብሔር ፈተናን የሚፈቅደው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ፈተና የተኛውን እምነታችንን ቀስቅሶ ንቁ እንዲሆን ያደርገዋል፤ ከዚያም በእያንዳንዱ የሕይወታችን ክፍል ራሱን ይገልጣል፡፡ እምነታችን ካልተፈተነ በስተቀር ምን ያህል እንደሆነ ወይም ምን ያህል ጠንካራ እንደሆነ ለማወቅ ፈጽሞ አንችልም፡፡

የእምነታችን ጥንካሬ በምናልፈው ፈተና መጠን ነው፡፡ ደግሞም ልብ በሉ፣ እግዚአብሔር ለማሸነፍ ከምንችለው በላይ እንድንፈተን አይፈቅድም (1ቆሮ 10፥13 ይመልከቱ)፡፡ ይህ ማለት እግዚአብሔር የፈተናዎችን መጠን



ይቆጣጠራል ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር የሚፈቅደውን ፈተና እኛ ራሳችን ከምናመጣው ፈተና ጋር እንዳናምታታ መጠንቀቅ አለብን፡፡ ያዕቆብ፣ የጌታ ወንድም፣ ልዩነቱን እንዲህ በማለት ገልጾታል፦

> በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ምክንያቱም ፈተናን ሲቋቋም፣ እግዚአብሔር ለሚወዱት የሰጠውን ተስፋ የሕይወትን አክሊል ያገኛል፡፡
>
> ማንም ሲፈተን "እግዚአብሔር ፈተነኝ" አይበል፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር በክፉ አይፈትንም፣ እርሱ ማንንም አይፈትንም፤ ነገር ግን እያንዳንዱ የሚፈተነው በራሱ ክፉ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ነው፡፡ ምኞትም ከፀነሰች በኋላ ኀጢአትን ትወልዳለች፤ ኀጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች፡፡
>
> የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፣ አትታለሉ፡፡ በጎ ስጦታና ፍጹም በረከት ሁሉ ከላይ ከሰማይ ብርሃናት አባት ይወርዳሉ፤ በእርሱ ዘንድ መለዋወጥ፣ ከመዞር የተነሣ የሚያርፍ ጥላም የለም (ያዕቆብ 1፥12-17)፡፡

ያዕቆብ በመከራና በፈተና መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነትን አስቀምጧል፡፡ በዚህ ሁኔታ፣ መከራዎች በሕይወታችን የሚያጋጥሙን እግዚአብሔርም እምነታችንን ለማረጋገጥና ለማሳደግ የሚፈቅዳቸው የተለመዱ ፍተሻዎች ናቸው፡፡ ፈተናዎች በራሳችን ኀጢአት ወይም የሞኝነት ተግባርና ውሳኔ ምክንያት በራሳችን ላይ የምናመጣቸው ችግሮች ናቸው፡፡ እነዚህ ነገሮች ካልተገቱ በስተቀር በሕይወታችን ጥፋትን ያመጣሉ፡፡ እነርሱ እድገትን ሳይሆን የባሰ ብልሽትን ያስከትላሉ፡፡

ስለዚህ አንድ ተግዳሮት ወይም ችግር ከሕይወትህ ሲመጣ ከእግዚአብሔር የመጣ ነው ብለህ ከመወሰንህ በፊት በራስህ የተሳሳተ አካሄድ ምክንያት የፈጠርኸው ችግር አለመሆኑን ለማረጋገጥ ራስህን መርምር፡፡ ችግሩ በራስህ ከሆነ ትክክለኛው አካሄድ ኑዛዜና ንስሐ ነው፡፡ በኀጢአትህ ምክንያት የመጣውን ችግር በመታገሥ "ጨዋነት" አይሰማህ፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ራስህን ዝቅ አድርግ፣ ኀጢአትህን ተናዘዝ፤ ከዚያም ይቅርታውን ተቀበል፡፡

በሕይወታችን ውስጥ የፈተናዎችን ምንጭ ለመለየት ያለን ችሎታ ከፈተናዎቹ ባሻገር በስኬታማነት ለመኖር ችሎታችን ወሳኝ ነው። እግዚአብሔር የሚፈቅደው ፈተና እኛ ከፈቀድንለት እኛን የሚገነባና የሚያጠነክር ሲሆን እኛ በራሳችን ያመጣነው ፈተና ግን ያፈርሰናል።

## እምነት በኃይል ላይ እንጂ በድርጊት ላይ አይደለም

የሚሠራ እምነት በትክክለኛ ሥፍራ ላይ የተቀመጠ እምነት ነው። በሌላ አነጋገር፣ የእምነታችን ማረፊያ ሥፍራ - የምናምነው ማን ወይም ምን መሆኑ - በስኬትና በውድቀት፣ እንዲሁም በሕይወትና በሞት መካከል የሚኖር ልዩነት ነው። ከፈተና ባሻገር ለመኖር የሚያስችል እምነት - የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት የሚጠነከረው በእግዚአብሔር ኃይል ባለ ፅኑ እምነት ነው እንጂ በሥራዎቹ አይደለም። ይህንን አስቀድሜ ብዙ ጊዜ ተናግሬአለሁ፣ ነገር ግን እንደገና የምናገረው በጣም አስፈላጊ ስለሆነ ነው። ዛሬ ብዙ አማኞች በድርጊት የተቃኙ ናቸው። አዝናኝ በሆኑ ነገሮች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፣ ስለዚህ በሕይወታቸው የሚኖረው ጥንካሬና የእምነታቸው ቀጣይነት የተመሠረተው እግዚአብሔር በራሳቸው ወይም በቅርብ ወዳጆቻቸው ሕይወት አንድን አስደናቂ ነገር ሲያደርግ ዘወትር በማየት ላይ ነው። እግዚአብሔር አንድ ተጨባጭ፣ በዓይን የሚታይ ነገር ካላደረገ፣ ግራ የሚጋቡና የሚጠራጠሩ ይሆናሉ፤ ከዚያም እምነታቸው ይወላውላል።

ከዚህ ራስን ከማታለልና ከውሸት እምነት ወጥመድ የምንወጣበት መንገድ እምነታችንን በእግዚአብሔር ሥራዎች ላይ ሳይሆን ነገር ግን እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ኃይል  እና መብትም ያለው በመሆኑ ሐቅ ላይ ስናሳርፍ ነው። እግዚአብሔር ሁልጊዜ እኛ በጠበቅነው መንገድ ባይሠራም በእርሱና በኃይሉ ላይ መተማመን ይኖርብናል። እግዚአብሔር ለመሥራትም ላለመሥራትም ሥልጣን አለው፤ ለመርዳትም ላለመርዳትም ሥልጣን አለው፤ አንዳንድ ጊዜ ይህንን እንረሳለን። እምነታችን በእግዚአብሔርና በኃይሉ ላይ መሆን አለበት፤ ምክንያቱም የእርሱ ኃይል ከሥራዎቹ ይበልጥ ዋና ነገር ስለሆነ ነው። የእግዚአብሔር ኃይል በሚታይና በሚጨበጥ ሁኔታ ስላልተገለጠ ብቻ የእርሱ ኃይል የለም ማለት አይደለም።

በእግዚአብሔር ላይ (በኃይሉ ሳይሆን) ያለ እምነት ኃይሉን ያነሳሳዋል። ኢየሱስ ማንነቱን "ለማረጋገጥ" ምልክትን እንዲያደርግ የቀረበለትን ጥያቄ ሁሉ በጽናት ተቃውሞአል፤ ምክንያቱም እንዲህ ያለው ጥያቄ እውነተኛ



እምነት አለመኖሩን የሚገልጽ ስለሆነ ነው። እምነትም በሌለበት ሥፍራ የእግዚአብሔር ኃይል አይገለጥም። በማቴዎስ 13፥58 ኢየሱስ የትውልድ ሥፍራውን ናዝሬትን ለመጐብኘት በሄደ ጊዜ "ባለማመናቸውም ምክንያት ብዙ ታምራትን በዚያ አላደረገም" ይላል። ኢየሱስ ተአምር የሚያደርግ ኃይል አለው፤ ነገር ግን የሕዝቡ አለማመን ኃይሉን ዘጋው። አለማመናቸው ተአምር ሠሪ ወደ ሆነው የእግዚአብሔር ኃይል እንዳይገቡ ከለከላቸው።

እግዚአብሔር ለመሥራትም ላለመሥራትም ሥልጣን አለው። የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት እግዚአብሔር ሲሠራ በማየት ላይ የተመሠረተ አይደለም። የመንግሥቱ እምነት እግዚአብሔር ቢሠራም ባይሠራም በርሱ ላይ ይተማመናል። የመንግሥቱ እምነት በእግዚአብሔር ዝምታ መካከል ያምናል።

አብርሃም ለዚህ ትክክለኛ ምሳሌ ነው። አብርሃም 75 ዓመት ሲሆነው፣ እግዚአብሔር ወንድ ልጅ እንደሚሰጠው ቃል ገባለት። ይስሐቅ ሲወለድ አብርሃም የ100 ዓመት ሰው ነበር። የእግዚአብሔር ተስፋ እስኪፈጸም ድረስ አብርሃም ለ25 ዓመት ቆይቷል። አንተስ? ለምን ያህል ጊዜ ለመቆየት ትፈቅዳለህ? አብርሃም እምነቱን ለ25 ዓመታት ጠበቀ፤ ምክንያቱም ተስፋ የሰጠውን አምላክ ስለ ተማመነ ነው። የእግዚአብሔር ቃል የታመነ እንደሆነ አወቀ፤ እግዚአብሔርም በዚሁ መሠረት ባረከው። ጳውሎስ ይህንን እንዲህ ሲል ገልጾታል፤

> "ዘርህም እንዲሁ ይሆናል" ተብሎ ለእርሱ በተነገረው መሠረት ምንም ተስፋ በሌለበት አብርሃም በተስፋ አምኖ የብዙ ሕዝብ አባት ሆነ። እርሱ የመቶ ዓመት ሰው ሆኖ ሳለ የራሱም ሰውነት ሆነ የሣራ ማሕፀን ምውት እንደነበረ እያወቀ በእምነቱ አልደከመም። ይልቁንም በእምነቱ በመጽናት ለእግዚአብሔር ክብርን ሰጠ እንጂ የእግዚአብሔርን ተስፋ አልተጠራጠረም፤ እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ እንደሚፈጽም በሙሉ ልብ ርግጠኛ ነበር። ስለዚህ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት" (ሮሜ 4፥18-22)።

አብርሃም "የእምነት አባት" መባሉ አያስደንቅም። በዓይኑ ጨርሶ ላላየው ሕፃን ለ25 ዓመት አመነ። በፈተና ውስጥ በልበ ሙሉነት የሚያጸናን እምነት ነው። የሚያስጠብቀው ጊዜ ምንም ያህል ርዝመት ቢኖረውም የአብርሃም እምነት በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ላይ አላወላወለም። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ አብርሃም ለረጅም ዘመን በጠበቀ መጠን እምነቱ እያደር

እየጠነከረ መጣ:: እምነቱን አጽንቶ ያቆየው ምንድነው? አብርሃም "እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ እንደሚፈጽም በሙሉ ልብ ርግጠኛ" ስለነበር ነው:: እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን እንደሚጠብቅ ያለ ጥርጥር አምኖ ነበር::

እንደ አማኞች ለኛ ለድካማችን ምክንያት ከሚሆኑት ታላላቅ ነገሮች አንዱ እምነታችንን እኛ ባለን ኃይል ላይ ማሳረፋችን ነው:: አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ዜሮ የሚያደርገን ምናልባት ለዚህ ይሆናል:: በጴጥሮስ የሆነውን ነገር አስታውሱ:: "ጽኑ ኃይል አለኝ" ብሎ ከተናገረ በኋላ ብዙ ሳይቆይ ወዲያው በሚያዋርድ ሽንፈት ውስጥ ገባ:: ጴጥሮስ እምነቱን ሙሉ በሙሉ በጌታ ላይ መመሥረትን የተማረውና በማንኛውም ፈተና ውስጥ የሚያቆመውን ኃይል ያገኘው በራሱ ላይ የነበረውን አመኔታ ፈጽሞ ካስወገደ በኋላ ነበር:: እግዚአብሔር ለአብርሃም ወንድ ልጅን እንደሚሰጠው ቃል ገብቶለታል:: አብርሃምና ሣራ ሁለቱም አርጅተው ነበር፣ ልጅ የመውለጃ ዕድሜአቸው ዐልፎ ነበር:: የአብርሃምን የወራሽነት ፍላጐት የሚያሟላ ምንም አልነበራቸውም:: እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ካልጠበቀ በስተቀር ሊሆን የሚችል ነገር አልነበረም:: ስለዚህ አብርሃም ለ25 ዓመታት ያለ ማወላወል በእግዚአብሔር አመነና ተስፋው ተፈጽሞ አየ::

እግዚአብሔር ለጥቅማችን ሲል ሙሉ በሙሉ በእርሱ ላይ ወደምንመካበት ሥፍራ ለማምጣት ማንኛውንም ነገር ያደርጋል:: አስፈላጊ ከሆነም ወደ ዜሮ ያስገባናል፤ ይህም እምነታችን ባለን ነገር ላይ ሳይሆን እርሱ "እንዲህ አደርጋለሁ" ባለው ነገር ላይ እንዲሆንና ያንን ነገር ለማድረግ ምንም ያህል ጊዜ ቢያዘገየው በእርሱ ላይ መተማመናችንን እንድንቀጥል ነው::

### የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት የማይቋረጥ ነው

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ባሕርይና ኃይል (ወይም፣ ይልቁንም፣ እምነታችንን የምናሳርፍበትን እርሱን) መረዳት ከጀመርን የመንግሥቱ እምነት የማይቋረጥ መሆኑን ወደ መረዳት እንመጣለን:: በጌታ ላይ የሚታመኑትን ሰዎች ምንም ዐይነት ኃይል፣ ፍልስፍና፣ አስተዳደር ወይም ከሰው የሚመጣ መከራ ሊያሸንፋቸው አይችልም:: ጳውሎስ ይህንን ሐቅ የገለጸበት አገላለጽ ተወዳዳሪ የለውም፤

> እግዚአብሔር ለሚወዱትና እንደ ሐሳቡ ለተጠሩት ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጐ እንዲሠራ እንደሚያደርግላቸው እናውቃለን:: እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን



> መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰናቸው፤ ይኸውም ከብዙ ወንድሞች መካከል እርሱ በኩር እንዲሆን ነው:: አስቀድሞ የወሰናቸውን ጠራቸው፤ የጠራቸውን አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውን አከበራቸው::
>
> ታዲያ ለዚህ ምን እንመልሳለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ሊቃወመን ይችላል? ለገዛ ልጁ ያልሳሳለት ነገር ግን ለሁላችንም አሳልፎ የሰጠው እርሱ ሁሉንስ ነገር ከእርሱ ጋር እንደ ምን በልግስና አይሰጠን? እግዚአብሔር የመረጣቸውን የሚከስ ማን ነው? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፤ ታዲያ የሚፈርድ ማን ነው? የሞተው፣ እንዲሁም ከሞት የተነሣው በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠው ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ እኛ ይማልዳል:: ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን ማን ነው? ችግር ወይስ ሥቃይ ወይስ ስደት ወይስ ረሀብ ወይስ ዕራቁትነት ወይስ አደጋ፣ ወይስ ሰይፍ? ይህም "ስለ አንተ ቀኑን ሙሉ ከሞት ጋር እንጋፈጣለን፣ እንደሚታረዱ በጐች ተቆጠርን" ተብሎ እንደተጻፈ ነው:: ምንም አይለየንም፤ በዚህ ሁሉ በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን (ሮሜ 8፥28-37)::

እግዚአብሔር በክርስቶስ አማካይነት አጽድቆናል:: "መጽደቅ" የሚለው ቃል የሕግ ቃል ነው:: ልብ እንበል፣ የምንነጋገረው ስለ መንግሥትና ስለ አገዛዝ ነው:: መጽደቅ ሕጋዊ መብትን የሚመለከት ነገር ነው:: በእግዚአብሔር መጽደቅ ማለት በእርሱ መንግሥት ውስጥ ያለንን የልጅነትና የዜግነት መብታችንን ሰጥቶናል ማለት ነው:: በመብትነት የእኛ የሆነውን ነገር በጸጋው ሰጥቶናል:: ሁኔታው እንደዚህ በመሆኑ፣ ጳውሎስ ምን እንመልሳለን? ይላል:: ከዚያም ተከታታይ የሆኑ ምላሻቸው የማይጠበቅ ጥያቄዎችን ይጠይቃል::

"እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?" ማንም:: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት የማይቋረጥ ነው::

"ለገዛ ልጁ ያልሳሳለት፣ ነገር ግን ለሁላችንም አሳልፎ የሰጠው እርሱ ሁሉንስ ነገር ከእርሱ ጋር እንደ ምን በልግስና አይሰጠን?" ይሰጠናል:: እግዚአብሔር የሰጠውን፣ ማንም ሰው ሊወስድ አይችልም:: የመንግሥቱ እምነት የማይቋረጥ ነው::

"እግዚአብሔር የመረጣቸውን የሚከስ ማን ነው?" ማንም የለም፡፡ እግዚአብሔር አንድ ጊዜ አጽድቆናል፤ ስለዚህ አሁን በክርስቶስ ላሉት ኩነኔ የለባቸውም (ሮሜ 8፥1 ይመልከቱ)፡፡ የመንግሥቱ እምነት የማይቋረጥ ነው፡፡

"ታዲያ የሚፈርድ ማን ነው"? ማንም የለም፡፡ ይህን ሊያደርግ የሚችል ክርስቶስ ብቻ ነው፤ እርሱ ይህን አያደርግም፤ ምክንያቱም እርሱ የሞተው እኛን ከፍርድ ለማዳን ስለሆነ ነው፡፡ እርሱ በእኛ ላይ በመፍረድ ፈንታ፣ በመንግሥተ ሰማይ በአባቱ ፊት ስለእኛ ይማልዳል፡፡ የመንግሥቱ እምነት የማይቋረጥ ነው፡፡

"ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን ማን ነው?" ማንም የለም፡፡ የእርሱ ፍቅር ዘላለማዊና እስከ መጨረሻው እስከ ፍጥረት ርቀት፣ ከዚያም ዐልፎ የሚሄድ ነው፡፡ የመንግሥቱ እምነት የማይቋረጥ ነው፡፡

"ችግር ወይስ ሥቃይ ወይስ ስደት ወይስ ረሀብ ወይስ ዕራቁትነት ወይስ አደጋ ወይስ ሰይፍ? ምንም፡፡ ከእነዚህ ነገሮች ማንኛቸውም ከክርስቶስ ፍቅር ሊለየን አይችልም፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ በእምነት እነዚህ ነገሮች ወደ እርሱ የበለጠ ያቀርቡናል፡፡ የመንግሥቱ እምነት የማይቋረጥ ነው፡፡

እነዚህ ሁሉ ለእኛ ከሆኑ፣ ጳውሎስ፣ "በዚህ ሁሉ በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን" ብሎ ማወጁ ያስደንቃልን? የመንግሥቱ እምነት የማይቋረጥ ነው፡፡

ከእግዚአብሔር ፍቅር የሚለየን ነገር የለም፤ መከራ፣ ችግር ወይም ስደት እንኳ አይለየንም፡፡ ደግሞም ከእግዚአብሔር ፍቅር የሚለየን ምንም ነገር ስለሌለ የእርሱ ኃይል በውስጣችን እንዳይሠራ የሚከለክል ምንም ነገር የለም፡፡ በጥቂት መከራዎች፣ በትንሽ ችግር ወይም በስደት ውስጥ ልናልፍ እንችላለን፡፡ ይህ ሁሉ ግን እግዚአብሔር እኛን ወደ ብስለት የሚያመጣበት ሂደት ነው፡፡

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ሌሎችን ሰዎች ከችግር ውስጥ ለማውጣት ሲል እኛን በችግር ውስጥ እንድንገባ ይፈቅዳል፡፡ የእኛ ተግባር እነርሱ ይህን እንዴት እንደሚያስተናግዱት መርዳት ነው፡፡ እግዚአብሔር ጳውሎስንና ሲላስን ከእሥር ለማስለቀቅ የመሬት መናወጥን ከማምጣቱ በፊት በፊሊጵሲዩስ በግርፋትና በእሥር ለአንድ ሌሊት አሳለፉ፡፡ ከዚህም የተነሣ፣ ብዙ እስረኞች ነፃ ከመለቀቃቸውም በላይ የወህኒ ጠባቂውና ቤተሰቡ በክርስቶስ አመኑ፡፡ እግዚአብሔር በመከራ ውስጥ እንድንገባ የሚፈቅደው ከዚያ ስንወጣ ሌሎች ብዙ ሰዎችን ከእኛ ጋር ይዘን እንድንወጣ ፈልጐ ሊሆን ይችላል፡፡ የመንግሥቱ እምነት የማይቋረጥ ነው፡፡



### ሁለት ዓይነት እምነቶች

በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ሁለት ዓይነት እምነቶች አሉ፤ እነርሱም በተስፋ ቃሎቹ ላይ ያለ እምነትና በመከራ ውስጥ የሚያልፍ እምነት ናቸው፡፡ ሁለቱም ተገቢ የሆኑ እምነቶች ናቸው፤ ነገር ግን ሁለተኛው ከመጀመሪያው የበለጠ የጥልቀትና የብስለት ደረጃ ያለው እምነት ነው፡፡ በተስፋ ቃሎቹ ላይ ያለው እምነት የአብዛኛውን አማኞችና የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጐችን የእምነት ደረጃ የሚገልጽ ነው፡፡ እነዚህ ከእርሱ ለሚያገኙት ነገር እግዚአብሔርን ለማገልገል የሚወዱና እርሱን የሚያምኑ ሰዎች ናቸው፡፡ አንዳንዶች ምናልባት ራስን ከማገልገል የግብዝነት ሕይወት ተነሣስተው "ያምናሉ"፣ አብዛኞች ግን እግዚአብሔር እርሱን ለሚወዱትና ለሚያገለግሉት የሰጠውን የበረከት ተስፋ ለመቀበል ባላቸው ምኞት ምክንያት ያምናሉ፡፡ በመሠረቱ፣ በዚህ ምንም ስህተት የለበትም፣ ምክንያቱም በርግጥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ብዙ የከበሩ ተስፋዎችን የሰጠ ስለሆነና እነዚህንም መመኘት ምንም ክፋት ስለሌለበት ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከዚህ የበለጠ ብስለት ያለው እምነት መነሻ ምክንያቱ ከዚህ የተለየ ነው፡፡

በእግዚአብሔር ተስፋ ላይ በሚያተኩር እምነት ውስጥ ወደ ኋላ ጐታች ከሆኑት ዋና ዋና ነገሮች አንዱ ተስፋዎቹ እኛ በመረጥነው መርሐ ግብር መሠረት እንዲፈጸሙ ወደሚጠብቅ አስተሳሰብ ውስጥ ለመሹለክ በጣም ቀላል መሆኑ ነው፣ ከዚህም የተነሣ ብዙዎቻችን በቀላሉ ትዕግሥታችን ያልቃል፡፡ ተስፋው እኛ በጠበቅነው ጊዜ ወይም ሁኔታ ካልመጣስ ምን ይሆናል? በእግዚአብሔር መታመንን እንቀጥላለን? ወይስ በተስፋቢስነት እጃችንን ወደ ላይ በማንሣት፣ "ደህና፣ እንግዲህ እምነት የሚሠራ አይመስለኝም" እንላለን? በእግዚአብሔር ላይ ያለን እምነት እርሱ ለእኛ በሰጠው ተስፋ ላይ የተመሠረተ ቅድመ ሁኔታ መሆን የለበትም፡፡ ተስፋዎች በብስኩት ላይ እንዳለ ክሬም ናቸው፤ ተስፋዎች እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ላደረገልን አስደናቂ ነገሮች ተጨማሪ ጣዕም የሚሰጡ ናቸው፡፡ እግዚአብሔርን ራሱን ማግኘት በረከቶቹን ከማግኘት የተሻለ ነው፡፡ ከስጦታዎቹ ይልቅ የስጦታዎቹ ሁሉ ምንጭ ቢኖራችሁ አይሻልም? እርሱ በሚሰጠው ስጦታዎች ራስን ከማርካት ይልቅ ሰጪውን ማወቅ አይሻልምን?

ሁለተኛውና ይበልጥ ጥብቅ የሆነው እምነት በመከራ ውስጥ ያለ እምነት ነው፤ ይህ እምነት በመከራና በችግር መካከል ጸንቶ የሚቆም እምነት ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ ከዳር እስከ ዳር ስንነጋገርበት የነበረው እምነት ሁለተኛው ዐይነት እምነት ነው፡፡ የመንግሥቱ እምነት ማለት በጥራቱና በከፍታው ደረጃ ሁልጊዜ ይህን መሰል እምነት ማለት ነው፡፡ ተስፋዎቹ በመፈጸም ላይ

እስካሉ ድረስ ማመን አንድ ነገር ነው፤ ሁሉም ነገር በመፈራረስ ላይ ባለበት ጊዜ በእምነት መቀጠል ግን ሌላ ነገር ነው:: ማንም ሰው ተጨማሪ ክፍያ (ጉርሻን) ሲያገኝ እምነት ሊኖረው ይችላል:: ማንም ሰው ቋሚ ሥራ ሲያገኝ እምነት ሊኖረው ይችላል:: ማንም ሰው ሁሉም ነገር እርሱ በፈለገው መንገድ ሲከናወንለት እምነት ሊኖረው ይችላል:: ነገር ግን ሥራችሁን ስታጡስ? የመሥሪያ ቤት ፖለቲካ ወይም የአድልዎ አሠራር ለእናንተ የሚገባውን ዕድገት ሳይሰጥ ቢቀርስ? ንብረታችሁ በውስጡ እንዳለ ቤታችሁ ቢቃጠልስ? በበሽታ ወይም በአደጋ ልጃችሁን በሞት ብታጡስ እንዴት ነው?

እነዚህ ነገሮች አንዳንድ ጊዜ ሕይወት በመንገዳችን የሚታስቀምጣቸው ተግዳሮቶች ናቸው:: ምንም ነገር ቢሆን እምነትህን አጥብቀህ ትይዛለህን? እምነትህ በተስፋዎች ላይ የሚያተኩር ከሆነ ይህን ልታደርግ አትችልም:: አንተ በረከቶችን ትጠባበቃለህ፤ ነገር ግን አደጋ በመንገድህ ላይ ይገጥምሃል:: ወደ ላቀ ብልጽግና መሸጋገርን ትጠባበቃለህ፤ ነገር ግን በድንገት የገንዘብ ድህነት ያገኝሃል። በተስፋዎች ላይ ከሚያተኩር እምነት ይልቅ የተሻለ እምነት የሚያስፈልገንም ለዚህ ነው:: መከራን የሚታገስ እምነት ያስፈልገናል፤ ወደ አንበሶች ጉድጓድ የሚሄድ ወይም ወደ እቶን እሳት የሚገባ እምነት ያስፈልገናል፤ ከእኛ ዐሥር ጊዜ የሚበልጠውን ግዙፍ የሚጋፈጥ እምነት ያስፈልገናል፤ በእሥር ቤት ውስጥ ወድቆ መዝሙርን የሚቀሰቅስ እምነት ያስፈልገናል:: ከፈተናዎች ባሻገር ስኬታማ ሆኖ ለመኖር፣ ሁልጊዜ ከሰማይ የገና ስጦታን ከመጠበቅ ያለፈ እምነትን ይጠይቃል:: ለመቆም አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ የሚቆም፣ ለማመን አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ የሚያምን እምነትን ይጠይቃል:: ፈተናን ዐልፎ የሚሄድ እምነት ከኢዮብ ጋር "ቢገድለኝም እንኳ በእርሱ ተስፋ አደርጋለሁ" የሚል እምነት ነው (ኢዮብ 13፥15)::

### እምነት ያለ ዕይታ

በመከራ ውስጥ የፀና እምነት ማለት የመጨረሻው ውጤት ባይታይም እንኳ ለመጨረሻው ውጤት በእግዚአብሔር ላይ መተማመን ማለት ነው:: ጳውሎስ ለቆሮንቶስ አማኞች "ስለዚህ ሁልጊዜ በመታመን እንኖራለን:: በሥጋ እስካለን ድረስ ከጌታ ርቀን እንደምንገኝ እናውቃለን፤ ምክንያቱም የምንኖረው በእምነት እንጂ በማየት አይደለም" በማለት ጻፈላቸው (2ቆሮ 5፥6-7):: ምንም እንኳ ሁሉንም ነገር ባናይም በእግዚአብሔር ላይ መታመን አለብን:: በመንግሥተ ሰማያት በመንፈሳዊው ዓለም ብንሆን ኖሮ ሁሉንም



ነገር ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ለማየት እንችል ነበር:: ነገር ግን አይደለንም፤ እኛ ያለነው በምድር ላይ በሁሉም ነገር መካከል ነው፤ ይህም ሙሉውን ስዕል ለማየት አንችልም ማለት ነው:: ስለዚህ ሙሉውን ስዕል በሚያየው በእግዚአብሔር ላይ መታመን ይኖርብናል:: ይህም በምናየው ሳይሆን በምናምነው ነገር መራመድን ይጠይቀናል፤ በዚህም ሁልጊዜ የማናየውን ነገር ሁሉንም ነገር ለሚያየውና ለሚያውቀው አሳልፈን መስጠትን ይጠይቀናል:: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ማለት ምንም ዐይነት ሁኔታ ዘላቂነት ወይም መጨረሻነት እንደሌለውና ዞሮ ዞሮ ሁሉም ነገር በመንግሥቱ ንጉሥ ቁጥጥር ሥር መሆኑን ማመን ነው::

ይህንን እንደሚከተለው ልግለጸው:: እስቲ በቤተ ሙከራ ውስጥ የጠመዝማዛ መንገድን ችግር ለመፍታት ስለምትሞክር ስለ አንዲት አይጥ አስቡ:: በጠመዝማዛው መንገድ በአንደኛው ጫፍ ላይ አይጧ አለች፤ በሌላው ጫፍ ደግሞ አይብ አለ:: ከጠመዝማዛው መንገድ በውጪ በኩል አንድ ሳይንቲስት ሁሉንም ነገር ይመለከታል:: ሳይንቲስቱ እንደ እግዚአብሔር ነው እንበል፤ እርሱ ጠመዝማዛውን መንገድ ሙሉ በሙሉ በአንድ ጊዜ ለማየት ይችላል፤ እንዲሁም አይጧ ወደ አይቡ ለመድረስ ምን ማድረግ እንደሚያስፈልጋት እያንዳንዱን መጠምዘዣ ያስተውላል:: ይሁን እንጂ፣ አይጧ በአንድ ጊዜ የምታየው የመንገዱን አንድ ትንሽ ክፍል ብቻ ነው:: ለተመልካቹ ሳይንቲስት እንደ መስተዋት ግልጽ የሆነው ጠመዝማዛ መንገድ ለአይጧ ምስጢር ነው:: አይጧ በጠመዝማዛው መንገድ ውስጥ ቀስ በቀስ ደረጃ በደረጃ መጓዝ ይኖርባታል፤ በፊቷ ያለውን ክፍል ስትጨርስ ቀጥሎ ያለውን ክፍል ታያለች:: አይጧ ሁሉንም መንገድ የምታውቀው በመጨረሻው አይቡን ለመብላት ስትችል ነው::

እግዚአብሔር በጠመዝማዛ መንገድ አጠገብ አይጥን ከሚመለከት ሳይንቲስት የበለጠ ነው:: እርሱ አፍቃሪ አባታችን ስለሆነ እንደዚህ ይለናል፣ "እኔ ሙሉውን ስዕል ለማየት እችላለሁ፣ እናንተ ግን አትችሉም፤ ስለዚህ እስከ አሁን በገለጥሁላችሁ መሠረት ተራመዱ፣ ከዚያም ቀጥሎ የምትሄዱበትን እንዳሳያችሁ በእኔ ተማመኑ":: በእምነት መኖር ማለት ሁኔታው ተስፋ የሌለው ቢመስልም እግዚአብሔር በመከራው ውስጥ እንደሚያሳልፈን በእርሱ መተማመን ማለት ነው፣ መንገድ በሌለበት እርሱ መንገድን እንደሚያዘጋጅ ማመን ማለት ነው:: ስለዚህ አንድን ነገር በማትረዳበት ጊዜ አትርበትበት:: እግዚአብሔር ያንን ነገር ይረዳል፤ ይቆጣጠራልም:: በመከራህ ውስጥ ሰላምን ለማግኘት ትፈልጋለህን? ስለዚህ "እኔ አላውቅም፣ እግዚአብሔር ግን ያውቃል" ማለትን ተማር::

ኢየሱስ “ልባችሁ አይጨነቅ በእግዚአብሔር እመኑ፤ በእኔም ደግሞ እመኑ” አለ (ዮሐ 14፥1)። ለምን? ምክንያቱም እርሱ ሙሉውን ስዕል ስለሚያይ ነው። አንድንድ ጊዜ ለስኬት በጣም ቅርብ ነን፤ ነገር ግን አሁንም በፊታችን ግድግዳ ስላለ ልናየው አንችልም። የሚቀረን ሁለት ዙር ብቻ ይሆናል፤ ነገር ግን እኛ በዚያው እናቆማለን (እናቋርጣለን)። በመጨረሻው ስኬትን የማያገኙ ሰዎች ከመጨረሻቸው በፊት የሚያቋርጡ ሰዎች ብቻ ናቸው። መንገድህን ቀጥል፤ በጌታ ላይ መታመንህን ቀጥል፤ ከዚያም ወደ አሰብህበት ሥፍራ ትደርሳለህ። በመጨረሻም፣ ሩጫ ለፈጣኖች ወይም ለጠንካሮች ሳይሆን ነገር ግን ጥለው ለማይሸሹ ነው፣ ምንም ነገር ቢሆን ጉዞአቸውን ለሚቀጥሉ ይሆናል።

ጳውሎስ እኛ የምንመላለሰው በእምነት ነው እንጂ በማየት አይደለም በማለት የተናገረው አዋጅ ከዚህ የሚከተለውን ምሳሌ የመግለጫ ሌላው መንገድ ነው:- “በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፣ በራስህ ማስተዋል አትደገፍ፤ በመንገድህ ሁሉ እርሱን ዕወቅ እርሱም ጐዳናህን ቀና ያደርገዋል” (ምሳሌ 3፥5-6)። የእኛ መረዳት ውሱን ነው፤ ራዕያችንም ሙሉ አይደለም። የሕይወትን ሩጫ በራሳችን ለመሮጥ ብንሞክር መጨረሻችን በጉድጓድ ውስጥ መውደቅ ነው። በሩጫው ላይ ለመቆየትና በውድድሩ ለመጽናት ያለን ብቸኛው መንገድ ጌታ መንገዱን እንዲያሳየን በእርሱ ላይ መታመን ነው።

በእምነት የመመላለስ አንዱ ክፍል ራሳችንን ለመመርመር ክፍት መሆን ነው፤ ይህም ሌላ ዐይነት ፈተና ነው። ስኬታማ የሆኑ ሰዎች ሁልጊዜ ራሳቸውን ይፈትሻሉ፤ ራሳቸውን ይገመግማሉ፤ ወደፊት ምን እንደሚያደርጉ ለማየትም ለዐዲስ ተግዳሮትና ለዐዲስ የሕይወት ደረጃ ራሳቸውን ያዘጋጃሉ። በጥንካሬ ለማደግ ብቸኛው መንገድ ልምምድ ማድረግ፣ በፊት ከነበርንበት ደረጃ ለማለፍ ወደፊት መዘርጋት ነው። እምነትም እንዲሁ ነው። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች “በእምነት መሆናችሁን ለማወቅ ራሳችሁን መርምሩ፣ ራሳችሁን ፈትኑ፣ ከፈር የወጣችሁ ካልሆነ በስተቀር ኢየሱስ ክርስቶስ በውስጣችሁ እንዳለ አታውቁምን?” ይላል (2ቆሮ 13፥5)። በሌላ አነጋገር እምነት እንዳላችሁና እንደሌላችሁ ለማወቅ ከፈለጋችሁ ራሳችሁን ፈትሹ። የእምነታችሁን ጥልቀት ወይም ጥንካሬ ለማወቅ ከፈለጋችሁ ራሳችሁን ፈትሹ። ምን ያህል ለመቋቋም እንደምትችሉ ለማየት ሞክሩ ማለቱ ነው።

እንደ ጳውሎስ ከሆነ ክርስቶስ በውስጥህ መሆኑን የምታውቀው በምታልፈው ፈተና ልክ ነው። ሁልጊዜ ከበድ በሚሉ ፈተናዎች ጥንካሬህን ታዳብራለህ። ከባድ ፈተና ባለፍህ መጠን፣ ጥንካሬህ እየጨመረ ይሄዳል።



ከዚህ የተነሣ፣ ጳውሎስ የሚለው፣ “ወደ ሕይወት ግባ፣ ማንም ለማንሣት የማይሞክረውን ዕቃ አንሣ፤ ከዚያም ትችለው እንደሆነ ለማወቅ ራስህን ፈትን፤ ከቻልኸው ክርስቶስ በአንተ ውስጥ ለመሆኑ ማረጋገጫ” ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት ሕይወትና እምነት ውበት ይህ ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ፈተናን የማይፈራ እምነት ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ የመንግሥቱ እምነት ፈተናው እንዲመጣ የሚያደርግ እምነት ነው። ይህ እምነት በእውነቱ ራሱን የሚፈትን ነው። ፈተናንና መከራን መፍራት የሌለብን ለዚህ ነው፣ ነገር ግን እምነታችንን እንደሚያሳድጉ፣ እንደሚያጠሩና እንደሚያረጋግጡ መልካም አጋጣሚዎች አድርገን መቀበል ያለብንም በዚህ ምክንያት ነው። በመንግሥቱ ውስጥ ገዢዎች ለመሆን የታጨን የእግዚአብሔር ልጆች እንደ መሆናችን መጠን የምናልፈው እያንዳንዱ ፈተና እኛን ትንሽ ጠንከር በማድረግ እግዚአብሔር ወደ ዐቀደልን የብስለት ደረጃ ትንሽ ጠጋ ያደርገናል።

## የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ይጸናል

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ገደብ የሌለው ኃይል ባለው በዘላለማዊው አምላክ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ የማይቋረጥ ነው። ይህ ማለት የመንግሥቱ እምነት በማንኛውም መከራ እየበረታና ማንኛውንም ፈተና እየተቋቋመ ለዘላለም ይጸናል ማለት ነው። ስለ እምነት ጽናት ባሕርይ በምናስብበት ጊዜ፣ በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ከኢዮብ ልምምድ የተሻለ ምሳሌ አናገኝም። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ቀደም ሲል ስለ ኢዮብ አውሥተናል፤ ነገር ግን የኢዮብ ሕይወት በጣም ኃይለኛና አጽናኝ የሆነ ትምህርትን ስለሚሰጠን እንደ ገና ወደ እርሱ መመለስ ግድ ይለናል። የአንተ እምነት የሚጸናው እስከ ምን ድረስ ነው? ኢዮብ ባለፈበት ውስጥ አልፈህ ለመቆም ትችላለህን?

ኢዮብ በዘመኑ እጅግ ከበርቴና የበለጸገ ሰው ነበር፤ በቤተሰብ፣ በንብረትና በሀብት የበለጸገ ሰው ነበር። ደግሞም እግዚአብሔርን ሁልጊዜ የሚያመልክ የእምነት ሰው ነበር። ችግሩ የተከሰተው ከመንግሥተ ሰማያት በወጣ ተግዳሮት ምክንያት ነበር።

> እግዚአብሔርም ሰይጣንን፣ “አገልጋዬን ኢዮብን ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ነቀፋ የሌለበት ቅን፣ እግዚአብሔርን የሚፈራና ከክፋት የራቀ ሰው የለም” አለው።

> ሰይጣንም ለእግዚአብሔር እንዲህ ሲል መለሰለት፡- “ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚፈራው እንዲሁ ነውን? በእርሱና በቤተሰቦቹ ባለው ንብረትስ ሁሉ ዙሪያ ዐጥር ሠርተህለት የለምን? የበጐቹና የላሞቹ መንጋ ምድርን ሁሉ እስኪሞሉ ድረስ የእጁን ሥራ በርከህለታል። እስቲ እጅህን ዘርግተህ ያለውን ሁሉ ንካበት፣ በእርግጥ ፊት ለፊት ይረግምሃል”።
>
> እግዚአብሔርም ሰይጣንን “እነሆ እርሱ ያለው ሁሉ በእጅህ ነው፤ እርሱን ራሱን ግን እንዳትነካው” አለው።
>
> ከዚህ በኋላ ሰይጣን ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ ሄደ (ኢዮብ 1፥8-12)።

ሰይጣን ፈጣን በሆኑ ተከታታይ አደጋዎች ከኢዮብ ሀብቱንና ልጆቹን በመውሰድና ያለውን ሁሉ እንዲያጣ በማድረግ ፍጹም ምስኪን አደረገው። አንተ በድንገት ሁሉንም ነገር ብታጣ ምላሽህ ምን ይሆናል እንደ ኢዮብ ያለ ምላሽ ትሰጣለህን? ኢዮብ አደጋ ሲገጥመው ትእግሥቱን አስመሰከረ፤ በውስጡ ያለውን ማንነት አሳየ፡-

> ኢዮብም ተነሣ፣ ልብሱን ቀደደ፣ ራሱን ተላጨ። በምድርም ላይ ተደፍቶ ሰገደ፤ እንዲህም አለ፣ “ዕራቁቴን ከእናቴ ማሕፀን ወጣሁ፣ ዕራቁቴንም እሄዳለሁ። እግዚአብሔር ሰጠ፣ እግዚአብሔር ነሣ፤ የእግዚአብሔር ስም ቡሩክ ይሁን። በዚህ ሁሉ ኢዮብ አልበደለም፤ በእግዚአብሔርም ላይ ክፉ አልተናገረም (ኢዮብ 1፥20-22)

ኢዮብ በሕይወቱ እጅግ ታላቅ አደጋ በገጠመው ጊዜ አልተነጫነጨም፤ ነገር ግን አመለከ! ከእኛ አብዛኞቻችን በእንዲህ ያለ ሁኔታ ብንሆን በእግዚአብሔር ላይ እንጮሃለን፤ እናጉረመርማለን፣ ጥያቄም እናነሣለን፤ በመጣብን ነገር ግራ እንጋባለን። ለመሆኑ እግዚአብሔር ሁልጊዜ በእኛ ላይ በረከትንና ብልጽግናን ማፍሰስ የለበትምን? ይህ ዛሬ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለ የብዙ ሰዎች አስተሳሰብ ነው፤ ምክንያቱም አንዳንድ ሚዛኑን ያልጠበቀ ትምህርት ከእግዚአብሔር ችግርን ሳይሆን በረከትን ብቻ እንድንጠባበቅ ስለ ተማርን ነው። ይህ ዐዲስ ሁኔታ አይደለም፤ የኢዮብ ሦስት ወዳጆች እንኳን ችግሩ በኀጢአቱ ምክንያት የመጣ ነው ብለው ዐስበው ነበር። ጻድቅ የሆነ



አምላክ ከልጆቹ በአንዱ ላይ እንዲህ ያለ የሚያሰቃይ ችግር ያመጣል ወይም ይፈቅዳል የሚለውን አሳብ ወዳጆቹ ለመቀበል አልቻሉም።

ኢዮብ የእግዚአብሔርን መንግሥት እምነት፣ የሚታገስ እምነት፣ በተግባር አሳየ። ሁሉንም ነገር ያጣ ቢሆንም እግዚአብሔርን አመለከ፤ ምክንያቱም የእርሱ እምነት በነገሮች ላይ ሳይሆን ነገሮቹን በሰጠው አምላክ ላይ ስለ ነበረ ነው። ኢዮብ እምነቱን በበረከቶች ላይ ከማሳረፍ የተሻለ እውቀት ነበረው፤ ምክንያቱም በረከቶች ጊዜያዊ ናቸው። እርሱ ቤትና እርሻ፣ በጐች፣ ፍየሎችና አህዮች ሁሉ ጊዜያዊ መሆናቸውን ተረድቶ ነበር። ቤተሰብ እንኳ ሚስትና ልጆች ጊዜያዊ መሆናቸውን ተረድቷል። ኢዮብ ሁሉም ነገር የእግዚአብሔር እንደሆነ አውቆአል፣ ስለዚህ እግዚአብሔር ለመስጠት መብትና ሥልጣን እንዳለው ሁሉ ለመውሰድም መብትና ሥልጣን እንዳለው አውቆአል። ኢዮብ ያለው ሁሉ የእግዚአብሔር ነበር፤ እግዚአብሔር ለመስጠት ወይም ለመውሰድ የመረጠውን ያደርጋል።

አንተ በእምነትህ ከዚህ ደረጃ ደርሰሃልን? ሁሉንም ነገር ብታጣ እምነትህ ይህን ለመቋቋም ይችላልን? እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንድታጣ ቢፈቅድ እርሱን ታመልከዋለህን? በዚህ ምድር ሌላ በረከት ባይሰጥህ እንኳ እርሱን አምነህ ትከተለዋለህን? የመንግሥቱ እምነት ይህ ነው፤ የሚታገሥና ሁሉን ነገር የሚለውጥ እምነት ይህ ነው። በእግዚአብሔር ላይ ያለህ እምነት ባለህ ነገር ላይ የተመሠረተ ከሆነ፣ ያለህን ነገር ስታጣ እምነትህንም ታጣለህ። የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር በመታመን “በነገሮች” ላይ ያለውን አያያዝ ላላ ያደርጋል።

ኢዮብ ስለ መከራው እግዚአብሔርን እንዳልወቀሰ ደግሞ ተመልከት። “ኢዮብ አልበደለም፤ በእግዚአብሔርም ላይ ክፉ አልተናገረም”። እኛ ነገሮች ሲበላሹብን ስንት ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ እናማርራለን? አንተ በሕይወትህ ላይ ስለሚሆነው ነገር ስንት ጊዜ እግዚአብሔርን ወቅሰሃል? ጌታ ሆይ ይህ ነገር በእኔ ላይ እንዲደርስ ለምን አደረግህ? “ጌታ ሆይ፤ ይህ የደረሰብኝ ምን አጥፍቼ ነው? ለምን ይህን ታደርግብኛለህ?” እንላለን። እግዚአብሔርን ለመክሰስ የምናሳየው ዝንባሌ በውስጠኛው ልባችን እግዚአብሔር እንደሚወደን ወይም እርሱ ሊታመን እንደሚችል ያልተዋጠልን መሆኑን ያሳያል። ይህ ጥርጥር በኤደን ገነት የተጀመረ ነው፤ በዚያን ጊዜ ሰይጣን አዳምና ሄዋን የእግዚአብሔርን መልካምነት እንዲጠራጠሩ በማድረግ ተሳክቶለታል።

እግዚአብሔር ሁልጊዜ መልካም ነው፤ በዘላለማዊ ፍቅሩ ይወደናል። ይህ እውነታ የገባን ከሆነ በሚሆነው በማንኛውም ነገር እርሱን

አንወቅስም:: በዚህ ፈንታ፣ በእርሱ ፍቅርና ሠልካሃነት እንታመናለን፤ እንዲሁም እኛ በወቅቱ ከምናየው የበለጠ ታላቅ ዐላማ እንደሚፈጽም በእምነት እናስተውላለን:: ኢዮብ እምነቱን ባለው ነገር ላይ ወይም በሚያየው ነገር ላይ አልመሠረተም:: ኢዮብ እምነቱን የመሠረተው ጻድቅና ትክክለኛ እንደሆነ በሚያውቀው በእግዚአብሔር ባሕርይና ፀባይ ላይ ነው::

## ምንም ቢሆን ምን እምነት ይኑር

ኢዮብ የመጀመሪያውን የእምነት ፈተና ዐለፈ:: ኢዮብ እግዚአብሔርን ያመለከው (ያገለገለው) ስለ ተቀበለው በረከት ነው በማለት ሰይጣን አጥብቆ ተናገረ:: ሰይጣን የኢዮብን ሀብትና ብልጽግና እንዲወስድበት እግዚአብሔር በፈቀደለት ጊዜም ኢዮብ እግዚአብሔርን ማምለኩን ቀጠለ:: የውድድሩ የመጀመሪያው ዙር ድሉ ለኢዮብ ሆነ:: ስለዚህ ሰይጣን እንደ ገና ሞከረ::

> እግዚአብሔርም ሰይጣንን "አገልጋዬን ኢዮብን ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ነቀፋ የሌለበት፣ ቅን እግዚአብሔርን የሚፈራና ከክፋት የራቀ ሰው የለም ያለ ምክንያት እንዳጠፋው ብትወተውተኝም ይኸው ፍጹምነቱን እንደ ጠበቀ ነው አለው::
>
> ሰይጣንም፣ "ቍርበት ስለ ቍርበት ነው" ሲል መለሰ:: ሰው ለሕይወቱ ሲል ያለውን ሁሉ ይሰጣል፤ እስቲ እጅህን ዘርግተህ ዐጥንቱንና ሥጋውን ዳስስ፤ በእርግጥ ፊት ለፊት ይሰድብሃል::
>
> እግዚአብሔርም ሰይጣንን፣ "እነሆ እርሱ በእጅህ ነው፤ ሕይወቱን ግን እንዳትነካ" አለው::
>
> ከዚህ በኋላ ሰይጣን ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ ሄደ፤ ኢዮብን ከእግር ጥፍሩ እስከ ራስ ጠጉሩ በክፉ ቍስል መታው:: ኢዮብም ገላውን ለማከክ ገል ወሰደ፤ በዐመድም ላይ ተቀመጠ::
>
> ሚስቱም "አሁንም ታማኝነትህን አልተውህምን? ይልቁን እግዚአብሔርን ርገምና ሙት" አለችው::



> እርሱም "እነጋገርሽ እንደማታስተውል ሴት ነው፤ መልካሙን ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ተቀበልን፤ ክፉውንስ አንቀበልምን?" አላት::
>
> በዚህ ሁሉ ኢዮብ በንግግሩ አልበደለም (ኢዮብ 2፥3-10)

አንድ ሰው በማንነቱና በአካሉ ላይ አንድ አደጋ እስካልደረሰበት ድረስ በእግዚአብሔር ላይ ያለውን ታማኝነትና እምነቱን ለመጠበቅ ይችላል ሲል ሰይጣን ተከራከረ:: ነገር ግን ሥጋውን በስቃይ ብትነካው እምነቱን እንደ ጋለ ብረት ይጥለዋል አለ:: ስለዚህ ሰይጣን ኢዮብን ለሁለተኛ ጊዜ እንዲፈትነው እግዚአብሔር ፈቀደለት፤ በዚህ ጊዜ ግን ፈተናው ጤንነቱን በማጥቃት ነበር:: ሰይጣን ኢዮብን ከእግር ጣቱ እስከ ራስ ጠጉሩ ድረስ በሚመግል ቁስል መታው፤ ይህም በእርሱ ላይ ታላቅ ስቃይ ማድረስ ብቻ ሳይሆን ለዓይንም እንዲቀፍ አደረገው:: ይሁን እንጂ በዚህ እንኳ ኢዮብ እምነቱንና ታማኝነቱን በማጽናት እግዚአብሔርን ለመውቀስ እምቢ አለ:: ሚስቱ እንኳ የእግዚአብሔርን መንግሥት እምነት ባለመረዳቷ ታማኝነቱን እንዲተው በመምከር፣ "እግዚአብሔርን ርገምና ሙት" ባለችው ጊዜ፣ ኢዮብ መልሶ "መልካሙን ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ተቀበልን፤ ክፉውንስ አንቀበልምን?" አለ::

መልካሙን ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ተቀበልን፤ ክፉውንስ አንቀበልምን? ይህ ለእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ቁልፍ አስተሳሰብ ነው:: እኛ ከመልካሙ ጋር ክፉ ነገሮችን ለመቀበል ዝግጁ መሆን አለብን፣ በሁለቱም መንገድ በእግዚአብሔር ላይ መተማመን ይኖርብናል:: እግዚአብሔር በሕይወታችን ፈተናዎች እንዲመጡ የሚፈቅደው ሊሰብረን ሳይሆን ሊፈትነን ነው:: እኛ እንድንፈተን የሚፈቅደው ስንወድቅ ለማየት ሳይሆን ለመቆም እምነት እንዳለን ስለሚያውቅ ነው:: ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ እኛ ይህን አናውቀውም፤ ደግሞም በፈተናው ወቅት ራሳችን እስከምናየው ድረስ አናውቀውም::

እንደ ኢዮብ ሁሉ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ያላቸው ሰዎች በፈተና ውስጥ እንኳ ሀቀኝነታቸውን አጽንተው ይይዛሉ:: ሀቀኝነት ማለት ሙሉ በሙሉ የተዋሀደ፤ ከራስ ማንነት ጋር አንድ የሆነ፤ አንድነት፣ በመንፈስ መሆን፣ በአእምሮና በሥጋ ያልተከፋፈለ መሆን ማለት ነው:: ሀቀኝነት ያላቸው ሰዎች የሚናገሩት የሆኑትን ነው፤ የሆኑት የሚናገሩትን ነው:: ፀባያቸው ከቃላቸው ጋር የሚስማማ ሲሆን ብቻቸውንም ሆኑ ከሰው ጋር ሁኔታው ተመሳሳይ ነው:: ከሌሎች ጋር ያላቸው ግንኙነትና ትስስር በሙሉ

የግልጽነትና የእውነተኛነት ባሕርይ የተላበሰ ነው:: ስለ አንተ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ሊባሉ ይችላሉን? ምንም ነገር ምን ቢሆን በእግዚአብሔር የምታምን፤ በመልካም ጊዜና በክፉ ጊዜ በእርሱ የምትታመን፤ ሁሉንም ነገር ብታጣ እርሱን የምታገለግል ታማኝ የሆንህ የእምነት ሰው ነህን?

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት በመልካም ወይም በክፉ ነገር አይታጠፍም:: የመንግሥቱ እምነት መልካም ጊዜንና ክፉ ጊዜን ማስተናገድ ይችላል:: የመንግሥቱ እምነት የተረጋጋ ነው:: ምንም ነገር ምን ቢሆን ለውጥ የለውም:: አንዳንድ ሰዎች የኑሮ ስኬትን ማለፍ አይችሉም:: ለእኛ አንዳንድ ጊዜ ውድቀት ይሻለናል፤ ውድቀት በራሳችን ጥበብ፣ ችሎታና ሀብት ላይ አጥብቀን እንዳንደገፍ ያስተምረናል:: ውድቀት ትህትናን በማስተማር ከራሳችን ይልቅ በእግዚአብሔር ላይ የመታመንን አስፈላጊነት እንድናይ ይረዳናል:: ውድቀትን የምንፈራው እርሱ ቋሚ ሁኔታ ነው ብለን ስለምናስብ ነው:: ውድቀት ከበፊት ይልቅ ጠቢብ ሆነን እንወጣ ዘንድ እምነታችንን ለማሳደግ የሚያገለግል ጊዜያዊ እንቅፋት ነው::

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ችግር እንዲመጣ አይጠይቅም፤ ነገር ግን ከመጣ ደግሞ በማፈር አይሸሽም:: የመንግሥቱ እምነት ምንም ነገር ምን ቢሆን ችግርን ፊት ለፊት በመጋፈጥ ይቆማል፤ ደግሞም ድልን እንደሚያገኝ ይተማመናል፤ ምክንያቱም እምነቱ በማይጥለው አምላክ ላይ ስለሆነ ነው:: የመንግሥቱ እምነት ዓለምን የሚያሸንፍ እምነት ነው::

### የእግዚአብሔር መንግሥት መርሆች

- በሕይወታችን የፈተናዎችን ምንጭ ለማወቅ ያለን ችሎታ ከፈተናው ባሻገር በተሳካ ሁኔታ ለመኖር ላለን ችሎታ ወሳኝ ነው::
- ከፈተና ባሻገር ለመኖር የሚያስችል እምነት የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት የሚጠነክረው በእግዚአብሔር ኃይል ላይ በጸና እምነት እንጂ በሥራዎቹ አይደለም::
- በመከራ ውስጥ ማመን ማለት የመጨረሻውን ውጤት ለማየት በማንችልበት ጊዜ እንኳ ለመጨረሻው ውጤት በእግዚአብሔር ላይ መታመን ነው::
- የመንግሥቱ እምነት፤ ምንም ሁኔታ ቋሚ ወይም የመጨረሻ የሆነ እንደሌለ፣ ግን ሁሉም በመጨረሻው በመንግሥቱ ንጉሥ ግዛት ሥር እንደሆነ ያምናል::



- የመንግሥቱ እምነት ለዘላለም የሚጸና ሲሆን ማንኛውንም መከራ ተሻግሮ የሚሄድና ማንኛውንም ፈተና የሚያልፍ ነው::
- የኢዮብን ጥያቄ አስተውሉ:- "መልካሙን ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ተቀበልን፤ ክፉውንስ አንቀበልምን?"
- የመንግሥቱ እምነት ያላቸው ሰዎች በፈተና ውስጥ እንኳ ሀቀኝነታቸውን አጽንተው ይይዛሉ::

## እምነት ከፈተናው ባሻገር፣ ክፍል 2

*"እምነት ነገሮችን ያስችላል እንጂ ቀላል አያደርጋቸውም።"*

*የማይታወቅ ፀሐፊ*

ምግብ፣ ውሀና ገንዘብ ለምድራዊ ሕይወት አስፈላጊ ነገሮች እንደሆኑ ሁሉ፣ እምነትም ለእግዚአብሔር መንግሥት ሕይወት አስፈላጊ ነገር ነው። ሥጋዊ ሕይወታችንን ለማቆየት ምግብና ውሀ እንፈልጋለን፣ የሚያስፈልገንን ነገር ለመግዛት ደግሞ ገንዘብ ያስፈልገናል። እምነት የእግዚአብሔር መንግሥት ገንዘብ መሆኑን ልብ በሉ፤ ያለ እምነት የእግዚአብሔርን መንግሥት ጉዳይ ልንዋዋል አንችልም። ቅዱስ መጽሐፍም "ጻድቅ በእምነት ይኖራል" የሚለው ለዚህ ነው (ሮሜ 1፥17)። የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት በክርስቶስ የሆነ እምነት የእኛ መንፈሳዊ ምግብ፣ ውሀና ገንዘብ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ "የሕይወት እንጀራ" ነው (ዮሐንስ 6፥35)። እርሱ "የሕይወት ውሀ" ምንጭ ነው (ዮሐ 7፥38)። በእርሱ ላይ ያለ እምነት (የእግዚአብሔር መንግሥት ገንዘብ) ለመንግሥተ ሰማያት ብልጽግናና ሀብት ገደብ የሌለበት በርን ይከፍትልናል፣ ምክንያቱም "ለሚያምን ሰው ሁሉም ነገር ስለሚቻለው ነው" (ማርቆስ 9፥23)።

ስለዚህ አንተ ሀብታም ነህ ወይስ ድሀ? በማንኛውም አገር ውስጥ፣ ድሆች ሰዎች የሚባሉት ትንሽ ወይም ምንም ገንዘብ የሌላቸው ናቸው። እነርሱ ኃይል ወይም ብዙም ተጽእኖ የላቸውም፣ ምክንያቱም የመዋዋያ (የመገበያያ) ገንዘብ (መሣሪያ) ስለሌላቸው ነው። ገንዘብ ባለህ መጠን የበለጠ ትሠራለህ፤ የምታመጣው ተጽእኖ ታላቅ ነው፤ የምትፈጥረውም ልዩነት ከፍተኛ ይሆናል። ብዙ ሀብታም ሰዎች በጐ አድራጊዎች የሚሆኑት፣ የድርጅት መሥራችና የልግስና ድርጅቶች የሚያቋቁሙት በዚህ ምክንያት ነው። እነርሱ ለሕብረተሰቡ አንድ ወሮታ ለመክፈል፣ ገንዘባቸውን በበጐ ሥራ ላይ ለማዋል የሞራል ግዴታ እንዳለባቸው ይሰማቸዋል። እንደ እግዚአብሔር መንግሥት ዜግነታችን እምነታችን ለኛ ሕይወት የዚህ ዐይነት ዋጋ ይኖረዋል። በምድራዊ አገራችን ያለ ገንዘብ ለመኖር ከማንችለው የበለጠ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያለ እምነት ለመኖር ከቶ አንችልም።



### የገንዘብህ ዋጋ ምን ያህል ነው?

ሀብት የሚለካው ገንዘቡ በያዘው ዋጋ ነው። የአንድ አገር አስተዳደር (መንግሥት) ገንዘብ ዋጋውን ካጣ፣ አንድ ሰው ምንም ያህል ገንዘብ ቢኖረው ልዩነት የለውም። ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በኋላ ባሉት ዓመታት የጀርመን መንግሥት ምጣኔ ሀብት (ኢኮኖሚ) ወደቀ። የጀርመን ገንዘብ (ማርክ) ዋጋ በአፍንጫው ተደፋ። በፊት ባለጠጋ የነበሩ ጀርመኖች ያላቸው በሺዎች ወይም በሚሊዮኖች የሚቆጠር ማርክ የሚታተምበትን ወረቀት ያህል እንኳ ዋጋ ባጣ ጊዜ ጭራሽ ባዶአቸውን ቀሩ። በእኛም ዘመን በዚምባቡዌ አገር ተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጽሞአል።

የሀብታችን ምንጭ የሀብታችንን ጥራት ይወስናል። በእምነትም ረገድ እንደዚሁ ነው። የእምነታችን ምንጭ የእምነታችንን ጥራት ይወስናል። በሌላ አነጋገር፣ የእምነታችን ዋጋ በምንጩ አስተማማኝነት ላይ የተመሠረተ ነው። እምነታችን በገንዘብ ላይ ከሆነ፣ እምነታችን የሚቆየው ገንዘቡ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ ብቻ ይሆናል። አንዳንድ ሰዎች የገንዘብ ተገላቢጦሽ ስለ ገጠማቸው ራሳቸውን በራሳቸው አጥፍተዋል። የነበራቸውን ገንዘብ ማጣታቸው እምነታቸውን ወደ ማጣት መራቸው፤ ይህም ደግሞ በተራው ወደ ተስፋ ማጣት መራቸው። ያለ ተስፋ፣ በሕይወት መኖር ዋጋ የሌለው ሆኖ ተሰማቸው። ፈተናው በመጣ ጊዜ፣ እምነታቸውን አስተማማኝ ባልሆነ ምንጭ ላይ ስለ መሠረቱ ወደቁ።

የአንተ የእምነት ምንጭ ምንድነው? የምትታመነው በማን ወይም በምን ላይ ነው? ምንጭህ አስተማማኝ ነውን? የጊዜውንና ከዚያም ባሻገር ያለውን ፈተና ያልፋልን? የእምነትህ ጥራት ከምንጭህ ጥራት ጋር ዐብሮ የሚሄድ ነው፤ ስለዚህ ትክክለኛው ምንጭ እንዳለህ ማረጋገጥ ይኖርብሃል።

እምነት ሁልጊዜ የሚታመንበትን ነገር ይፈልጋል፣ ይህም አንድን ነገር ወይም አንድ ሰው ማለት ነው። እምነታችንን የምናሳርፍበት ነገር የእምነታችንን ብዛት ወይም መጠን ይወስናል። የእምነታችን መጠን እምነቱ ከሚያርፍበት ነገር መጠን አይበልጥም። ገደብ ከሌለው እምቅ ኀይል ጋር የሆነ እምነት ከፈለግን፣ እምነታችንን የምናሳርፍበት ያልተገደበ ችሎታ ያለው የእምነት ማረፊያ ነገር ያስፈልገናል። በአሁኑ ጊዜ በዓለም ዐቀፍ የኢኮኖሚ (የምጣኔ ሀብት) ድቀት ውስጥ እንገኛለን። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች ቤታቸውን፣ ሥራቸውንና በሕይወት ዘመናቸው ያካበቱትን ገንዘብ ዐጥተዋል። የንግድ ሥራዎች አሽቆልቁለዋል ወይም በኪሣራ ተዘግተዋል። ባንኮች ከስረዋል። ዕዳ ያለባቸው ብዙ ባለ ቤቶች የብድሩን

ገንዘብ ከፍያ ባለመፈጸማቸው አበዳሪ ኩባንያዎችን በከፍተኛ የገንዘብ ኪሣራ ላይ ጥለዋቸዋል፡፡ አጠቃላይ የሆነ የምጣኔ ሀብት ጭንቀት በማንኛውም የሕብረተሰብ ደረጃ ሰፍኖ ይታያል፡፡ ለምን? ምክንያቱም አብዛኞቹ ሰዎች አስተማማኝ ነው ብለው ያሰቡት ነገር የሕብረተ ሰብ የምጣኔ ሀብት መዋቅር፣ የሸቀጥ ገበያና የባንክን አያያዝ ጨምሮ እነርሱ እንዳሰቡት አስተማማኝ ሆኖ አልተገኘም፡፡ መሠረቱ ከተናጋ፣ በዚያ መሠረት ላይ ያረፈው ነገር ሁሉ ይናጋል፡፡ እምነታችንን በማይናጋ ነገር ላይ መመሥረት የሚገባንም ለዚህ ነው፡፡

ለሰው ልጆች ሁሉ የጋራ መሠረታዊ ፍላጐቶች ከሆኑት መካከል አንዱ ደህንነት (ሴከዩሪቲ) ነው፡፡ ሁላችንም በሕይወታችን ውስጥ የደህንነት ስሜት እንዲኖረን እንመኛለን፣ ይህም ሕይወታችንን በምንተማመንበት ነገር ላይ ለመመሥረታችን ልበ ሙሉነት እንዲኖረን ነው፡፡ እምነታችን ሥጋት የሌለበት መሆኑ እምነታችን ከሚያርፍበት ነገር ጋር ዐብሮ የሚሄድ ነው፡፡ እምነታችሁን በሥራችሁ ላይ አታሳርፉ፣ ሥራውን ሊታጡ (ሊጠፋ) ይችላል፡፡ እምነታችሁን በባንክ ላይ አታድርጉ፤ ባንኮች ሊወድቁ ይችላሉ፡፡ እምነታችሁን በምድራዊ አስተዳደር (አገዛዝ) ላይ አታደርጉ፤ አስተዳደር ሊለወጥ ይችላል፤ እምነታችሁን በመጋቢው (በቄሱ) ላይ አታድርጉ፤ ውሎ አድሮ በአንድ ምክንያት ተስፋ ሊያስቆርጣችሁ ይችላል፡፡ እምነታችሁን በምልክቶች፣ በድንቆችና በተአምራት ላይ አታድርጉ፤ እነርሱ ጊዜያዊ ናቸው፡፡

በብዙ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሊያሳልፈኝ የቻለውን ትምህርት ከብዙ ዓመታት በፊት ተምሬአለሁ፤ አስቀድሞ ባልጠበቅኸው ነገር ፈጽሞ ተስፋ ልትቆርጥ አትችልም የሚል ነው፡፡ መዝሙረኛው ንጉሥ ዳዊት፣ "እግዚአብሔር ሆይ፣ በአንተ ተተግኛለሁ፤ እንግዲህ እፍረት ከቶ አይድረስብኝ፤ በጽድቅህም ታደገኝ" ብሏል (መዝ 31፥1)፡፡ ብቸኛው አስተማማኝ የእምነት ማሳረፊያ ጌታ እግዚአብሔር እንደሆነ ዳዊት ዐውቆአል፡፡ ሰዎች ይወድቃሉ፣ ነገሮችም ያልፋሉ፤ ዘላለማዊና የማይለወጥ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ በሰዎች መካከል የሚኖረው መተማመን ለስኬታማ ግንኙነት አስፈላጊ ቢሆንም የመጨረሻ እምነታችንን በሌላ በማንም ሰው ላይ ማድረግ ከቶ የለብንም፡፡ ልንታመንበት የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ የእምነታችን ዋስትና እምነታችን ከሚያርፍበት ነገር ጋር ዐብሮ የሚሄድ ነው፡፡ እምነትህን በእግዚአብሔር ላይ አሳርፍ እናም ፈጽሞ ተስፋ አትቆርጥም፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የእምነታችን ጽናት እምነታችን በሚያርፍበት ነገር ጽናት የሚወሰን ነው፡፡ በሌላ አነጋገር እምነታችን የሚያርፍበት ነገር ጽኑ



ከሆነ እምነታችንም ጽኑ ይሆናል፡፡ እምነታችን የሚያርፍበት ነገር የሚንገዳገድ ከሆነ እምነታችንም አብሮ የሚንገዳገድ ይሆናል፡፡ የሚንገዳገድ እምነትም በችግር ጊዜ ይወድቃል፡፡ ባለፉት ቅርብ ወራት በዓለም ዐቀፍ ደረጃ እምነታቸውን ጽኑ ዐለት ነው ብለው ባሰቡት የገንዘብ ገበያ ላይ ያሳረፉ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች እምነታቸው ከፍተኛ መናወጥ ሲደርስበት ተመልክተናል፡፡ ማንኛውም ሰብአዊ ተቋም ለእምነታችን አስተማማኝ ምንጭ ወይም ማሳረፊያ ነገር ሊሆን አይችልም፡፡ ጽናትን ለማግኘት ተፈጥሮአዊ ከሆነው ባሻገር መመልከት ይኖርብናል፡፡ ፈተናን ለማለፍ የሚችል ጽኑ እምነትን ለመገንባት የጽኑ መሠረትን አስፈላጊነት በሚመለከት ኢየሱስ ከሁሉም የተሻለ መግለጫን ሰጥቶአል፡-

> እኔ የምለውን አታደርጉም፤ ታዲያ ለምን "ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ" ትሉኛላችሁ? ወደ እኔ የሚመጣ ቃሌንም ሰምቶ የሚፈጽም ሁሉ ማንን እንደሚመስል ላሳያችሁ፡፡ ቤት ለመሥራት አጥልቆ የቆፈረና በዐለት ላይ መሠረቱን የመሠረተ ሰው ይመስላል፡፡ ጐርፍ በመጣ ጊዜ የውሀ ሙላት ያን ቤት ገፋው በሚገባ ስለ ታነጸም ሊያነቃንቀው አልቻለም፡፡ ቃሌን ሰምቶ የማይፈጽም ግን ቤቱን ያለ መሠረት በዐፈር ላይ የሠራን ሰው ይመስላል፤ የወንዝ ሙላትም ቤቱን በመታው ጊዜ ወዲያው ወደቀ ክፉኛም ፈራረሰ (ሉቃ 6፥46-49)፡፡

የእምነታችን ጽናት በሚያርፍበት ነገር፣ ማለትም በመሠረቱ፣ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ማለት እኛ "አጥልቀን" በመቆፈር በእምነታችን መሠረት በክርስቶስ "በዐለቱ" ላይ መመሥረት አለብን ማለት ነው፡፡ በዚህ መንገድ፣ የሕይወት ማዕበልና የመከራ ጐርፍ በሚያጠቁን ጊዜ ልክ በዐለቱ ላይ እንደተገነባ ዐይነት ጠንካራና የማንነቃነቅ ሆነን በጽናት እንቆማለን፡፡

የአንተ እምነት በምን ላይ ነው ያረፈው? እምነትህን የገነባኸው በምን (ወይም በማን) ላይ ነው? እምነትህን በማይነቃነቅ መሠረት ላይ መሥርተሃልን? ኢየሱስ፣ "በእግዚአብሔር እመኑ" ብሏል (ማርቆስ 11፥22)፡፡ እግዚአብሔር ፍጹም ሊታመን የሚገባውና ፍጹም ጽኑ ነው፡፡ እርሱ ትናንትና፣ ዛሬም ለዘላለምም ያው ነው (ዕብ 13፥8 ይመልከቱ)፡፡ በእርሱ ዘንድ መለዋወጥ ከመዞር የተነሣ የሚያርፍ ጥላም የለም (ያዕቆብ 1፥17)፡፡ እግዚአብሔር ጽኑ ነው፡፡ እግዚአብሔር ጠንካራ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለዘላለም ነው፡፡ በእርሱ ላይ እምነታቸውን የሚያሳርፉትም እንደዚያው ናቸው፡፡

## የማይናወጥ የእግዚአብሔር መንግሥት

የምድር መንግሥታት ይመጣሉ ይሄዳሉ:: ግዛቶች ይነሣሉ ይወድቃሉ:: የእግዚአብሔር መንግሥት ግን ዘላለማዊ፣ ዘላለም የሚኖር፣ ለዘላለም የፀና፣ እንዲሁም በብልጽግናውና በኃይሉ ፍጹም ገደብ የሌለው ነው:: በዚህ ዓለም ውስጥ ጽናት የሌለውንና አላፊ የሆነውን የሕይወትን ሁኔታ ለማምለጥ ብቸኛው መንገድ ከማይናወጠው የእግዚአብሔር መንግሥት ጋር በእምነት መያያዝ ነው:: ቅዱስ መጽሐፍ፤

> ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር ሳይሆን ሕያው በሆነና ጸንቶ በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ከማይጠፋ ዘር ነው:: ምክንያቱም መጽሐፍ እንደሚል “ሥጋ ለባሽ ሁሉ ሣር ነው፤ ክብሩም ሁሉ እንደ ሜዳ አበባ ነው፤ ሣሩ ይጠወልጋል፤ አበባውም ይረግፋል፤ የጌታ ቃል ግን ለዘላለም ይኖራል”:: የተሰበከላችሁም የምሥራች ቃል ይህ ነው (1ጴጥሮስ 1፥23-25) ይላል::

ይህ ዓለምና በውስጡ ያሉት ሁሉ ጠፊዎች ናቸው፤ እነርሱ አንድ ቀን ያልፋሉ:: የእግዚአብሔር መንግሥት ግን ጸንቶ ይኖራል:: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የጽናት ኃይል አለው፤ ምክንያቱም በማይናወጠው የፍጥረታት ንጉሥ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ነው:: ከዚህ የደህንነት፣ የዋስትናና የጽናት ሥፍራ እጅግ ጉጂ የሆኑ ፈተናዎች እንኳ ሊያስለቅቁን አይችሉም:: በተቃራኒው፣ መከራዎችና ፈተናዎች እምነታችንን ለማጠንከርና ለማጥራት የሚያገለግሉ ይሆናሉ፤ የእምነታችን ጥንካሬና ጥልቀት በምናልፋቸው ፈተናዎችና በምናሸንፋቸው እንቅፋቶች ይረጋገጣል::

በዓለማችን ውስጥ ያለው ግርግር፣ ጦርነት ሆነ የምጣኔ ሀብት ወድቀት፣ የግብረ ገብነት ብልሽት ሆነ ማህበራዊ ብጥብጥ፣ የፖሊቲካ ረብሻ ሆነ ወይም ሌላ ነገር፣ መንፈሳዊ ሚዛናችንን ሊያቃውስ ወይም ሰላማችንን ሊነጥቀን አይገባም:: እኛ የምናደርገው፣ ጊዜያዊ ብቻ የሆኑ ነገሮችን መናወጥ ዝም ብሎ መመልከት ነው:: የእኛ ተስፋ የእኛ ርግጠኝነት የተገነባው በማይናወጠው በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ ነው:: የዚህ ሐቅ ዕውቀት ልባችንን በደስታና በምስጋና ሊሞላው ይገባል:: የዕብራውያን ጸሐፊ በዚህ መልክ አስቀምጦታል:-



> እናንተ ግን ወደ ጽዮን ተራራ ወደ ሰማያዊት ኢየሩሳሌም ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ መጥታችኋል:: በደስታ ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት፤ ስማቸው በሰማይ ወደ ተጻፈው ወደ በኩራት ማኅበር ቀርባችኋል:: የሁሉ ዳኛ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ፍጹምነትን ወዳገኙት ወደ ጻድቃን መንፈሶች፣ የዐዲስ ኪዳን መካከለኛ ወደ ሆነው ወደ ኢየሱስ፣ እንዲሁም ከአቤል ደም የተሻለ ቃል ወደሚናገረው ወደ ተረጨው ደም ደርሳችኋል::
>
> የሚናገረውን እርሱን እምቢ እንዳትሉት ተጠንቀቁ:: እነዚያ ከምድር ሆኖ ሲያስጠነቅቃቸው የነበረውን እምቢ ባሉ ጊዜ ካላመለጡ፣ እኛ ከሰማይ የመጣው ሲያስጠነቅቀን ከእርሱ ብንርቅ እንዴት ልናመልጥ እንችላለን? በዚያን ጊዜ ድምጹ ያናወጠው ምድርን ነበር፤ “አሁን ግን ምድርን ብቻ ሳይሆን ሰማያትንም አንድ ጊዜ ደግሞ እናውጣለሁ” ብሎ ቃል ገብቶአል፤ “አንድ ጊዜ ደግሜ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው የማይናወጡት ጸንተው ይኖሩ ዘንድ የሚናወጡት ይኸውም የተፈጠሩት የሚወገዱ መሆናቸውን ነው::
>
> ስለዚህ ከቶ የማይናወጥ መንግሥት ስለምንቀበል እግዚአብሔርን እናመስግን፤ ደግሞም ደስ በሚያሰኘው መንገድ በአክብሮትና በፍርሀት እናምልከው፣ አምላካችን የሚያጠፋ እሳት ነውና (ዕብራውያን 12፥22-29)::

ማንኛውም የተፈጠረ ነገር ሊናወጥ ይችላልና በርሱ አትተማመንበት:: መኪናህ የተፈጠረ ነገር ነውን? ቤትህ የተፈጠረ ነገር ነውን? ሥራህስ እንዴት ነው? የባንክ ሂሳብህስ? እነዚህ ሁሉ የተፈጠሩ ነገሮች ናቸው፤ ስለዚህ ልታጣቸው ትችላለህ:: እግዚአብሔር ሊያናውጣቸውና ሊያስወግዳቸው ይችላል:: ታዲያ አንተ ምን ይተርፍሃል? እግዚአብሔር ይወደናል፣ እንድንታመንበትም ይፈልጋል:: እንደ እውነቱ ከሆነ፣ በጣም ስለሚወደን በራሳችን ወይም ባለን ነገር ላይ እንዳንታመን አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እኛን ወይም ያለንን ነገር ያናውጠዋል:: ይህን የሚያደርገው እምነታችንን በማይናወጠው ላይ እናሳርፍ ዘንድ ነው:: ሊናወጥ የማይችለው ደግሞ እግዚአብሔር ብቻ ነው::

እኛ የኢየሱስ የክርስቶስ ተከታዮች በመሆናችን በማይናወጠው መንግሥት ውስጥ እንኖራለን:: እኛ ከቶ የማይወድቅ፣ የማይነጥፍ፣ የማይከስር፣ ከቶ ረሀብ ወይም ድህነት ወይም በሽታ ወይም አደጋ ወይም ማንኛውም ዐይነት ውድቀት የማያውቀው ግዛት ዜጐች ነን:: በዚህ ዓለም ሳለን እንደዚህ ያሉትን ነገሮች እንለማመዳለን፣ ምክንያቱም በዚህ ምድር ላይ ስንኖር የምንኖረው በእንግድነት አገር ስለሆነ ነው፤ እውነተኛው ቤታችን በሌላ አገር ነው:: ንጉሡ በምድራዊው ዓለም ሰማያዊውን ግዛት ለማስፋፋት በጥብቅ እየሠራ ነው፣ ሰይጣን በኤደን ገነት ከአዳምና ከሄዋን ሥልጣንን ያለ አግባብ በወሰደ ጊዜ የተቀሙትን ግዛት መልሶ እየወሰደ ነው::

እኛ በዚህ ተልእኮ የንጉሡ አምባሳደሮች ነን:: እኛ በምድር ላይ ሳለን እርሱ በሰማያዊ ነገር በጥቂቱ ሲባርከን ልባችን በደስታና በምስጋና ሊሞላ ይገባዋል፤ ይህም በረከት ባልተረጋጋ ዓለም ውስጥ የግል መረጋጋትን እንዲሁም በአካባቢያችን ግርግር እያለ ፍጹም የሆነ ሰላምን ማግኘታችን ነው:: ነገር ግን ሰላማችንና ጽናታችን፣ ባሉን ነፋስ በሚወስዳቸው ነገሮቻችን ላይ የተመሠረተ አይደለም:: ሰላምና መረጋጋት ያገኘነው ልባችን በሌላ ሳይሆን በእርሱ ላይ ስላረፈ ነው::

በዕብራውያን 12፥28 የማይናወጥን የእግዚአብሔር መንግሥት ወደፊት እንደምንቀበል ሳይሆን አሁን በመቀበል ላይ እንደሆንን ይናገራል:: አሁኑኑ የእኛ ነው:: እኛ ሊናወጥ የማይችለውን መንግሥት፣ የሕይወት ዘይቤ፣ ባሕልና ሙሉ ማህበረ ሰብ በመቀበል ላይ ነን:: መኖር እንደሚገባን በምንኖርበት ጊዜ በማይናወጥ በመንግሥቱ እምነት በምንኖርበት ጊዜ እያበደ ባለው ዓለም ውስጥ እኛ እንደዚህ ፀጥና ረጋ እንዲሁም ልበ ሙሉ ልንሆን እንዴት እንደቻልን የቀረው ዓለም እያየ ይደነቃል:: ከዚህ የተነሣ እነርሱም እኛ ያለንን ለማግኘት ይፈልጋሉ:: ቀደም ብሎ ብዙ ጊዜ እንዳልሁት፣ እያንዳንዱ ሰው የእግዚአብሔርን መንግሥት ይፈልጋል፤ ብዙ ሰዎች ግን ይህንን ገና አልተገነዘቡትም:: አንድ ነገር እንደሚፈልጉ ያውቃሉ፤ የሚልጉት ግን ምን እንደሆነ አያውቁትም:: በመላው ዓለም ያሉ ሰዎች የሚያምኑበትን አንድ ነገር፣ የሚታመኑበትን ለሕይወታቸው ሰላምን፣ መረጋጋትን፣ ሚዛናዊነትን፣ ሥነ ሥርዓትንና ትርጉምን የሚሰጣቸውን አንድ ነገር ይፈልጋሉ:: ይህንን ፍላጐት ሊያሟላላቸው የሚችለው የእግዚአብሔር መንግሥት ብቻ ነው::

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ምንም ነገር አይፈራም፤ ምክንያቱም ከቶ በማይወድቀው ወይም በማይሸነፈው ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ነው:: ዓለም በየትኛውም ሥፍራ ሰዎችን አዳክማለች:: በዓለም ውስጥ ያሉ ብዙ



ሰዎች ተቀጥቅጠው፣ ተሰብረው፣ በበሽታና በአደጋ ተጐሳቁለው፣ በሀዘንና በእጦት ተፈረካክሰው እንዲሁም የሕይወት ዘመናቸው (ቀኖቻቸው) የሚያልፉት ፍጹም ተስፋቢስ በሚመስል ሁኔታ ነው:: ሊሠራ በሚችል፣ በሽንፈት ፈንታ ድልን በሚያቀዳጅና ዓለምን ለማሸነፍ በሚያስችላቸው በአንድ ነገር ለማመን ይናፍቃሉ:: እነርሱ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ያለንን ምንም ነገር ቢገጥመን እምነታችን የማይወድቀውን ሰዎች እኛን ማየት ያስፈልጋቸዋል:: በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር መንግሥት ተጨባጭና የሚሠራ መሆኑን ያውቃሉ::

## በፈጣሪ ላይ መታመን

በሰው ሠራሽ ሃይማኖቶችና ፍልስፍናዎች ውስጥ ያለው ከፍተኛ ችግር አስከፊ ድክመታቸው ፍጥረታዊውን ዓለም የመጨረሻው ተጨባጭ ነገር አድርገው መቁጠራቸው ነው:: በሰው ልጆች ታሪክ ብዙ ሕዝቦች በፈጣሪ ፈንታ የተፈጠሩትን ነገሮች እንደ አማልክት የሚያመልኩ ሃይማኖቶችን ተከትለዋል በሠራቸው ፈጣሪ ፈንታ፤ አሣዎችን፣ ወፎችን፣ ድመቶችን፣ በሬዎችን፣ ዛፎችን፣ ውሀንና ማናቸውንም ሌሎች ነገሮች አምልከዋል:: የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት፣ በአንፃሩ የሚያመልከው ፈጣሪውን እንጂ ፍጥረቱን አይደለም:: ይህ አምልኮ ከእግዚአብሔር ፈቃድና ምኞት ጋር የሚስማማ ሲሆን እርሱ እንዲህ ብሎአል፦ "ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኑሩህ:: በላይ በሰማይ ወይም በታች በምድር ካለው ወይም በውሀ ውስጥ ከሚኖሩት ነገሮች በማናቸውም ምስል ለራስህ ጣዖታትን አታብጅ:: አትስገድላቸው ወይም አታምልካቸው" (ዘፀአት 20፥3-5)::

እኛ የሰው ልጆች ልናስወግደው የማንችለው ዝንባሌ አለን፤ በተጨባጭ ነገሮች የማመን ዝንባሌ:: ተጨባጭ የሚባሉ ነገሮች በስሜታችን የምንረዳቸው፣ የምናያቸውና የምንዳስሳቸው ናቸው:: ነገር ግን ውጫዊ ገጽታ አሳሳች ሊሆን ይችላል፤ ነገሮች ሁልጊዜ እኛ እንደጠበቅናቸው ሆነው አናገኛቸውም:: ጥበበኛው ንጉሥ ሰሎሞን እንዲህ ብሎአል፦ "ሌላም ነገር ከፀሐይ በታች አየሁ፤ ሩጫ ለፈጣኖች ውጊያም ለኃያላን አይደለም፤ እንጀራ ለጥበበኞች ወይም ባለጠግነት ለብልሆች ወይም ሞገስ ለዐዋቂዎች አይሆንም፤ ጊዜና ዕድል ግን ሁሉን ያገናኛቸዋል" (መክብብ 9፥11):: ይህ አባባል የዕድል ጉዳይ ቢያስመስለውም፣ የንጉሥ ሰሎሞን ነጥብ ግን በዚህ ዓለም ውስጥ ከእግዚአብሔር ውጭ ምንም ነገር ርግጠኝነት የለውም የሚል ነው:: በዚህ ዓለም ባሉ ነገሮች ላይ እምነታችንን ማሳረፍ የሌለብንም ለዚህ ነው:: ንጉሥ ዳዊትም በቃሉ እንዳረጋገጠው፣ በትክክል ይህን ተረድቶ

"እነዚህ በሰረገላ፣ እነዚያ በፈረስ ይመካሉ፤ እኛ ግን ትምክህታችን የአምላካችን የእግዚአብሔር ስም ነው" አለ (መዝ 20፥7)።

የዳዊትን አመለካከት ለመረዳት፣ በሐሳብ ወደ ኋላ 3,000 ዓመታት መጓዝ አለብን። በዚያን ዘመን፣ ማንኛውም ድል አድራጊ የጦር ጀኔራል ቢያንስ ሁለት ነገሮች ያስፈልጉት ነበር፤ እነርሱም ፈረሶችና ሰረገሎች ነበሩ። ለምን? ምክንያቱም እነርሱ ከዋናዎቹ የውጊያ ዘዴዎች መካከል ቁልፍ ነገሮች ስለ ነበሩ ነው። እግረኛ ወታደሮች ዝግተኞች ነበሩ፤ ሰረገለኞች ግን ጠላትን ለመቅደምና ለመከበብ ፈጣኖች ነበሩ። ካለነርሱ አንድ የጦር ሠራዊት ሽንፈት እንደሚገጥመው የተረጋገጠ ነው። ዳዊት ጐበዝና የሠለጠነ ጦረኛ እንዲሁም የጦረኞች መሪ ነበር። ለነበረው ለወታደራዊ ጥንካሬ የሰረገሎችንና የፈረሶችን ጥቅም በርግጥ ያውቃል። ሆኖም በእግዚአብሔር እንጂ በሰረገሎችና በፈረሶች እንደማይታመን በግልጽ ተናግሮአል። ዳዊት ያገኛቸው ድሎች በእግዚአብሔር ሞገስ እንጂ በወታደራዊ ኃይሉና በውጊያ ችሎታው እንዳልሆኑ አውቋል። በታማኝነቱ እስከጸና ድረስ፣ እግዚአብሔር ድልን እንደሚሰጠው ይተማመን ነበር።

ጌዴዎንም ተመሳሳይ እውነትን ተምሮአል። እርሱ የችቦ መብራትና የሸክላ ማሰሮዎች ብቻ በያዙ 300 ሰዎች መላውን የምዲያማውያንን ሠራዊት አሸነፈ። ይህን ያደረገው እንዴት ነበር? በእግዚአብሔር በመታመንና መመሪያውን በመከተል ነበር። በቀይ ባሕር አካባቢ የነበረው የሙሴና የእስራኤላውያን ሁኔታም ተመሳሳይ ነበር። የግብፅ ሠራዊት ከኋላቸው፣ ቀይ ባሕርም ከፊታቸው ሆኖ የሚሸሹበት መንገድ ስላልነበረ መጥፋታቸው የማይቀር ነበር። ከዚያም ሙሴ በትሩን በውሀው ላይ አነሣ፤ እግዚአብሔርም ባሕሩን ለሁለት ከፈለውና እስራኤላውያን በደረቅ ምድር ተሻገሩ። ግብፃውያን በኋላቸው ሲከተሉአቸው እግዚአብሔር ውሀውን እንደ ገና መለሰውና ግብፃውያን በባሕሩ ውስጥ ሰጠሙ። ይህ ከዚህ በፊት እንዳልሁት፣ ነገሮች ምንም ያህል ተስፋ የሌላቸው ቢመስሉም ሁኔታውን በእግዚአብሔር አንፃር ካላየነው በስተቀር እውነቱን ለማወቅ እንደማንችል የሚያሳይ ነው።

ዳዊት፤ "በፈረሶችና በሰረገሎች አልተማመንም፤ የእኔ እምነት ፈረሱን በሠራው በእግዚአብሔር ላይ ነው፤ የእኔ እምነት ሰረገሎቹ የተሠሩበትን እንጨትና ብረት በሠራው በእግዚአብሔር ላይ ነው። ሰረገሎቹ እንኳ ቢበላሹ የሰረገሎቹ አምላክ ከእኔ ጋር ነው" ብሏል። ዳዊት ብዙ ውጊያዎችን ማሸነፉ ያስደንቃልን? በነገሥታት ታሪክ ውስጥ ዳዊት ከሁሉም በላይ የተሳካለት ንጉሥ ነበር። የእርሱ ስኬት ምሥጢር በወታደሮች ወይም በሰይፍ፣ በፈረሶች ወይም በሰረገሎች አለመታመኑ ነበር። በዚህ ፈንታ፣ ወደ



እግዚአብሔር ጸለየ፤ ራሱን፣ ሠራዊቱንና የውጊያውን ውጤት ለእግዚአብሔር አሳልፎ ሰጠ። ቢያሸንፍ ወይም ቢሸነፍ በእግዚአብሔር ታመነ። መጽሐፍ ቅዱስ ዳዊትን እንደ እግዚአብሔር ልብ የሆነ በማለት የሚገልጸው በዳዊት ውስጥ ከነበረው ከዚህ ከጠራ ባሕርይ ካለው እምነት የተነሣ ነው።

የእናንተ እምነት የት ነው? እምነታችሁን በእግዚአብሔር ላይ ጣሉ። በትዳር አጋራችሁ፣ በወንድ ወይም በሴት ጓደኛችሁ፣ በቤተ ሰባችሁ፣ በንግድ፣ በሥራ፣ በትምህርት ቤት፣ ወይም በባንክ ሂሳብ አትተማመኑ። ዛሬ ወይም ነገ ወይም በሚቀጥለው ቀን ስለሚሆነው ነገር ግድ የለም፤ እግዚአብሔር ተስፋህ ከሆነ ታሸንፋለህ ዋስትና አለህ። እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ከሆነ፣ ማን ይቃወምሃል?

## እምነት በመልካሙና በከፋው ጊዜ

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ማለት በዕለታዊ የሕይወት ዝርዝር ሁኔታዎች ላይ ሳይሆን በትልቁ በእግዚአብሔር ማንነት ላይ ማመን ነው። የኢዮብ ሚስት ይህን አልተረዳችም ነበር። እርስዋ በእግዚአብሔር አተያየት አንፃር ስላለው ሰፊው ሥዕል ምንም ፍንጭ አልነበራትም። እርሷ በአንድ ወቅት ጤነኛና ሀብታም የነበረው ባሏ አሁን በሽተኛና ድሀ የመሆኑን ነበር ያየችው፤ ከዚያም እምነት አይሠራም ከሚል ድምዳሜ ላይ ደረሰች። ባሏንም "እግዚአብሔርን ርገምና ሙት" ያለችው በዚህ ምክንያት ነበር። "እግዚአብሔርን መከተል ጥቅም የለውም፤ የት እንዳደረሰህ ተመልከት፤ ራስህን ገድለህ ለምን አትገላገልም" ማለቷ ነበር። አንድ ነገር ልብ እንበል፤ እርስዋ ያገባችው ሰው መጽሐፍ ቅዱስ በምድር ላይ ሁሉ እጅግ ጻድቅ እንደነበረ የሚገልጸው ሰው ነው። ዐብራው የኖረችው ሰው በየቀኑ የሚጸልይ፣ የሚጾም፣ ዐሥራቱን የሚከፍል እንዲሁም እንከን የሌለውና በጽድቅ የሚኖር ሰው ነበር። አሁን ግን፣ ልጆቻቸውንና ያላቸውን ሀብት ሁሉ ካጡ በኋላ ኢዮብ በሚያሰቃይ ቁስልና እባጭ ተሸፈነ። በምታየው ነገር ላይ ብቻ እምነቷን ለመሠረተች ሴት፣ እግዚአብሔርን ማገልገል ትርጉም የለውም ከሚል ድምዳሜ ላይ መድረሷ ተገቢ ነበር።

የኢዮብ መልስ ዘመን የማይሽረው ነው፤ "መልካሙን ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ተቀበልን፤ ክፋውንስ አንቀበልምን?" አለ (ኢዮብ 2፥10)። ያ ቀላል ጥያቄ ስለ እግዚአብሔር ሉዓላዊነት እርቆ የማስተዋል ሁኔታን ያሳያል። ምንም ነገር ቢሆን ምን እግዚአብሔር አምላክ ነው። በመልካምም ይሁን በክፉ ጊዜ እግዚአብሔር አምላክ ነው። የኢዮብ ሁኔታ "በአንድ ወቅት ሀብታም ነበርሁ፤ አሁን ግን ድሀ ነኝ። በአንድ ወቅት ብዙ ነበረኝ፤ አሁን ግን ምንም የለኝም። በአንድ ወቅት ጤናማ ነበርሁ፤ አሁን

ግን ሕመምተኛ ነኝ:: የነበረኝ ሁሉ እግዚአብሔር የሰጠኝ ነበር:: እርሱ ከፈለገ፣ ሊወስዳቸው ይችላል:: እግዚአብሔርን ገንዘብ ቢኖረኝም ባይኖረኝም እወደዋለሁ:: ሀብት ቢኖረኝም ባይኖረኝም እግዚአብሔርን አገለግላለሁ:: በሕመምም ይሁን በጤንነት በእግዚአብሔር እታመናለሁ" ማለቱ ነበር::

ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ባሕርይ ነው:: የመንግሥቱ እምነት በሙሉ ጽናትና ተመስጦ "በብዙ አደጋዎች፣ ችግሮችና ወጥመዶች ውስጥ ዐልፌ እዚህ ደርሻለሁ፤ እዚህ ያደረሰኝ ጸጋው ብቻ ነው:: ወደ ቤቴም የሚወስደኝ ጸጋው ነው" ብለን እንድንዘምር ልባችንን ያነቃቀዋል:: በአደጋዎች፣ በችግሮችና በወጥመዶች ውስጥ ለማለፍ የሚያስችለን እምነት ነው፤ መልካሙንም ሆነ ክፉውን ጊዜ በእኩል ሚዛን ለመጋፈጥ ኃይል የሚሰጠን እምነት ነው:: ፈተናን ለማለፍና ከዚያም በአንፀባራቂነት ለመውጣት እግዚአብሔር ጸጋውን እንደሚሰጠን የሚያረጋግጥልን እምነት ነው::

"መልካሙን ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ተቀበልን፣ ክፉውንስ አንቀበልምን?" ምን ዓይነት መግለጫ ነው! ነገር ግን "መልካም" የሚለውን ቃል መተርጐም አለብን:: በእግዚአብሔር ዓይን መልካም የሆነው ነገር ምናልባት በእኛ በኩል መልካም ላይሆን ይችላል:: ሁሉም ነገር የእግዚአብሔርን ታላቅ ዐላማ በማገልገሉ ላይ የተመሠረተ ነው:: በሲድራቅ፣ በሚሳቅና በአብድናጐ ላይ እንደሆነው ሁሉ "መልካም" ማለት የዕቶን እሳት ሊሆን ይችላል:: በዳንኤል ላይ እንደሆነው ሁሉ የአንበሶች ጉድጓድ ማለት ሊሆን ይችላል:: በክርስቶስ ላይ እንደሆነው ሁሉ መስቀል ማለት ሊሆን ይችላል:: በእስጢፋኖስ ላይ እንደሆነው ሁሉ በድንጋይ መወገር ሊሆን ይችላል:: በጳውሎስ ላይ እንደሆነው ሁሉ ድብደባ፣ የመርከብ አደጋ መታሰርና የሰማዕትነት ሞት ሊሆን ይችላል:: በፍጥሞ ደሴት በዮሐንስ ላይ እንደሆነው ሁሉ ግዞት ሊሆን ይችላል:: እነዚህ ሁሉ በእግዚአብሔር ዓይን "መልካም" ነበሩ፤ ምክንያቱም የእርሱን ዐላማ አገልግለዋል:: በእያንዳንዱ መከራና ችግር፣ እርሱ ተከበረ፤ የሰው ሕይወት ተለወጠ፤ መንግሥቱ በምድር ላይ ተስፋፋ::

እምላካችን በማንኛውም ጊዜ እኛን ከሚያጋጥመን ችግር ሁሉ በላይ ትልቅ ነው:: የሥራ እጦት ነው? እግዚአብሔር ከዚህ በላይ ትልቅ ነው:: የገንዘብ ድህነት ነው? እግዚአብሔር ከዚህ በላይ ትልቅ ነው:: የምንወደው ሰው የሀሽሽ ወይም የአልኮል መጠጥ ሱሰኛ ሆኖአል? እግዚአብሔር ከዚህ በላይ ትልቅ ነው:: ልጅህ ወህኒ ቤት ገባ? እግዚአብሔር ትልቅ ነው:: የኪራይ ገንዘብ አጣህ? እግዚአብሔር ትልቅ ነው:: የካንሰር በሽታ ነው?



እግዚአብሔር ትልቅ ነው:: በእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ችግርን መቋቋም እንችላለን፤ ምክንያቱም ሁልጊዜ ችግር ጊዜያዊ ስለሆነ ነው:: እግዚአብሔር እንድንጋፈጠው ትጥቅ ያልሰጠን ፈተና ወደ እኛ አይመጣም፤ እኛ ልንሸከመው እንችል ዘንድ እርሱ ጸጋውን የማይሰጥበት ሸክም የለም:: እኛ መመለስ የሚገባን ጥያቄ፤ በእርሱ እንታመናለን? በእርሱ በማያበቃ ፍቅር እንታመናለን? በሕይወታችን እንዲደርስብን የሚፈቅደው ነገር ሁሉ ለእኛ ጥቅምና ለእርሱ ክብር መሆኑን እናምናለን? ነው::

በኢዮብ 2፥10 በዚህ ሁሉ ሥቃይና ማጣት ውስጥ ሆኖ፣ "በዚህ ሁሉ ኢዮብ በንግግሩ አልበደለም" ይላል:: አንዳንዶች ኢዮብን አሉታዊ ሰው ነው በማለት ይከሱታል:: ነገር ግን በሕይወታችን እንደ መልካሙ ሁሉ ክፉውንም የምንቀበል ለመሆናችን እውቅና በመስጠት ረገድ ኢዮብ አሉታዊ አልነበረም፤ እርሱ ሀቀኛ መሆኑ ነበር:: ልዩነቱ ምንድነው? ሀቀኝነት ማለት ምንም እንኳ ገሃዱ ሁኔታ የማያስደስት ቢሆን፣ ሁኔታውን መቀበል ማለት ነው:: አሉታዊነት ማለት ስህተት ለሆነው ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ መነሳትና እርሱን መንቀፍ ነው:: ዛሬ በዓለማችን በአማኞች መካከል እንኳ፣ እጅግ የበዛ አሉታዊነትና እጅግ አነስተኛ ሀቀኝነት ሰፍኖ ይገኛል:: ኢዮብ እንዳደረገው፣ መልካሙን ወይም ክፉውን፣ በረከቱን ወይም ችግሩን ተቀብለን፣ እግዚአብሔር ለእኛ ጥንካሬንና ብስለትን የሚሰጥበት የራሱ መርሃ ግብር መሆኑን ማመን ያስፈልገናል:: የእኛ እምነት ከመልካም ወይም ከክፉ ገጠመኝ በላይ መሆን አለበት::

አንዳንድ ሰዎች በስኬት ማለፍ አይችሉም:: እግዚአብሔር ብዙ ከመስጠቱ በፊት ወደ ከስረት የሚያወርደን በዚህ ምክንያት ነው:: ከዚያም በኋላ የምንረሳው ከሆነ፣ በአንድ ወቅት የከሠርን እንደነበርን ለማስታወስ ሲል እንደ ገና ወደ ከስረት ያወርደናል:: እግዚአብሔር ከሳንቲማችን ይልቅ የበለጠ የሚገደው ለጠባያችን ነው:: እርሱ የፈለገውን ነገር ሊሰጠን ይችላል፣ ጠባይን ግን ሊሰጠን አይችልም:: በፈተናና በመከራ ውስጥ ጠባይን ማዳበር አለብን::

## እምነታችንን መለማመድ

እምነትን ከጠባይ ጋር ለማዳበር አንዱ መንገድ እምነታችንን መለማመድ ነው:: ይህን ስል፣ አስቸጋሪ ሁኔታዎች በገጠሙን ጊዜ ለእግዚአብሔር ምን ዐይነት ምላሽ እንደምንሰጥ ጊዜ ወስደን ማሰብ ወይም "መለማመድ" ማለቴ ነው:: ቤትህ ቢቃጠል፣ ምን ዐይነት ምላሽ ትሰጣለህ? የትዳር ጓደኛህ ወይም ከልጆችህ አንዱ በሞት ቢለይህ፣ ምላሽህ ምን ይሆናል? እምነታችንን

መለማመድ በሕይወታችን ያሉ የተለያዩ ሁኔታዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ካለን ግንኙነት አንጻር ለመገምገም ይረዳናል፡፡ እንዲሁም በመጨረሻው ከእምነት የበለጠ ብርቱ ነገር እንደሌለ እንድናውቅ ይረዳናል፡፡

ኢዮብ በከባድ ፈተና ውስጥ ሊጸና የቻለው እምነትን ለመለማመድ ጊዜ ስለ ወሰደ ነበር፡፡ እርሱ የተናገረውን ተመልከት፡- "የፈራሁት ነገር መጥቶብኛል፤ የደነገጥሁበትም ደርሶብኛል፡፡ ሰላም የለኝም፤ ርጋታም የለኝም ሁከት እንጂ ዕረፍት የለኝም" (ኢዮብ 3፥25-26)፡፡ ኢዮብን የገጠሙት አደጋዎች አንድ ቀን ይደርሱብኛል ብሎ የፈራቸው ነበሩ፡፡ ይህም ማለት፣ ይህ ነገር ሊሆን እንደሚችል ከአንድ ጊዜ በላይ ዐስቦበት ነበር ማለት ነው፡፡ ያለውን ሁሉ የማጣትና በስቃይ ውስጥ የማለፉ ሐሳብ አስፈርቶት ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን ለሚፈራ ሰው እንኳ፣ ይህ ነገር ሊከሰት እንደሚችል ተገንዝቦ ነበር፡፡ ከዚያም በኋላ የተፈራው አደጋ በመጣ ጊዜ፣ በሕይወቱ ውስጥ ሰላምንና ዕረፍትን የሚነሳ ግርግርን ፈጠረበት፡፡ ሆኖም፣ እምነቱን እንዳልወሰደበት ልብ በሉ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ኢዮብ እምነቱን በሚለማመድበት ጊዜ ስለ መጥፎ ሁኔታዎች በሚያስብበት ጊዜ በመልካም ወይም በክፉ፣ በአደጋ ወይም በበረከት፣ በመብዛት ወይም በጉድለት፣ እግዚአብሔር አምላክ እንደሆነና ሊመለክም እንደሚገባው ስለተገነዘበ ነበር፡፡ በሕይወቱ የሚደርስ ምንም ዐይነት ነገር እምነትን ለመተው ምክንያት ሊሆን እንደማይችል ኢዮብ ከድምዳሜ ላይ ደርሶ ነበር፡፡

አንተ መጥፎውን ነገር ስንት ጊዜ ፈርተሃል? በሕይወትህ ስለሚደርሰው አሳዛኝ ነገር ለምትሰጠው ምላሽ ምን ያህል ዐስበህበት ታውቃለህ? በሕይወታቸው መልካምን፣ ብልጽግናንና በረከቶችን ብቻ መጠባበቅ እንዳለባቸው ትምህርት የተሰጣቸው አማኞች አንድ መጥፎ ነገር በሚደርስባቸው ጊዜ ይጠፋሉ፡፡ ለመከራና ለችግር ስላልተዘጋጁ አንዳንድ ጊዜ እምነታቸው ይፈረካከሳል፡፡ አስቀድሞ የዘመመው እምነታቸው ለመከራ ሥፍራ የለውም፡፡

ሊመጡ ስለሚችሉ ከባድ መከራዎችና እንቅፋቶች ማሰብ፣ ሽባ ወደሚያደርግና ወደ ከባድ ፍርሀት የሚያደርስ ካልሆነ በስተቀር አሉታዊ ወይም ጤናማ ያልሆነ ተብሎ ሊጠራ አይችልም፡፡ ለችግር አስቀድሞ መዘጋጀት የብስለት ምልክት ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ቁልፍ ተግባራዊ መርሕ፣ "መልካሙን ተጠባበቅ ለመጥፎው ተዘጋጅ" የሚል ነው፡፡ ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚነግረን፣ ይህ ጥበብ ያለበት አካሄድ ነው፡- "አስተዋይ ሰው አደጋ ሲያይ መጠጊያ ይሻል፤ ብስለት የጐደለው ግን በዚያው ይቀጥላል፣ መከራም ይገኘዋል" ይላል



(ምሳሌ 22፥3)፡፡ ዛሬ ለችግር መዘጋጀት በነገው ላይ የሚኖረውን ውጤት ለማቃለል ይረዳል፡፡

እምነትን መለማመድ ማለት ከእግዚአብሔር የተሰጡ ነገሮች ድንገት ሊናወጡ ስለሚችሉ፣ እምነትህን በነገሮች ላይ ማሳረፍ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ማሳረፍህን ለማረጋገጥ ፍተሻ ማድረግ ማለት ነው፡፡ በእግዚአብሔር የምታምነው ስለ ባረከህ ብቻ ነውን? "በረከቶች" የሚለውን ቃል የምትተረጉመው እንደ መልካሞች፣ እድገቶች፣ እርምጃዎች፣ ብልጽግናዎች አድርገህ ነው ወይስ ዕቶን እሳትንና የአንበሳ ጉድጓዶችን ይጨምራል?

እግዚአብሔር ለአብርሃም "በወንድ ልጅ እባርክሃለሁ" የሚል ተስፋ ሰጠው፤ ነገር ግን ያ በረከት በዚያን ጊዜ የ75 ዓመት ዕድሜ ለነበረው ሰው ለ25 ዓመታት አስጠበቀው፡፡ "ሁሉም ነገር አሁኑኑ ይሁን" በሚለው ባሕል ውስጥ ያደግን ስለሆንን ለእኛ ይህ ሁኔታ እንደ በረከት የሚቆጠር አይመስልም፡፡ ልክ የእርሱ አሳብ እንደ አሳባችን፣ ወይም የእኛ መንገድ እንደ መንገዱ እንዳልሆነ ሁሉ (ኢሳ 55፥8 ይመልከቱ)፣ እግዚአብሔር ስለ በረከት ያለው ትርጉም ከትርጉማችን ጋር ተመሳሳይ አይደለም፡፡ የአብርሃም በረከት ይስሐቅ ብቻ አልነበረም፡፡ እግዚአብሔርን ስለ ተስፋው ፍጻሜ ለ25 ዓመታት ታምኖ መጠበቅን፤ ይህም ለ25 ዓመታት በብስለትና በጥልቀት የሚያድግ እምነትን የሚያካትት ነበር፡፡ የተስፋው ቃል ከተሰጠ በኋላ ይስሐቅ በዘጠኝ ወር ውስጥ ቢወለድ ኖሮ ከአብርሃም የምንማረው ምንም ነገር አይኖረንም ነበር፡፡ አብርሃምን "የእምነት አባት" እንዲሆን ያደረገው የእግዚአብሔር ተስፋ እስኪፈጸም ድረስ ለ25 ዓመታት በትዕግስት መጠበቁ ነው፡፡ በረከቱ፣ በጠቅላላው ለ25 ዓመታት መጠበቅን፣ የዘጠኝ ወር እርግዝናንና የተአምራዊውን ሕፃን መወለድን ያካተተ ጥቅል ነበር፡፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ አብርሃም የማይናወጥ የእምነት ሰው ወደ መሆን ደረጃ ደረሰ፡፡

በአሁኑ ጊዜ በውስጡ እያለፍህበት ያለው ማንኛውም ነገር የሚመለከቱህን ሌሎች ሰዎች የሚጠቅም ይሆናል፡፡ በፈተና ጊዜ በጽናት ቁም፤ ከዚያም እንዲህ ይላሉ፡- "ከሩቅ ሆኜ እመለከትህ እንደነበር ታውቃለህ? እናም በዚህ ሁሉ ውስጥ እንዴት በጽናት ልትቆም እንደቻልህ ለማመን ይቸግረኛል፡፡ በሥራህ ውስጥ በምን ሁኔታ እንዳለፍህ አውቃለሁ፡፡ ያደረጉብህን አውቃለሁ፡፡ ለራሴ እንዲህ አልሁ፤ 'እርሱ በእግዚአብሔር ይታመናል፤ እኛም አሁን እስኪ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚሠራ አሁን እንይ'፡፡ አንተ በዚህ ጫና ውስጥ በዚህ ጊዜ ሁሉ ልትጸና መቻልህን ማመን ያቅተኛል! በእግዚአብሔር ላይ ያረፈ እምነት ሊሠራ እንደሚችል አስተምረኸኛል፡፡ ይህንን እምነት አስተምረኸኝ" ይላሉ፡፡

ይህም የአንተ ምስክርነት ይሆናል።

ሕይወትህ በግርግር ውስጥ ነውን? መከራዎችና ችግሮች የአንተን ሰላም፣ ፀጥታና እረፍት ይሠርቁብሃል? እግዚአብሔር አይተውህም። ሕይወትህ እንዲናወጥ የሚያደርገው እምነትህ የት እንዳለ ለማወቅ ነው፣ ከዚህም በላይ ዋናው ነገር፣ እምነትህ የት እንዳለ ራስህ እንድታውቅ ሊሆን ይችላል። ሰላም በሌለበት እምነት ሊኖርህ ይችላል? በአካባቢህ ሁሉም ነገር በሚናወጥበት ጊዜ አንተ ተረጋግተህ ልትኖር ትችላለህ? ትችላለህ፤ ግን ይህ የሚሆነው እምነትህ በትክክለኛው ሥፍራ ላይ ያረፈ መሆኑን ለማረጋገጥ ስትመረምረው ብቻ ነው፤ ይህም እምነትህ በነገሮች ላይ ሳይሆን ንጉሥና የሁሉ ጌታ በሆነው በፈጣሪ አምላክ ላይ ያረፈ እንደሆነ ነው።

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ቅድመ ሁኔታ የሌለበት እምነት ነው። ይህ እምነት በሚሆነው ወይም በማይሆነው ነገር ላይ የተመሠረተ አይደለም። በበረከቶች ሙላት ወይም በበረከቶች ጉድለት ምክንያት የሚነሣ ወይም የሚወድቅ አይደለም። የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት "እግዚአብሔር ሆይ ይህንን ብታደርግልኝ እወድሃለሁ" ወይም "ጌታ ሆይ፣ ያንን ብታደርግልኝ አገለግልሃለሁ" አይልም። ከቶ አይልም፣ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት "ጌታ ሆይ፣ ምንም ቢሆን ምን እወድሃለሁ፣ አገለግልህማለሁ" ይላል። ይህ በኢዮብ ልብ የነበረ አስተሳሰብ ነበር፤ እርሱም "ቢገድለኝም እንኳ በእርሱ ተስፋ አደርጋለሁ፤ ስለ መንገዴም ፊት ለፊት እከራከረዋለሁ። ኀጢአተኛ በእርሱ ፊት መቅረብ ስለማይችል ይህ ድፍረቴ ለመዳኔ ይሆናል" አለ (ኢዮብ 13፥15-16)። በችግር ውስጥ እንኳ ቢሆን፣ የኢዮብ እምነት በድል አድራጊነት ከዚያ ለመውጣት ተስፋን ሰጠው። ደግሞም እምነት ብቸኛ ተስፋው እንደሆነ ዐውቆአል፤ "ቢገድለኝም እንኳ በእርሱ ተስፋ አደርጋለሁ" ያለውም ለዚህ ነበር። በእግዚአብሔር በመታመኑ፣ ኢዮብ ሁሉንም ነገር አተረፈ እንጂ ምንም ነገር አላጣም።

የኢዮብ የጸና እምነት ጠቀመው። በፈተናው ጸና፣ በመጨረሻም እግዚአብሔር ከበፊቱ ይልቅ ዕጥፍ አድርጎ ባረከው። እዚህ ላይ አንድ ሌላ ቁልፍ የሆነ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት መርሕ እንመለከታለን፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ሁልጊዜ ይሸለማል። እስኪታይ ያስጠብቃል፣ አብርሃም ለ25 ዓመታት ጠበቀ፤ ነገር ግን ይመጣል። የሽልማቱ ዐይነት በባህርዩ ቁሳዊ ሊሆን ወይም ላይሆን ይችላል፤ እግዚአብሔር በታላቅ ሀብት ወይም በቁሳዊ ብልጽግና ላይ ባርከህ ይችላል። ነገር ግን እምነትን ጠብቅ፣ ሩጫውን ሩጥ፤ መልካሙን ገድል ተጋደል፤ ጌታም አካሄድህን ያጸናል። በመንገድህ ይጠብቅሃል፣ በጐዳናህም



ይመራሃል። ጸጋ፣ ኃይል፣ ትርጉምና ዐላማ ወዳለበት ሕይወት ይመራሃል፣ ይህም ሕይወት የተሟላ እምቅ ኃይል ያለበት ሕይወት ነው። የእግዚአብሔር ልጅና የመንግሥቱ ዜጋ እንደ መሆንህ በእምነት መድረሻህን ሙሉ በሙሉ ታውቃለህ።

## የእግዚአብሔር መንግሥት መርሆች

- የእምነታችን ምንጭ የእምነታችንን ጥራት ይወስናል።
- እምነታችን የሚያርፍበት ነገር የእምነታችንን ብዛት ወይም መጠን ይወስናል።
- የእምነታችን ደህንነት እምነታችን ከሚያርፍበት ነገር ጋር የተወሰነ ነው።
- የእምነታችን ጽናት እምነቱ በሚያርፍበት ነገር ጽናት ይወሰናል።
- የመንግሥቱ እምነት ከየዕለት የሕይወት ዝርዝር ጉዳይ በሰፊው የእግዚአብሔር ማንነት ላይ የማመን ጉዳይ ነው።
- የመንግሥቱ እምነት ሁልጊዜ ይሸለማል።

ምዕራፍ ዘጠኝ

## የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ኃይል

*"እምነት የተፈጥሮ ዕውቀት አትመን የሚልህን ነገሮች ማመን ማለት ነው"::*

ጆርጅ ሲቶን

ለጋብቻ ታጭተሃል እንበል:: ለሠርጉ ቀን ጥቂት ሳምንታት ብቻ ቀርቶታል:: ዝግጅቱ ሁሉ ተከናውኖአል፤ ሁሉም ነገር ተገዝቶአል፤ የግብዣ ካርዱም ተሠራጭቶአል:: የአንተም ተስፋና ጉጉት ትኩሳቱ ጨምሯል:: ከዚያም በድንገት እጮኛህ ትሞታለች:: ምን ታደርጋለህ? እንግዲህ አንድን ሰው ሥፍራውን እንዲለቅ፣ በሕይወቱ ተስፋ እንዲቆርጥ፤ ምናልባትም እግዚአብሔርን እንዲረግም የሚያደርገው ይህ ዐይነቱ ገጠመኝ ነው:: "እግዚአብሔር ሆይ፣ ይህ ነገር በእኔ ላይ ለምን ደረሰ? ይህን ያህል በድንጋጤ ውስጥ ልትተወኝ እስከዚህ ርቀት ለምን አመጣኸኝ?" ሳትል አትቀርም::

ለነገሩ ይህ እውነተኛ ታሪክ ነው:: አንድ ሰው አንዲት ውብ ወጣት ሴት ሊያገባ ዐጭቶ ነበር:: የሠርጉ ዝግጅት በሙሉ አልቆ ሁሉም ነገር ተስተካክሎ ነበር፤ የሠርጉን ቀን ብቻ እየተጠባበቁ ነበር:: ከዚያም ጥቂት ቀናት ብቻ ሲቀሩ፣ እጮኛው በድንገት ታመመችና ሞተችበት:: ሀዘንተኛው እጮኛዋ ወደ ከባድ ትካዜ ውስጥ ገባ:: እንዲያውም ራሱን ለማጥፋት ያስብ ጀመር:: ሀፍረትም ተሰማው:: የጓደኞቹንና የቤተሰቡን ፊት የሚያየው እንዴት ነው? ከዚህ አሰቃቂ አደጋ እንዴት ሊወጣ ይችላል?

የሚወጣ አልመሰለም:: የሀዘን ስሜቱ በጣም ከባድ ከመሆኑ የተነሣ ሕክምና ወደሚያገኝበት ወደ አእምሮ ሆስፒታል ገባ:: ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ጥቂት ተሻለው:: ከሁለት ወራት በኋላም ከዚያ ሁኔታው አገግሞ ከሆስፒታል ወጣ:: ፍቅሩን ቀበረና እንደ ቀድሞው ኑሮውን ቀጠለ:: በመጨረሻም ሌላ አገባና ቤተሰብ መሠረተ:: ነገር ግን ወጣት እንደ መሆኑ መጠን፣ በዚያ የችግር ወቅት ሥፍራውን ሊለቅቅ፤ ራሱን ለማጥፋት ሁሉንም ነገር ለመተው ተቃርቦ ነበር::

ያ ሰው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት እስከ መሆን ደረሰ:: ስሙ አብርሃም ሊንከልን ነበር:: ዛሬም በአሜሪካ ታሪክ ውስጥ እጅግ ታላቁና የተሳካለት ፕሬዚዳንት ሆኖ ይታወሳል:: አውዳሚ በሆነ የእርስ በርስ ጦርነት ወቅት አሜሪካ እንዳትበታተን ጠብቆ በአንድነት እንድትቆይ መርቶአታል:: ባሪያዎችን ነፃ አውጥቷል፤ ሊንከን በእውነትም ታላቅ ሰው ነበር:: ይሁን



እንጂ እርሱ ሕይወቱን በቀላሉ በአእምሮ ሆስፒታል ውስጥ ሊያሳልፍ ይችል ነበር:: እምነት ግን ከዚያ አዳነው::

ከሊንከን አነስ ባለ ሁኔታ ታዋቂነት የነበረው ሌላ አንድ ሰው ተመሳሳይ የሆነ የሀዘን ገጠመኝ አጋጥሞታል:: ለሠርጉ ጥቂት ቀናት ብቻ ሲቀረው የጆሴፍ ስክሪቬን እጮኛ በጀልባ አደጋ ሰጠመች:: ይህ ወጣት ለሠርጉ ጥቂት ቀን ሲቀረው እጮኛውን በሞት ሲያጣ ይህ ለሁለተኛው ጊዜ በመሆኑ ሁኔታውን የባሰ አስከፊ አድርጎት ነበር:: በጥልቅ ሀዘን ውስጥ ሳለ ራሱን በእምነት አጠናክሮ ከዚህ የሚከተለውን መዝሙር ጻፈ:-

ኢየሱስ እንዴት ያለ ወዳጅ ነው

ኀጢአታችንንና ሀዘናችንን የሚሸከም!

እንዴት ያለ መብት ነው

ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር በጸሎት ማስረከብ!

ምን ያህል ሰላም እናጣለን፣

ምን ያህል አላስፈላጊ ስቃይ እንሸከማለን፣

ሁሉንም ነገር በጸሎት

ለእግዚአብሔር ባለማስረከባችን::

መከራና ፈተና አለብን ወይ?

አንድ ችግር አለብን ወይ?

ተስፋ መቁረጥ የለብንም፤

ለጌታ በጸሎት አስረክቡት::

እንዲህ ያለ ታማኝ ወዳጅ ከየት እናገኛለን?

ሀዘናችንን ሁሉ የሚሸከም?

ኢየሱስ ድካማችንን ሁሉ ያውቃል፤

ለጌታ በጸሎት አስረክቡት::

ሸክም ከብዶብን ደክመናል ወይ?

የጭንቀት ሸክም በዝቶብናል ወይ?
ውዱ አዳኝ አሁንም ምሽጋችን ነው
ለጌታ በጸሎት አስረክቡት፡፡
ጓደኞችህ ንቀው ትተውሃል ወይ?
ለጌታ በጸሎት አስረክበው፡፡
በክንዱ ተሸክሞ ይጠብቅሃል፤
በዚያም ሰላምን ታገኛለህ፡፡[1]

ጆሴፍ ስክሪቬን ፈጽሞ አላገባም፤ ነገር ግን በዚህ አስከፊ ስቃይ ውስጥ ያጸናውንና ያሳለፈውን ጌታ በመውደድና በማገልገል ዕድሜውን ፈጸመ፡፡

ሆራቲዮ ጂ. ስፖፎርድ የተባለ አደጋ በአደጋ ላይ የተደራረበበት አሜሪካዊ የሕግ ጠበቃ ነበር፡፡ በ1871 በተከሰተው በታላቁ የቺካጐ የእሳት ቃጠሎ መላውን የቤቱን መዋዕለ ንዋይ አጣ፡፡ በዚያን ወቅት ቤተሰቡን ለዕረፍት ወደ አውሮፓ ለመውሰድ ወስኖ ነበር፤ በዚያውም ደግሞ በወቅቱ በእንግሊዝ አገር በመካሄድ ላይ የነበረውን የዲ.ኤል ሙዲን የወንጌል ስርጭት ዘመቻ ለመርዳት ዐቅዶ ነበር፡፡ በ1873 በህዳር ወር፣ ስፖፎርድ አስቸኳይ የሆነ ሥራ ስለ ያዘው እርሱ ወደ ኋላ ቀርቶ ሚስቱንና አራት ሴቶች ልጆቹን በቅድሚያ ላካቸው፤ ዐቅዱ እነርሱን በኋላ ሊገናቸው ነበር፡፡ ይህም ሦስተኛው አስቃቂ አደጋ በእርሱ ላይ የደረሰበት ጊዜ ነበር፡፡ የአትላንቲክ ወቅያኖስን በመሻገር ላይ ሳሉ መርከባቸው ከአንድ የእንግሊዝ መርከብ ጋር ተጋጨችና በ12 ደቂቃ ውስጥ ሰጠመች፡፡ ስፖፎርድ ከሚስቱ ዘንድ የተቆራረጠ የስልክ መልእክት፡- "ብቻዬን ተርፌአለሁ" የሚል ተቀበለ፡፡ ሚስቱ ተረፈች፤ ነገር ግን አራቱ ውድ ሴቶች ልጆቻቸው ከሰጠሙት ከ226 ሰዎች መካከል ነበሩ፡፡

በመጨረሻም፣ ስፖፎርድ ሚስቱን በዌልስ ለመገናኘት ወደ ምሥራቅ ሲሄድ የሚጓዝባት መርከብ የተወደዱት ልጆቹ በሞቱበት አካባቢ ዐለፈች፡፡ አደጋ በአደጋ ላይ ተደራረበበት፤ ይሁን እንጂ ልጆቹን ባጣበት ሥፍራ ላይ የመሆኑ ሁኔታ ከዚህ የሚከተለውን ግጥም እንዲጽፍ አነሳሰው፤

ሰላም እንደ ወንዝ መንገዴን ሲከብ፣
ሀዘን እንደ ባሕር ወጀብ ሲንከባለል፤



ዕጣ ፈንታዬ ምንም ይሁን ምን፣
አስተምረኸኛል አንተ አንድ ነገር፡፡
ነፍሴ ደህና ነች ብዬ እንድናገር፡፡

እነዚህን የአደጋ ታሪኮች በአንድነት የሚያስተሳስራቸው አንድ የጋራ የሆነ ነገር አለ፡- እርሱም የእምነት ኃይል ነው፡፡

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ከአደጋ በኋላ ሕይወት፣ ከውድቀት በኋላ ደግሞ የወደፊት ተስፋ መኖሩን ያስተምረናል፡፡ ሙሴን አስታውሱ፡፡ በትውልዱ ዕብራዊ ነበር፤ ያደገው በፈርዖን ቤት በታላቅ ሀብት፣ ኃይልና ክብር መካከል ነበር፤ የተማረው በምድሪቱ ውስጥ እጅግ ከፍተኛ ዕውቀት ባላቸው ምሑራን ነበር፤ ሙሴ ሁሉም ነገር ያለው ሰው ነበር፡፡ ከዚያም ከዕብራውያን ወገኖቹ መካከል አንዱን ለማዳን ሲል ግድያ ፈጸመና የሚቀጥለውን 40 ዓመታት በምድረ በዳ በበጐች እረኝነት አሳለፈ፡፡ ምን ዐይነት ውድቀት ነው!

ነገር ግን ደግሞ ምን ዐይነት ለውጥ ነው! እግዚአብሔር ሙሴን በዚያ በምድረ በዳ ተገናኘውና ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ለታቀደለት ዐላማ ጠራው፡፡ ሙሴ በግብፅ ቤተ መንግሥት ውስጥ ያሳለፋቸው አርባ ዓመታት በከፍተኛ የፖለቲካ ሥልጣን ማዕከል ውስጥ እንዲሠለጥን አድርገውታል፡፡ በምድረ በዳ ያሳለፋቸው አርባ ዓመታት ደግሞ እግዚአብሔርን ለማዳመጥና ለመታዘዝ ትህትናን አስተምረውታል፡፡ ሙሴ ከምድረ በዳ የተገለጠው ወገኖቹ ነፃ ሆነው ለማየት ከእግዚአብሔር ግልጽ የሆነ ራዕይንና ኃላፊነትን ይዞ ነበር፡፡ ሙሴ በዘመኑ እጅግ ኃይለኛ በነበረው ንጉሥ ፊት በመቆም ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሆነውን ሕዝብ ከባርነት ነፃ አወጣ፡፡ በእግዚአብሔር መንፈስ በመመራት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመጀመሪያዎቹን ዐምስት መጻሕፍት ለመጻፍ የበቃው ሙሴ ነበር፤ እነዚህ መጻሕፍት እስካሁን የአብዛኛው የምዕራብ ዓለም ሕግጋትና መንግሥታት የሚቀረጹበት መሠረታዊ መርሆች ሆነዋል፡፡

## የእግዚአብሔር መንግሥት ባሕል ኃይል

ከእኛ መካከል በአንድ ወይም በሌላ ወቅት ሥፍራውን ለመልቀቅ (ለመተው) ያላሰበ ማን አለ? ወደፊት ለመቀጠል እንደማንችል ስሜት ያሳደሩብን የሀዘን ወይም የተስፋ መቁረጥ ወቅቶች ሁላችንንም አጋጥመውናል፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ጣልቃ የሚገባው በዚህ ጊዜ ነው፡፡ የመንግሥቱ እምነት ከውድቀት በኋላ ሕይወት እንዳለ

ያረጋግጥልናል:: ተስፋን ይሰጠናል፣ ተስፋው መከራዎቻችንና ችግሮቻችን ጊዜያዊ ብቻ መሆናቸውን፣ በፊት ለፊታችን ታላቅ፣ ሙሉና ወሰን የሌለው ሕይወት እንዳለን የሚገልጽልን እርግጠኛ የሆነ ማረጋገጫ ነው:: ዓለምን ለማሸነፍ የሚያስችለን በክርስቶስ እምነት ኃይልን የተሞላው ይህ ተስፋ ነው:: በአብዛኛው በጨለማ ኃይላት ቁጥጥር ሥር ባለ ዓለማዊ ባሕል ውስጥ እንኳ ቢሆን የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ለመንግሥቱ ሕይወትና ባሕል በታማኝነት ጸንተን ለመቆም ያስችለናል::

በምዕራፍ ሁለት ውስጥ እምነት የእግዚአብሔር መንግሥት ባሕል መሆኑን ተመልክተናል:: ባሕል ምናልባት በሰዎች ሕብረተ ሰብ መካከል እጅግ ብቁ የሆነ ኃይል ሳይሆን አይቀርም:: ሆነ ብለው የባሕል ተቃዋሚዎች ለመሆን ከመረጡ ሰዎች በስተቀር፣ ባሕልን የሚቆጣጠር ማንም ሰው ሕዝቡን ደግሞ ይቆጣጠራል:: የባሕል ኃይል አንዳንድ ነገሮችን እንድናስብ ያደርገናል::

በመጀመሪያ፣ *የአንድ አገር ትልቁ የመለያ ፈተና ባሕሉን ለመንከባከብና ለመጠበቅ ያለው ችሎታ ነው፤* በታሪክ ውስጥ ከአሸናፊነትና ከቅኝ አገዛዝ ውጤቶች መካከል አንዱ አገር በቀል የሆኑት ባሕሎች በድል አድራጊዎች ባሕሎች መሸርሸራቸው ወይም መለወጣቸው ነው:: የአሦር መንግሥት ዐሥሩን ነገዶች ያቀፈውን የእስራኤልን ሰሜናዊ መንግሥት ድል አደረገ፤ ከዚያም በኋላ እነርሱ የደቡባዊው የይሁዳ ግዛት ሕጋዊ ሥርወ መንግሥት ከነበረው ከዳዊት ቤት ተለዩ:: የአሦር ባሕል የእስራኤላውያኑን ባሕል ሙሉ በሙሉ አጠፋው፤ ዐሥሩ ሰሜናዊ ነገዶች የራሳቸውን ልዩ ማንነት ይዘው መኖራቸው አበቃ:: ከአንድ ምዕተ ዓመት በኋላም ባቢሎናውያን ደቡባዊውን የይሁዳ መንግሥት አሸንፏና አብዛኛውን ሕዝብ በምርኮ ወደ ባቢሎን ወሰዱት:: ይሁን እንጂ፣ በዚህኛው ሁኔታ፣ ለእግዚአብሔር በታማኝነት የቆሙት ዳንኤል፣ ሲድራቅ፣ ሚሳቅ አብድናጐና ሌሎች የአይሁድ መሪዎች ሊመሰገኑ የሚገባቸው ሲሆን በነሱ ታማኝነት የአይሁድ ባሕል አልጠፋም ነበር:: ከ70 ዓመታት በኋላ የፋርስ መንግሥት ባቢሎናውያንን አሸንፏና የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ አይሁዳውያኑ ምርኮኞች ወደ አገራቸው እንዲመለሱ በዐዋጅ ፈቀደላቸው:: ከዚያም በኋላ የፋርስ መንግሥት በግሪክ ተሸነፈ፤ ግሪክም በሮም ተሸነፈ::

አንዳንድ ጊዜ አንድ ባሕል በሽንፈት ውስጥ ሳይጠፋ መቀጠሉ ብቻ ሳይሆን በድል አድራጊዎቹ ባሕል ላይ ተጽእኖ ያመጣል፣ እንዲለወጡም ያደርጋቸዋል:: ግሪክ ለዚህ ትልቅ ምሳሌ ነው:: ግሪክ በሮም የተሸነፈ ቢሆንም የግሪክ ባሕል በመላው በሮማውያን ግዛትና ከዚያም ባሻገር



በነበረው ባሕል ላይ ሁሉ ኃይለኛ ተጽእኖ በማድረግ መስፋፋቱን ቀጠለ፤ ይህም ተጽእኖ እስከ ዛሬ ድረስ ስሜቱ አልጠፋም::

አንዳንድ ጊዜ ተቃራኒ ባሕል በጣም ጠንካራ ይሆንና ዋናውን ባሕል ይለውጠዋል:: በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የተፈጸመው ነገር ይኸው ነበር፤ ይኸውም በሮማውያን ግዛት ውስጥ ሕጋዊነት የሌላት አንድ ትንሽ ቡድን በመሆን የጀመረች ስትሆን በኋላ መጠኗና ተጽእኖዋ እየጨመረ ሲመጣ የሮማውያኑ ግዛት "ክርስቲያናዊ" እስከ መሆን ደረሰ:: የአንድ ባሕል የጥንካሬው መለያ ፈተና ራሱን ለመጠበቅና ለመንከባከብ ብቻ ሳይሆን ዋናውን ወይም ተወዳዳሪውን ባሕል ለመለወጥ ያለው ችሎታ ነው::

ይህም ወደ ሁለተኛ አሳብ ያመጣናል፤ *የአንድ አገር ባሕል ጥንካሬ ሌሎችን ባሕሎች ለማሸነፍ ያለው ችሎታ ነው::* በእኛው በራሳችን ዘመን፣ ተቃውሞን የማሸነፍ ጫና በዙሪያችን የሞላ ጉዳይ ነው:: አገሮች የሚወድቁት ወይም የሚነሱት ሌሎችን ተቃራኒ ባሕሎች ለማሸነፍ ባላቸው ችሎታ መሠረት መሆኑን እምናለሁ:: ተቃራኒ ማለት ቀላል በሆነ አነጋገር በአንድ ሕብረተሰብ ውስጥ ዋናውን ባሕል የሚቋቋም ባሕል ማለት ነው:: ዛሬ ባሃማስ፣ ጃማይካ፣ አሜሪካ እንግሊዝ፣ ካናዳ፣ ፊሊፒንስ፣ ሐይቲ፣ የአውሮፓ አገሮችና ሌሎች ብዙ አገሮች በባሕል ውጊያ ተጠምደዋል:: የእስልምናው ዓለም በግርግር ውስጥ የሚገኝበት አንዱ ምክንያት የምዕራቡ ዓለም የተበላሸው "ክርስቲያናዊ" ባሕል "ንጹህ" የሆነውን የእስልምና ባሕል እየሸረሸረው ነው ብለው ከማሰባቸው የተነሣ በሚያካሂዱት የዐመፅ ተቃውሞ ምክንያት ነው::

የእግዚአብሔር መንግሥት የመጀመሪያ ዜጐች የነበሩት፣ የመጀመሪያዎቹ የክርስቶስ ተከታዮች፣ በሮማውያኑ ግዛት ውስጥ ተቃራኒ ባሕል በማሳየት ጀመሩ:: ምንም እንኳ የኋላ ኋላ "የክርስትና" ባሕል በመባል እየታወቀ የመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት ባሕል በምዕራቡ ዓለም የበላይነትን ቢያገኝም፣ ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜ እጅግ ጠንካራ እጅግ ኃይለኛና እጅግ ውጤታማ የምትሆነው እርሷ በምትገኝበት ህብረተሰብ ውስጥ ተቃራኒ ባሕል ያላት ሆና በምትንቀሳቀስበት ጊዜ ነው:: ዛሬ በቤተክርስቲያን እጅግ ታላላቅ ከሆኑት ችግሮች አንዱ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ህብረት የተቃራኒ ባሕል ስለታቸው መደነዙና አማኞች በግለሰብ ደረጃ አብዛኛውን የዓለማዊውን ባሕል አስተሳሰብና ዘዴዎች ከራሳቸው ጋር ማዋሃዳቸው ነው፤ በዚህም ሂደት ከዓለም ተለይተው የማይታዩ ሆነዋል::

ይህም ሦስተኛውን አሳብ የበለጠ ቁም ነገር ያለው እንዲሆን ያደርገዋል፤ *ትልቁ የባሕል መለያ ፈተናው ሊያልፈው የሚችለው ማህበራዊ ማዕበል ነው::* ቤተ ክርስቲያን የምታመቻምች እንድትሆን በዙሪያዋ ጫና

ከሚያደርሱባት ማዕበሎች ልትተርፍ ትችላላችን? ምናልባት ሌሎች አገሮች ወይም ባሕሎች የሚያደርጉትን እንዳያደርጉ ልንከለክላቸው አንችልም ይሆናል፤ ነገር ግን እነርሱ የሚያደርጉትን ላለማድረግ ራሳችንን ልንከለክል እንችላለን፡፡ ማዕበል ማለት ጐርፍ ወይም ጫና ማለት ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ የሰዎች ጫና (ተጽእኖ) ብለን እንጠራዋለን፡፡ በአካባቢያችን ሁሉም ነገር ተቃራኒ ሲሆንብን እንዴት እንተርፋለን? ከጐርፉ በተቃራኒ አቅጣጫ እንዴት ዋኝተን ልንወጣ እንችላለን? ከማህበራዊ ተጽእኖ ማዕበል ማንነታችን ሳይነካ በደህና ሁኔታ እንዴት ልንወጣ እንችላለን? ይህ ያለ እምነት አይቻልም፡፡

በዚህም ወደ አራተኛው አሳብ እንመጣለን፡- የሰማያዊው መንግሥት ባሕል (እምነት) ምድራዊውን ባሕል በሙሉ ያሸንፋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን በጣም ግልጽ ያደርገዋል፤ "የዓለም መንግሥታት የጌታችንና የእርሱ የክርስቶስ መንግሥት ሆነች፡፡ እርሱም ከዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሣል" (ራዕይ 11፥15)፡፡ በዚህ ሥፍራ ዓለም የሚለው ቃል የማህበራዊና የፖለቲካዊ አወቃቀርን ያመለክታል፡፡ በዚህ ዐውድ ውስጥ ደግሞ ከባሕል ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገር ብቻ ሳይሆን ባሕል ነው፡፡ ዋናው አገር መንግሥተ ሰማያት ሲሆን ምድር ደግሞ ቅኝ አገር ናት፡፡ ቤተክርስቲያን ለእግዚአብሔር መንግሥት ምድርን ቅኝ ግዛት የማድረግ ተልእኰ ያላት የእግዚአብሔር መንግሥት የሥራ ጣቢያ ናት፡፡ ስለዚህ፣ ምድር፣ በመንግሥተ ሰማያት ባሕል የተሞላች እንድትሆን ይጠበቅባታል፡፡

## ርግጠኛ የሆነ መንግሥት

ባሕል የኑሮ ዘይቤ ነው፡፡ አንድ መርሐ ግብር ወይም ውጥን አይደለም፡፡ ባሕል ሰዎች የሚኖሩበት መንገድ ነው፡፡ ባሕልን እንለማመደውም፡፡ እኛ በባሕሉ ውስጥ አድገናል፣ በባሕሉ መሠረት መኖር ለእኛ ተፈጥሮአዊ ነው፡፡ ባሕል ተፈጥሮአዊ ነው፣ ሰዎች ራሳቸውን የሚሆኑበት መንገድ ነው፡፡ እንደ ማንኛውም ሌላ አገር፤ የእግዚአብሔር መንግሥትም የራሱ ባሕል አለው፤ ከእግዚአብሔር መንግሥት ባሕል ዋና ዋና የመለያ ባሕርያት መካከል አንዱ ፍጹም ርግጠኛ መሆኑ ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ባሕል ማንኛውንም ሌላ ባሕል ያሸንፋል፤ ይህ አይቀሬ ነው፡፡ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ብሎአል፤ "በእኔ ሰላም እንዲኖራችሁ ይህን ነግሬአችኋለሁ፣ በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፡፡ ነገር ግን አይዞአችሁ! እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ" (ዮሐንስ 16፥33)፡፡



ኢየሱስ እነዚህን ቃሎች የተናገረው ከመሰቀሉ በዋዜማው ሌሊት ነው፡፡ ወደፊት ለሚገሙአቸው ችግሮችና ተግዳሮቶች ደቀመዛሙርቱን ማዘጋጀት እየሞከረ ነበር፡፡ በመጀመሪያ ክፉ ዜና ነገራቸው፡፡ "በዓለም ሳላችሁ ብዙ መከራ አለባችሁ፡፡ ያልጠበቃችሁት ብዙ ነገር ይገጥማችኋል፤ ያልጠየቃችሁት ብዙ ነገር፤ ይገባናል ብላችሁ የማታስቡት ብዙ ነገር ይገጥማችኋል፡፡ እንገባበታለን (እንወሳሰብበታለን) ብላችሁ ፈጽሞ ያላመናችሁበት አንዳንድ ነገር ይገጥማችኋል፡፡ ተቃውሞ፣ ነቀፋና ማንኛውም ዓይነት ጥቃት ይደርስባችኋል፡፡ በአንድነት ለማያያዝ (ለማሰባሰብ) በሙሉ ኃይላችሁ ስትጥሩለት የነበረው ነገር ሲፈራርስ ታዩታላችሁ፡፡ በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፡፡ እነዚህን በቅድሚያ የምነግራችሁ በሚመጡባችሁ ጊዜ ድንገተኛ መስለው እንዳትደናገጡና ሰላም እንዲኖራችሁ ነው፡፡"

ከዚያም በኋላ መልካሙን ዜና ነገራቸው፡፡ "ነገር ግን አይዞአችሁ!" ያ ማለት "ተጽናኑ፤ ተዝናኑ፡፡ አትንቀጥቀጡ" ማለት ነው፡፡ ለምን? "ምክንያቱም እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ፡፡" በሌላ አነጋገር፣ እኔ የኃይላትን መዋቅር የባሕልን መዋቅር፣ የማህበራዊ ማዕበልን መዋቅርና እንዲሁም የሰዎችን የሥልጣኔ ግብረ ገባዊ እሴቶች መዋቅር አሸንፌዋለሁ ማለቱ ነው፡፡

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ዓለምን ያሸንፋል፡፡ በእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ከእብዶች ጥገኝነት ሥፍራ ወጥተህ ፕሬዚዳንት ለመሆን ትበቃለህ፡፡ የደረሰብህን የከፍተኛ ጥፋት ስቃይና ሀዘን ድል አድርገህ ጠንካራ ሆነህ ትወጣለህ፡፡ እንደ ሙሴ ክብርህን፤ ጠባይህንና ነፃነትህን አጥተህ ከምድረ በዳ ልትመለስ ትችላለህ፤ ነገር ግን ብዙዎችን የምትታደግ ሰው ልትሆን ትችላለህ፡፡ በእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ልታሸንፍ ትችላለህ፤ ምክንያቱም የመንግሥት እምነት ዓለምን ስለሚያሸንፍ ነው፡፡

## ኃያል የእግዚአብሔር መንግሥት

ሰማያዊው መንግሥት የኃይል መንግሥት ነው፡፡ ጠንካራና አሸናፊ ነው፡፡ የሰዎች የሆኑ (ምድራዊ) ብዙ መንግሥታት የእግዚአብሔርን መንግሥትና ዜጐቹን ለማጥፋት ሞክረው ነበር፡፡ ሁሉም አልተሳካላቸውም ሁልጊዜ ሞክረዋል፤ ሁልጊዜም ይሞክራሉ፡፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማጥፋት መሞከር መላውን ሥነ ፍጥረት ለማጥፋት እንደ መሞከር ነው፡፡ ፍጥረት ራሱ በእግዚአብሔር መንግሥት መርሆች የተያያዘና የሚመራ ነው፡፡

ሰማያዊው መንግሥት ከምድራዊው መንግሥታት የበለጠ ዘላቂነት አለው፡፡ ምድራዊ መንግሥታት በሙሉ ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት

ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል፡፡ ከዘላቂነት ባሕርያት አንዱ ትእግሥት ነው፡፡ ችኩላ ዐልሞት (ማለም) የማያውቀውን ነገር ትዕግሥት ሊፈጽም ይችላል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ በሕይወት ውስጥ ተሸናፊ የሚሆነው ሰው ለመጠበቅና መከራውን ለመቀጠል ትእግሥት ያጣ አሸናፊ ሰው ነው፡፡ ትእግሥት ዛሬ ዛሬ በማህበረሰባችን ውስጥ በብዛት የማይገኝ ውድ ዕቃ ነው፡፡ በጣም ውድ ከመሆኑ የተነሣ ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች አንዱ በመሆን ተጠቅሶአል (ገላ 5፥22-23 ይመልከቱ)፡፡ እግዚአብሔር ለማንኛችንም ከሰጠን ታላላቅ ስጦታዎች መካከል ትዕግሥት አንዱ መሆኑን አምናለሁ፡፡ በመጽሐፈ ምሳሌ 16፥32 "ታጋሽ ሰው ከጦረኛ፣ ሰሜቱን የሚገዛም ከተማን በጉልበቱ ከሚይዝ ይበልጣል" ይላል፡፡

የትእግሥት ጸጋ ቅጽበታዊ ርካታ ፈላጊ ከሆነውና "አሁኑኑ ማግኘት አለብኝ" ከሚለው ከዛሬው ከእኛ ዓለም ዘንድ አብዛኛው የጠፋ ነገር ነው፡፡ ብዙ ዐዲስ ተጋቢዎች ወላጆቻቸው 30 ዓመታት ያህል ጠብቀው ያፈሩትን ቤት ዐይነት በቅጽበት ለመግዛት ካልቻሉ በውድቀት ውስጥ እንዳሉ ያስባሉ፡፡ ዛሬ ብዙ ቤተሰቦች በዕዳ ተራራ ሥር የተቀበሩት የሚፈልጉትን የኑሮ ደረጃ ለማግኘት እስኪችሉ ድረስ መጠበቅ ስለ አቃታቸው ነው፡፡ ሁሉንም ነገር አሁኑኑ ማግኘት ሙጭጭ ስላሉ በገንዘብ ረገድ ያላቸውን ነጻነት ሸጠው ራሳቸውን የብድር ባሪያዎች አድርገዋል፡፡

የእግዚአብሔር መንግሥት ከዓለም ይልቅ ዘላቂነት አለው፡፡ ይህ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? እኛ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች እንደ መሆናችን፣ የማይሸነፍ ባሕል አካል የመሆናችንን ሐቅ መረዳት ስለ አለብን ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጽናት እንድንቆም፣ ሩጫውን እንድንሮጥ፣ መልካሙን ገድል እንድንጋደል፣ ውድድሩን እንድንፈጽም ተነግሮናል፡፡ ችግራችን በቀላሉ ተስፋ የምንቆርጥ መሆናችን ነው፡፡ ብዙ አማኞች፣ በተለይ በምዕራቡ ዓለም፣ ለችግር የተዘጋጁ አይደሉም፡፡ የችግሩን የመጀመሪያ ምልክት ካዩ ሩጫውን ይወረውራሉ፡፡ "ደህና፣ እንግዲህ ይህ አልሠራም፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይመስለኝም፡፡ ሌላ ነገር እንሞክር" ይላሉ፡፡ በቤተክርስቲያን አንድ ሰው ስሜታቸውን ከጐዳው ወደ ቤተክርስቲያን መምጣት ያቆማሉ፡፡ ምናልባት ሰባኪው በስብከቱ ከመጠን በላይ "የግል ሕይወት" የሚነካካ ከሆነ ይሄዳሉ (ይጠፋሉ)፡፡ ዘላቂነት፣ ትእግሥት፣ የመጽናት ኃይል የላቸውም፡፡

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት "ከሞቀ ጨዋታ"፣ ከመልካም ስሜትና ከበረከቶች በላይ ነው፡፡ እነዚህን ሁሉ ያካትታል፤ ነገር ግን በተጨማሪ ጠለቅ አድርጐ ይገባል፡፡ የበለጠ ነገርም ይጠይቃል፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ጥሪ የጽናት ጥሪ ነው፡፡ ጥሪው በመከራ፣



በችግር፣ በተቃውሞ ወይም በፍርሀት ፊት ጸንቶ የመቆምና ተስፋ ያለ መቁረጥ ጥሪ ነው፡፡ የመንግሥቱ ዜጎች፣ ሞትንም ጨምሮ፣ ማናቸውንም ወይም ሁሉንም ተግዳሮቶች ለመቋቋም የሚችል ባሕል አካል ናቸው፡፡ እስኪ በመጋዝ እንደ ተሰነጠቀ ትውፊት የሚገልጽለትን ነቢዩን ኢሳይያስን ጠይቁት፡፡ እስኪ ድንጋዮች ሰውነቱን በሚወግሩበት ጊዜ ገዳዮቹን ይቅር ያለውን እስጢፋኖስን ጠይቁት፡፡ ደግሞም ጌታው በሞተበት ሁኔታ ለመሞት የማይገባ መሆኑን በማሰብ በራሱ ጥያቄ ተዘቅዝቆ የተሰቀለውን ጴጥሮስን እስቲ ጠይቁት፡፡ ከክርስቶስ ጋር በነበረው ግንኙነት ምክንያት አንገቱን ለሰይፍ የሰጠውን ጳውሎስንም ጠይቁት፡፡ ስለ እምነታቸው የተሰቃዩትንና የሞቱትን በሁለት ሺህ ዓመታት ውስጥ ስፍር ቁጥር የሌላቸውን አማኞች እስኪ ጠይቋቸው፡፡ እያንዳንዳቸውን "ያደረጋችሁት ተገቢ ነበርን?" ብለን ብንጠይቃቸው፣ ሁላቸውም በአንድ ድምፅ እንደ መብረቅ "አዎ!" ብለው ይመልሱልናል፡፡ ለአንድ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ ጌታውን ወይም ጌታዋን ለማገልገል ምንም ዐይነት ዋጋ ከመጠን በላይ ሊሆን አይችልም፡፡

በክርስቶስ ከሆኑ ሞት እንኳ ጭራሽ የሚያስፈራ ነገር አይደለም፤ የመንግሥቱ ዜጐች ጊዜያዊ መከራን፣ ፈተናንና ተቃውሞን አይፈሩም፡፡ መከራዎች በሙሉ ጊዜያዊ ናቸው፡፡ ማድረግ ያለብን እኛ ጊዜያዊ አለመሆናችንን ማረጋገጥ ነው፡፡ አውሎ ነፋሶች በሚያስፈራ ፍጥነት ይመጣሉ፤ ነገር ግን ደግሞ እንደ ገና ዐልፈው ይሄዳሉ፡፡ በምንም ዐይነት ሁኔታ ውስጥ ብትሆን ያ ነገር ያልፋልና ስለዚህ አትንቀጥቀጥ፤ በእምነትህ ጸንተህ ቁምና ያንን ነገር አሳልፈው፡፡ ንጉሣችን በጽናት እንድንቆም ይጠይቀናል፤ እንድናደርግም ያስታጥቀናል፡፡ ወደዚያ ለመድረስ ቁልፉ እምነት ነው፡፡ የመንግሥቱ እምነት የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ ያለብሰናል፤ የዚያ የጦር ዕቃ አካል ተፈጥሮአዊ ይሁን ወይም ልዕለ ተፈጥሮአዊ ቢሆን፣ ማንኛውም ጠላት ወይም ተግዳሮት ፊት ለመቋቋም ያስችለናል፡፡ ጳውሎስ ይህንን በዝርዝር ይገልጽልናል፡-

> በተረፈ በጌታና ብርቱ በሆነው ኃይሉ ጠንከሩ፡፡ የዲያብሎስን የተንኰል ሥራ መቋቋም ትችሉ ዘንድ የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር ዕቃ ልበሱ፡፡ ምክንያቱም ተጋድሎአችን ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን ከዚህ ከጨለማ ዓለም ገዦች ከሥልጣናትና ከኃይላት፣ እንዲሁም በሰማያዊ ስፍራ ካሉ ክርኩሳን መናፍስት ሰራዊት ጋር ነው፡፡ ክፉው ቀን ሲመጣ መቋቋም ትችሉ ዘንድ የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር ዕቃ ልበሱ፤ ሁሉን ከፈጸማችሁ በኋላ ጸንታችሁ

> መቆም ትችላላችሁና። እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ዝናር ታጥቃችሁ፤ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፣ በሰላም ወንጌል ዝግጁነት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ። ከእነዚህም ሁሉ ጋር የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፤ የመዳንን ራስ ቁር አድርጉ፤ የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፤ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው። በጸሎትና በልመና ሁሉ፤ በማንኛውም ሁኔታ በመንፈስ ጸልዩ። ይህንም በማሰብ ንቁ፤ ስለ ቅዱሳንም ሁሉ በትጋት ልመና አቅርቡ (ኤፌሶን 6፥10-18)።

ጳውሎስ እምነትን የመከላከያ መሣሪያ ከሆነው ከጋሻ ጋር እንዳመሳሰለው አስተውሉ። የምንዋጋው ጦርነት ባይኖር ኖሮ እምነት አያስፈልገንም ነበር። እምነት በጦርነቶቹ መካከል ይከላከልልናል። ፈተናዎችህ ጊዜያዊ ናቸው፤ ስለዚህ ታገሳቸው። በዐሥር ዓመታት ውስጥ የአሁኑ ተቃዋሚህ ወዳጅህ ይሆናልና አትጨነቅበት፤ ብቻ ጸልይ። ሚስቴን ለመጀመሪያ ጊዜ ባየኋት ጊዜ፣ አልወደድኋትም ነበር። ግን እመኑኝ፣ በዚያን ጊዜ ንቁ ስላልተውኳት ዛሬ በጣም ደስ ይለኛል! ወደፊት ምን ዐይነት ድልና በረከት እንደሚገጥምህ ፈጽሞ አታውቅም፤ ስለዚህ አሁን ያሉት ጊዜያዊ ችግሮች እንዲያሸንፉህና ወደፊት የሚመጡትን ታላላቅ ነገሮችህን እንዲያስቀሩብህ አትፍቀድላቸው።

## የእምነት ጥቅም

በሕይወቴ ውስጥ ለመረጋጋቴ ምክንያት ከሆኑት ምስጢሮች አንዱ በማንም ሰው ላይ የማልታመን መሆኔ ነው። አንዳንድ ሰዎች ይህ አሉታዊ አስተሳሰብ ነው ብለው ሊያስቡ ይችላሉ። ግን አይደለም። ይህም ማለት የመጨረሻ አመኔታዬን በማንኛውም ሰው ላይ አላሳርፍም ማለቴ ነው። ሕይወትህ ሰዎች ስለ አንተ በሚያስቡት ወይም ለአንተ ባላቸው አመለካከት ላይ የተመሠረተ ከሆነ አሁኑኑ ማቋረጥ ተችላለህ፤ ምክንያቱም ዛሬ ሊወዱህ ነገ ደግሞ ሊጠሉህ ስለሚችሉ ነው። ዛሬ ከአንተ ጋር ይሆናሉ፤ ነገር ግን ትተውህ ይሄዳሉ። ጸንቶ ለመቆየት ብቸኛው መንገድ በጌታ ላይ ያለህን እምነት መጠበቅ ነው።

ልብ በል፣ እምነትህ አንተ ያለህ ዋናና አስፈላጊ ኃይል ነው፣ ስለዚህ የሕይወትን ሩጫ ስትሮጥ፣ እምነትህን ጠብቅ። ሕይወትህን በእምነት በእግዚአብሔር ላይ ስታሳርፍ፣ ከእርሱ የሚገኝ የፀና እምነት፣ ለየዕለት ኑሮህ



በውስጥህ ሙሉ ልብን እንዲፈጥርልህ አድርግ። ከዚያም በመንገድህ የሚገጥሙህን ፈተናዎችና መከራዎች ለመጋፈጥ ስትነሣ እምነትህ ይገለጣል፣ ለሌሎችም የሚታይ ይሆናል። እነርሱም የእግዚአብሔር ኃይል በአንተ እየሠራ እንዳለ ያዩና ያከብሩታል።

እምነትህ ፈተናን ይፈልጋል። አስቀድሜ እንዳልሁት፣ ማንኛውም የእምነት ቃል ይፈተናል። በሕይወትህ ቀለል ባለ ሁኔታ መጓዝ ከፈለግህ፣ እምነት አለኝ እያልህ ጉራ አትንዛ። ለመፈተን ካልፈለግህ፣ አፍህን ዝጋ። የመንግሥቱ መሠረታዊ ሕግ ይህ ነው። ዋናው ችግር አፍህን ዘግተህ ለመኖር አለመቻልህ ነው። ስለዚህ ስለምትናገረው ነገር ተጠንቀቅ። እንደ ጴጥሮስ አትሁን፤ እርሱ ጌታን ከቶ እንደማይክድ በጉራ ከተናገረ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ሦስት ጊዜ ካደው።

ኢየሱስ ጴጥሮስን አስቀድሞ አስጠንቅቆት ነበር፡- “ስምዖን ስምዖን ሆይ እነሆ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ (ጠየቀ)። እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ ጸለይሁ። አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አበርታ (ሉቃስ 22፥31-32)። ማንኛውም የእምነት ቃል ይፈተናል። ጴጥሮስ ፎከረ፤ ሰይጣንም “እስቲ ቃልህን ልፈትነው” አለ። ግልጽ የሆነው ሐቅ ደግሞ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እምነት ሳንናገር ልንኖረው አለመቻላችን ነው። ስለ እምነት በምንናገርበት ጊዜ፣ ራሳችንን ለፈተና ማስቀመጣችን ወይም ማዘጋጀታችን ነው። ስለዚህ በሚገባ ልንዘጋጅበት ይገባናል። የእምነትህ ጥንካሬ እንዴት ነው? ፈተናው ሲመጣ ታውቀዋለህ። እስከዚያ ድረስ ግን እምነትህን ለመገንባት በጸሎትና የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት የቻልኸውን ሁሉ አድርግ፤ ከዚያም በኋላ ፈተናው ሲመጣ ለመቆም ትችላለህ።

ኢየሱስ ለጴጥሮስ የተናገረውን አስተውል፣ “አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አበርታ”። ማንኛችንም ብንሆን ለእምነታችን የሚገባውን ፈተና ካላለፍን በስተቀር ለሌሎች ለመስበክ መብት የለንም። ብዙ ጊዜ ነቀፋን እጅግ የሚያበዙት ሰዎች ስለ ሁኔታው እውቀት (ፍንጭ) አልባ ሰዎች ናቸው፤ ምክንያቱም በዚያ ጐዳና አልተራመዱበትምና ነው። በሚያጠራው የፈተና እሳት ውስጥ አልተፈተኑም። ስለዚህ አንድን ሰው (ወንድም ወይም እህት) ከመንቀፍህ በፊት “እርሱ ባለፈበት እኔ አልፌአለሁን?” “እርሷ ያደረገችውን እኔ አድርጌአለሁን?” ብለህ ራስህን ጠይቅ። ራስህ በዚያ ፈተና ውስጥ ሳታልፍ እንዴት በፍርድ ወንበር ላይ ልትቀመጥ ትችላለህ? ኢየሱስ ለጴጥሮስ፣ “አንተ ከተፈተንህ በኋላ ሌሎችን ሰዎች ስለ ማበርታት ልትናገር ትችላለህ” አለው።

ነቀፋ የያለመብሰል ምልክት ነው:: የሚመነጨውም እኛ ከሌላ ሰው እንሻላለን ከሚል የተሳሳተ እምነት ነው:: ታሪኩን የማታውቀውን ሰው ለመንቀፍ ከቶ አትሞክር:: ምን ጠባሳ እንዳላባቸው፣ ምን ትምህርት እንደተማሩ፣ ወይም በልባቸው ውስጥ ምን ጥበብ እንዳላቸው ምንም የምታውቀው ነገር የለምና::

የእምነትህ መፈተን የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ የመሆንህ ምልክት ነው:: መፈተን በሳል ያደርገናል:: ደግሞም ሥነ ሥርዓትን ለመማር ይረዳናል:: ልክ እንደ ማንኛውም አፍቃሪ ወላጅ፣ የሰማያዊ አባታችንም ሥነ ሥርዓት በኑሮ ውስጥ ለስኬት እንደሚያዘጋጀን ያውቃል::

በሥነ ሥርዓት (በቅጣት) እና አሸናፊ በሆነ የእምነት ዕድገት መካከል ያለውን ትስስር የዕብራውያኑ ጸሓፊ እንዲህ በማለት ይገልፃል፤

> ከኀጢአት ጋር ስትታገሉ ገና ደማችሁን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተቃወማችሁም:: ልጆች እንደ መሆናችሁ እንዲህ በማለት የተናገራችሁን ማበረታቻ ቃልም ረስታችኋል "ልጄ ሆይ የጌታን ቅጣት አታቃልል፤ በሚገሥጽህም ጊዜ ተስፋ አትቁረጥ፤ ምክንያቱም ጌታ የሚወደውን ይገሥጻል፤ እንደ ልጅ የሚቀበለውንም ይቀጣል::"
>
> እግዚአብሔር እንደ ልጆቹ ይዞአችኋልና የተግሣጽን ምክር ታገሡ፤ ለመሆኑ አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማነው? ልጆች ሁሉ በሚቀጡበት ቅጣት ተካፋይ ካልሆናችሁ ዲቃሎች እንጂ ልጆች አይደላችሁም:: ከዚህም በላይ እኛ ሁላችን የሚቀጡን ምድራዊ አባቶች ነበሩን፤ እናከብራቸውም ነበር፤ ታዲያ ለመናፍስት አባት እንዴት አብልጠን በመገዛት በሕይወት አንኖርም! አባቶቻችን መልካም መስሎ እንደታያቸው ለጥቂት ጊዜ ይቀጡን ነበር:: እግዚአብሔር ግን የቅድስናው ተካፋዮች እንድንሆን ለእኛ ጥቅም ሲል ይቀጣናል (ዕብራውያን 12፥4-10)::

ችግር ሲገጥም የገጠመህ ችግር ለእምነትህና ለእግዚአብሔር መንግሥት ዜግነትህ ማስረጃ መሆኑን በማወቅ ተጽናና:: እግዚአብሔር ሲቀጣ፣ እንደ ወንድ ልጁ ወይም እንደ ሴት ልጁ በማየት ነው:: የእርሱ ግብ የቅድስናው ተካፋዮች እንድትሆኑ ማዘጋጀት ነው:: በሌላ አነጋገር፣ እናንተ እርሱን እንድትመስሉ እየቀረፃችሁ ነው:: መሆን ያለበት ልክ እንደዚሁ ነው፤ ጴጥሮስም ይህንኑ አመልክቶአል፤



> ወዳጆች ሆይ፣ እንደ እሳት የሚፈትን ብርቱ መከራ በመቀበላችሁ እንግዳ ነገር እንደደረሰባችሁ በመቁጠር አትደነቁ:: ነገር ግን ክብሩ በሚገለጥበት ጊዜ ደስታችሁ ታላቅ እንዲሆን የክርስቶስ መከራ ተካፋዮች በመሆናችሁ ደስ ይበላችሁ ስለ ክርስቶስ ስም ብትሰደቡ፣ የክብር መንፈስ የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ላይ ስለሚያርፍ ብፁዓን ናችሁ:: ... ክርስቲያን በመሆኑ መከራ ቢደርስበት ግን ስለዚህ ስም እግዚአብሔርን ያመስግን እንጂ አይፈር (1ጴጥሮስ 4፥12-14፥16)::

ጴጥሮስ "እንደ እሳት የሚፈትን" ብርቱ መከራ ቢደርስብን መደነቅ እንደሌለብን ይመክረናል:: ለምን እንደነቅም? ምክንያቱም በዚህ ዓለም ውስጥ መከራ ለእግዚአብሔር መንግሥት ሕይወትና ባሕል የተለመደ ሁኔታ (አካል) ስለሆነ ነው:: መከራ በመጪው ሕይወት አይኖርም፤ በዚህኛው ሕይወት መኖሩ ግን ለሚመጣው ሕይወት እንድንዘጋጅ ይረዳናል:: የመንግሥተ ሰማያት ባሕል ተካፋዮች የሆንን ማንኛችንም፣ "ይህ በእኔ ላይ ለምን እንደ ደረሰ ግራ ገባኝ" ማለት ከቶ የለብንም:: መከራ በሚደርስብን ጊዜ መደነቅ ወይም ተስፋ መቁረጥ ፈጽሞ የለብንም:: አንዳንድ ሰዎች "በእግዚአብሔር የምታምን ከሆነ ይህ ነገር ለምን ደረሰብህ?" ብለው ሊጠይቁን ይችላሉ:: የእኛ ምላሽ "ምንም አይደለም እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ይህ ለእኛ የተለመደ ነው፤ የባሕላችን አካል ነው:: የሚያልፍ ነገር ነው:: እኛ ከዚያ ሁሉ ይልቅ ጠንካራዎች ነን" የሚል መሆን አለበት:: አቤት! ይህ ተስፋንና መልስን በጉጉት ለሚፈልገው ዓለም ምን ዐይነት ምስክርነት ነው!

ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት ባሕል ነው:: እንዲያውም ትንፋሻችንን "ለምን በእኔ?" የሚል ቃል በመናገር ማባከን የለብንም፤ ምክንያቱም መከራ በልባችን ውስጥ ትእግሥትን የሚገነባ፣ በአእምሮአችንም ውስጥ ሥነ ሥርዓትን የሚመሠርት መሆኑን እናውቃለን::

ብዙ አማኞች በክርስቶስ መታመን ከችግሮች ይጋርዳል የሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ አላቸው:: ያ ሃይማኖታዊ ሐሳብ ነው:: የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጐች ነን የምንል ከሆነ ይህንን ለማረጋገጥ መዘጋጀት አለብን:: በክርስቶስ ኢየሱስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ እንደሚሰደዱ ጳውሎስ ተናግሮአል፤ ይህ ያለ ነገር ነው:: ለምን? ከሌላ ባሕል (ወገን) መሆናችንን የምናረጋግጥበት መንገድ ይህ ነው:: ጴጥሮስ እንዳለው በመከራችን በመነጫነጭ ፈንታ "የክርስቶስ መከራ ተካፋዮች" በመሆናችን "መደሰት" ይገባናል:: በዐጭሩ፣ በመከራችን ስንደሰት የእግዚአብሔር መንግሥት ባሕል ተካፋዮች መሆናችንን ስለሚያረጋግጡ

ነው:: ኢየሱስ ማንኛውንም ችግር ተቋቁሟል፤ ሁሉንም ችግር በስቃይ ዐለፈና በአሸናፊነት ወጣ::

ኢየሱስ እንዳደረገው በተመሳሳይ ሁኔታና ከተመሳሳይ ኃይል ጋር ዓለምን እንደምናሸንፍ ጴጥሮስ ተናግሮአል:: በሁሉም ችግር ውስጥ ካለፍን በኋላ የምንቆም፣ የምንጸና፣ የምንዘልቅ እንዲያውም ከጅማሬው ይልቅ በይበልጥ የምንጠነክር እንሆናለን:: በዚህ መንገድ "ክብሩ በሚገለጥበት ጊዜ" ደስታችን ታላቅ ይሆናል:: የእግዚአብሔር ክብር ምንድነው? የእርሱ ባሕርይ ነው:: በምንፈተነው ፈተና የእግዚአብሔር ባሕርይ በእኛ ውስጥ ይገለጣል:: እግዚአብሔር ፈርጣጮች እንድንሆን አይፈልግም፤ ሽሽት (ፍርጠጣ) ለእርሱ ባሕርይ እንግዳ ስለሆነ ነው:: በእርሱ ባለን እምነት ጽኑ፣ ጠንካራና፣ የማንወላውል እንሆናለን፤ ዓለምም የእርሱ ክብር በእኛ ውስጥ ሲገለጥ ያያል:: ስለ ክርስቶስ ስም ብንሰደብ እንደ ተባረክን እንቆጥረዋለን:: ይህም የእግዚአብሔር ባሕርይ በእኛ ላይ ማረፉን ያረጋግጥልናል::

### የእግዚአብሔር መንግሥት መርሆች

- የአንድ አገር የመለያ ፈተና ባሕሉን ለመጠበቅና ለመንከባከብ ያለው ችሎታ ነው::
- የአንድ አገር ባሕል ጥንካሬ ተቃራኒ ባሕሎችን ለማሸነፍ ያለው ችሎታ ነው::
- የባሕል ታላቁ የመለያ ፈተና እርሱ በጽናት የሚያልፍበት ማህበራዊ ማዕበል ነው::
- የሰማያዊው መንግሥት ባሕል እምነት የምድርን ባሕሎች በሙሉ ያሸንፋል::
- የእምነታችን መፈተን የመንግሥት ዜጎች የመሆናችን ምልክት ነው፤ ፈተናው በሳል ያደርገናል፤ ደግሞም ሥነ ሥርዓትን እንድንማር ይረዳናል::





## ዓለምን የሚያሸንፍ እምነት

*"እምነት ማለት እንዳለ (በሙሉ) ደረጃዎችን ባታይም እንኳ የመጀመሪያውን ርምጃ መውሰድ ማለት ነው"::*

ማርቲን ሉተር ኪንግ

የእግዚአብሔር መንግሥት ፍርሀት አልባ መንግሥት ነው:: በእምነት ሕይወታችን ስናድግ፣ ከአሁኑ ሁኔታና ወደፊት ሊደረስ ከሚችል ነገር አኳያ ጤናማ ወደ ሆነ የድፍረት ደረጃ እናድጋለን:: በእድገት ደረጃህ የት ላይ ትገኛለህ? አሁንም ገና ከፍርሀት ጋር ትታገላለህ? ለየዕለቱ ፍላጐትህስ በእግዚብሔር ላይ መታመን ተስኖህ በእምነት ጉዳዮች ጋር በመታገል ላይ ነህን? ወይስ ለጓደኛህ ወይም ለጐረቤትህ በእውነተኛነት "ከአሁን ወዲያ ምንም ነገር ቢመጣ አልፈራም" ከምትልበት የብስለት ደረጃ ደርሰሃል?

ዞሮ ዞሮ ለእግዚአብሔር መንግሥት ዜጐች፣ ኢኮኖሚውን፣ የሥራ ቅነሳን፣ ወለድ አግድን፣ የመዋዕለ ንዋይ ኪሣራን፣ የንብረት ጥፋትን፣ የንግድ ኪሣራን፣ የእሳት አደጋን፣ የጐርፍ አደጋን፤ የተፈጥሮ አደጋንና የመሳሰሉትን በሚመለከት ምንም ነገር ቢከሰት ችግር የለውም:: እነዚህ ክስተቶች ስቃይንና ችግርን የሚያስከትሉ ቢሆንም ከዘላለማዊ ጉዳዮች አንጻር ሲታዩ የማይረቡ ናቸው:: የመንግሥቱ ዜጋ ሆነህ በእምነት የምትራመድ ከሆነ፣ ስለ እነዚህ ነገሮች ፍርሀት ወይም ጭንቀት አይኖርብህም:: ምክንያቱም እምነትህ በእነርሱ ላይ ያረፈ ስላልሆነ ነው፤ ሕይወትህና ደህንነትህ በእነርሱ ላይ የተመሠረተ አይደለም:: ሕይወትንና ተግዳሮቶቹን ያለ ፍርሀት መጋፈጥ የምትችለው፤ አንተ የምትታመነው በማይለወጠው፤ በማይናወጠውና በዘላለማዊ መንግሥት ላይ በሚገዛው በእግዚአብሔር ስለሆነ ነው::

ስለዚህ ፍርሀትን እንዴት ታስወግዳለህ? ልብህን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ፍቅር ክፈት:: የእርሱ ፍቅር እንዲሞላህና እንዲትረፈረፍ ፍቀድለት:: የእግዚአብሔር ፍቅር ፍጹም ነው፤ ፍጹም የሆነ ፍቅርም ፍርሀትን አውጥቶ ይጥላል (1ዮሐንስ 4፥18 ይመልከቱ):: ሌላው የፍርሀት ማርከሻ መሣሪያ በፈተና ውስጥ በመጽናት የሚገኘው ልምምድና ልበ ሙሉነት ነው:: የምትታገሠው እያንዳንዱ ፈተና አንድን የፍርሀት ምክንያት ይቀንስልሃል:: አንድን ፈተና በመታገሥ ካለፍከው፣ ወደፊት ያንን የመሰለ ፈተና ሊያስፈራህ አይችልም፤ ምክንያቱም አንተ ማን እንደሆንክ ስለምታውቅ ነው::

እምነትህ እስከ ምን ድረስ ተፈትኖአል? አንድን የተለየ ሁኔታ ተመልክተህ "ነገሩ እንደዚህ ይሆናል ብዬ አላሰብሁም ነበር" በማለት ተናግረህ ታውቃለህን? ደህና፣ እንግዲህ ተዘጋጅ፣ ምክንያቱም ገና ምንም ነገር አላየህም! ነገሮች ከዚህ የባሰ መጥፎ አይሆኑም ብለህ በምታስብበት ጊዜ እየባሱ ይሄዳሉ:: ትንሽ ጊዜ ጠብቅ፣ ከዚያም ታያለህ:: ያም ቢሆን ግን ለፍርሀት ምክንያት አይሆንም፤ ምክንያቱም እምነት የሚያጋጥምህን እንቅፋት ሁሉ ለማሸነፍ ብርታትን ይሰጥሃል::

እምነትህ እስከ ምን ድረስ ተፈትኖአል? አብዛኞቻችን የመከራችንን ክብደት ከመጠን በላይ እናጋንነዋለን:: ትንሽ የመከራ ጫፍ ሲነካን ከባድ ስቃይ እንደ ደረሰብን አድርገን የማሰብ ዝንባሌ አለብን:: የዕብራውያን ጸሐፊ "ከኀጢአት ጋር ስትታገሉ ገና ደማችሁን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተቃወማችም" በማለት የጻፈው ሁላችንንም የሚመለከት ነው (ዕብ 12፥4):: በሌላ አነጋገር፣ አብዛኞቻችን እውነተኛ ሥቃይ ምን እንደሚመስል አናውቅም:: እግዚአብሔር፣ በጸጋው፣ እስከ አሁን ድረስ ከእንዲህ ዐይነት ሥቃይ ጠብቆናል::

ልብ ባሉ፣ እግዚአብሔር ማንኛችንንም ከምንችለው በላይ እንድንፈተን አይፈቅድም:: ፈተናዎቹን የሚያከፋፍለው በእኛ ዝግጁነት መጠን ነው:: እምነታችን ባደገ መጠን፣ እግዚአብሔር በሕይወታችን ላይ እንዲደርስ የሚፈቅደው ፈተና ክብደትም እንደዚሁ ያድጋል:: ይሁን እንጂ፣ በመጨረሻ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ከሞት ይልቅ የበረታ ይሆናል:: በዘመናት ሁሉ ቁጥር የሌላቸው አማኞች የሰማዕትነትን ሞት በድፍረት፣ በጀግንነትና እንዲያውም በደስታ የተጋፈጡት በዚህ ምክንያት ነው:: እነርሱም ሞትም እንኳ ሊያጠፋቸው እንደማይችል ዐውቀው ነበር::

### መከራዎች የሚያስገኙት የእግዚአብሔር መንግሥት ጥቅም

በመከራ ውስጥ በማለፍ የምናገኘው ጥቅም ምንድነው? በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለ ጥቂቶቹ ብቻ ተናግረናል፤ ተስፋ፣ መረጋጋት፣ ብስለት፣ ልበ ሙሉነት፣ ቅጣት (ሥነ ሥርዓት)፣ ጥበብ፣ ዘላቂነት፣ ጽናት፣ አመለካከት (ከራሳችን ይልቅ ከእግዚአብሔር አንጻር ለማየት መቻል)፣ ኃይል፣ ድፍረት እና መለየት (ጥቃቅኑን ከትልቁ ነገር ለመለየት መቻል) ናቸው:: ምናልባት ከሁሉም ይልቅ ታላቁ ጥቅም የእምነታችንን እውነተኛነት ለራሳችንም ሆነ ለሌሎች ለማረጋገጥ መቻል ነው:: ይህም ለእግዚአብሔር ክብርን ያስገኛል:: ይህ ሁሉ ከእግዚአብሔር የምንቀበለው የድነት ሙሉ "ጥቅል" አካል ነው:: ጴጥሮስ እንደሚከተለው ይገልጸዋል:-



> የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ ይባረክ! እርሱ ከታላቅ ምሕረቱ የተነሣ በኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሣት ምክንያት ለሕያው ተስፋ በሚሆን ዐዲስ ልደት፣ እንዲሁም በሰማይ ለማይጠፋ፣ ለማይበላሽና ለማይለወጥ ርስት እንደገና ወለደን:: እናንተም በመጨረሻው ዘመን ሊገለጥ የተዘጋጀው ድነት እስኪመጣ ድረስ በእምነት አማካይነት በእግዚአብሔር ኃይል ተጠብቃችኋል:: አሁን በብዙ ዐይነት ፈተና ውስጥ ሆናችሁ ለጥቂት ጊዜ መከራን ብትቀበሉም እንኳ በዚህ እጅግ ደስ ይላችኋል:: እነዚህ ነገሮች በእናንተ ላይ የደረሱት በእሳት ተፈትኖ ቢጠራም ጠፊ ከሆነው ወርቅ ይልቅ እጅግ የከበረው እምነታችሁ እውነተኛ መሆኑ እንደተረጋገጠና ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ምስጋናን፣ ክብርንና ውዳሴን እንዲያስገኝላችሁ ነው:: እርሱንም ሳታዩት ትወዱታላችሁ፤ አሁን ባታዩትም በእርሱ ታምናችሁ መግለጽ በማይቻልና ክብር በሞላበት ሐሴት ደስ ብሎአችኋል፡ የእምነታችሁን ፍጻሜ እርሱም የነፍሳችሁን ድነት እየተቀበላችሁ ነውና (1ጴጥሮስ 1፥3-9)::

በመከራ አማካይነት ጠለቅ ወዳለ እምነት እንገባለን፣ ከዚህም የተነሣ በክርስቶስ ያገኘነው ድነት በተጨባጭ ምን ማለት እንደሆነ ጠለቅ ወዳለ መረዳት እንመጣለን:: ለትንሽ ጊዜ በዚህ በጴጥሮስ መልዕክት ውስጥ የተጠቀሱትን የድነት ጥቅሞች ተመልከቱ፤ ዐዲስ ልደት፣ ሕያው ተስፋ፣ የማይጠፋ ርስት፣ በእግዚአብሔር ኃይል መጠበቅ፣ ከመከራ የሚያልፍ ደስታ፣ የተፈተነ ስለ ሆነም የከበረ እምነት፣ ለእግዚአብሔር የጠበቀ ፍቅርና እግዚአብሔር ለእኛ ስላለው ፍቅር የሚያስደስት ማረጋገጫ ናቸው::

በክርስቶስ ያገኘነውን ነገር አንድ ጊዜ ካረጋገጥን፣ ለምን ጴጥሮስ በመከራ እንድንደሰት እንደ ነገረን ለመረዳት ቀላል ይሆንልናል:: መከራዎች የእምነታችንን እውነተኛነት እንድናረጋግጥ ይረዱናል:: ይህም በበኩሉ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች እንደመሆናችን መጠን እነዚህ የድነት ጥቅሞች ሁሉ የእኛ ስለ መሆናቸው የማይናወጥ ግንዛቤን ይሰጠናል:: ደግሞም እግዚአብሔር ወደ እኛ እንዲመጣ የሚፈቅደው ፈተና ልንቋቋመው የምንችለውን ብቻ መሆኑን ስናስታውስ በመከራ ውስጥ ሳለን ድፍረታችን ያድጋል:: ስለዚህ የሚያጋጥመንን ማንኛውንም ፈተና ከእግዚአብሔር የመጣ የመተማመኛ ምርጫ እንደሆነ አድርገን መመልከት ይኖርብናል::

የሚያጋጥሙን ፈተናዎች እግዚአብሔር ስለ እኛ ምን እንደሚያስብ የሚያሳዩ ናቸው::

## የእውነተኛ እምነት አስፈላጊነት

የእምነታችንን እውነተኛነት ማረጋገጥ እጅግ አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም እምነታቸው የውሸት የሆነ፣ ወይም ስለ እምነት የተምታታ ወይም የተሳሳተ ግንዛቤ ያላቸው "አማኝ" ተብዬዎች ስላሉ ነው:: የውሸት እምነት እውነተኛ መስሎ ትልልቅና ትክክለኛ ነገሮችን ሊናገር ይችል ይሆናል፤ ነገር ግን በመከራ ውስጥ ያለውን የሚፈትንና የሚያጠራ እሳት ለማለፍ ከቶ አይችልም:: ወሬ ርካሽና ብዙ ጊዜም ግልብ ነው:: የእምነት ወሬ በእምነት አካሄድ መደገፍ አለበት:: የጳውሎስን ቃሎች አስታውሱ፣ "የምንኖረው በእምነት እንጂ በማየት አይደለም" አለ (2ቆሮ 5፥7):: በተመሳሳይ ሁኔታ በሌላ ቦታ እንደዚህ ጽፎአል፤ "እንግዲህ በመንፈስ ኑሩ እላለሁ፤ የሥጋንም ምኞት አትፈጽሙ" (ገላ 5፥16)::

የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ቀላል መንገድን ብዙ አይፈልግም፣ ምክንያቱም ያ የዓለም መንገድ ስለሆነ ነው:: ኢየሱስም እንዲህ አለ፤

> በጠባቡ በር ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው መንገድ ትልቅ፣ በሩም ሰፊ ነውና፣ ብዙዎችም በዚያ ይገባሉ:: ወደ ሕይወት የሚወስደው ግን መንገዱ ቀጭን በሩም ጠባብ ነው፤ የሚገቡበትም ጥቂቶች ብቻ ናቸው (ማቴዎስ 7፥13-14)::

ብዙ ሰዎች እምነት፣ የእምነት መግለጫዎችን በተመለከተ ከአእምሮ ስምምነት በላይ ምንም ነገር እንደሌለው አድርገው ያስባሉ:: እውነተኛ እምነት ከዚህ የበለጠ ነገር ነው:: እውነተኛ እምነት የምናስበውንና የምናምነውን ነገር የሚለውጥ ብቻ ሳይሆን የምንኖረውንና የምናደርገውን ጭምር ይለውጣል:: እውነተኛ እምነት ከውስጣችን ጀምሮ ይለውጠናል፤ ሁልጊዜም ራሱን የሚገልጠው በትክክለኛ ንግግርና በትክክለኛ ኑሮ ነው:: ያዕቆብ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፡-

> ወንድሞቼ ሆይ አንድ ሰው እምነት አለኝ ቢል ሥራ ግን ባይኖረው ምን ይጠቅመዋል? እንዲህ ያለው እምነት ሊያድነው ይችላልን? አንድ ወንድም ወይም እንዲት እህት የሚለብሱት ልብስም ሆነ የሚመገቡት ምግብ አጥተው ከእናንተ መከካል አንዱ "በሰላም ሂዱ፣ አይብረዳችሁ፣ ጥገቡ" ቢላቸው ለሰውነታቸው ግን የሚያስፈልጋቸውን ባይሰጣቸው ምን ይጠቅማቸዋል? እንዲሁ ሥራ የሌለው እምነት በራሱ የሞተ ነው::
>
> ነገር ግን አንድ ሰው አንተ እምነት አለህ፤ እኔ ሥራ አለኝ ይላል::
>
> እምነትህን ከሥራ ለይተህ አሳየኝ፤ እኔም እምነቴን በሥራዬ አሳይሃለሁ (ያዕቆብ 2፥14-18)::

እውነተኛ እምነትና ተግባር አይለያዩም፤ ኢየሱስ እንዲህ አለ፤

> በውስጣቸው ነጣቂ ተኩላዎች ሆነው ሳሉ የበግ ለምድ ለብሰው መካከላችሁ በመግባት ከሚያሸምቁ ሐሰተኛ ነቢያት ተጠንቀቁ:: ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ:: ከእሾህ ቁጥቋጦ ወይን፣ ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን? እንዲሁም ጥሩ ዛፍ ሁሉ ጥሩ ፍሬ፣ መጥፎ ዛፍ ግን መጥፎ ፍሬ ያፈራል:: ጥሩ ዛፍ መጥፎ ፍሬ፣ መጥፎም ዛፍ ጥሩ ፍሬ ማፍራት አይችልም:: ጥሩ ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል፤ ወደ እሳትም ይጣላል:: ስለዚህ በፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ::
>
> በሰማይ ያለውን የአባቴን ፈቃድ ሳይፈጽም ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማይ አይገባም (ማቴዎስ 7፥15-21)::

እምነትን በሚመለከት ረገድ የሕይወት ፈተናዎችና መከራዎች ውሸትን ከእውነት ውስጥ በፍጥነት ነቅለው ይጥሉታል:: ውሸት የመቆየት ኃይል የለውም:: ኢየሱስ ይህንን ልዩነት በዘሩና በዘሪው ምሳሌ ውስጥ ግልጽ አድርጎታል፡-

> አንድ ገበሬ ዘር ሊዘራ ወጣ:: ሲዘራም ሳለ፣ አንዳንዱ ዘር መንገድ ዳር ወደቀ ወፎችም መጥተው ለቀመው በሉት::

> አንዳንዱ ዘር ዐፈሩ ስስ በሆነ ድንጋያማ መሬት ላይ ወደቀ፤ ዐፈሩ ስስ ስለሆነም ፈጥኖ በቀለ። ነገር ግን ፀሐይ ሲመታው ጠወለገ፤ ሥር ባለመስደዱም ደረቀ። አንዳንዱም ዘር በእሾህ መካከል ወደቀ፤ እሾኹም ቡቃያውን አንቆ አስቀረው። ሌላው ዘር ደግሞ በጥሩ መሬት ላይ ወደቀ፤ ፍሬም አፈራ፣ አንዱ መቶ አንዱ ሥልሳ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ። ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ ....
>
> እንግዲህ የዘሪውን ምሳሌ ስሙ፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት ቃል ሰምቶ ከሚያስተውል ከማናቸውም ሰው ልብ ውስጥ ክፉው መጥቶ የተዘራውን ዘር ይነጥቃል። ይህ እንግዲህ በመንገድ ዳር የተዘራው ዘር ነው። በድንጋያማ መሬት ላይ የተዘራው ቃሉን ሰምቶ ወዲያውኑ በደስታ የሚቀበለውን ሰው ይመስላል። ነገር ግን ሥር መስደድ ባለመቻሉ ብዙ አይቆይም በቃሉ ምክንያት መከራ ወይም ስደት ሲመጣ ወዲያውኑ ይሰናከላል። በእሾኽ መካከል የተዘራው ዘር ቃሉን ሰምቶ ለዚህ ዓለም በመጨነቅና በብልጽግና ሐሳብ በመታለል ታንቆ ያላፈራውን ሰው ይመስላል። በጥሩ መሬት ላይ የተዘራው ዘር ግን ቃሉን ሰምቶ የሚያስተውለውን ሰው ይመስላል፤ በርግጥም ፍሬ ያፈራል፤ አንዱ መቶ፣ አንዱ ሥልሳ፣ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ (ማቴዎስ 13፥3-9፤ 18-23)።

በዚህ ታሪክ ያሉትን የ"ፈተና" ቃሎች ተመልከቱ፦ ደንጋያማ፣ ደረቅ፣ አንቆ፣ መከራ፣ ስደት፣ መጨነቅ፣ ብልጽግና፣ መታለል የሚሉ ናቸው። እነዚህ እውነቱን ከውሸት የሚለዩ ነገሮች ናቸው። ብዙ ሰዎች ያላቸው እምነት ሥር ወይም ጥልቀት የሌለው ግልብ የሆነ እምነት ነው። እነርሱ ነገሮች በመልካም ሁኔታ እስከሄዱ ድረስ ለጥቂት ጊዜ ደህና ይመስላሉ። ነገር ግን ትንሽ ከባድ ውሀ (ችግር) ባጋጠማቸው ጊዜ የእምነታቸው እውነተኛ ምንነት ይገለጣል፤ እምነታቸው በሕይወት ውስጥ ያለውን የተለመደ ፈተናና ተግዳሮት ለመቋቋም ፈጽሞ ብቃት የሌለው ግልብ የሆነና "ባርከኝ" የሚል አስተሳሰብ ያለው እምነት ነው።

እምነትን ለራሳቸው ዐላማ ሊጠቀሙበት የሚፈልጉ ሌሎች ሰዎች ደግሞ አሉ፤ ዐላማቸው ከጭንቀት ነፃ የሆነ ሕይወት ማግኘት ወይም ሀብትን ማግኘትና የመሳሰሉት ናቸው። እነዚህ ነገሮች ተግባራዊ በማይሆኑበት ጊዜ በፍጥነት እምነታቸውን ይተውና ወደ ሌላ ነገር ዘወር ይላሉ። እስከ



መጨረሻ የሚጸናው እውነተኛ እምነት ብቻ ነው፦ ከዚያም ከተትረፈረፈ መከር የሚገኘውን በረከትና ሽልማት ይቀበላል።

እግርህን በጠንካራ መሬት ላይ ትከል። እምነትህን ዐለት በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ መሥርት። እርሱ ከቶ ስለማይጥልህ በእርሱ ላይ ብቻ ታመን። በእርሱ ብርታት ጸንተህ ስትቆም ለእርሱ ክብርን ታስገኝለታለህ። ሰዎች በፈተና ውስጥ ስታልፍ በሚያዩበት ጊዜ እግዚአብሔርን ስለ አንተ ያመሰግናሉ። እነርሱም "ወይ ጉድ! እምላክህ አጠንክሮሃል። የምትወድቅ መስሎን ነበር፤ እርሱ አሳለፈህ!" ይላሉ። እነርሱ ጥንካሬን እንጂ ሽሽትን አያዩም። ከመከራ በመሸሻችን ከቶ መታወቅ የለብንም። የአንተ ዝና መገንባት ያለበት በምታልፈው ፈተና ላይ ነው። ሰዎች በእግዚአብሔር የሚነኩት አንተ በምትሰጠው ምስክርነት ነው እንጂ በማትሰጠው ወይም በሌለህ ምስክርነት አይደለም።

አስመሳይ እምነት ውድቀትን ይፈራል፤ ምክንያቱም ውድቀትን እንደ ድክመት ምልክት ስለሚቆጥረው ነው፤ የውሸት እምነትም ውጫዊ መልክ (ገጽታ) ብቻ ነው። ውድቀትን አትፍራ። ስላላሸነፍህ ብቻ አትበሳጭ። አንዳንድ ጊዜ ማጣት መልካም ነገር ነው። ውሳኔአችንን ይፈትነዋል። ብዙ ጊዜ ከስኬታችን የምንማረውን ያህል ወይም ከዚያም የበለጠ፣ ከስህተታችንና ከውድቀታችን እንማራለን። አንድ ነገር ጠፍቶበት የማያውቀውን ሰው እንዳትተማመንበት በጣም ጥንቃቄ አድርግ።

መፈተን ለመሪነት ቅድመ ሁኔታ (መመዘኛ) የሚሆነው በዚህ ምክንያት ነው። ማንም ያልተፈተነ ሰው ለቤተክርስቲያን መሪነት እንዳይመደብ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ መመሪያ ሰጥቶታል (1ጢሞ 3፥10 ይመልከቱ)። በዚህ ክፍል የሚናገረው በተለይ ስለ ዲያቆናት ቢሆንም መመዘኛው ለሁሉም መሪዎች ለሚሆኑ ተግባራዊ የሚሆን ነው። ትምህርት ለመሪነት ችሎታ ዋስትና ሊሆን አይችልም። ዋናው አስፈላጊ ነገር በፈተና ውስጥ የተረጋገጠ እምነት ነው። ቤተክርስቲያን ለመሪነት የማያስፈልጓት "ቅጥር ሙያተኞች" አይደሉም። ኢየሱስ እንዲህ አለ፤

> መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ሕይወቱን ስለ በጐቹ አሳልፎ ይሰጣል። ተቀጣሪው እረኛ ግን በጐቹ የእርሱ ስላልሆኑ ተኲላ ሲመጣ ጥሎአቸው ይሸሻል። ተኲላውም በጐቹን ይነጥቃል፤ ይበትናቸዋል። የሚሸሸውም ተቀጣሪ ስለ ሆነና ለበጐቹ ደንታ ስለሌላው ነው (ዮሐንስ 10፥11-13)።

ተቀጣሪ ማለት ምንም ዐይነት የግል ወይም የስሜት ፍላጐት ሳይኖረው ለአንድ ኃላፊነት የተመደበ ሰው ነው:: የመጽናት ኃይል እንዳለውና እንደሌለው ለመታወቅ አልተፈተነም:: ችግር በመጣ ጊዜ፣ ተቀጣሪው የኃላፊነቱን ሥፍራ ትቶ ይሄዳል፤ ምክንያቱም ለደመወዙ ከሚፈልገው ባሻገር ምንም ዐይነት የልብ መስጠት ስለሌለው ነው:: ከዚያም በላይ፣ ሌሎች ሥራዎች ሞልተዋል:: የታማኝ መሪዎች መፈተን ጌታ ሕዝቡን በጠበቀበት መንፈስ ለመጠበቅ ይችሉ ዘንድ ሥርዓታቸውንና ባሕርያቸውን ያስተካክልላቸዋል::

## ሰባቱ የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ሚናዎች

ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እምነት ጥናት ማጠናቀቂያው ላይ በመቃረባችን እኛንና በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያለንን ስፍራ በሚመለከት ሰባት የመንግሥቱን እምነት ቁልፍ ሚናዎችን ላካፍላችሁ እፈልጋለሁ:: ይህ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እስከ አሁን ያየናቸውን እውነታዎች እንደ አጭር ክለሳ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን፣ በተጨማሪ በመንግሥቱ ሕይወት ውስጥ የእምነትን አስፈላጊ ባሕርይ በአጽንኦት እንደ ገና ለማጉላት ነው::

1. የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ወደ መንግሥቱ የምንገባበት ነው:: ይህ እምነት ከውስጣችን የሚመነጭ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጸጋና ፍቅር የሚሰጥ ስጦታ ነው:-

> ነገር ግን በምሕረቱ ባለ ጠጋ የሆነ እግዚአብሔር ለእኛ ካለው ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን ሆነን ሳለ በክርስቶስ ሕያዋን አደረገን፤ የዳናችሁት በጸጋ ነው:: እግዚአብሔርም ከክርስቶስ ጋር አስነሣን፤ በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን፤ ይኸውም በሚመጣው ዘመን በክርስቶስ ኢየሱስ በቸርነቱ የገለጠልንን ወደር የሌለውን የጸጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ ነው:: በእምነት በጸጋ ድናችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም ምክንያቱም፤ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀልንን መልካም ሥራ እንድንሠራ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርን የእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች ነን (ኤፌሶን 2፥4-10)



ያለ እምነትም እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም (ዕብ 11፥6 ይመልከቱ):: ይህ ማለት ያለ እምነት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚገባ ማንም ሰው የለም ማለት ነው::

2. የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት በመንግሥቱ ውስጥ የሰላማችን ምንጭ ነው:: እንደ እምነት ሁሉ ሰላምም ከእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ የሚመጣ ስጦታ ነው፤

> ሰላምን እተውላችኋለሁ፤ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ:: እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጣችሁ አይደለም:: ልባችሁ አይጨነቅ፣ አይፍራም (ዮሐንስ 14፥27)::

> በእኔ ሰላም እንዲኖራችሁ ይህን ነግሬአችኋለሁ:: በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ (ዮሐንስ 16፥33)::

ኢየሱስ የሚሰጠው ሰላም ከዓለም የሚገኝ ስላልሆነ ዓለም አያውቀውም፤ ሊያወቀውም አይችልም:: የክርስቶስ ሰላም ዓለም ሊገምተው ከሚችለው ሰላም በላይ ከፍ ያለ፣ ጠለቅ ያለ፣ የበለጸገና ሙሉ የሆነ ሰላም ነው፤ ምክንያቱም ምንጩ ከእግዚአብሔር የሆነ ሰላም ስለሆነ ነው:: ከእግዚአብሔር ውጪ ምንም ሰላም የለም::

> በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋናም ጋር ልመናችሁን በእግዚአብሔር ፊት አቅርቡ እንጂ ስለ ማንኛውም ነገር አትጨነቁ:: ከማስተዋል በላይ የሆነው የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል (ፊሊጶሲዮስ 4፥6-7)::

3. የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት የመንግሥቱ የመገበያያ ገንዘብ ነው:: ያለ እርሱ ምንም ዐይነት ስለ መንግሥቱ ጉዳይ ልውውጥ ማድረግ ወይም መዋዋል አይቻልም::

> . . . እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ (ማቴዎስ 9፥29)::

> ደግሞም ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሁሉ

እግዚአብሔር መኖሩንና ከልብ ለሚሹትም ዋጋ እንደሚሰጥ ማመን አለበት (ዕብራውያን 11፥6)።

እምነት (የመንግሥቱ መገበያያ ገንዘብ) ወደ መንግሥቱ ብልጽግናና ሀብት ያስገባናል፦

ለሚያምን ሰው ሁሉም ነገር ይቻላል (ማርቆስ 9፥23ለ)።

እምነት ካላችሁ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ (ማቴዎስ 21፥22)።

ስለዚህ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ እንደ ተቀበላችሁት አድርጋችሁ ብታምኑ ይሆንላችኋል (ማርቆስ 11፥24)።

በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ ማንኛውንም ነገር እንደ ፈቃዱ ብንለምን እርሱ ይሰማናል፤ የምንለምነውን ሁሉ እንደሚሰማን ካወቅን የለመነውንም ነገር እንደ ተቀበልን እናውቃለን (1ዮሐንስ 5፥14-15)።

በመንግሥቱ ውስጥ ማናቸውንም ነገሮች የምናገኘው እምነታችንን በመክፈል ነው።

4. የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት የመንግሥቱ ባህል ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት የሚኖረውና የሚተነፍሰው በእምነት ነው።

መጽሐፍስ ምን ይላል? "አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት" (ሮሜ 4፥3)።

በወንጌል የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጦአልና፤ ጽድቁም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በእምነት የሆነ ነው፤ "ጻድቅ በእምነት ይኖራል" ተብሎ እንደ ተጻፈው (ሮሜ 1፥17)።

የምንኖረው በእምነት እንጂ በማየት አይደለም (2ቆሮንቶስ 5፥7)።



ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ ከእንግዲህ እኔ አልኖርም፤ ነገር ግን ክርስቶስ በውስጤ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖረው ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን አሳልፎ በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለኝ እምነት ነው (ገላትያ 2፥20)።

"ጻድቅ በእምነት ይኖራል" ስለተባለ ማንም በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንደማይጸድቅ ግልጽ ነው (ገላትያ 3፥11)።

ያለ እምነት የሆነ ማንኛውም ባሕል የእግዚአብሔር መንግሥት ባሕል አይደለም። ያለ እምነት የእግዚአብሔር መንግሥት ባሕል የለም።

5. የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ለመንግሥቱ ማስረጃ ነው። ዓለም የእግዚአብሔርን መንግሥት ተጨባጭነት የሚያይበትና የሚያውቅበት ቀዳሚ መንገድ በመንግሥቱ ዜጎች እምነት ነው።

እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው የጨውነት ጣዕሙን ቢያጣ ጣዕሙን መልሶ ሊያገኝ ይችላልን? ወደ ውጭ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ጥቅም አይኖረውም።
እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ። በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትደበቅ አትችልም። ሰዎችም መብራት አብርተው ከዕንቅብ ሥር አያስቀምጡትም። በቤት ውስጥ ላሉት እንዲያበራ በመቅረዝ ላይ ያስቀምጡታል እንጂ። እንደዚሁም ሥራችሁን አይተው በሰማይ ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰዎች ፊት ይብራ (ማቴዎስ 5፥13-16)።

ዐዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤ ይኸውም እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ነው። እንግዲህ እኔ እንደወደድኋችሁ፤ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ። እርስ በርሳችሁ ብትዋደዱ ሰዎች ሁሉ የእኔ ደቀመዛሙርት እንደሆናችሁ በዚህ ያውቃሉ (ዮሐንስ 13፥34-35)።

በክርስቶስ ፊት እግዚአብሔር የክብሩን ዕውቀት ብርሃን ይሰጠን ዘንድ "በጨለማ ብርሃን ይብራ" ያለው እግዚአብሔር ብርሃኑን በልባችን አብርቶአልና::

ነገር ግን ይህ እጅግ ታላቅ ኃይል ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ አለመሆኑን ለማሳየት ይህ የከበረ ነገር በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን (2ቆሮንቶስ 4፥6-7)::

ለእግዚአብሔር የምናሳየው እምነትና ፍቅር፣ እንዲሁም ለእምነት ጓደኞቻችን እና ለሰዎች ሁሉ የምናሳየው ፍቅር፣ የእግዚአብሔር መንግሥት እውነተኛና ተጨባጭ መሆኑን ለዓለም የሚመሰከር ማስረጃ ነው::

6. የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት የመንግሥቱ ሕይወት ነው:: ሕይወት የሚገኘው በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ብቻ ነው:: ይህ ሕይወት እውነተኛ ሕይወት፣ የተትረፈረፈ ሕይወት፣ ዘላለማዊ ሕይወት ነው:- ይህንንም የምንቀበለው በእምነት ነው::

በጽድቅ መንገድ ላይ ሕይወት አለ፤ በዚያ ጐዳና ላይ ሞት የለም (ምሳሌ 12፥28)::

በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና:: እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም የላከው በዓለም ለመፍረድ ሳይሆን ዓለምን በእርሱ ለማዳን ነው:: በእርሱ የሚያምን ሁሉ አይፈረድበትም፤ በእርሱ የማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁኑኑ ተፈርዶበታል (ዮሐንስ 3፥16-18)::

የሥጋን ነገር ማሰብ ሞት ነው፤ የመንፈስን ነገር ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው (ሮሜ 8፥6)::

እምነት ለእያንዳንዱ የመንግሥት ዜጋ በደም ውስጥ ያለ ሕይወት ነው::

7. የእግዚአብሔር መንግሥት እምነት ለመንግሥቱ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል:: በእምነት የተሞላ አካባቢ ተአምራትን ሊሠራ ይችላል:: እምነት



ባለበት ሥፍራ፣ የሰው ሕይወት ይለወጣል፤ ይህም ከሁሉ የሚበልጥ ተአምር ነው::

ከዚያም ዐሥራ ሁለት ዓመት ሙሉ ደም እየፈሰሳት ትሠቃይ የነበረች አንዲት ሴት ከኋላው መጥታ የልብሱን ጫፍ ነካች:: እርሷም በልቧ "የልብሱን ጫፍ እንኳ ብነካ እፈወሳለሁ" የሚል እምነት ነበራት::

ኢየሱስም ወደ ኋላ ዘወር ብሎ ሴቲቱን አያትና "አይዞሽ ልጄ ሆይ፣ እምነትሽ አድኖሻል" አላት፤ ሴቲቱም ወዲያውኑ ተፈወሰች (ማቴዎስ 9፥20-22)::

በዚህ ጊዜ ኢየሱስ "አንቺ ሴት እምነትሽ ታላቅ ነው፤ እንደ ፈለግሽው ይሁንልሽ አላት:: ልጇም ከዚያ ሰዓት ጀምሮ ተፈወሰች (ማቴዎስ 15፥28)::

ኢየሱስም "ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ" አለው:: ዐይነ ስውሩም "መምህር ሆይ፤ እንዳይ እፈልጋለሁ" አለው::ኢየሱስም ሂድ እምነትህ አድኖሃል አለው:: ወዲያውም ዐይኑ በራለት በመንገድም ኢየሱስን ተከትሎት ሄደ (ማርቆስ 10፥51-52)::

በልስጥራንም እግሩ እንካሳ የሆነና ከተወለደ ጀምሮ ፈጽሞ በእግሩ ሄዶ የማያውቅ ሽባ ሰው ተቀምጦ ነበር:: ይህም ሰው ጳውሎስ ሲናገር ያዳምጥ ነበር፤ ጳውሎስም ወደ እርሱ ትኩር ብሎ ተመለከተና ለመዳን እምነት እንዳለው ባየ ጊዜ በታላቅ ድምጽ "ቀጥ ብለህ በእግርህ ቁም" አለው:: በዚህ ጊዜ ዘሎ ተነሣና መራመድ ጀመረ (የሐዋ 14፥8-10)::

እምነት የሚገኘው ከመስማት ነው፣ መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው (ሮሜ 10፥17 ይመልከቱ):: እምነታችን የሚነሣው በእምነት አካባቢ ነው፤ በእግዚአብሔር መንግሥት ንቁ ዜጐች የምንሆነውም በዚህ ሁኔታ ነው:: ነገሮችን ከእግዚአብሔር የምናገኘው በእግዚአብሔር ማመናችንን በመናገራችን አይደለም፤ ነገሮችን ከእግዚአብሔር የምናገኘው በእግዚአብሔር ስናምን ነው:: ብዙ ጊዜ የዚህ ልዩነት የተመሠረተው በፈተና መኖር ወይም አለመኖር ላይ ነው:: በኑሮ ሲእል ውስጥ ካላለፍን በስተቀር በተጨባጭ እግዚአብሔርን ወደ ማወቅም ሆነ ወደ ማመን ልንደርስ

አንችልም:: የእግዚአብሔርን ሙሉ ብቃት ልናውቅ የምንችለው የራሳችን ኃይል አለን የምንለው ሁሉ በሙሉ ከእኛ ተጠራርጐ ሲወሰድና በመንገዳችን መጨረሻ ላይ ስንደርስ ነው::

## ዓለምን የሚያሸንፍ እምነት

እምነት እስካለህ ድረስ፣ በሕይወት ጨዋታ ውስጥ ነህ:: ብዙ እምነት እንዲኖርህ አይጠበቅብህም፤ ነገር ግን እምነትህ እውነተኛ መሆን አለበት:: በጣም የመጨረሻዋ ትንሽ የምትባል እውነተኛ እምነት እንኳ የማይታመን ነገር ልታደርግ ትችላለች፤

> ሐዋርያትም ጌታን፣ "እምነታችንን ጨምርልን" አሉት:: ጌታም የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል እምነት ቢኖራችሁ ይህን ሾላ ተነቅለህ ባሕር ውስጥ ተተከል ብትሉት ይታዘዝላችኋል አላቸው (ሉቃስ 17፥56)::

> ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፣ "በእግዚአብሔር እመኑ:: እውነት እላችኋለሁ ማንም ይህን ተራራ 'ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር' ቢለውና ይህንንም በልቡ ሳይጠራጠር ቢያምን ይሆንለታል:: ስለዚህ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ እንደ ተቀበላችሁት አድርጋችሁ ብታምኑ ይሆንላችኋል" (ማርቆስ 11፥22-24)::

አንድ ዛፍ ወይም ተራራ ተነቅሎ ወደ ባሕር ሲጣል አይተህ ታውቃለህን? አላየህም? ይህ ስለ እምነታችን ጥራት ወይም ደረጃ ምን ይነግረናል? እነዚህ ጥቅሶች እንደሚያመለክቱት ጉዳዩ የእምነታችን መጠን አይደለም፤ ጉዳዩ እምነት መኖሩ ላይ ነው! ተራራን ለማስወገድ የሚያስፈልገው በእግዚአብሔር ላይ ያለች፣ እውነተኛ፣ ያልተቀጠጠችና ያልተገደበች የመጨረሻዋ ትንሽ የእምነት ፍሬ ናት:: ተራራው የሕመም ተራራ፣ የገንዘብ ችግር ተራራ፣ የነቀፋና የተቃውሞ ተራራ ወይም የሥራ አጥነት ተራራ ቢሆን ልዩነት የለውም:: ተራራህ ምንም ዓይነት ቢሆን፣ የሚያስፈልግህ የእግዚአብሔር መንግሥት ገንዘብ የመጨረሻዋ አነስተኛ ሳንቲም የሆነችው ንጹሕ የእምነት ዘር ናት:: መጽሐፍ ቅዱስ እምነታችን ዓለምን ያሸንፋል በማለት የተናገረው ለምን እንደሆነ አሁን ይታይሃል?

የእግዚአብሔርን ድምጽ አድምጥ:: እርሱ "ጉዳዩ የተራራህ መጠን አይደለም:: ጉዳዩ የሚያጋጥሙህ ፈተናዎች ክብደት አይደለም:: ጉዳዩ :- በእኔ ታምናለህ ወይ? ይላል::



ለዚህ ጥያቄ በእውነት "አዎን" የምትል ከሆነ፣ እንግዲያውስ ተራራዎች ከዚህ በፊት ባልታየ ሁኔታ ከሕይወትህ ሲወገዱ ለማየት ተዘጋጅ:: ምናልባት የሚወገደው ዛሬ ወይም ነገ ወይም የዛሬ ዓመት ላይሆን ይችላል፤ ነገር ግን "የመወገድ ቀን" የመጣል:: በራሱ በእግዚአብሔር ጊዜና መንገድ ይመጣል:: የመንግሥቱ እምነት ዓለምን ያሸንፋል፤ የተረጋገጠ ነው!

> ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋል:: ዓለምን የሚያሸንፈውም እምነታችን ነው:: ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ከሚያምን በስተቀር ዓለምን የሚያሸንፍ ማነው? (1ዮሐንስ 5፥4-5)::

## የእግዚአብሔር መንግሥት መርሆች

- የመንግሥቱ እምነት ወደ መንግሥቱ የምንገባበት ነው::
- የመንግሥቱ እምነት በመንግሥቱ ውስጥ የሰላማችን ምንጭ ነው::
- የመንግሥቱ እምነት የመንግሥቱ ገንዘብ ነው::
- የመንግሥቱ እምነት የመንግሥቱ ባሕል ነው::
- የመንግሥቱ እምነት የመንግሥቱ ማስረጃ (ምስክር) ነው::
- የመንግሥቱ እምነት የመንግሥቱ ሕይወት ነው::
- የመንግሥቱ እምነት የመንግሥቱን አካባቢ ይፈጥራል::
- የመንግሥቱ እምነት ዓለምን ያሸንፋል፤ የተረጋገጠ ነው!

## መደምደሚያ

ሕይወት ሁልጊዜ ልንመልሳቸው በማንችላቸው ምስጢሮችና ጥያቄዎች የተሞላ ነው:: ሁልጊዜ የድፍረታችንንና የጽናታችንን ማዕከል የሚገዳደሩ ፈተናዎችና ሁኔታዎች ያጋጥሙናል:: እኛ ተስፋ ቢስና ትጥቃችንን እንድንፈታ የሚያደርገንን ጥርጥር የሚወልዱ የፍርሀት፣ የምሬት፣ የተስፋ ቢስነትና የግራ መጋባት ወቅቶች ያጋጥሙናል:: ሕይወት የማይጠበቀውንና የማይታመነውን ነገር ያመጣብናል፤ ይህም የቆየውን አቋማችንን የሚያነቃንቅ ማዕበል ሲሆን ስለ ሁኔታችን የሚገደው የፍቅር አምላክ በእውነት መኖሩን እንድንጠራጠር ያደርገናል::

ሕይወት ብዙ ጊዜ የተወሰነ (የታወቀ) ስልት በሌላቸው እንቅፋቶችና ጫናዎች ከጨለማው በኩል ሆኖ ይመታናል:: ባጭሩ፣ ሕይወት ለእያንዳንዳችን፣ መመሪያ ካርታ የሌለው ምድራዊ ጉዞ ነው:: የተፈጠርነው በእምነት እንድንኖርና ያልታወቀውን ነገር አቅጣጫ አመልካች (ኮምፓስ) በሆነው በእምነት እንድንጓዝው ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሻለሁ:: በዚህ ምድር ላይ ስኬታማ ኑሮ ለመኖር የጥርጥር ወቅት እንደሚጋጥመንና የምናምነው ነገር ሁሉ ተግዳሮት የሚገጥመው የመሆኑን ሐቅ መቀበል ይኖርብናል:: ይህ የሕይወት ባሕርይ ነው፤ አንተም በዚህ ምድር ላይ እስከኖርህ ድረስ ፈተናዎችና መከራዎች የታወቁና የተለመዱ ነገሮች ናቸው::

የመከራዎችና የፈተናዎች ተጨባጭነት በዚህ ምድር ላይ የምንኖረው ሕይወት ባሕርይ መሆናቸውን ከተቀበልህ፣ እንግዲያውስ በሚያጋጥሙህ ጊዜ ተስፋ መቁረጥ ሆነ ወይም ሽንፈት አይደርስብህም:: እንደ እውነቱ ከሆነ፣ መከራዎችን ለመዋጋት ከሁሉ የተሻለው መሣሪያ ከጠቅላላው የሕልውናህ ዐለት ላይ ንጹህ የሆነውን እውነተኛ ማንነትህን ፈልፍሎ ለማውጣት በተሠማራው የቅርጽ ባለሙያ እጅ ያሉ መሣሪያዎች እንደሆኑ አድርገህ መቀበል ነው:: አንተ በመለኮታዊው የቅርጽ ሠራተኛ እንድትተማመንና እርሱ ስለ እውነተኛ ማንነትህ ያለውን ራዕይ እንድታምንበት አሳስብሃለሁ:: አንተም በመጀመሪያው ምዕት ዓመት ታላቅ ሐዋርያ በሆነው በያዕቆብ ቃሎች መንፈስ ለመኖር ያብቃህ:: እርሱ እንዲህ ብሎአል፤

> ወንድሞቼ ሆይ፣ ልዩ ልዩ መከራ ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት፤ ምክንያቱም የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ ታውቃላችሁ:: ምንም የማይጐድላችሁ ፍጹማንና ምሉኣን እንድትሆኑ ትዕግሥት ሥራውን ይፈጽም (ያዕቆብ 1፥2-4)::



> በፈተና የሚጸና የተባረከ ነው፤ ምክንያቱም ፈተናን ሲቋቋም እግዚአብሔር ለሚወዱት የሰጠውን ተስፋ የሕይወትን አክሊል ያገኛል (ያዕቆብ 1፥12)

ታላቅ የቤተክርስቲያን አባት በሆነው በጴጥሮስ ቃሎች ተጽናኑ:: እርሱም በሚከተለው አነጋገር ይህንኑ አሳብ ያሠምርበታል፥ "አሁን በብዙ ዐይነት ፈተና ውስጥ ሆናችሁ ለጥቂት ጊዜ መከራን ብትቀበሉም እንኳ በዚህ እጅግ ደስ ይላችኋል:: እነዚህ ነገሮች በእናንተ ላይ የደረሱት በእሳት ተፈትኖ ቢጠራም ጠፊ ከሆነው ወርቅ ይልቅ እጅግ የከበረው እምነታችሁ እውነተኛ መሆኑ እንደተረጋገጠና ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ምስጋናን፣ ክብርንና ውዳሴን እንዲያስገኝላችሁ ነው" (1ጴጥሮስ 1፥6-7)::

የተወደደው ሐዋርያ ዮሐንስ ይህንኑ የእምነት መንፈስ በማጠናከር በሕይወት ውስጥ አንተና እኔ ማንኛውንም እንቅፋት የምናሸንፍበትን ምስጢር ይሰጠናል፦ "ትእዛዛቱም ከባድ አይደሉም፤ ምክንያቱም ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋል:: ዓለምን የሚያሸንፈውም እምነታችን ነው" (1ዮሐንስ 5፥3-4)::

የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሐፊ ይህንን ሁሉ እንደሚከተለው ያጠቃልለዋል፦

> ጻድቅ ግን በእምነት ይኖራል፤ ወደ ኋላ ቢያፈገፍግ ነፍሴ በእርሱ ደስ አትሰኝም (ዕብራውያን 10፥38)::

> ደግሞም ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡ ሁሉ እግዚአብሔር መኖሩንና ከልብ ለሚሹትም ዋጋ እንደሚሰጥ ማመን አለበት (ዕብራውያን 11፥6)::

አንተ በእምነት የተሞላህ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ እንድትሆን አሳስብሃለሁ:: በማንኛውም ሁኔታ በጽናት እንድትቆምና የወደፊቱን በልበ ሙሉነት እንድትጋፈጠው ያድርግህ፣ ይህም የእምነትህን ኃይል ምንም ነገር ሊያቆመው እንደማይችል ከመገንዘብህ የተነሣ መከራዎችን የሚያስፈራራና ተጠራጣሪዎችንም የሚያሳፍር ይሆናል:: "በጥርጥር ጊዜ እምነት ይኑርህ" በሚለው መመሪያ ለመኖር ያስችልህ:: ሁልጊዜ የፈጣሪህ መልክና ባሕርይ

ያለብህ መሆንህን አስታውስ፡፡ ይህም ባሕርይ ፍርሀት የሌለው፣ ደፋርና እንዲሁም ከሞትና ከሕይወት የበለጠ ጥንካሬ ያለው ነው፡፡ እስካመንህ ድረስ፣ ታሸንፋለህ፡፡ ከግብህ በስተቀር ሁሉም ነገር ጊዜያዊ መሆኑን በማወቅ ለማመን ያለህን ችሎታ ተንከባከበው፡፡ ጥርጥር አማራጭ አይደለም፤ እምነትም አስፈላጊ የሆነ ነገር ነው፡፡ በየቀኑ በእግዚአብሔር መንግሥት እምነት መኖርና መራመድ ይሁንልህ፤ ከዚያም ከመከራዎችህ በኋላ አገኝሃለሁ፡፡